# ስውሩ አደጋ

## ኦርቶዶክሳውያንን ስለ ፕሮቴስታንቱ ዓለም የተሳሳተ አቅጣጫ ለማስጠንቀቅ

(የከሳሾቻችንን ማንነትና ስህተታቸውን የሚገልጥ)

በቀሲስ መላኩ ባወቀ ተረፈ

ፓቴር መጻሕፍት
Pater Books

www.ethiopianorthodox.org

ያለ ደራሲው ፈቃድ ይህንን መጽሐፍ ማባዛት ወይም በሙሉም ሆነ በከፊል መልሶ ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው።

መጽሐፉን ለመግዛት ቢፈልጉ ወይም ስለ መጽሐፉ አስተያየት ቢኖርዎ በሚከተለው አድራሻ መጠቀም ይችላሉ።

Kesis Melaku Bawoke Terefe
P. O. Box 90328
Los Angeles, CA 90009

MelakuBawoke@hotmail.com

Printed in:
Los Angeles, California
January, 2005



ወአንተሰ ለእመ ትፈቅድ ታእምር ኅድግ ህሉና ዘበምድር ወእድዎሙ ለከዋክብት ሥነሥርዓቶሙ ወኑባሬሆሙ እምዝንቱ ኵሉ ተሊዒለከ በህሊናከ ሐሊ አሐደ ሥሉስ ዘኢይሰደቅ።

*አንተ ግን ታውቅ ዘንድ የምትፈልግ ከሆንህ የምድሩን አኗኗርህን ተው፤ የከዋክብትንና የሥርዓታቸውን አቀማመጥ ተሻገር፤ ከዚህ ሁሉ በላይም ከፍ ካልህ በኋላ የማይጨፈለቀውን አንዱን ልዩ ሦስትነትን በልቡናህ አስብ።*

ዘይትቀነይ ለክርስቶስ በጽድቅ ይደልዎ ይትመሀር ዘየአምር ወይምሀር ዘየአምር ዘእንበለ ቅንአት ወእመሰ ኢይፈቅድ ይትመሀር ወይምሀር እንዘ ይትከሀሎ፤ ቦቱ ህማመ ጋኔን እስመ ርእሳ ለክህደት ጸጊበ ትምህርት ውእቱ።

*በእውነት ክርስቶስን ለማገልገል የሚፈቅድ ሰው ቢኖር ያላወቀውን መማር ያወቀውን ደግሞ ያለምቀኝነት ማስተማር አለበት። ነገር ግን ይህን ማድረግ ሲቻለው መማርንና ማስተማርን የማይፈልግ ሰው ከሆነ፤ ክፉ የመንፈስ በሽታ አለበት። ትምህርትን መጥገብ የክህደት ሁሉ ራስ ነውና።*

ከመጽሐፈ ገነት

www.ethiopianorthodox.org

## ምስጋና

በመጀመሪያ ከእናቴ ማህጸን ጀምሮ የጠበቀኝን እጄንም ይዞ እስከዚህች ድረስ የመራኝን በንስሓ ያጠብኝን ያዳነኝን ፈጣሪዬንና ጌታዬን ኢየሱስ ክርስቶስን አመሰግናለሁ።

ለእርሳቸው እጅግ አስቸጋሪ በሆኑ ወቅቶች ሁሉ ሳይቀር አባታዊ ፍቅራቸው ያልተለየኝን በሥጋም በትምህርትም ወልደው ያሳደጉኝን ወላጅ አባቴን መሪጌታ ባወቀ ተረፈን አመሰግናለሁ። አባቴ ሆይ፥ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ርቄ እንዳልቀር የእርስዎ ምክር፥ ተግሳጽ፥ እንባና « ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም » ከወደቅሁበት አንሥታኛለች። ለከበረው ማዕረገ ክህነትም አድርሳኛለችና። ያችም የእርስዎን እጅ ይዤ ስጓዝ ያስጠኑኝን መዝሙር መዘመር ጀምሬአለሁ « ኢተዘኪሮ አበሳ ዚአነ ኢሐደገነ ፍጹመ ንማስን ሔር እግዚአብሔር » የምትለውን።

ከህጻንነቴ ጀምሮ እንደ አባት እየመከሩኝ ያሳደጉኝን፥ ብዙም ያስቡልኝ የነበሩትንና ስለኔ በሰሙትም ባዩትም ፍቅራቸው ላልራቀብኝ ለብፁዕ አቡነ በርተሎሜዎስ፥ በውስጤ ያለውን የሰባኬ ወንጌልነት ጥሪ መሠረታዊ በሆነ ኦርቶዶክሳዊ ትምህርተ ወንጌል ላይ እንዲታነጽ ላስተማሩኝ ለመምህር ኃይለ ሥላሴ ይግዛው፥ ለመላከ ምህረት ጳውሎስ ቀጸላ ባደኩባት በአዋሳ መካነ ሥላሴ ላሉት አባቶች ካህናትና ምእመናን ምስጋና አቀርባለሁ።

እንደ አባቶቻቸው ኦርቶዶክሳዊነትን ከመከራ ጋር አስተባብረው ለያዙ፥ ለብዙ ዘመን ካገለገሉበት ደብር

www.ethiopianorthodox.org

በገዛ ወገኖቻቸው እንደ ዮሐንስ አፈወርቅ በሐሰት ለተሰደዱትና መከራን ለተቀበሉት፥ የህጻንነት አስተሳሰቤን የአንደበቴን ፍጥነት ተመልክተው « ተው ረጋ በል » ይሉኝ ለነበሩትን ፥በ« ስብራቴም » ፍቅራቸውንም ፊታቸውንም ሳልቀየሩብኝ መምህሬ መልአከ ሰላም ጴጥሮስ አዘነ በነበረኝ አገልግሎትም ውድቀትም በጸሎቱ ያሰበኝ ለነበረው ለሐረር መድኃኔ ዓለምና ለአደሬ ጢቆ መካነ ሥላሴ ሕዝበ ክርስቲያን ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በቅዱስ ጳውሎስ የቴዎሎጂ ሴሚናሪ በነበረኝ ቆይታ ከማያልቀው ኦርቶዶክሳዊ ማዕዳቸው እንድመገብ ላደረጉኝና ፥ በግፍ ከትምህርት ቤቱ እንድባረር ሲደረግ ላበረታቱኝ ለመከሩኝ ለመምህሬ ለብፁዕ አቡነ መርሐ ክርስቶስ ሊቀ ጳጳስ፣ ለኦርቶዶክሳውያን መምህራኖቼ ለመጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ፣ ለመምህር ሉሌ መላኩ፣ ለዶ/ር የማነ ገብረ ማርያም በአባታዊ ምክራቸው ሁል ጊዜ ይመክሩኝ ለነበሩት ኢትዮጵያዊው የአራቱ ጉባኤያት ሊቅ መልአከ ገነት ገብረ ሥላሴ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ከቤተ ክርስቲያን በግፍ መባረሬን ተከትሎ፥ በችኩልነት በብስጭትና ግራ በመጋባት በቤተ ክርስቲያኔ ላይ ላደረስኩት ጉዳት ለብዙዎችም የስህተት ምክንያት በመሆኔ አዝኜና ተጸጽቼ ወደ ቤተ ክርስቲያኔ ስመጣ፥ « የጠፋው ልጄ መጣ » ብለው በአባታዊ ፍቅርና በደስታ ለተቀበሉኝ፥ ከፍ ወዳለችውም ማዕረገ ክህነት ላደረሱኝ በዚህም በእኔ ምክንያት ነቀፌታን ለተቀበሉና በመቀበል ላይ ላሉት ለኦርቶዶክሳዊው ብርሃን ለብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ በጸሎታቸውና በአባታዊ ማበረታታቸው እስከ ዛሬ ያልረሱኝን በተቀደሰች ሲኖዶሳዊ ጉባኤያቸውም በፍቅር ለተቀበሉኝ ለብፁዕ ወቅዱስ



አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ፥ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ፥ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ባሳለፍኩዋቸው ደስ የማያሰኙ ዓመታት ውስጥ በጸሎታቸው ያልረሱኝን በምክራቸውም ያጽናኑኝን የወቀሱኝን ብሎም እያለቀሱ ስለኔ ከቤተ ክርስቲያን ርቆ መቅረት የተወያዩትን ሁሉ፥ ወደ ቤተ ክርስቲያኔም ከተመለስኩም በኋላ በተለይም ወደ አሜሪካ ከመጣሁ በኋላ በብዙ ያገዙኝን አባቶች ካህናት ወንድሞች ዲያቆናት አባቶች እናቶች ወንድሞችና እህቶች አመሰግናለሁ።

ላለፉት ሦስት ዓመታት በብዙ ፍቅርና ትዕግሥት፥ አገልግሎቴን አክብረው ቤተ ሰቤን ተንከባክበው፥ እየመከሩኝና አገልግሎቴን እየደገፉ እዚህ ያደረሱኝን፥ ትምህርቴን በጽሑፍ እንዳስቀምጥ ያበረታቱኝንና በገንዘብም በጉልበትም የረዱኝን የሎስ አንጀለስ ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ካህናት የቦርድ አባላት እና ምእመናንን አመሰግናለሁ።

በመጨረሻም፥ በዚህ ሁሉ ውስጥ ከጎኔ ላልተለየችን የበረከቱ ምክንያትና የህይወቴ አጋር የሆነችውን ወ/ሮ ዕሌኒ ብሥራትን፥ የእግዚአብሔር ይቅርታ በኔ ላይ እንደሆነ ያወቅሁበትን ልጄን ህጻን ምህረት መልአኩን አመሰግናለሁ።

ደራሲው

www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ

መግቢያ

የታላቁ ኢትዮጵያዊ ሰማዕት የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ቃለ ሃይማኖት

ምእራፍ አንድ፤ የችግሩ ምንጭ የት ነው? ..................... 1

የዶክተር ቶሎሳ ክስና እውነታው ..................... 6

ምዕራፍ ሁለት፤

የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ እውነተኛ ገጽታ ..................... 10

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ..................... 12

ማርቲን ሉተርና የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ..................... 13

ማርቲን ሉተርና የፖለቲካ አቋሙ ..................... 15

የጀርመን ገበሬዎችና ማርቲን ሉተር ..................... 17

እውነት በማርቲን ሉተር እጅ ..................... 18

ማርቲን ሉተርና የመንፈስ ጭንቀት ..................... 21

ማርቲን ሉተርና የትምህርቱ አካሄድ ..................... 21

ለዘብተኛ ( ሊበራል ) ቴዎሎጂ ..................... 22

የሊበራል ቴዎሎጂ አባቶች ..................... 24

ምዕራፍ ሦስት፤

የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንቲዝም አጀማመር ..................... 28

የመጀመሪያው ሚስዮናዊ ..................... 30

ሚሽነሪ ሲንድረም ..................... 31

ምዕራፍ አራት፤

ፕሮቴስታንትና መጽሐፍ ቅዱስ ..................... 37

የተሳሳተው አመለካከት ..................... 39

ማርቲን ሉተርና መጽሐፍ ቅዱስ ..................... 40

አናባፕቲስቶችና መጽሐፍ ቅዱስ ..................... 44

የጀርመን ቴዎሎጂና መጽሐፍ ቅዱስ ..................... 46

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምርመራ ..................... 47

የእምነት እንቅስቃሴና መጽሐፍ ቅዱስ ..................... 51

ምዕራፍ አምስት፤

ፕሮቴስታንትና ነገረ እግዚአብሔር ..................... 56

«ቴዎታናሲያ» ..................... 66

«አፕን ቴይዝም» ..................... 67

«የእምነት እንቅስቃሴ»ና ነገረ እግዚአብሔር ..................... 69

እግዚአብሔር በሰው ቁመት ..................... 69

ሰው እንደ አምላክ ..................... 71

ምዕራፍ ስድስት፤

ፕሮቴስታንትና ነገረ ሥጋዌ ..................... 73

የኤፌሶን ጉባኤና ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን .. 75

የንስጥሮስ አስተሳሰብና የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንቶች .. 77

«የታሪካዊ ኢየሱስ» ትምህርት በፕሮቴስታንቱ ዓለም .. 80

የእምነት እንቅስቃሴና ምሥጢረ ሥጋዌ ..................... 82

www.ethiopianorthodox.org

አምላክነት የሌለው ኢየሱስ ...................... 83

መስቀልና ሰይጣን ...................... 84

ምዕራፍ ሰባት፤

ፕሮቴስታንቶች በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የሚያነሱት ክሶችና መልሶቻቸው ...................... 90

በጌታችን በኩል የሆነልን እርቅ ...................... 91

ገድላት ተአምራትና ድርሳናት ...................... 95

ክብረ ቅድስት ድንግል ማርያም ...................... 98

ለእመቤታችን የተሰጡ ምስጋናዎች ...................... 100

የታቦት ክብር ...................... 101

ገዳማዊ ሕይወት ...................... 106

ምዕራፍ ስምንት፤

የታላላቅ ፕሮቴስታንት ሊቃውንት ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት መመለስ ...................... 109

ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የመጡ ...................... 112

ፒተር ጊልክርስት ...................... 113

ፍራንክ ሼፈር ...................... 114

ጆርስላቭ ፔልካን ...................... 116

በኦርቶዶክሳውያን አበው ትምህርት ከስህተት የተመለሱ፤ 117

ቶማስ ኦዴን ......................

ቅጥያ፡፡ የአንድ ትውልድ ሮሮ፡፡

ተሐድሶ ማኅበረ ቅዱሳን፥ ሃይማኖተ አበውና እኔ ..... 120




## መግቢያ

ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ዋና ምክንያት የሆነኝ በዚህ በሀገረ አሜሪካ በኢትዮጵያዊ ፕሮቴስታንት በዶ/ር ቶሎሳ ጉዲና የተሰበከው ስብከት ነው፡፡ ዶክተሩ ከአንድ ከተማረ ሰው በማይጠበቅ ሁኔታ ስለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የተናገሩት ጽርፈት (ስድብ) ብዙዎችን ከማስቆጣቱም በላይ ከሃይማኖት በላይ የሆነ ፖለቲካዊና የዘር አንድምታም ስላለው በብዙም አወያይቶአል፡፡ በተለይም ደግሞ ዶ/ሩ በማያውቁትና በማያገባቸው ርእስ ጉዳይ ላይ ገብተው መዘባረቃቸው አንሶ የዶክተሩን ስድብና መደዴ ንግግር እየሰማ ይስቅና በጭብጨባ ያጅባቸው የነበረው ሕዝብም እንደ እርሳቸው የብዙ ኢትዮጵያውያንን ልብ የሰበረ ነበር፡፡ ይህም በፕሮቴስታንቱ ዓለም እብደት ዕውቀት እየሆነ ለመምጣቱ ግልጥ ማስረጃ ነበር፡፡

ይህንንም ስድብ ተከትሎ የማስተምራቸው የሎስ እንጀለስ ድንግል ማርያም ምእመናን በዚህ ዘለፋና የስህተት ትምህርት ላይ አንዳች እንድናገር ጠየቁኝ፡፡ እኔም የዶ/ሩን ስድብ እንደገና ከማስተጋባትና ማለቂያ ለሌለው ክሳቸው ሁል ጊዜ አተካራ ውስጥ ከምንገባ፥ ፕሮቴስታንቱ ዓለም በራሱ ቤት ውስጥ ያለውን ጉድ፥ ምንስ ዓይነት አደጋ ውስጥ እንዳሉ ለምን አላስተምርም ብዬ በመነሣት ለሦስት ተከታታይ እሑዶች የፕሮቴስታንቱ ሃይማኖት ስላለበት አደጋና የስህተት ትምህርት ትምህርት ሰጠሁ፡፡ ትምህርቱ ብዙዎች «ያላስተዋልነውን ያየንበት ነው» ሲሉኝ፥ እንግዲያውስ በሚገባ ጽፌ ለምን በመጽሐፍ

www.ethiopianorthodox.org

አላቀርበውም አልሁ። በስብከት የቀረበን ነገር የመጽሐፍ መልክ እንዲኖረው ለማድረግ ስለሚያስቸግር እንደገና በአዲስ መልክ ለማዘጋጀት ግድ ሆነ።

ከዚሁ ጋር ግን ለፕሮቴስታንቱ አለም በኢትዮጵያ ምድር መስፋፋት ቀጥተኛ ተጠቃሽነት ያላቸውን የተሐድሶንና የማኅበረ ቅዱሳንን አካሄድ የሚመረምር ሐተታ በቅጥያ አስገብቻለሁ።

የመጽሐፉ አጠቃላይ ሐሳብ በኢትዮጵያውያን መካከል እውነተኛ የሆነ ውይይት እንዲፈጠር ለማነሣሣት ነው። ወንጌል ተብሎ የሚሰበከው ስህተት ፈልጎ ማውጣት ከሆነ፥ ፕሮቴስታንቶችም ጉዳቸውን ቆም ብለው የሚያዩበት ጊዜው አሁን ነው የሚል መልእክትም አለው። ስለሆነም አንዳንድ ሐሳቦቼ « እንደወረደ» እንዲቀመጡ አድርጌአቸዋለሁ። ሆን ብዬ ነው። መቀባባትና የለበጣ ወይም የ« ኢኩሚኒዝም » ለስላሳ ቃል አልተጠቀምኩም። መጽሐፉን ዶክተሩ ለወረወሩት ኃይለ ቃል አጸፋ አድርገው የሚያዩት ካሉ አይደለም አልልም። ከዚያ ባሻገር ያለውን መልእክት ተረድተው ከስህተታቸው የሚመለሱ ሰዎችን ካገኘሁ ግን ዓላማዬ ግቡን መቶአል። ምክንያቱም የጽሑፌ ዓላማ ከሳቸው ጋር እንኪያ ሰላንቲያ ለመክፈት አይደለምና።

በጽሑፉ ውስጥ ጉድለት የለም ብዬ አልመጻደቅም። ጽሑፉን የተሟላ ለማድረግ መጻሕፍትን ለማገላበጥ ተሞክሮአል። ሆኖም ከየትኛውም አቅጣጫ የሚሰጠኝን ገንቢና ወንድማዊ የሆነ አስተያየት ለመቀበል ግን ዝግጁ ነኝ። በተለይም ከቤተ ክርስቲያን አበውና ምእመናን የሚሰጠኝን እርማት በታላቅ ትህትና ለመቀበል ዝግጁ ነኝ።



ለዚህ መጽሐፍ መዘጋጀት ምክንያት የሆኑትንና አገልግሎቴን በብዙ መልኩ የሚደግፉልኝን የሎስ አንጀለስ ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን፥ ጽሑፉን መጽሐፍ ሆኖ እንዲወጣ አስተያየት በመስጠት፥ በማረም፥ ለመጽሐፉ ውበትና ለገጾቹ ዝግጅት በብዙ በመድከም የረዱኝንና ለመጽሐፉ ህትመት ሙሉ ወጪውን የሸፈኑልኝን ቤተ ሰብ እግዚአብሔር ከማያልቀው በረከቱ ይስጥልኝ እላለሁ።

በአገልግሎቴ ሁል ጊዜ ከጎኔ የማይለዩኝንና አብሬአቸው የማሳልፈውን ጊዜ ለንባብና ለጽሑፍ የሰጡኝን ባለቤቴን ወ/ሮ እሌኒ ብሥራትንና ልጄን ምህረት መላኩን አመሰግናለሁ። መጽሐፉ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅምና ለብዙዎች ከስህተታቸውም መመለስ ምክንያት እንዲሆን ጸሎቴ ነው።

ቀሲስ መላኩ ባወቀ ተረፈ
በዓለ ጥምቀት
1997 ዓ.ም
ሎስ አንጀለስ

www.ethiopianorthodox.org

# የታላቁ ኢትዮጵያዊ ሰማዕት የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ቃለ ሃይማኖት(1)

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ሎቱ ክብር ወስብሐት ወላዕሌነ ሣህል ወምህረት ለዓለመ ዓለም። አሜን።
የእግዚአብሔር ኃይልና ረድኤት ካለፈው ጊዜ ሁሉ ይልቅ በዚች ቅጽበት በተለይ የሚያስፈልገኝ መሆኑ ስለሚሰማኝ አባቶቻችንን ረድቶ እኛንም ደግፎ እስከ ዛሬ ያደረሰ አምላክ ሁሉን በሚችል ክንዱ ይመራኝ ዘንድ ህሊናዬን በሙሉ ለርሱ እሰጣለሁ።

በመጀመሪያ ጸጋውን የሚያድልበት ምስጢራት እንዳገለግል መጠን በሌለው ቸርነቱ ስለሰጠኝ ለእግዚአብሔር ለቅድስት ሦስትነቱ ምስጋና አቀርባለሁ። አሁን ደግሞ እርሱ መሥርቶ እስከ ዛሬ ደርስ ራሱ በመምራት እስከዚህ ያደረሳትን የኢትዮጵያን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንዳገለግል በማይገመት ፍቅሩና ጸጋው ጠራኝ። ወንድሞቼ ሆይ ይህ ጥሪ እጅግ ከባድ ሓላፊነት ያለበት ጥሪ መሆኑን ስለምገነዘብ ሁሉን የሚችል አምላክ በሥራዬም ቀዳሚ ሆኖ እንዲመራኝ እጸልያለሁ። የተሰጠኝንም ተግባር በሚቻለኝ ሁሉ በእርሱ ፈቃድ መሠረት ለመፈጸምና ቅድስት ቤተ ክርስቲያኑን ለመጠበቅ ያበረታኝ ዘንድ ሁላችሁም በጸጋው ዙፋን ፊት

*(1) ሐዲስ ሕይወት፥ የብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ 1ኛ ዓመት የፓትርያርክነት በዓለ ሢመት መጽሔት። ቁጥር 1። ግንቦት 1ቀን 1964 ዓ.ም። ገጽ38-41።*



በምታደርጉት ጸሎት ሁል ጊዜ ያለማቋረጥ እንድታስታውሱኝ እለምናችኋለሁ። የጸሎታችሁን እርዳታ በምጠይቅበት ጊዜ ከሁላችሁም ጋር አብሬ ስለምካፈለው በእግዚአብሔር ጸጋ ልጠብቀውና ላስፋፋው ስለምፈልገው እምነት ምስክር መስጠት መልካም ዕድል ሆኖ ታይቶኛል።

የቤተ ክርስቲያናችን እምነት በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት መሠረት በሃይማኖት ቀኖናዎች የተወሰነ ነው። እነዚህም ሐዋርያት የወሰኑት በ325 ዓ. ም. በኒቅያ ሲኖዶስ የተሰበሰቡት 318 አበው የወሰኑአቸው ቀኖናዎች ናቸው ። ወልድ ፍጡር ነው የሚለው የመናፍቅ ትምህርት የተወገዘበት ይህ ሁለተኛው ቀኖና የመንፈስ ቅዱስን ፍጹም አምላክነት ባረጋገጠው በቁስጥንጥንያ ሲኖዶስ በ381 ዓ. ም. ጸድቆአል። ዳግመኛም በ431 ዓ. ም. በኤፌሶን የተሰበሰቡት ሁለት መቶ አበው አንድ ክርስቶስን ከሁለት ከፍለው ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ብለው ያስተማሩ መናፍቃንን ሲያወግዙ ይህንን ቀኖና አጽድቀዋል።

በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት እየተመሩ ያስተማሩትን የእነዚህን ሲኖዶሶች ቅዱሳን አበው፥ የተከታዮቻቸውንም የተቀደሰ ሥርዓት በመከተል አንድ አምላክ በሚሆን በቅድስት ሥላሴ ያለኝን እምነት እመሰክራለሁ። እግዚአብሔር አንድ ነው። እርሱም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይባላል። አብ ፍጹም አምላክ ነው። ወልድ ፍጹም አምላክ ነው። መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ ነው። ግን አንድ አምላክ ይባላል እንጂ ሦስት አማልክት አይባልም። እግዚአብሔር በመለኮት በባሕርይ በፈቃድ አንድ ነው። በአካልና በገጽ በግብር ሦስትነቱን አምነን አንድ አምልኮትና ስግደት እናቀርባለን። አንድነት በሦስትነት፥ ሦስትነትም በአንድነት አለ። በአካል

www.ethiopianorthodox.org

ሦስት በመለኮት አንድ ናቸው። አንድ ሲሆኑ ሦስት፥ ሦስት ሲሆኑ አንድ ናቸው። ያለትድምርት ሦስት፥ ያለመለያየት አንድ ናቸው። አንዱን ከሌላው የሚለየው በግብር ብቻ ነው። አብ አብ ይባላል እንጂ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አይባልም።ወልድም ወልድ ይባላል እንጂ አብ መንፈስ ቅዱስ አይባልም። መንፈስ ቅዱስም መንፈስ ቅዱስ ይባላል እንጂ አብ ወልድ አይባልም።

የመለኮት አንድነት ማለት አብ በሚሠራው ሁሉ ወልድም መንፈስ ቅዱስም አብረው አሉ። ወልድም በሚሠራው ሁሉ አብም መንፈስ ቅዱስም አብረው አሉ። መንፈስ ቅዱስ በሚሠራው ሁሉ አብም ወልድም አብረው አሉ። ለምሳሌ ያህል አብ በወልድ ዓለምን ይፈጥራል፤ በመንፈስ ቅዱስ ይፈጽማል። ደግሞ አብ በወልድ ዓለምን ያድናል፤ በመንፈስ ቅዱስ የዓለምን ደህንነት ይፈጽማል።

ማናቸውም በእርሱ ካለመኖር ወደ መኖር የመጣበት፥ ከሥላሴ አንዱ እግዚአብሔር ወልድ፥ ለእኛና ለደህንነታችን ሲል ከሰማይ መውረዱን፥ ሥጋ መልበሱን፥ ከድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ አምላክ ተወልዶ በእውነት ፍጹም ሰው መሆኑን እመሰክራለሁ። ከድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ የነሣውን አካል ከራሱ ጋር አዋሕዶ፥ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋር በባሕርይ አንድ የሆነው ዘለዓለማዊው እግዚአብሔር ወልድ እንደኛ ፍጹም ሰው ሆነ፤ የእኛንም ባሕርይ ነሣ። ሳይለወጥ ሳይቀላቀል ሳይለያይ ሳይከፋፈል እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ድንግል የነሣውን ሥጋና ለባዊት ነፍስ ከራሱ ጋር በአንድ አካል አዋሐደ። አንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ነው፤ እርሱም ፍጹም ሰው ነው።



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ የባሕርይ ልጅ ነው። በሱም የመለኮት ባሕርይና የሥጋ ባህርይ ያለመለያየትና ያለመከፋፈል አንድ ሆነዋል። ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው። አንድ አካል አንድ ባሕርይ ስንል፥ አንድ ማለት የሚያስረዳው ፍጹም ተዋሕዶን ነው እንጂ፥ አልፎ አልፎ በስህተት እንደሚነገረው መጠፋፋትን የሚያሳይ አይደለም። ስለዚህ ክርስቶስ በምድር የተናገራቸው ቃላትም ሆኑ የፈጸማቸው ተግባራት መለኮትና ሥጋ በአንድ አካልና ባሕርይ ፍጹም መዋሐዳቸውን ይገልጣሉ። በክርስቶስ መለኮትና ሥጋ ፈጽሞ ተዋሕደዋል። በዚህም ተዋሕዶ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል በመሆን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ለዘለዓለም ይኖራል።

ቅዱስ አትናቴዎስ እንደተናገረው ሰው አምላክ ይሆን ዘንድ አምላክ ሰው ሆነ። በዚህም ቸርነት ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለምን ድኅነት ፈጸመ። በአዳኝነቱም ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቆ ለሰው የእግዚአብሔርን ልጅነት እንደገና መለሰለት። ሰውም በሚመጣው ዓለም የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት በተስፋና በፍቅር እንዲኖር አስቻለው። ከእመቤታችን ድንግል ማርያም ተወልዶ ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአት በስተቀር ማናቸውንም የሰውን ሥራ እየሠራ በምድር ኖረ።

ነገር ግን ይህ የሆነው ከአባቱ ከእግዚአብሔር ሳይለይ ነው። የሰይጣንንም ኃይል ድል ለመንሣት ክርስቶስ ለእኛ በመስቀል ላይ ሞተ። በሦስተኛውም ቀን በአሸናፊነት ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። ክርስቶስ በትንሣኤው ያስገኘው ድል በመላው ዓለም ለሚገኘው ለሰው ልጅ ሁሉ ነው። ዘርና ወገን ሳይለይ ድኅነቱ ለሁሉም ተሰጥቶአል።

www.ethiopianorthodox.org

የተሰቀለውና ከሙታን ተለይቶ የተነሣው ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተው፥ በመስቀሉና በትንሣኤው ያስገኘው ድህነት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ለመላው ዓለም ይገለጥ ዘንድ ነው። ክርስቶስ ሁል ጊዜ በቤተክርስቲያን አድሮ ይኖራል። መንፈስ ቅዱስም ሁል ጊዜ የቤተ ክርስቲያንን ሕይወትና ተግባር ይመራል። ቤተ ክርስቲያን የሁሉ ናት። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የዚህች የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ክፍል ናት።

... በአንድነት በሦስትነት የሚመሰገን እግዚአብሔር ሁላችሁን ይባርካችሁ በሥራችሁም ሁሉ ይምራችሁ። የእመቤታችን ድንግል ማርያም የመላእክት የሐዋርያት የጻድቃን የሰማዕታት የቅዱሳን ሁሉ በረከትና ጸሎት ከሁላችንም ጋር ይሁን። አሜን።



# ምዕራፍ አንድ

## የችግሩ ምንጭ የት ነው?

*የሚያስተምር ሰው ... አካሄዱን ይጠብቅ፤ ከማይታየው ቃሉ ይልቅ የሕይወቱ አካሄድ ይናገርለት። የነፍሱ ደኅንነት ከታወቀ ለሌሎች መዳንም ይተርፋል። ያድናቸውማል።*

*ማር ይስሐቅ ም. 10*

የፕሮቴስታንቱ ዓለም በቀውስ ውስጥ ነው። ይህም ቀውስ ሁለት ዓይነት ገጽታ ያለው ነው። በአንድ በኩል ሰዋዊ በሆነ አመክንዮ (ራሽናሊዝም) ላይ በመመሥረት የሚያምነውና የሚተወው ግራ ስለገባው ከጥንታውያኑ የግሪክ አማልክት ጀምሮ እስከ ምሥራቃውያን የህንድ ፍልስፍናዎች ድረስ እያግበሰበሰ ነው። ለዚህ ምሳሌ ሊሆን ለዘብተኞች ፕሮቴስታንቶችና አንዳንድ የካሪዝማቲክ (ፔንቴኮስታል) መሪዎች ክርስትናን ከሕንድ ፍልስፍና ጋር እያቀላቀሉ ማስተማርና መስበክ ጀምረዋል።[2]

በሌላ ደግሞ ይህንኑ የተወናበደ አስተሳሰቡን በምን ዓይነት ሁኔታ መግለጥ እንዳለበት ግራ ስለገባው በአምልኮ ቀውስ ውስጥም ገብቶአል። በዚህም ምክንያት በአሁኑ ወቅት ግብረ ሰዶምን የሚፈጽም ሰው ጳጳስ አድርጎ ከመሾም ጀምሮ በነቤንሂንና መሰሎቹ «የመገለጥ ንግድ» እስከማከናወን ከዚያም

---

*(2) ዴቪድ (ፖል) ዮንግ ቾ የሚባለው ታዋቂ የኮርያ ፕሮቴስታንት የሚጠቀምበት መመሪያ ከምሥራቅ ሃይማኖቶች የተቀዳ ነው። ለምሳሌ ስሙን የቀያየረው ለብዙ ጊዜያት ሲሆን በዚህ ወቅትም ስሜን በቀየርኩ ወቅቶች ኃይል አገኛለሁ የሚል እምነት አለው። ይህ ደግሞ የታወቀ የምሥራቃውያን ልማድ ነው። ይህም ሆኖ በኢትዮጵያውያን ፕሮቴስታንቶች ዘንድም ብዙ ተከታዮች አሉት።*



www.ethiopianorthodox.org

በላይ በቅርቡ እያየን እንዳለነው መንፈስ ወርዶብን ነው እያለ እንደ ውሻ እንደ ጅብ እንደ አህያ በመጮህና በሳቅ በመንከትከት የሚይዘውን የሚጨብጠውን አጥቶአል።[(3)]

ከዚህ ከፋ ወዳለው ሁኔታ ደግሞ ስንሄድ የፕሮቴስታንቱ ዓለም መነሻና መፈጠሪያ የሆነው አውሮፓ ከፕሮቴስታንቱ የተወናበደ ትምህርት የተነሣ መንፈሳዊነቱን ስላጣ፥ ዛሬ በከፍተኛ የመንፈሳዊ ድርቅ ውስጥ ነው። ሁኔታዎች መልክ ካልያዙ አውሮፓ በሃያዎቹ ዓመታት ውስጥ «ዩሮ አረቢያ» ልትሆን እንደምትችልም የማህበራዊ ኑሮ ጠበብቶች እየነገሩን ነው። ከፕሮቴስታንቱ መድረክ ግብረ ሰዶምና ክህደተ እግዚአብሔር ሲሰበክ የታላላቆቹ የአውሮፓ ከተሞች መንገዶች በአክራሪ ጂሐዲስቶች እየተወረሩ ናቸው። ይህ ሁኔታ በዚህ በውጭው ዓለም ያለውን የፕሮቴስታንት አማኝ መሄጃ መቆሚያ ስላሳጣው በከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ነው ያለው።[(4)]

ይህን ሃይማኖታዊ ቀውስ መፍትሔ ለመስጠት

(3) «የቶሮንቶ በረከት» ( Toronto blessing ) በመባል የሚታወቀውና በካሪዝማቲክ ቡድኖች የተጀመረው ይህ እንቅስቃሴ፥ በብዙዎች ዘንድ የተተቸበት፥ የሚያስቅም የሚያስለቅስም አይን ያወጣ እብደት ነው። በራሱ በፕሮቴስታንቱ አለም ታዋቂ ከሆኑት ሰባኪዎች አንዱ የሆኑት እንግሊዛዊው ጆን አስቶት ስለ እዚህ እንቅስቃሴና ስለሚያከናውነው « በመንፈስ መገንደስ » ወይም « በመንፈስ መታረድ » ልምምድ ሲናገሩ እኔ የማውቀው መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ለእግዚአብሔር ክብር በግምባራቸው ተደፍተው እንዲያመሰግኑ ሲያደርግ ነው እንጂ ሲያንደባልልና ሲያስጓራ አይደለም ብለዋል።

(4) ይህን በምጽፈበት ወቅት ከፍተኛ የሆነ ክህደትና ኢሥነ ምግባራዊ ድርጊት እየተካሄደባት ባለችው በኔዘርላንድ አክራሪ ሙስሊሞች የቫን ጎህ የልጅ ልጅ ልጅ የሆነውን ታዋቂ ጋዜጠኛ እስልምናን አንቋሸሃል ብለው የገደሉት ሲሆን፥ ሌሎችንም ለመግደል እየዛቱ ናቸው። በለንደን የእንግሊዝ ጽንፈኛ ሙስሊሞች እንግሊዝ በጥቂት ወቅቶች የእስልምና ሀገር እንደምትሆን በይፋ እየተናገሩ ናቸው። በጀርመን ከፍተኛ የሆኑ የፖለቲካ ባለስልጣናትንም ጨምሮ ወደ እስልምና እየገቡ ናቸው። እነዚህ በሙሉ ከመቶ አመት በፊት መቶ በመቶ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ነበሩ።





የፕሮቴስታንቱ ዓለም ከመነሻው ጀምሮ የሞከረ ሲሆን መፍትሔው ውሎ አድሮ ራሱ የክህደት ምንጭ ሲሆን እንመለከታለን። ዛሬ እያንዳንዱ የፕሮቴስታንት ዲኖሚኔሽን በብዙ ችግር ውስጥ ሰጥሞአል። ዋና ዋናዎቹ የፕሮቴስታንት ዲኖሚኔሽኖች ሜኖናይት ባፕቲስት ሜቶዲስት ፕሬስቢቴሪያን አንገሊካን ከአባላቶቻቸው ጋር ስለ ድርጅቶቻቸው የወደፊት ሁኔታ ከፍተኛ ውይይትእያደረጉ ሲሆን ከውይይቶቻቸው ርዕሶች በከፊል፥

- መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ ነው አይደለም?
- ክርስቶስ ከድንግል ተወልዶአል ወይስ የዮሴፍ ልጅ ነው?
- ግብረ ሰዶምን ሕጋዊ አድርገን የምናስፋፋው እንዴት ነው?
- የጸሎት መጽሐፋችን የሌሎችንም ሕዝቦች አማልክት ሊይዝ የሚችለው እንዴት ነው?
- እግዚአብሔር ወንድ ነው ወይስ ሴት?
- ከእግዚአብሔር ሌላ ሌሎች አማልክት አሉ ወይስ የሉም?
- የመጽሐፍ ቅዱስን እግዚአብሔር ለማምለክ ዘመናችን ይፈቅድልናል ወይ?
- እግዚአብሔር የለም የሚሉ ሰዎችን የቤተ ክርስቲያናችን አባላት ብናደርጋቸው ምን ችግር አለው? የሚሉና ሌሎችም ናቸው።[(5)]

እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው የውይይት ጥያቄዎች በራሳቸው እግዚኦ የሚያሰኙ ቢሆኑም ከውይይት አልፈው አብዛኛው የድርጅቶቻቸው አባላት

(5) በአሁኑ ወቅት አብዛኛዎቹ ስለዚሁ ሁኔታ ታላቅ ስብሰባ (ኮንቬንሽን) እያደረጉ ነው። የአንገሊካኑ ኮንቬንሽን ሚስቱንና ልጆቹን ትቶ ከሌላ ወንድ ጋር ግብረ ሰዶም የሚፈጽመውን ጳጳስ አድርጎ ሲያጸድቅ፥ የሜቶዲስቱ የአገልጋዮች ስብሰባ ደግሞ ግብረ ሰዶምን ለማጽደቅ እየተወያየ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

የሚቀበሉአቸው ናቸው ብንል ምን ትላላችሁ?

ዛሬ በፕሮቴስታንቱ ዓለም ውስጥ ግብረ ሰዶምን የተቀበለ ወይም የሚፈጽም፥ እግዚአብሔር የለም፥ ክርስቶስ ከሙታን አልተነሣም፥ መጽሐፍ ቅዱስ አፈ ታሪክ ነው፥ የዓለም ሃይማኖቶች በሙሉ የመዳን መንገድ አላቸው የሚሉ ፓስተሮችን ወይም አገልጋዮችን ማግኘት በጣም የተለመደ ነው። አንድ ሰው ወይም ጥቂት ግለሰቦች ቢሳሳቱ የእነርሱ ስህተት ነው እንላለን። እዚህ ላይ ጥያቄው ይህን ያህል ህዝብ እንዴት ወደዚህ ዓይነት ስህተት ሊደርስ ቻለ? ምክንያቱም በአንድም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ይህ ዓይነቱ ክህደት ያልነካው ያልዳሰሰው የፕሮቴስታንት ክፍል የለምና።

መልሳችን ፕሮቴስታንቲዝም በተሳሳተ አቅጣጫ ላይ የቆመ ስለሆነ ነው የሚል ነው። የሚመራኝ መንገድ የሚወስደኝ ወደ ገደል ከሆነ ስለመንገዱ መከራከር የለብኝም መንገዱ በራሱ የተሳሳተ ነውና። በአሁኑ ወቅት የፕሮቴስታንቱን ዓለም ለማስተካከልና ለማዳን ከፍተኛ ርብርቦሽ አለ። ነገር ግን ትርፉ ድካም ብቻ እየሆነ ነው። ከምዕት ዓመት በፊት እነ ስፔንሰር ሉተራንን በፔይቲዝም(6) እነጆን ዌስሊ አንገሊካንን በሜቶዲዝም(7) እነ ቻርልስ ፓርሃም የባፕቲስቱንና የሜቶዲዝሙን ዓለም በፔንቴኮስታሊዝም(8) ለማስተካከል ሞክረዋል፥ ዛሬ ግን ፔይቲዝምም ሜቶዲዝምም ፔንቴኮስታሊዘምም የከሠረ ንግድ እንደሆነ እየተመለከትን ነው።

(6) ከ1635-1705 ዓ.ም የኖረው ሉተራዊው ፊልፕ ጃኮብ ስፔንሰር በሉተራን ውስጥ የታየውን እምነት አልባነትና አለመርካት ለማስተካከል የምከረና የ«ፔይቲዝም» እንቅስቃሴ አባት ነው። ፔይትዝም ቃሉ የተወሰደው በጊዜው የእንቅስቃሴው ዋና መጽሐፍ ከነበረው ከ« ፒያ ዴዚዴሪያ» (ተቀደሰ መሻት ) ከሚለው መጽሐፍ ነው። ሃይማኖተኝነት በቅድስና መስጠት እንደማለት ነው። ነገር ግን እንቅስቃሴው የተመሠረተው በዚያው በሉተር መንገድ ስለሆነ ሉተራንን የሚያድን ሆኖ አልተገኘም።





ምክንያቱም ፔይቲዝምና ሜቶዲዝም በለዘብተኛ ቴዎሎጂ ሲዋጡ፥ ፔንቴኮስታሊዝም ደግሞ ከምሥረታው ጀምሮ በሰባልዮሳውያን ኑፋቄ ሲበከል፥ አሁን ደግሞ ይባስ ብሎ በሜታፊዚክስ አስተሳሰብ በተመሠረተው የ«እምነት እንቅስቃሴ» ሙሉ በሙሉ እየተዋጠ ነው። እነዚህ እንቅስቃሴዎች እግዚአብሔር ያዘጋጃቸው ሳይሆኑ ሰው ሠራሽ መፍትሔዎች ስለሆኑ ውጤታማ ሊሆኑ አልቻሉም።

ይህን ግራ የሚያጋባና የሚያሳዝን የፕሮቴስታንት አካሄድ በጥሞና የተከታተሉ አንዳንድ የእምነቱ ተከታዮች እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን መፍትሔ ተከትለዋል። ያም እግዚአብሔር ከቀድሞ ጀምሮ ያዘጋጃትን እውነተኛውን ቤተ ክርስቲያን መከተል ነው።

(7) በፕሮቴስታንቱ ዓለም ውስጥ ስለሚታዩት እንቅስቃሴዎች ዓይነተኛ ምሳሌ የሚሆነን ሜቶዲዝም ነው። በ1703-1791 ዓ. ም. በኖረው በጆን ዌስሊ የተመሠረተው ይህ እንቅስቃሴ፥ መነሻ ዓላማው በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታየውን ዓለማዊነትና የተሳሳተ አስተምህሮ አርማለሁ በማለት ነው። ጆን ዌስሊ ከወንድሙ ከቻርለስ ዌስሊና በስተኋላም ከታዋቂው የሚቶዲስት ሰባኪ ከጆርጅ ዋይት ፊልድ ጋር «ሜቶዲስት» የተባለ ስም የተሰጠውን እንቅሲቃሴ ጀመሩ። በስተኋላም የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ስታባርራቸው ሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ተባሉ። ብዙም ሳይቆዩ ግን ራሳቸው እንደ እንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ሆኑ። ዛሬ ወንድ ለወንድ ለማጋባትና የእግዚአብሔር ቃል ሐሰት እንደሆነ ለመወሰን ደፋ ቀና ከሚሉት አንዱ የሜቶዲስት ቤተ ቤተ ክርስቲያን የተባለው ነው ።

(8) «ጴንቴቆስጤ» በሚል መለያ የሚታወቀውን እንቅስቃሴ የጀመረው ቻርለስ ፓርሃም የተባለ በአሜሪካ በካንሳስ ስቴት ቶፔካ በሚባል ከተማ ይኖር የነበረና ከሜቶዲዝም ተገንጥሎ በወጣ « ቅድስና » በሚባል ቡድን ውስጥ ሰባኪ የነበረ ነው። በሐዋርያት ሥራ ላይ የታዩትን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ማግኘት አለብን ብሎ አርባ የሚያህሉ ተማሪዎቹን ይዞ የሐዋርያት ሥራን ያጠና የነበረው ቻርለስ አንድ ቀን በአንዲት የአሥራ ስምንት ዓመት ወጣት ላይ እጁን ሲያሳርፍ ልጅቱ የሆኑ እንግዳ የሆኑ ቃላት ማውጣት ጀመረች። ይህን ጊዜ ቻርለስ ፓርሃም ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክት ነው። ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ከተሞሉ በ«ልሳን» ይናገራሉ በማለት የጴንጤቆስጤ እንቅስቃሴ የተባለውን ጀመረ። የሚያሳዝነው ግን ብዙዎቹ የመጀመሪያዎቹ ጴንጤዎች በሥላሴ የማያምኑ የነበሩ መሆናቸው ነበር። ስለእነርሱ በነገረ እግዚአብሔር ምእራፍ ላይ በሰፊው ታትቶአል።



www.ethiopianorthodox.org

በዚህም መሠረት በአሁኑ ወቅት በሺዎች የሚቆጠሩ ፕሮቴስታንት አገልጋዮችና የነገረ መለኮት ሊቃውንት መጽሐፍ ቅዱሳቸውን እየመረመሩ ወደ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የሚመለሱና ሌሎቸንም የሚመልሱ ሆነዋል። ስለ እነዚህ ወደ እናት ቤታቸው ስለተመለሱት ሰፋ ባለ ሁኔታ ዘርዘር አድርገን በሌላ ምእራፍ ላይ እንገልጣለን።

## የዶ/ር ቶሎሳ ክስና እውነታው

በውጭ ያሉት ፕሮቴስታንቶች በእንደዚህ ዓይነት ግራ መጋባት ውስጥ ሲሆኑ፥ በኢትዮጵያውያን ፕሮቴስታንቶች ዘንድ የሚታየው ነገር ደግሞ ራሱን የቻለ ሰፊ ሐተታ የሚያስፈልገው ነው። በተለይም ላለፉት ሠላሳ ዓመታት በኢትዮጵያ ምድር ላይ የተነሡት ፍልስፍናዎች ሊያፈርሱዋት ወይም ሊያደክሙአት የሞከሩአት፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ነበር።[9] በሀገሪቱ ውስጥ የታየውን ተከታታይ የሆነ የመንግሥት ለውጥ ተከትሎ በቤተ ክርስቲያኒቱ በተከሠተው አስተዳደራዊ ችግር መዳከሙዋ የልብ ልብ ስለሰጣቸው፥ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንቶች ለያዥ ለገራዥ ያስቸገሩ ሆነዋል።

የዐረብ ሊግ ዓይን አውጥቶ ኢትዮጵያ የዐረብ ሊግ አባል እንድትሆን ሲጠይቅ፥ ከሳውዲ ዐረቢያና ከፓኪስታን መድራሳዎች[10] የሚወጡ ወጣቶች በሰላም

---

*(9) ጥብቅ ምስጢር ተብሎ የወጣው የደርግ የውስጥ መግለጫ የዐረቦችን ፔትሮ ዶላር ከመናፈቅና ውግዞታቸውንም ከመፍራት የተነሳ በእስላሙ ላይ ጫናው ላላ እንዲል ሲያዝ «ተከላካይ» የሌላት የመሰላቸውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ግን ለማጥፋት ገዳማቱን ለማዳከም ምን መደረግ እንዳለበት በሰፊው ይተርካል። ኢትዮጵያውያን ፕሮቴስታንቶችም አሁን ሊከተሉት የሚፈልጉት ይህን የማርክሲስቶች መመሪያ ይሆን እንዴ?*

*(10) የቁርአን ትምህርት ቤቶች*





በአንድነት የኖረውን የኢትዮጵያ ሙስሊም በጭፍን አክራሪነት ሊለውጡት ደፋ ቀና ሲሉና በፔትሮ ዶላር የደለቡ ሰባኪዎቻቸው ኢትዮጵያን በመስጊድ ግንባታ ሊያጥለቀልቁ ሲሞክሩ የኛዎቹ ፕሮቴስታንቶች የታያቸው «አዲስ መገለጥ»፥ በዓለም ካሉት ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት አንድዋ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ማጥቃት ነው። ምክንያቱም ለእነርሱ ከክርስቶስ መንግሥት በላይ የእነርሱ ጎጥ (ዲኖሚኔሽን) ትልቅ ሥፍራ አለውና ። ለነገሩ አንድ ታዋቂ ተናጋሪ «ክርስትና ኢየሩሳሌም ሳለ ሕይወት ነበር። ሮም ሳለ ድርጅት ሆነ አሜሪካ ሲደርስ ንግድ ሆነ» እንዳለው ከሕይወት ይልቅ ንግዱና ጥቅሙ ስለበለጠ እንዲህ የሆነው። ስለሆነም የምዕራቡ ዓለም ክርስትና የዓለም መሳቂያ በሆነበት በአሁኑ ወቅት፥የኛዎቹ ደግሞ ክርስቶስን ሳይሆን ማጠፊያ ያጠረውን ፕሮቴስታንቲዝምን በፖለቲካ በጦርነት በረሃብና በበሽታ ግራ ለተጋባው ወገናችን ለመሸጥ ደፋ ቀና ይላሉ።

ለዚህ ንግዳቸው ደግሞ እንቅፋት የሆነችባቸው፥ ለሁለት ሺህ ዓመት በዚህች ምድር ላይ ብቸኛዋ አማራጭ ሆና ሕዝቡዋን ከስህተት የጠበቀችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ናት። ይህ ደግሞ እጅግ ያስቸገራቸው ሊሸሹት የማይችሉት እውነት ስለሆነባቸው፥ይህችን ሕያው የእግዚአብሔርና የታሪክ ምስክር የሆነችውን ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ በስውር ያለ የሌለ ኃይላቸውን ከማሠማራታቸው ባሻገር በአደባባይ እየፎከሩ ይገኛሉ።

በቅርቡ በዚህ በሀገረ አሜሪካ የሰማነው፥ የአትላንታ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መሪ የሆኑት የዶ/ር ቶሎሳ ስብከት፥ ይኸንኑ ጥልቅ የሆነ ጥላቻ መንፈሳዊነት በሌለው ቋንቋ ይፋ ያወጣ ነበር። ዶ/ሩ እንደበታቸው



www.ethiopianorthodox.org

ሊገልጠው የቻለውን ያህል ቤተ ክርስቲያኒቱን በዛፍ አምላኪነት፥በፍጡራን አምልኮ፥ በአእምሮ በሽተኝነት፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ኢ-አማኒነት ወይም አላዋቂነት፥ በድህነትና በችግር አምጪነትና ለሕዝቡዋ መጨቆን ምክንያት ምክንያት በማድረግ ከሰዋታል።

ይህ የዶክተር ቶሎሳ ስብከት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና ምእመናንን ያስቆጣና ልብ የሰበረ ድርጊት ሲሆን፥ ስብከቱም የፖለቲካና የዘረኝነት አንድምታም ስለነበረው ከቤተ ክርስቲያኑዋ ውጭም በሰፊው ያነጋገረ ነበር። ለዚሁ ለዶ/ሩ ክስ ከየአቅጣጫው መልስ ለመስጠት እየተሞከረ ሲሆን በአጠቃላይ በቤተ ክርስቲያናችን ካህናትና ምእመናን መካከል የታየው ጥልቅ የሆነ በሳልነት ሁላችንን ያስደሰተ ነው። ነገር ግን የተሰጡት አጸፋዎች ለክሱ መልስ ነው እንጂ ክሱ ስለተነሳበት ጥልቅ የሆነ የተሳሳተ አስተሳሰብና ትምህርት የሚያብራሩ አይደሉም።

ከሁሉ የሚገርመው ዶ/ሩ ይህን ሲናገሩ የራሳቸው የእምነት ድርጅት በብርሃን ፍጥነት ወደ ገሃነማዊ ትምህርት እየተምዘገዘገ መሆኑ ነው። የራሳቸውን ቤት ሳያጸዱና ሳይመለከቱ የሰውን ቤት ለዚያውም ከጥላቻና ከባዶ ኩራት በመነጨ ንግግር እንዲያ መሳደባቸው «የራሱዋ እያረረባት የጎረቤቱዋን ታማስላለች» የሚለው ምሳሌያዊ ንግግር እንዲፈጸምባቸው አድርጎባቸዋል።

ስለዚህ ይህች አነስተኛ መጽሐፍ ዶ/ር ቶሎሳ ላነሱት ክስ መልስ ከመስጠት ባሻገር፥ ስለ ዶ/ሩ የአስተሳሰብ መሠረት የምትመረምርና ታሪካዊና ሥነ መለኮታዊ ስህተቱንም የምትገልጥ ናት። ከሳሽ የክሱን ቃል በወረወረ ቁጥር መልስ ለመስጠት መጽሐፍ





ከማገላበጣችን በፊት ከሳሾቻችን እነማናቸው የሚለውን ማጤን አለብን። «ያረረውን» የእነርሱን ምድጃ በደንብ እንመለከተዋልን። ከዚሁ ጋር ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከሚስዮናውያን የተወለዱ የዚህች ቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ለምን ይህችን ቤተ ክርስቲያን አምርረው እንደሚጠሉ ማወቅ አለብን።



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ሁለት

## የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ እውነተኛ ገጽታ

*እግዚአብሔር ያሳፍረውና ጠላታችን ዲያብሎስ በዓይኖቻችን ፊት ይቆማል። ክፍት የሆነ የልባችን በር በየት በኩል እንደሆነ እስከሚያገኝ ድረስም ይጠብቃል። ባገኘም ጊዜ ጦሩን ወደ ነፍስ ይወረውራል። የዚህን ዓለም ፍቅር፥ ዋዛ ፈዛዛን ትእቢትን ሐኬትን ያመጣል። የህማምን ምንጭና የልቡና መደፍረስንም ይሰጣል።*

*ማር ይስሐቅ አንቀጽ 20 ም.*

ብዙዎች የታሪክ ምሁራን በአጽንኦት እንደሚናገሩት የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ የተነሣው ከመንፈሳዊ እይታ ወይም ከእግዚአብሔር ቃል አስተውሎት፥ ሳይሆን ከጊዜው የሰዋዊ ፍልስፍና (ሂዩማኒዝም) ከፖለቲካ ጥቅምና ጭፍን ከሆነ ሀገር ወዳድነት ነው። በአውሮፓ ዩኒቨርስቲዎችና የሥነ ጥበብ አደባባዮች ይታይ የነበረው ምድራዊውን ነገር ማዕከል ማድረግና መንፈሳዊ ነገሮችን ከሥነ ጥበብ፥ ከሥነ ጽሑፍና ከፍልስፍና የማውጣት ሂደት ሬኔሳንስን ተከትሎ በሰዋዊ አመክንዮ የእግዚአብሔርን ቃል መመርመር መላዋን አውሮፓ አጥለቅልቆአት ነበር። በዚህም ምርመራቸው ብዙዎች ወደ ብዙ ስህተትና ህልዎተ እግዚአብሔርንም እስከ መካድ አድርሶአቸዋል።(11)

*(11) በተለይ በኢጣሊያ የተጀመረው የሂውማኒዝም እንቅስቃሴ የጥንቶቹን አህዛብ አስተሳሰብና ባህል ለማንሰራራት ከፍተኛ ትግል ያደረገ ሲሆን መሪ መፍከራቸውም « አድ ፎንቴ» ወደ ምንጩ መመለስ የሚል ነበር። በማርቲን ሉተር ለተነሳው እንቅስቃሴ ከፍተኛ ድጋፍ ከማድረጋቸውም በላይ በስተኋላ እስከሚጣሉ ድረስም ተባባሪዎች ናቸው። ፕሮቴስታንቶች ላይ ከፍተኛ የአስተሳሰብ ተጽእኖ አድርጎአል የሚባለው በጊዜው ...*





በአውሮፓው የፕሮቴስታንቶች እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ተካፋይነት የነበራቸው ማርቲን ሉተር፥ ካልቪን፥ ቶማስ ክራንመር፥ ዝዊንጊሊና ሜላንክቶን በሂውማኒስቶች አስተሳሰብ ውስጥ የተማሩ ናቸው። በብዙ አስተሳሰባቸው ላይም የእነርሱ ተጽእኖ የሚታይባቸው እንደሆኑ የፕሮቴስታንቶችን እንቅስቃሴ ያጠኑ ሰዎች ይናገራሉ። ይህም ባዶ የሆነ የታሪክ ሰዎች አስተያየት ብቻ እንዳልሆነ ይታወቅ ዘንድ ፥ እነማርቲን ሉተር ለአመለካከታቸው በአብዛኛው መሠረት ያደረጉት ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ ሰዋዊ አመክንዮን ነው።

ማርቲን ሉተርም ሆነ ሌሎቹ የፕሮቴስታንት መሥራቾች በተነሡበት ወቅት፥ ከሂውማኒዝም በተጨማሪ የረዳቸው፥ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እጅግ አስከፊ ወደ ሆነ የሥልጣን፥ የገንዘብና የመንፈሳዊ ዝቅጠት ውስጥ መግባትዋ ነበር። ከዚህም ጋር ስፍር ቁጥር የሌለውን ሀብትዋን የራሳቸው ለማድረግ፥ በየሀገሩ ያሉት መሣፍንት አሰፍስፈው የሚጠብቁበት ወቅትም ነበር። በዚህ ጊዜ ነው ከሂውማኒስት፥ ከፖለቲካው ዓለም እንዲሁም ከተማረበትና ከኖረበት የአውግስጢኖሳዊና ስኮላስቲካዊ አስተሳሰብ ጋር የተቀያየጠ አስተሳሰብ ይዞ፥ ቤተ ክርስቲያንን ማለቂያ ወደሌለው ክፍፍል ውስጥ ይጥላት ዘንድ ማርቲን ሉተር የተነሣው።

---

*... የሂውማኒስቶች አባት በመባል የሚታወቀው ኤራስመስ ነው። 1469-1535 ዓ. ም. የኖረው ዴዚዴሪየስ ኤራስመስ ምንም እንኳዋን አንዳንድ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ስህተቶች ማርቲን ሉተር መተቸቱን ቢደግፍም በቤተ ክርስቲያን ላይ ያሳየውን አመጽ ግን በጥብቅ ተቃውሞአል። በሁለቱ መካከል የተከናወነው ታላቁ ግጭት የነገረ መለኮት ግጭት ሲሆን ማርቲን ርእሱም ስለ ሰው ነጻ ፈቃድ ነበር።*



www.ethiopianorthodox.org

## የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ

ቀዳማዊ ልዮ 451 ዓ.ም. በአምባገነንት ያለምንም ውይይት ቤተ ክርስቲያንን ለሁለት ከከፈለ በኋላ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ወደ ተለየ አቅጣጫ ነበር ያመራችው። ፓፓዎቹዋ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አድራጊ ፈላጬቹ እኛ ነን ከማለት አልፈው፥ ነገሥታትን መሾምና መሻር ብሎም ለራሳቸው ምድራዊውን ሥልጣን መፈለግ ጀመሩ። ይህን ሥልጣናቸውን ለማሳየትም ፓፓው ቀድሞ በቤተ ክርስቲያን የሌለና አዲስ ዶግማ (የእምነት አንቀጽ) መደንገግ ይችላል ማለት ጀመሩ። በዚህም መሠረት በቁስጥንጥንያ የቤተ ክርስቲያን ኢኩሜንካል ሲኖዶስ በ381 ዓ.ም የተወሰነውን ወደጎን በማድረግ «መንፈስ ቅዱስ ከአብም ከወልድም ይሠርጻል» ብለው አወጁ። ይህም በላቲኑ «ፊልዮኬ» ይባላል።

ከኬልቄዶን ጉባኤ ጀምሮ የሮም ካቶሊክን ስትከተል የነበረችው የቁስጥንጥንያ (ግሪክ) ቤተ ክርስቲያንም ድርጊቱን ብትቃወምም የሮም ባለሥልጣናት ቁስጥንጥንያ ምንም ሥልጣን እንደሌላትና ጸጥ ብላ መገዛት እንዳለባት አስታወቁ። የቁስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን ለረጅም ጊዜ ብታስታምም ሁኔታው ስላልተስተካከለ ከሮም ቤተ ክርስቲያን በ1054 ዓ.ም ተለየች። ይህም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ «ታላቁ መከፋፈል» The Great Schism ይባላል።

የሮም ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ሆነ ችግር ውስጥ ያመራችው፥ በውስጥዋ አዳዲስ የነገረ መለኮትና የፍልስፍና አስተሳሰብ ያላቸው ትምህርት ቤቶች በተጀመሩ ወቅት ነው። ብዙዎች የአውሮፓን ታሪክ ያጠኑ የታሪክ ሊቃውንት እንደሚናገሩ የአውሮፓ ሬኔሳንስ፥ የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ፥ ዘመነ





አብርሆትና የፈረንሳይ አብዮት (ፓሪስ ኮሚዩን) ብሎም በመጨረሻ የጀርመን ናሽናል ሶሻሊስት ፓርቲ (ናዚ) እርስ በእርሳቸው የተያያዙና ሊነጣጠሉ የማይችሉ የታሪክ ሂደቶች ናቸው ለዚህ ደግሞ የቴዎሎጂ መሠረት የሆነው በነቶማስ አኩናስ መሰረቱን አድርጎ የተጀመረው የስኮላስቲክስ እንቅስቃሴ ነው። ይህ እንቅስቃሴ በአንድ በኩል በነገብርኤል በዬ የሚመራና የሰው ልጅ በፈለገው ሁኔታ ውስጥ የማለፍ ሁሉን ነገር የማወቅ ነጻነትና ፈቃድ አለው የሚል ቡድን ሲኖር፥ በሌላ በኩል ደግሞ በአውግስጢኖስ የመጨረሻ የአገልግሎት ዘመን ላይ ጳላግዮስ በሚባል የእንግሊዝ መነኩሴ ላይ የተነሳውን ተቃውሞ ላይ በማተኮር የሰውን ነጻ ፈቃድ ሙሉ በሙሉ የሚክዱ የአውግስጢኖስ ተከታዮች ነን በሚሉ ይመራ ነበር። የእነዚህ ሁለት ተቃራኒ ቡድኖች የቴዎሎጂ ልዩነትና የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናት ዝቅጠት የሮማ ቤተ ክርስቲያንን በአጠቃላይ ወደ አልታሰበ ሁኔታ ውስጥ እንድትገባ አደረገ። የነዚህን ሁለት ትምህርት ቤቶች ማለትም የአውግስጢኖሳውያንን ትምህርትና የስኮላስቲክስን ትንታኔ ከሂውማኒዝም አጣምሮ የያዘው ማርቲን ሉተር አቅጣጫ በጠፋባት በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ላይ ተነሳባት።

## ማርቲን ሉተርና የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን

ማርቲን ሉተር የአውግሰጢኖሳውያን ተከታይ የሆነ ካቶሊካዊ መነኩሴ ነበር። ወደ ምንኩስናው ዓለም የገባውም በአንድ ዝናባማ ወቅት በመብረቅ ደንግጦ ለቅድስት ሐና ብጽአት በመግባት እንደሆነ ይነገራል። ማርቲን ሉተር በካቶሊክ ቤተ ክርሰቲያን ውስጥ ሆኖም ይሁን የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ ከመሠረተ



www.ethiopianorthodox.org

በሁዋላም፥ ስለ መዳኑ በጣም የሚጨነቅና አንዳንዶች እንደሚሉትም በመንፈስ ጭንቀት ይሰቃይ የነበረ ነው። ማርቲን ሉተር በስፋት የሚታወቅባቸውን የፕሮቴስታንት እምነት መሠረቶቹን የተረዳው ወይም ወደዚያ አመለካከት የደረሰው ከእንቅስቃሴው አቅጣጫ መቀያየር ጋር ነው። ለማርቲን ሉተር በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ላይ በተቃውሞ መነሳት ምክንያት የሆነው የልፋፊ ጽድቅ (ኢንደልጀንስ) ሽያጭ ነው። ነገሩ እንዲህ ነው።

የሮሙ ፓፓ ልዮን አሥረኛ በቫቲካን የሚገኘውን ታላቁን የቅዱስ ጴጥሮስ ባሲሊካ ያሠራ ነበር። ለህንጻው ማሠሪያ እንዲሆን ገንዘብ ለሚሰጡትም ከፑርጋቶሪ እሳት የሚድኑበት አዋጅ (ኢንደልጀንስ) እንደሚሰጣቸው አወጀ። ይህ በሮም ፓፓዎች ዘንድ በመካከለኛው ዘመን የተለመደ ልምምድ ነበር። ይህ የፓፓው አዋጅና የኢንደልጀንስ ትምህርት ቅር ያሰኛቸው አንዳንድ የጀርመን መሣፍንት ነበሩ። ከነዚህም መካከል ጠቢቡ ፍሬድሪክ የተሰኘውና እርሱን የመሳሰሉ መሣፍንት «ጀርመን የፓፓው ላም ሆነች» የሚል ቅሬታ ማሰማት ጀመሩ። በግዛታቸውም ይህ አይነቱ ስብከት እንዳይሰበክ መከልከል ጀመሩ። በአንዳንድ የጀርመን ግዛቶች ግን የፓፓው የኢንደልጀንስ አዋጅ ይሰበክ ነበር። በተለይም ይህን የፓፓውን ትእዛዝ በዋናነት የሚያስፈጽሙት የዶሚኒካን ማህበር መነኮሳት ሲሆኑ በጀርመን በተለይ ታዋቂ የነበረው ዮሐንስ ቴዝል የተባለው የፓፓውን አዋጅ «ገንዘባችሁን ወደ ሙዳዩ ስትጥሉና የሳንቲሙዋ ድምጽ ሲሰማ ሌላዋ ነፍስ ከፑርጋቶሪ ዘላ ትወጣለች» ከሚል ማስታወቂያ ጋር ይሸጥ ነበር።

በዚህ ወቅት ማርቲን ሉተር በዊተርበርግ ዩንቨርስቲ የቴዎሎጂ አስተማሪና በጠቢቡ ፍሬድሪክ ቤተ





መንግስት የመሥፍኑ ሰባኪ (መምህረ ንስሐ) ነበር። ይህን የመሣፍንቱን አለመደሰትና የፓፓው ተከታዮች በሚሰበስበው ገንዘብ የሚያደርጉትን ስለተመለከተ በኦክቶበር ሠላሳ አንድ 1517 ዓ. ም. ላይ ዘጠና አምስት አንቀጾች ያሉት መግለጫ ይፋ አደረገ። በአብዛኛው አንቀጾቹ የፓፓውን ሥልጣን የሚጋፋ ነበሩ። ይህ ደግሞ በፓፓው ጭቆና ጠርዝ ላይ ያለውን የጀርመን ባላባት ሁሉ በአንዴ አነሣሣው።

ሉተር ዘጠና አምስቱን አንቀጾች ለጀርመን ሕዝብ ቢያቀርብም የሚቀጥለው ምን እንደሆነ አያውቅም ነበር። ሌላው ቀርቶ በስተኋላ የፕሮቴስታንት እምነት መለያ የሆኑት «ሦስቱ ሶላዎች ማለትም እምነት ብቻ (ሶላ ፊዴ) ጸጋ ብቻ (ሶላ ግሬሽያ) መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ (ሶላ ስክሪፑቸራ) የመጡት ከካቶሊክ ሊቃውንት ጋር በሚያደርገው ክርክር ውስጥ ነው ። ለምሳሌ በክርክሩ የመጀመሪያ ወቅቶች ሉተር የአበውን መጻህፍት ይጠቅስ ነበር። በስተኋላ ግን ይህ አካሄዱ የማያዋጣው መሆኑን ሲያውቅና አበው ያስተማሩትን የምትከተል ከሆነ የምተወደውን ወስደህ ሌላውን መተው የሉብህም የሚለው አስተሳሰብ ከካቶሊክ ምሁራን እያየለበት መጣ። በዚህ ጊዜ «መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ» የሚለውን አስተሳሰብ አስቀመጠ። ይህ ደግሞ ዓይነተኛ የሆነ የፕሮቴስታንት ባህርይ ነው። የእንቅስቃሴአቸው አቅጣጫ የሚወሰነው በግለሰቦች ልምምድና አስተያየት ወይም «ልዩ መገለጥ ነው» እንጂ በእግዚአብሔር ቃል ወይም ለቅዱሳን ሐዋርያት ከዚያም ለአበው አንድ ጊዜ ፈጽሞ የተሰጠችው ሃይማኖት ላይ በመመርኮዝ አይደለም።

## ማርቲን ሉተርና የፓለቲካ አቅዋሙ



www.ethiopianorthodox.org

ዛሬ በብዙዎች የፕሮቴስታንት ሰባኪዎች እንደሚሰበክልን ማርቲን ሉተር የድሆች ወዳጅና ሰላማዊ አልነበረም። እንዲያውም ያካሄደው አብዮት ስኬታማ የሆነው ከመሣፍንቱ ጋር በነበረው ጥብቅ ዝምድና ስለሆነ የታሪክ ጸሐፊዎች ማጅስትሬት ሪፎርሜሽን በመሳፍንቱ የተመራ ተሐድሶ ብለው ነው የሚጠሩት።

በዚህ ምክንያት በማርቲን ሉተር የተመራው እንቅስቃሴ ሁለት ዓይነት የፖለቲካ ዓላማ ነበረው። አንደኛው የጀርመን መሣፍንት ልብ ውስጥ የተቀጣጠለውን ጀርመንን ከፓፓውና «ከተቀደሰው ሮማን ኢምፓየር» ነጻ የማድረግ እንቅስቃሴ መንፈሳዊ ድጋፍ መስጠት ነው። ይህ የፖለቲካ ዓላማ እንዲፈጸም ሉተር ስለ ጀርመን ሕዝብ ታላቅነት ከፍተኛነት ከመናገሩም በላይ፥ በዘራቸው ጀርመናውያን (አርያን) ስላይደሉ ሰዎችም፥ ወደ ፊት በጀርመን ታሪክ ውስጥ ጥቁር ነጥብ ለሆነው ዘር የማጥፋት ወንጀል መሠረት ሆኖ ያገለገለ የጥላቻና የዘረኝነት ንግግር አድርጓል፥ ጽሑፍም ጽፏል። በናዚ ጀርመን ውስጥ ተወዳጅ ከሆኑትና ከሚጠቀሱት መካከል ፍሬድሪክ ኒቼና ማርቲን ሉተር ዋናዎቹ ነበሩ።

---

*(12) በእንዲህ ያለ የፖለቲካ አስተሳሰብ ተነሥቶ የቤተ ክርስቲያንን አካሄድ መቀየር ለፕሮቴስታንት መሪዎች እንግዳ አልነበረም። ለምሳሌ በእንጊሊዝ አገር በካንተርበሪው ሊቀ ጳጳስ በቶማስ ክራመር የተመራውና ለአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን መመሥረት ምክንያት የሆነው እንቅስቃሴ፥ ለምሥረታው ምክንያት ያደረገው ሄንሪ ስምንተኛ የተባለው የእንግሊዝ ንጉሥ ከሮማ ፓፓ ጋር መጣላቱን ተከትሎ ነው። የጥላቻውም ምክንያት ሄንሪ ስምንተኛ ሚስቱን እንዳይፈታና ሌላ እንዳያገባ የሮማው ፓፓ መከልከሉ ነበር። በዚህ ወቅት የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ አራማጆች የንገሡን እርምጃ ስለደገፉና ንጉሡ የሚቆምጥለትን በእንግሊዝ ያለውን የሮም ሀብት በተለይም ገዳማቱን እንዲዘርፍ ስለፈቀዱለት የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ከሮም ቤተ ክርስቲያን ተለይታለች።*





በሁለተኛ ደረጃ ከላይ እንዳልነው ሥፍር ቁጥር የሌለውን የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሀብት በጀርመን መሣፍንት ሥር ማስቀመጥ ነው። የሮማ ካቶሊክ ካላት የፖለቲካና የመንፈሳዊ ሥልጣን የተነሳ ከፍተኛ ሀብት አካብታ ነበር። እነዚህም በየግዛቶቹ ባሉት ገዳማትና ጳጳሳት እጅ ነበሩ። ሉተር ባደረገው እንቅስቃሴ የሮማን ካቶሊክ ሀብቶችና ገዳማት እንዲዘረፉና በመሳፍንቱ እጅ እንዲወድቁ የሚያደርግ ነበር።(12)

## <u>የጀርመን ገበሬዎች አመጽና ሉተር</u>

የሉተርን የስርብትና (የፖለቲካ) አካሄድ ገሐድ ያወጣው በራሱ በሉተር ስብከት ተነሣሥተው በመሣፍንቶቻቸው ላይ ያመጹትን የጀርመን ገበሬዎች፥ እንዴት ከመሳፍንቱ ጋር አብሮ እንዳስጨፈጨፈ ስንመለከት ነው። ማርቲን ሉተር የሮማ ፓፓን ለመቃወም ይመቸው ዘንድ ጸረ ሥልጣን የሆነ አቀዋም ነበረው። በዚህም ምክንያት ይህን የሉተርን ትምህርት የሰሙና ሰው በማንም ተጽእኖ ሥር መውደቅ የለበትም ያሉ ደሆች የጀርመን ገበሬዎች የሮማ ካቶሊክን ሀብት ለመዝረፍ ይሽቀዳደሙ በነበሩት በጀርመን መሣፍንት ላይ ተነሡባቸው። ሉተር ሁኔታው እርሱ ወዳላሰበው አቅጣጫ መሄዱንና በድርጊቱም ቀጥተኛ ተጠያቂ እንደሆነ ሲያስተውል የጀርመን መሳፍንት ገበሬዎችን መጨፍጨፍ እንዳለባቸው የሚያነሳሳ ጽሁፍ ጻፈ። በተለይም ከአንድ መቶ ሺ በላይ የጀርመን ገበሬዎች በታረዱበት ምሽት ያወጣው ድርጊቱን የሚደግፍ ጽሁፍ እጅግ አሰቃቂ እና በግፍ የተሞላ ነበር።

ሉተር በዚያች የግፍ ምሽት ባወጣው መግለጫ ላይ «ማንኛውም መሪ፥ ሌላው ቀርቶ ወንጌልን



www.ethiopianorthodox.org

ያልተቀበለ (ፕሮቴስታንት ያልሆነ) ቢሆንም እንኳን፥ ያለምንም ፍርድ እነዚህን ገበሬዎች ቢቀጣቸውና ቢገድላቸው እኔ አልቃወመውም። ምክንያቱም መብቱ የእርሱ ነውና። እነዚህ ገበሬዎች ለወንጌል የሚከራከሩ አይደሉምና።እነዚህ የማይታመኑ፥ የማይታዘዙ ፥አመጸኞች፥ ነፍሰ ገዳዮች፥ዘራፊዎችና ተሳዳቢዎች ስለሆኑ፥ ሌላው ቀርቶ አህዛብ እንኳን ሊቀጡአቸው ይገባል።.....» ካለ በኋላ የእርሱ ተከታዮች የሆኑትን ፕሮቴስታንት መሪዎችንም፥ ገበሬዎቹ ሰይጣኖች እንደሆኑና እነርሱንም መጨፍጨፍ የጽድቅ ሥራ ስለሆነ በንጹህ ህሊና እንዲያከናውኑት መክሮአቸዋል።[13] በተለይም መሳፍንቱን «እነዚህን ገበሬዎች ጨፍጭፉአቸው እረዱአቸው ውጉአቸው» ብሎ የመከራቸው ምክር የጀርመን ገበሬዎች ወደ ባሰው የክህደት መንገድ ወደ አናባፕቲስት እንዲጓዋዙ ሲያደርጋቸው ሉተርንም «ባለመንታ ምላስ» ከሃዲ ብለው እንዲጠሩት አድርጎአቸዋል።[14]

## እውነት በማርቲን ሉተር እጅ

ስለ ማርቲን ሉተር የሕይወት ታሪክ የጻፉ ሰዎች ስለኋላ ታሪኩ ከመጻፍ በብዙ ታቅበዋል። ይህም ያለምክንያት አይደለም። ማርቲን ሉተር ከጊዜ በኋላ ትምህርቱና የተከተለው መንገድ በሕይወቱ ላይ መንጸባረቅ ጀምሮ ነበር። በዚህ ወቅቶች ያደረጋቸው አንዳንድ ነገሮች ብዙዎቹን ተከታዮቹን ቆም ብለው እንዲመረምሩ አድርጎአቸዋል።

---

*(13) Against the Robbing and Murdering Hordes of Peasants, in E. G.Rupp and Benjamin Drewery, Martin Luther : Documents Of Modern History. New York, St. Martin's Press 1970. pp.121-126.*

*(14) Roland H. Bainton, Here I Stand A Life of Martin Luther . New York 1950 Mentor book pp.217-220*



ሰውሩ አደጋ

ከእነዚህም አንዱ ለፖለቲካ ጥቅሙ ሲል ቀዋሚውንና መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የጋብቻ ህግ እንዴት አድርጎ ለማመቻመች እንደሞከረ ነው። ጉዳዩ እንዲህ ነው። በማርቲን ሉተር ትምህርት ተስቦ ወደ ፕሮቴስታንቱ ዓለም ከገቡት የጀርመን መሣፍንት አንዱ የሆነው ፊልፕ ዘሄስ በግል ሕይወቱ አስቸጋሪ ነገር ስለነበረበት፥ ወደ ቅዱስ ቁርባን ለመቅረብ እንደማይችል ለማርቲን ሉተር ይነግረዋል። መሥፍኑ ፊልፕ ዘሄስ የፈጸመው ጋብቻ የሥልጣን ጋብቻ፥ ማለትም ሥልጣኑን ለማስፋት ከሌላ ሥልጣን ካለው ክፍል ጋር የተደረገ ጋብቻ እንጂ በፍቅር ላይ የተመሠረተ ስላልነበረ፥ ከጋብቻ ውጭ ይሄድ ነበር።

ሉተር ይህን የመሥፍኑን ችግር እንደተረዳ መሥፍኑን ደስ የሚያሰኝ ነገር ግን ከክርስትና ውጭ የሆነ ምክር ሰጠው። ይኸውም መሥፍኑን ከሌላ ሴት ጋር በድብቅ በማጋባት ሕጋዊቷ ሚስቱ ሳታውቅ ሁለቱንም ሴቶች ይዞ እንዲቀመጥ የሚል ነበር።[15]

ነገር ግን ሁኔታው ማርቲን ሉተር እንደጠበቀው አልሆነም። ምክንያቱም መሥፍኑ በስውር ያገባት ሴት እናት፥ ጋብቻው ይፋ መውጣት እንዳለበት መናገር ጀመረች።

---

*(15) ሉተር ይህ ምሥጢር ቢወጣ የሚያመጣውን ችግር የገለጠበትና እርሱን በታማኝነት የተከተሉት ሰዎች ላይ ያለውን ንቀት የገለጠበት ከThe bigamy of Philip of hesse . in Rupp and Benjamin ገጽ 163 ላይ የሚገኘው ደብዳቤ የእንግሊዘኛው ሙሉ ቃል ይህ ነው።*

*Grace and peace . Most Serene, noble Prince, gracious Lord I have received Your Grace's letter and note that you are pleased with our counsel which we would willingly have kept secret. Melanchthon has written me nothing about your Grace but will certainly do so or tell me about it orally. But we want to keep the business a secret for the sake of the example which every one would follow, even at last the coarse peasants. There are also other reasons as great or even greater why you should keep it to yourself and not avow it which would make us a lot of trouble. Wherefore your Grace will please be secret and improve your life as you promised. Our dear Lord be with your Grace . Amen*

*Your Grace's obedient servant, Martin Luther*



www.ethiopianorthodox.org

ነገሩም በአንዴ ተዛምቶ ታላላቆቹ የጀርመን መሣፍንት ዘንድ ብቻ ሳይሆን ወደ ንጉሡ ነገሥቱም ዘንድ ደረሰ። ይህ ሁኔታ የማርቲን ሉተርን ሰብእና ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በጀርመን የተነሣውን የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ ጥያቄ ላይ የጣለው ነበር ።

መሰፍኑም የሉተርን እውነተኛ ማንነት ስለተገነዘበም ይመስላል ከፕሮቴስታንትነቱ ወጥ ወደ ካቶሊኩ አለም ተመለሰ። ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ ማርቲን ሉተር በዚህ ምንም ዓይነት የንስሃ ልብ አለማሳየቱ ነው። እንዲየውም ለመስፍኑ ለፍሬድሪክ በጻፈው ደብዳቤ ላይ «ይህን ሁኔታ ሌላ ሰው ቢያማክረኝ ቃሌን አልለውጥም» ይልና ይህን ቃሌን ግን አሁንም ቢሆን ለማንም አትንገርብኝ ይላል።

ይህ በፕሮቴስታንቱ ዓለም የተለመደ አካሄድ ነው። በተለይም ከኛ በላይ ቅዱስ የለም በማለት ሌሎችን በየመድረካቸው ላይ የሚከሱ የካሪዝማቲክና የፔንቴኮስታል ሰባክያን በየሥርቻው አጸያፊ ድርጊቶችን የሚፈጽሙ ለመሆናቸው ዛሬ ዛሬ የአደባባይ ምሥጢር ሆኖአል።[16]

---

*(16) የፕሮቴስታንቱ ዓለም መንፈሳዊ ዝቅጠት በግልጥ የሚታየው በፖለቲካ አደባባይ ነው ቢባል ማጋነን አይደለም። አንዳንድ የፕሮቴስታንት ሰባኪዎች፥ ፕሮቴስታንቲዝም በምድሪቱ ላይ ቢሰፍን ሀገሪቱ ወደገነትነት እንደምትለወጥ ሲሰብኩን ሰንብተዋል። ላለፉት አሥርና አሥራ አንድ ዓመታት በምድራችን የታየው ግን የተገላቢጦሽ ነው። አብዛኛውን የሀገራችንን የደቡብ ክልሎች ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክልል ድረስ በመንግሥት ሹመኝነት የያዙት ፕሮቴስታንቶች ናቸው። በዚህ ወቅት የታየው ዓይን ያወጣ ዘረኝነት፥ ሌብነት እና በሥልጣን መባለግ፥ በሀገራችን የቅርብ ጊዜ ታሪክ ውስጥ ታሪክ ውስጥ ያልታየ ነው። ጥብቅ የሆኑ የፕሮቴስታንት አማኞች የነበሩት የክልል ባለሥልጣናት፥ ዛሬ በሥልጣን መባለግና በሚሊዮን ብሮች የሚቆጠር የመንግስት ሀብት በመዝረፍ ተጠያቂዎች እየሆኑ ወደ እሥር እየተወረወሩ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለው ሕይወታቸውና በህዝቡ ላይ ያደረሱት ግፍ ያ ቀን አልወጣ ያለውን ሕዝብ በባሰ ድህነት ውስጥ እንዲማቅቅ አድርጎታል።*





## ማርቲን ሉተርና የመንፈስ ጭንቀት

ምንም እንኳ ማርቲን ሉተር ያገኘው «አዲስ እውነት» የመንፈስ ሰላምና እርካታ እንደሰጠው ቢናገርም፥ በሕይወቱ ዘመን በሙሉ በአእምሮ ጭንቀት ይሰቃይ ነበር። ይህም ጭንቀት በስቃይ ውስጥ እንዲሆንና እግዚአብሔርን እንዲሰድብ የሚያደርገው ነበር። ክርስቶስም ከእርሱ ይርቅ እንደነበር ጽፎአል።[17] ሉተር ይህን ሁኔታውን ሲናገር ትምህርቱ አስገኘልኝ ያለውን ሰላምና እረፍት የት አድርጎ እንደሆነ አይታወቅም።

ሆኖም ግን ይህ የሉተር የጭንቀት ሕይወት በዚህ ዘመን ላሉት የእርሱ ተከታዮች ተገቢ የሆነ ትምህርት የሚያስተምር ይመስላል። ይኸውም ግልብ በሆነ ትምህርት ላይ ተመስርቶ የማይደርሱበትን አለም መናገር ከነባራዊው ዓለም እውነታ መውጣት ነው። ወደ እኛ ድርጅት ስትመጡ ወይም ይህን ልምምድ ስታደርጉ ከድኅነት ትወጣላችሁ። ብር በቁና ታፍሳላችሁ የሚለው አባባል ምን ያህል ከእውነት የራቀ እንደሆነ የሚያመለክት ነው።

### ማርቲን ሉተርና የትምህርቱ አካሄድ

ማርቲን ሉተር የተከተለው አስተሳሰብ ወደፊት እንደምናየው በዚህ ዘመን በፕሮቴስታንቱ ዓለም ለሚታየው ቀውስ መሠረት የጣለ ነበር። ማርቲን ሉተር ጥንታዊ የሆኑትን የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች በሙሉ ከመሠረቱ እቀበላለሁ ቢልም፥ በዋናነት ግን ያስቀመጠው የትምህርቱ አደጃጀት ግን አሁን

---

*(17) በ1527 ዓ.ም ላይ ሉተር ስለነበረበት የመንፈስ ጭንቀት እንዲህ በማለት ተናግሮአል። «ከሳምንት በላይወደ ምትና ገሃነም ደጃፎች ተቃርቤ ነበር። መላ አካላቴ በሙሉ ይሸበሩ ነበር። ክርስቶስ ከአእምሮዬ ጠፍቶ በጭንቀትና እግዚአብሔርን በመስደብ እሰቃይ ነበር።»*



www.ethiopianorthodox.org

ፕሮቴስታንቱ ዓለም ያለበት ማጥ ውስጥ እንዲገባ ያደረገ ነው። ይህም በሁለት መንገድ ይታይ ነበር። በአንድ በኩል ፀረ ሥልጣን አቀዋም ስለነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን፥ የካህናት ሥልጣንና በአጠቃላይም የቤተ ክርስቲያን ሥልጣንን ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አደረገው።

በሌላ በኩል ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ የሥልጣን ምንጭ ነው ቢልም፥ ማንም እንደልቡ እንዲተረጉመው ከማድረጉም በላይ፥ ከእርሱ አስተሳሰብና አመለካከት ውጭ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍሎች አልቀበልም በማለት፥ ከእርሱ በኋላ ለተነሱት ለዘብተኛ የነገረ መለኮት አስተማሪዎች በር ከፍቶአል።

## ለዘብተኛ ነገረ መለኮት (ሊበራል ቴዎሎጂ)

«ለዘብተኛ» ወይም «ሊበራል» የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሙበት ዲሞክራሲያዊ አስተዳደርና የቤተ ክርስቲያን መሻሻል የፈለጉ የፈረንሳይ ካቶሊኮች ናቸው። ሆኖም በድህረ ዘመነ አብርሆት በአውሮፓና በአሜሪካ የተነሱ ፕሮቴስታንቶች ያስተማሩት የተሳሳተ ነገረ መለኮት በዚህ ስም በሰፊው ታውቆበታል። ይህም ለዘብተኛ ነገረ መለኮት (ሊበራል ቴዎሎጂ) ይባላል።

በፕሮቴስታንቱ ዓለም በዚህ የሚጠሩበት አስተማሪዎች ዛሬ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ድምጽ ሆነዋል። ሊበራል የነገረ መለኮት በዋናነት የተመሠረተው በማርቲን ሉተር አስተሳሰብና አመለካከት ላይ ነው። ዋና ዋና ባሕርያቸውም እንደሚከተለው ነው።





1. የእምነትን ዋና ዋና ክፍሎች ዘመነኛ ከሆነ ተፈጥሮአዊና ሰዋዊ ርዕዮት ጋር ማመሳሰልና አስፈላጊም ሆኖ ከተገኘ ታሪካዊና ትውፊታዊ የሆነውን የቤተ ክርስቲያን ዶግማ መተው።

2. ማናቸውንም የክርስቲያንን ልዕለ ተፈጥሮአዊ ክንውን በጥርጥር ዓይን መመልከት፤ ቤተ ክርስቲያንና መጽሐፍ ቅዱስ ስለተናገሩት ብቻ ማናቸውንም ነገር በእርግጠኝነት ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆን።

3. መጽሐፍ ቅዱስ ስህተት ያለበት ፥የሰዎች ታሪካዊ ዘገባ፥ ሃይማኖታዊ ልምድና ትምህርት ያለበት መጽሐፍ ነው እንጂ እስትንፋሰ እግዚአብሔር ፥ እውነትና ነባራዊ የሆነ መጽሐፍ አይደለም ብሎ ማስተማር፤ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪካዊ እውነትነት እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ስለ ክርስትና የጻፉትን በአብዛኛው መጠራጠር።

4. ምሥጢረ ሥላሴን ያፋለሰና በማህበራዊ በፍልስፍናና በሞራል አስተሳሰቦች ላይ ብቻ ያተኮረ ነገረ እግዚአብሔርን የሚያስተምር፤ ምሥጢረ ሥጋዌን በጠቅላላ በመካድ ክርስቶስ የሃይማኖት ጀማሪና ምሳሌ የሆነ እንጂ መለኮታዊ አዳኝ እንዳይደለ የሚያስተምር።

5. ሃይማኖቶች ሁሉ ስለ እግዚአብሔር ያላቸው አስተሳሰብና አመለካከት ሁሉ በዝርዝር ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር አንድ ነው ብሎ የሚያስተምርና፥ ከዝግመተ ለውጥ (ከኢቮሉሽን) መሠረታዊ የፍልስፍና ሀሳብ በመውሰድ ማናቸውም የሃይማኖታዊ አስተሳሰብ በዝግመተ ለውጥ የመጣ ነው ብሎ ማስተማር።



www.ethiopianorthodox.org

6. የሰው ልጆች በኃጢአት ውስጥ መውደቃቸውን የሚክድ፤ የክርስቶስ ሞት ለሥርየተ ኃጢአት ማለትም ለሰው ልጆች የኃጢአት ይቅርታ እንደ ሆነ የማያምን፥ የኃጢአትንም ህልውና የማይቀበልና አንጻራዊ የሆነ የሰዎች አስተሳብ ነው ብሎ የሚያምን ነው።

ሊበራል ቴዎሎጂ በእነዚህና በሌሎችም የክህደት ትምህርቶች ላይ በመመርኮዝ አብዛኛውን የፕሮቴስታንቱን የነገረ መለኮት ትምህርት ቤቶች ተቆጣጥሮታል። በሀገራችን ባሉትም የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናትም ይህ ክህደት በከፍተኛ ደረጃ እየገባ ነው።

## የሊበራል ቴዎሎጂ አባቶች

ይህንን ለዘመናችን ፕሮቴስታንቶች አስተሳሰብ መሠረት የሆነውን የሊበራሊዝም አስተሳሰብ አባቶች የሆኑት ጀርመኖች ፥ በቴዎሎጂው ሽለይማከርና ሪቼል፥ በፍልስፍና ሄግልና ካንት፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ምርመራ ስትራውስና ዌልሃውዝን ናቸው።

ከ1768-1834 ዓ. ም. የኖረው ሽለይማከር ክርስቶስን በሰውነት ተርታ ብቻ ያስቀመጠው ሲሆን ክርስቶስ እግዚአብሔርን ያወቀውና የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በሚገባ የተረዳ ሰው እንጂ አዳኝ የሆነ የባህርይ አምላክ እንደ ሆነ አያስተምርም። የሚያሳዝነው በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርቱ ከፍተኛ ስህተት ውስጥ ያለ ሰው ሲሆን፥ የቴዎሎጂ መጽሐፉ በፕሮቴስታንቱ ዓለም ውስጥ፥ ከጆን ካልቪን ክርስቲያን ኢንስቲቱት እና ከካርል ባርዝ ቸርች ዶግማቲክ ቀጥሎ በሦስተኛ ደረጃ የሚከበር መጽሐፍ ነው።





ከ1822-1889 ዓ. ም. የኖረው አልበርት ሪቼል እግዚአብሔር በራሱ አይታወቅም የሚታወቀው በሥራው ብቻ ነው የሚልና፥ የክርስቶስንም አዳኝነት በመካድ ክርስቶስ የሞራልና የሥነ ምግባር ምሳሌ ብቻ እንደሆነ ያስተማረ ነው።

ከ1724-1804 ዓ. ም. ታዋቂው የዘመነ አብርሆት የፍልስፍና አባት በመባል የሚታወቀው አማኑኤል ካንት እግዚአብሔርን የማይታወቅ አምላክ ከማድረጉም በላይ ስለ እግዚአብሔር እውቀት የሚኖረን የኛን የሃይማኖት ልምምድ በማስተዋል እንጂ ስለ እግዚአብሔር በማጥናት (ቴዎሎጂ) አይደለም በማለቱ ነገረ እግዚአብሔርን በማእከለ ሰብእ (አንትሮፖሴንቴሪክ) ለወጠው። መጽሐፍ ቅዱስንም የሰዎችን ልምምድ የዘገበ መጽሐፍና ከሰዎች ልምምድ ውጭ በማናቸውም ነገር ላይ ሥልጣን የሌለው መጽሐፍ አደረገው።

ጀርመን ካፈራቻቸው ፈላስፋዎች አንዱ የሆነው ሄግልን በሀገራችን በተሰራጩት የፍልስፍናና የአብዮት መጻሕፍቱ ያስተዋወቀን፥ የእርሱ ተከታይ የነበረውና በስተኋላም ቁጥር አንድ ጠላቱ የሆነው ካርል ማርክስ ነው።

ከ1770-1831 ዓ. ም. የኖረው የሄግልን የፍልስፍና ትምህርት በነገረ እግዚአብሔር ላይ ያመጣውን አንድምታ ለመረዳት ስለ እግዚአብሔር ያለውን አመለካከት መረዳት ይገባል። ለሄግል መንፈስ፥ ሀሳብ ፥ እውነት ፥ እግዚአብሔር የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ቃላት ናቸው። ለሄግል ፥ እግዚአብሔር ፍጹማዊ፥ ዘላለማዊና ዳይናሚክ የሆነ ነገር በሂደት ላይ ያለና በሶስት ደረጃዎች ወይም ወቅታዊ ክንውኖች የተደራጀ ሃሳብ ነው። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ለሄግል



www.ethiopianorthodox.org

አካላዊ ሳይሆን ዲያሌክቲካዊ ሂደት ነው። እግዚአብሔር ሲልም የሚናገረው ዝርው ስለሆነ ምናባዊ ሀሳብ ነው እንጂ መለኮታዊ ስለሆነ አካል አልነበረም። በዚህም ሄግልም ሆነ ሄግላውያን እየተናገሩ ያሉት የራሳቸውን መላምት ነበር እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠውን እግዚአብሔር አልነበረም።

ሄግል የጀመረውን የፍልስፍና መላምት ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ምርመራ ይዞ የመጣው የሄግል ተከታይ የሆነው ስትራውስ ነው። ከ1808-74 ዓ. ም. የኖረው ዴቪድ ፍሬድሪክ ስትራውስ ነው። የስትራውስ ትምህርትና ሕይወት የፕሮቴስታንቱ ስህተት ፍጻሜ የት እንደሚያደርስ በግልጥ ያሳየ ነበር ። ስትራውስ «የኢየሱስ ሕይወት» በሚለው ታዋቂ መጽሐፉ፥ እንደ መምህሩ እንደ ሄግል የእግዚአብሔርን አካላዊነት ከመካድ አልፎ ሓልዎቱን ጭምር የካደና «በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለሚነሡ ማናቸውም ተቃውሞዎች ሁሉ አባት» ተብሎ የሚጠራ ነው። ስትራውስ በዚህ መጽሐፉ ክርስቶስ ያከናወናቸውን ተአምራቶች ከመካዱም በላይ ወንጌላውያኑ የጻፉትም «አፈ ታሪክ» ነው በማለት ጽፎአል። በዚህም ከእርሱ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ለተነሡት እንደነ በልትማን፥ ካርል ባርዝ፥ ኤሚል ብሩነርና ዊልያም ቴምፑልን ለመሳሰሉት ለዘብተኛ ቴዎሎጂያን በር ከፍቶአል።[18] ፈላስፋውና የክርስትና ጠላት የነበረው ፍሬድሪክ ኒቼንም ወደ ክህደት በበለጠ እንዲጓዝ የገፋፋው ስትራውስ ነው።

ከ1844- 1918 ዓ. ም. የኖረው ጁልየስ ዌልሃውሰን በመጽሐፍ ቅዱስ ምርመራው የአሪት ክፍሎች በሙሉ

*(18) ቄስ ኮሊን ማንሰል፥ ትምህርተ እግዚአብሔር 1ኛ መጽሐፍ ።1995 ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት። ገጽ139 - 147።*





እውነትነት እንደሌላቸው አድርጎ የጻፈና የዘመናዊ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምርመራ አባት በመባል የሚታወቅ ነው ። እንግዲህ እነዚህ በሙሉ ፕሮቴስታንቱን ዓለም አሁን ወዳለበት ችግር በመምራት የሚታወቁ ናቸው።



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ሦስት

## የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንቲዝም አጀማመር

*ከብሉይ ኪዳን ትውፊትና ካልተቀናነሰው የክርስቶስ ትምህርት የተገኘው ሃይማኖቱዋ (ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ እምብርት ነው። በተደጋጋሚ ኢትዮጵያውያን የዚህን ዓለም ሀብትና ንብረት በመመኘት የሚመጣውን ፈተና ወደ ጎን አድርገውታል። ያላቸውንም ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር አውለውታል። በዚህም ምክንያት ከጥቂት ቦታዎች በስተቀር ትተውልን ያለፉት አብያተ ክርስቲያናትንና ገዳማትን ነው እንጂ የቤተ መንግሥትን ግምብ አይደለም።*

*ታዋቂው የአርኪዎሎጂና የታሪክ ሊቅ ዢን ዶርሴ*(19)

*ጌታ ኢየሱስ ተረስቶአል ልብ አድርጉ ወደ ገዳማት ሂዱ። እዩአቸው! ምን እንደሚያነቡ መጽሐፍ ቅዱስ እንኩዋን አያውቁም! ሰው እንዴት ያለ መጽሐፍ ቅዱስ ይመነኩሳል? ይህን ያህል ነው የወደቅነው፤ ይህን ያህል ነው የተሳሳትነው። እነዚህ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን አይተው አያውቁም ሲባል፥ ሃያ ስምንት መጽሐፍ ቅዱስ አዘዝኩላቸው።.... ሕዝቤ! መለቀስ አለበት። እኔና እናንተ ዝም ብለን መሄድ ያለብን ሰዎች አይደለንም... ከዚህ የተነሳ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ምድራዊውም ሰማያዊውም አልሆነለትም። ኢትዮጵያ ከዚህ የዘመናት ጉስቁልና የምትወጣው ይህ ነፍሱዋን ያሰረው ፍሬ ቢስ እምነት ከኢትዮጵያ ተጠራርጎ ሲወጣ ነው።*

*ፕሮቴስታንታዊው ዶ/ር ቶሎሳ*

### መግቢያ

ይህ ከላይ የተቀመጠው የሁለት ሰዎች ሰዎች ምስክርነት ያተኮረው ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ነው። አንደኛው ምንም

---

*(19) Jean Doresse, tra, Elsa Coult, Ethiopia.Elek books, London . p. 205*





እንኩዋን የውጭ ሰው ቢሆኑም ፥ በኢትዮጵያ ታሪካዊ ስፍራዎች በመገኘት ጥልቅ የሆነ ምርመራ ያደረጉ፥ የህዝቡን ባህል ማንነት የተገነዘቡ፥ ታሪካዊ መዛግብትን አብያተ ክርስቲያናትን ገዳማትን በሚገባ ያጠኑ ሲሆኑ፥ በሙያቸውም እጅግ የተመሰገኑ የአርኪዎሎጂና የታሪክ ሊቅ ናቸው። ይህንንም የተናገሩት እጅግ ጥልቅ የሆነ ጥናታቸውን እና የኢትዮጵያን ክብር ለዓለም ባሳወቁበት «ኢትዮጵያ» በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ነው።

ሁለተኛው ደግሞ፥ ምንም እንኳን በትውልዳቸው ኢትዮጵያዊ ቢሆኑም፥ ከልጅነት እስከ ዕውቀት የጀርመንና የስዊዲን ሚስዮናውያውያን ትምህርት ሲጋቱ ያደጉ፥ ስለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ዕውቀቱም ትምህርቱም የሌላቸው ናቸው። እንኩዋን የቤተ ክርስቲያናችንን ትምህርት ሊያውቁ፥ የህንጻ ቤተ ክርስቲያናችንን መግቢያና መውጫ በር በየት በኩል እንደሆነም አይተውትም ረግጠውትም አያውቁም። ይህንንም የስድብ ቃል ያኙጎደጎዱት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አዝነው ወይም ተጨንቀው ሳይሆን በሀገራችን በኢትዮጵያ በዚህም በሀገረ አሜሪካ በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ያለው የስብከተ ወንጌል እንቅስቃሴ የእነርሱን ድርጅት ወና እናዳያስቀረው በሰጉ የዋሸግንተን ዲሲ ፕሮቴስታንቶች የድረሱልኝ ጥሪ ነው።

የውጭው ሰው እውቀትን ታጥቀው ሕዝቡን አክብረው ሲጽፉ፥ የኛው ጉድ ደግሞ ጥላቻን ሰንቀው፥ በዶላር ኩራት ታውረው ነው የሰደቡን። መሰደብ ብቻ ሳይሆን ከምድረ ግብጽ ተጠራርገም እንድንጠፋ የተመኙልን። ይህንንም ያመጡት ካደጉበት ቤት ነው። ከእግዚአብሔር ቤት ሳይሆን ከሚስዮናውያኑ።



www.ethiopianorthodox.org

## የመጀመሪያው ሚስዮናዊ

የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት የጀመሩት ከአሥራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሲሆን፥ የመጀመሪያው የፕሮቴስታንት ሚሲዮናዊ እንደሆነ የሚነገርለት ፒተር (ጴጥሮስ) ሄይሊንግ የሚባለው ነው። ሄይሊንግ የቋንቋ ሊቅ ከመሆኑም ባሻገር የተዋጣለት የህክምና ባለሙያ ስለነበር በጊዜው በቤተ መንግሥቱም ከህክምና ሙያው አንጻር ቀረቤታ አግኝቶ ነበር። ሄይሊንግ ከጎንደር ካህናት ጋር መቀራረብ በመፍጠር ግእዝን ያጠና ሲሆን የተወሰኑ ሰዎችንም ሰብስቦ ግሪክና ዕብራይስጥ ያስጠና ነበር። ምንም እንኳን ያለውን ሙያ ተጠቅሞ የፕሮቴስታንት አስተሳሰብን ለማስፋፋት ቢሞክርም የተሳካለት አይመስልም። አንዳንድ የታሪክ ጸሐፊዎች ጴጥሮሳውያን የሚባሉ በብዛት በጎንደርና በሸዋ ነበሩ ብለው ቢጽፉም፥ እነዚህ በእውነት የሄይሊንግ ተከታዮች ለመሆናቸው ምንም ማረጋገጫ የለም።

ሄይሊንግ ወደ ግብጽ ሲሄድ በቱርኮች ተይዞ ከተገደለ በኋላ አልፎ አልፎ ብቅ ከሚሉ በስተቀር የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን በብዛት ወደ ሀገራችን የገቡት በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ነው።

በዚህ ወቅት ከተለያዩ የሚስዮናውያን ድርጅቶች የተለያዩ ሚስዮናውያናውያን የመጡ ሲሆን አንዳንዶቹ ንጹህ የሆነ የፖለቲካ ዓላማ ያላቸው፥ ሌሎቹ ሰላዮች ሌሎቹም ሀገሪቱን በብሔር በቋንቋ ለመለያየት መርዝ የዘሩ እሾህ የተከሉ ናቸው።(20)

(20) ዛሬ በአንዳንድ የጎሳ የፖለቲካ ድርጅቶች እንደ ፖለቲካ አጀንዳ ሆኖ የሚገኘውን ኢትዮጵያዊ ቋንቋን በላቲን ፊደል መጻፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያውያን የኦሮሞ ልጆች ዘንድ ለማስገባት የሞከረው ጀርመናዊ ሚስዮናዊ ነው።





## « ሚሽነሪ ሲንድረም »

የማህበራዊ ኑሮና የሥነ ሰብእ (አንትሮፖሎጂ) ተመራማሪዎች የፈጠሩትና በኢትዮጵያ ያለውን ሁኔታ በደንብ ሊገልጥ የሚችለው ሐረግ « ሚሽነሪ ሲንድረም » የሚለው ቃል ነው። ቃሉ ዘመናውያን ሚስዮናውያውያን በአብዛኛው የሚጠናወታቸውን የአስተሳሰብ የአመለካከትና የአእምሮ በሽታ የሚገልጥና ሰፊ ትርጉም ያለው ሐረግ ነው። ይኸውም አንድ ሚስዮናዊ ካደገበቱ አገርና ባህል ርቆ ሲሄድ በሄደበት ሥፍራ ያሉትን ህዝቦች ባህል እምነትና ታሪክ አሳንሶ መመልከት፥ ማንቋሸሽና ብሎም የተበላሸ ታሪክ ነው ያላቸው ብሎ ማስተማርንም ያጠቃልላል። ዛሬ እነ ዶ/ር ቶሎሳ የተጋባባቸው ይህ በሽታ ነው። የገዛ ታሪካቸውንና ባህላቸውን በአደባባይ እየሰደቡ፥ የረከሰውን ማጽደቃቸው።

የታሪክ ምሁራኖቹ ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራትና ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ የሚስዮናውያንን ተጽእኖ በመረመሩበት መጽሐፋቸው በግልጥ እንዳስቀመጡት ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ሚስዮናውያን የገጠማቸው ያላሰቡት ነበር። ከሀገራቸው ሲነሡ የመጡት፥ « በጨለማ » ላሉት ወንጌል ለመስበክ ነበር። ነገር ግን ሲመጡ ለዘመናት ክርስትናን ጠብቃ የያዘች ሀገርና ህዝብ አገኙ። በሕዝቦቹዋም መካከል ቅዱሳት መጻህፍትን ከእንግሊዝና ከፈረንሳይ ቀድመው የተረጎሙ፥ የዕብራይስጥና የግሪክ ሊቃውንት ነበሩባት። እነዚያ የበቁ ግሑሣን አበው ምድረ በዳውንና ባሕሩን አቋርጠው ሄደው በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም አምላካቸውን ያከበሩና የባለቤትነት ክብር ያገኙ ብቸኛዎቹ የጥቁር ሕዝብ መመኪያ ነበሩ። እነዚህ አባቶች ከነድካማቸው በመውደቅ



www.ethiopianorthodox.org

በመነሣታቸው ዓለመ መጻሕፍትን የዳሰሱ ለቤተ መንግስቱም ሆነ ለሀገሪቱ ሁሉ የዕውቀት ማህደር የሆኑ ነበሩ።

ይህ ሚስዮናውያኑን አስደነገጠ በድብቅ አስደነቀ።አስቆጣ ጥላቻንም አሳደረ። ለጊዜው እግራቸውን እስኪተክሉ ለቤተ ክርስቲያኒቱ እውቅና ሰጡ። ዛሬ ይህችን ቤተ ክርስቲያን የሚሰድቡት እነዶ/ር ቶሎሳን የመሳሰሉ ግራ የገባቸው ሰዎችን እስኪያገኙ፥ እኛ ወንጌልን የምንሰብከው ለኦርቶዶክሳውያን ሳይሆን ወንጌል ያልደረሳቸውን ነው አሉ። ውስጡን ውስጡን ግን ከበረት ቤተ ክርስቲያን በጎችን ለማስኮብለል በረት ለመገልበጥ ያደቡ ጀመር። አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱስን ሲያጠኑ ጥያቄ የተፈጠረባቸውን በተለያዩ ነገሮች ላይ ያኮረፉትን ያስኮበልሉ ጀመር። ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው ጋር እንዲነጋገሩ አመቺ መንገድ እንዳይፈጠር ነገሮችን በማባባስ ለያዩአቸው፤ አባበሉአቸው።(21)

የመጀመሪያው ነቅዕ የተፈጠረው ኤርትራ ላይ አስመራ አጠገብ በምትገኘው ጸአዘጋ በምትባለው መንደር ነው። በዚያ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት የነበሩትን ለሃይማኖታቸው ቀናኢ ከሆኑት

(21) የአንገሊካን ቤተ ክርስቲያን ምንም እንኳን ቤተ ክርስቲያናቸው በተሳሳተ መንገድ የተጓዘች ቢሆንም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በሙሉ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር በስምምነት ለማድረግ ሞክረዋል። እስከ ዛሬም ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ ለውጭ ሰዎች ከሚሰጡት አገልግሎት ውጭ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ተቃውመው ሌላ ቤተ ክርስቲያን አልከፈቱም። በዚህ ታሪክም እግዚአብሔርም ያመሰግናቸዋል።
ይህን በማየት ይመስላል በቅርቡ የካንተርበሪው ሊቀ ጳጳስ በጃንሜዳ በሚከናወነው የጥምቀት ስነ ሥርዓት ላይ የክብር እንግዳ ሆነው ተገኝተው የነበረው። ይህ ዓይነቱ የመግባባትና ኢኩሜኒካል የሆነ ግንኙነት የሚያስደስት ቢሆንም፥ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን እየተከተለችው ያለችውን እጅግ የተሳሳተ ኢክርስቲያናዊ አቅጣጫ መመርመርና ንስሐ በመግባት ራሱዋን ማስተካከል እንዳለባት በግልጥ ከቤተ ክርስቲያናችን ሊነገራት ይገባል።





ንጉሠ ነገሥት ከአጼ ዮሐንስ አራተኛ ጋር ጋር በማጣላት በተንኮል የለያዩአቸውና የራሳቸውን ድርጅት እንዲከፍቱ ያደረጉአቸው በአሥመራ አካባቢ ሠፍረው የነበሩት ሚስዮናውያን ናቸው። ዛሬ የኤርትራ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን (ከኒሻ) የምትባለውን የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን የመሠረቱት እነዚያ በሚስዮናውያን ተንኮል ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው እንዲኮበልሉ የተደረጉ ካህናት ናቸው።(22)

ሚስዮናውያኑ አሁንም የወንጌል ሳይሆን የተንኮል መረባቸውን በመዘርጋት በሌላ ግንባር በኩል መግቢያ ቀዳዳ ይፈልጉ ጀመር። ይህ ሁሉ ሲሆን ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ለሌሎች ከሰበካችሁ ደግ ብላ መኖራቸውን ሳትቃወም ነበር ያለችው።

የኤርትራው በሚገባ ሲጠናከርላቸው ቀደም ሲል በባርነት ተሸጦ የሄደውና በስተኋላም በሚስዮናውያን የተገዛው አናሲሞስ (ብዙዎች ሚስዮናውያን በባርነት ንግድ ተሳታፊዎች ስለመሆናቸው «ባርነትና ፕሮቴስታንቲዝም» የሚለውን ምዕራፍ ተመልከት።) በሚስዮናውያን በሚገባ ከሰለጠነ በኋላ ፕሮቴስታንትን በኦሮሞ ሕዝብ መካከል ለማስፋፋት በወለጋ በኩል ገባ።(23) አናሲሞስ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ኦሮምኛ

(22) ከሚስዮናዊ እይታ የተጻፈ ቢሆንም ማንም አንባቢ ያለውን ሁኔታ በቀላሉ ሊረዳ ስለሚችል ሚስዮናውያን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናትን እንዴት እንዳስኮበለሉና የራሳቸውን ድርጅት እንዳቋቋሙ Gustav Aren Evangelical Pioneers in Ethiopia. Origin of the Evangelical church Mekan Yesus, Upseliensia XXXIII. Stockholm. በሰፊው ያሳያል።
(23) በዛሬዋ ኢልባቡር በሁርሙ የተወለደው አናሲሞስ ታፍኖ ተወስዶ በባርነት እንደተሸጠና ሚስዮናውያን እንዳጠመቁት ታሪኩ ጉስታፍ አረን በጻፈው Envoys of The Gospel In Ethiopia በተባለው መጽሐፍ ላይ ተጠቅሶአል። ጉስታፍ አረን ታላላቆች ኢትዮጵያውያንን ሁሉ ፕሮቴስታንት እንደሆኑ ስለሚጽፍ ጥንቃቄ ይደረግ።



www.ethiopianorthodox.org

በመተርጎም ዝናን ስላተረፈ ጠቅላይ ገዢው ሳይቀሩ በክብር ነበር የተቀበሉት።[24] በወለጋም ተፈቅዶለት ትምህርት ቤት ከፍቶ ተማሪዎችን እያስተማረ ውስጥ ውስጡን የተላከበትን የፕሮቴስታንቱን ትምህርት ያስፋፋ ጀመር። ሆኖም ኦርቶዶክሳውያን የኦሮሞ ምእመናን ስብከቱን ስላልተቀበሉ እነርሱን ለማስኮብለል ይረዳ ዘንድ ከኤርትራ የቀድሞዎቹን ካህናት የአሁኖቹን የፕሮቴስታንት ሰባክያን የሆኑትን አስመጣ።

እነዚህ የፕሮቴስታንት ሰባክያን የሆኑ ፥ነገር ግን በቤተ ክርስቲያናችን የተማሩ ሰዎች በቦጂ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ «ፕሮቴስታንታዊ ዘር» ለመዝራትና ከዚያም በአሥመራ እንዳደረጉት ቤተ ክርስቲያኒቱን ገንጥሎ ሌላ የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም ሞክረው ስላልተቻላቸው አናሲሞስንና በጸጋ ባህል ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ክርክር የነበረባቸውን የመሃልና የሰሜን ሰዎችን እንዲሁም ከአሥመራ የመጡ ሌሎችንም ይዘው እንዳስለመዱት ዛሬ መካነ ኢየሱስ የተባለችውን የፕሮቴስታንት ድርጅት አቋቋሙ።

የመጀመሪያዎቹ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የተመሠረቱት በዚህ መንገድ ነው።ዛሬ አንዳንድ የጀርመንና የስዊድን ሚስዮናውያን ፍርፋሪን እየበሉ ያደጉ ሰዎች እንደሚግሩን በወንጌል ስብከት ሳይሆን በነገረ ሠሪነት ነው። አሁንም እነዶክተር ቶሎሳና መሰሎቻቸው ሊያከናውኑት የሚሞክሩት አባቶቻቸው ከምእት ዓመት በፊት ያደረጉትን ነገረ ሠሪነት ለመድገም ነው። ይህንንም የቀደመ ታሪካቸውን

(24) አጼ ምኒልክ ባቋቋሙት የመጀመሪያው ካቢኔ ውስጥ አናሲሞስ ቦታ ሊሰጠው የነበረውም ከዚህ ዝናው የተነሣ ሳይሆን አይቀርም።





ለመድገም በአሁኑ ወቅት በተለያየ ምክንያት ግራ የገባቸውን ጥቂት የቤተ ክርስቲያን ልጆችን በመውሰድና ኦርቶዶክሳዊ ከሆነው እምነት ትውፊትና ታሪክ ጋር ምንም ግንኙነት በሌለው ሁኔታ « ኦርቶዶክስ ተሐድሶ » ወይም « ኦርቶ ጴንጤ » ነን በማሰኘት ቤተ ክርስቲያኒቱን እየተዋጉ ይገኛሉ።

እዚህ ላይ ቤተ ክርስቲያናችን ካሳለፈችው አስቸጋሪ ጎዳና የምንማረው ነገር አለ። በዚያን ወቅት ከእነዚህ ሚስዮናውያውን ጋር በነበረው ትንቅንቅ ውስጥ የነበረው ታላቅ ሩጫ የቤተ ክርስቲያን ልጆችን ለማዳን ለማትረፍ ነበር እንጂ « በሉ ሚስዮናውያንን ወዳችሁ ተከትላችሃልና መንገዱን ጨርቅ ያርግላችሁ» የሚል አልነበረም። እርግጥ ነው፥ አንዳንድ ለሃይማኖታችን ቀናን ያሉ ጭፍን አክራሪዎች ከመስመር ሊወጡና « እነእከሌ የተጠረጠሩ ናቸው ፥ እከሌ መናፍቅ ነው እንግደለው » ለማለት ቢፈልጉም በጊዜው በነበሩት አስተዋይ ነገሥታትና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብርታት ጉዳቱ ውሱን ሆኖአል። ያ ባይሆን ኖሮ ዛሬ የነ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴን መጻሕፍት፥ የታላቁ ሊቅ የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌን የትርጉዋሜና የቃላት መዝገብ ባላገኘንም ነበር። እነዚህ ውድ የቤተ ክርስቲያናችን ልጆች አንደኛውን በፕሮቴስታንቶች ሌለኛውን በካቶሊኮች ሚስዮናውያን ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው እንዲወጡ ያልተሞከረና ያልተቆፈረ ጉድጓድ የለም። ጭፍን አክራሪዎችም «ኅሩይ ሚስዮናዊ ሆኖአል» «ኪዳነ ወልድ የጸጋ ልጅ ነው» በማለት ዝክረ ስማቸውን ለማጥፋት ቢሞክሩም እነሆ ዛሬ ስማቸው ከመቃብር በላይ ከፍ ከፍ ብሎ የእነዚህ ሁለት ታላላቅ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት መጻሕፍት በቤተ ክርስቲያናችን እየታተሙ ናቸው።



www.ethiopianorthodox.org

በዘመናችን ታሪክ ሲደግምና የቤተ ክርስቲያን ልጆችን ፕሮቴስታንቱ ዓለም ለማስኮብለል ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ፥ የጥንቶቹን ታላላቅ አባቶች ትዕግስትና አስተዋይነት መከተል አለብን። አለበለዚያ አሁን የሚታየው ጭፍን አክራሪነት የቤተ ክርስቲያን መንፈስ አይደለም፤ የፍቅርም መልክ የለውም። ነፍስ ለማዳን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ያስፈልጋሉ። ዝግ ባለ ሁኔታ መመርመር ያስፈልጋል። ጊዜ ያስፈልጋል። ዓላማው ለማባረር እንጂ ለማዳን ካልሆነ ግን፥ አሁን ራሱን «ማኅበረ ቅዱሳን» እያለ የሚጠራው ማኅበር እንደሚያደርገው፥ የሚያስፈልገው አባሩልኝ ግደሉልኝ እያሉ «የጫካ አደን» ማካሄድ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መንገድዋም ተልእኮዋም አይደለም።





# ምዕራፍ አራት

## ፕሮቴስታንትና መጽሐፍ ቅዱስ

*ዘወትር ወደ መልካም መንገድ የሚወስዱትን ቅዱሳት መጻሕፍት (መጽሐፍ ቅዱስን) የሚያነብ በውስጡ ይጸናል። ለነፍስም የኃጢአት የአመጣጡዋ ረቂቅነት ይታወቃታል።*

*ማር ይስሐቅ ም. 9*

*እዩአቸው ምን እንደሚያነቡ መጽሐፍ ቅዱስ እንኩዋን አያውቁም። ሰው እንዴት ያለ መጽሐፍ ቅዱስ ይመነኩሳል? እነዚህ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን አይተው አያውቁም ሲባል፥ ሂያ ስምንት መጽሐፍ ቅዱስ አዘዝኩላቸው።*

*ፕሮቴስታንታዊው ፓስተር ቶሎሳ ጉዲና*

### መግቢያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ አስረግጣ ከማስተማርዋ ባሻገር፥ ለዘመናት ይህን መጽሐፍ ሳይበረዝና ሳይሸቀጥ ጠብቃ የኖረችም ናት። በመሆኑም ዛሬ በዓለም ላይ ምስክር ከሚሆኑት ጥንታውያን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች መካከል የግእዙ መጽሐፍ ቅዱሳችን አንዱ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን የከበረ መጽሐፍ አምላካዊ መጽሐፍ ከማለት አልፋ ቤተ ክርስቲያናችን በአምልኮዋ ሰፊ ቦታ ሰጥታ የምትገለገልበት ነው ። በቤተ ክርስቲያን የሚሰጡት አገልግሎቶች በሙሉ እምብርታቸው (ማዕከላቸው) ወንጌል ነው። በሌሊት የጸሎት ሰዓት (በሰዓታትም ሆነ በማኅሌት) የአገልግሎቱ መምሪያ



www.ethiopianorthodox.org

የሐዋርያት መልእክታት፥ የቅዱስ ዳዊት መዝሙራት፥ የሐዋርያት ሥራ (ግብረ ሐዋርያት) እና ወንጌላት ናቸው።

በቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው አገልግሎት መደምደሚያ የሚሆነው የጸሎተ ቅዳሴው ክፍልም እንደሌሎቹ አገልግሎቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያሸበረቀ ነው ። በጸሎተ ቅዳሴው የመጀመሪያ ክፍል ከሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ከአጠቃላይ መልእክታትና ከሐዋርያት ሥራ የተውጣጡ ምንባባት ይነበባሉ። ወንጌል ከመነበቡ በፊት ከመዝሙረ ዳዊት ሦስት መስመር በዜማ ይባላል። ይህም ምስባክ ይባላል።

በመቀጠልም ካህኑ ወንጌሉን ከፍ አድርጎ ወንጌል ቅዱስ ብሎ በዜማ አሰምቶ ይጮኸል። ህዝቡም ይህ ወንጌል ቅዱስ ነው በማለት ወንጌሉን ለመስማት የተዘጋጀን አድርገን በማለት ወደ አምላኩ ይጸልያል። ካህኑም ለዕለቱ የተዘጋጀውን ወንጌል አውጥቶ ያነባል። በመቀጠልም የተነበቡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት አውጣጥቶ የዕለቱን ስብከተ ወንጌል ያከናውናል። አሁን አሁን አብዛኛው ሰው የሚገኘው በቅዳሴው የመጨረሻ ክፍል ስለሆነ ስብከቱም በመጨረሻው ክፍል ሆኖአል።

በተለይም በገዳማቱ የማኅበር ጸሎት በአንድነት የሚደርሰው በቤተ ክርስቲያን ስለሆነ አበው መነኮሳት በነግህ በቀትርና በሠርክ እየተገኙ ቅዱሳት መጻህፍትን ያነባሉ። በእነርሱም ተመስርተው ጸሎተ ማኅበርን ያደርሳሉ። ሕይወታቸውም ምን ያህል በወንጌል የተጌጠና ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ውበት ያለው መሆኑን ለማወቅ የሚፈልግ የእነርሱን መጻህፍት በሚገባ ማንበብ ይበቃል። እንግዲህ እንዲህ ያለ የወንጌል ክብር ያለባት ቤተ ክርስቲያን ናት፥ መጽሐፍ ቅዱስ





የማያውቁ መነኮሳት አሉባት ተብላ የምትወነጀለው።

## የተሳሳተው አመለካከት

ፕሮቴስታንቶች ራሳቸውን የሚጠሩትም ሆነ ሌሎች ቢጠሩአቸው በጣም ደስ የሚላቸው «የወንጌል አማኞች» ወይም «የመጽሐፍ ቅዱስ አማኞች» በሚል ስያሜ ነው። ይህንን ለማሳየትም በድርጅቶቻቸው አርማ ላይም ሆነ በስብሰባቸው መጽሐፍ ቅዱስ ከእጃቸው አይለይም። አንዳንድ የዋሆች የሆኑ ኦርቶዶክሳውያንም ፕሮቴስታንቶች መጽሐፍ ቅዱስን ያውቃሉ። መጽሐፍ ቅዱስን መማር እንደ እነርሱ ነው እያሉ ሲናገሩ ይሰማል። ጥያቄው ግን መጽሐፍ ቅዱስን ማወቅ ማለት ምን ማለት ነው? የሚል ነው። መጽሐፍ ቅዱስን እንደ አንድ የስነ ጽሑፍ ውጤት መሸምደድ፥ ወይም ለክርክር የሚሆኑ «ቅጠል በጣሽ» ጥቅሶችን መሸምደድ ከሆነ አንድ ነገር ነው። በትህትናና በጸሎት መንፈስ ማንበብ ግን ሌላ ነገር ነው።

ዛሬ ብዙዎች የፕሮቴስታንት መሪዎች በአዘኔታ እንደሚናገሩት መጽሐፍ ቅዱስ «እንደፈለጉት እንደሚቃኙት የአዝማሪ ክራር» የሆነበት ቦታ ቢኖር ራሱ የፕሮቴስታንቱ ዓለም ነው። አብዛኛው «የአምልኮ ጊዜ» የእግዚአብሔር ቃል ወደ ጎን የተተወበትና ስሜታዊነት የነገሠበት ነው። ጉባኤውም ዶክተር ሬቤካ የተባለች የፕሮቴስታንት ጸሐፊ እንዳጋለጠችው ለአጋንንት እስራት ሰዎች በሰፊው ሊጋለጡበት የሚችሉበት ነው። የ«ስብከት» ወይም «የቃል ጊዜ» የሚባለውም፥ ለስሙ የእግዚአብሔር ቃል በመግቢያው ላይ ከተነበበ በኋላ የሚደረግ እኔነትን ማዕከል ያደረገ የሥነ ልቡና ንግግር ነው። በዚህ ምክንያት በዚህ በሀገረ አሜሪካ፥



www.ethiopianorthodox.org

ብዙዎች የፕሮቴስታንት ሰባኪዎች «ኢንስፓይሬሽናል ስፒከር» መባልን እየፈለጉ ናቸው።

በሌላው ጽንፍ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ አፈ ታሪክ ወይም የራሳቸውን እምነት ለማራመድ ጥቂት ሰዎች የጻፉት የፈጠራ ሥራ እንደሆነ የሚናገሩት የፕሮቴስታንት ዋና ዋና ድርጅቶች፥ ስብከታቸውንም ሆነ ለአምልኮ መሰባሰባቸው ከሞት የተነሣውን አምላክ ለማክበር ሳይሆን የፖለቲካና የማኅበራዊ ኑሮ አጀንዳቸውን ለማራመድ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስም ተግባር ሥነ ምግባርን ከማስተማር ያለፈ አይደለም። ይህ በሰፊው የሚታየው ለዘብተኛ ወይም ሊበራል በመባል በሚታወቁት የፕሮቴስታንት ተከታዮች ክፍል ነው። ለመሆኑ እነዚህ አካሄዶች በፕሮቴስታንቱ ዓለም ለምን ታዩ? ፕሮቴስታንቶች በእርግጥ ለመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ጥንታውያኑ አብያተ ክርስቲያናት የከበረ ቦታ ይሰጣሉ? የሚለውን ለመመለስ የምንጀምረው ከመሥራቹ ከማርቲን ሉተር ነው።

## ማርቲን ሉተርና መጽሐፍ ቅዱስ

ማርቲን ሉተር በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተመለከተውን የሥነ ምግባር ችግር ለማስተካከል ቢነሣም፥ ካስተካከለው ይልቅ ወደ ባሰ ችግር የጨመረው ይበልጣል። ከነዚህም መካከል ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሰጠው ትምህርት አንዱ ነው። የእውነት ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ፥ ከቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ጀምሮ የማኅበር ቃል ነው እንጂ ግላዊ መሣሪያ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መካተት ያለባቸው የትኞቹ መጻሕፍት እንደሆኑ ቤተ ክርስቲያን በቀኖና እንደወሰነች ሁሉ፥ እንዴትም መረዳት እንዳለብን የምትነግረን ቤተ ክርስቲያን ናት።





በኦርቶዶክሳውያን አበው መጻሕፍት ከፕሮቴስታንቱ ዓለም ክህደት እንደተመለሰ የሚነገርለት የነገረ መለኮት ሊቅ ቶማስ ኦዴን እንዳለው «የሐዋርያዊ ስብከት የቃል ትውፊት ከአዲስ ኪዳን የጽሑፍ ትውፊት ይቀድማል። በዚህም ምክንያት በዘመን ቅደም ተከተልና በአመክንዮ (chronologically and logically) ትውፊት ከቅዱሳት መጻሕፍት ይቀድማል።» በዚህ ትውፊታዊ መሠረት ላይ ነው፥ መጽሐፍ ቅዱስን እንድንረዳ የሚያደርገን ።

ማርቲን ሉተር « መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ (ሶላ ስክሪፕቸራ) ብሎ ሲነሳ ይህን ቤተ ክርስቲያንን ማእከል ያደረገ የመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት ነው ግላዊ ያደረገው። ወይም ከዚህ በፊት የነበሩ ቅዱሳንና ቤተ ክርስቲያን እንዳልተጠቀሙበት አድርጎ ወደ ማየት አመጣው።[25] ይህም ማንም በየፊናው እንደፈለገው እንዲተረጉም ነው ያደረገው። ይህ አካሄድ ለመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን የሰጠ ቢመስልም፥ በቀጥታ የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን ከመሠረቱ የነጠቀ ነው። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስን ብቻውን ማንበብ፥ የመጽሐፍ ቅዱስን አተረጓጐም ብቻ ሳይሆን ራሱን መጽሐፍ ቅዱስን ጭምር ጥያቄ ውስጥ የጨመረ ነው። ይህም በራሱ በማርቲን ሉተርና የእርሱ ተከታዮች በነበሩት ነገር ግን ወዲያው በተለዩት አናባፕቲስቶች ከዚያም እስከ ዘመናችን በተነሱት የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ታይቶአል።

ማርቲን ሉተር ከእርሱ አስተሳሰብ ጋር የማይስማሙ ቅዱሳት መጻሕፍትን እውነተኝነታቸውን ተጠራጥሮአል ስህተት አለባቸው ብሎአል። የቤተ ክርስቲያንን ዶግማ

*(25) ስለዚሁ «መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ» ስለ ተባለው ትምህርት ናታን ሐች የተባለ ሰው ሲናገር « "the Bible very easily became ...a book dropped from the skies for all sorts of men to use on their own way." Reading Scripture. P. 25.*



www.ethiopianorthodox.org

ለራሱ ምኞትና ለፖለቲካ ጥቅም እንደተረጎመው፥ ቅዱሳት መጻሕፍትንም ከእርሱ ቴዎሎጂ አንጻር ብቻ ተቀብሎአቸዋል ወይም አጣጥሎአቸዋል።

የያዕቆብ መልእክት፤ ማርቲን ሉተር እጅግ ከተቃወማቸው የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ውስጥ አንዱ የያዕቆብ መልእክት ነው። ማርቲን ሉተር የያዕቆብ መልእክትን የተቃወመው አለምክንያት አይደለም። የያዕቆብ መልእክት የሉተርን ስለ እምነትና ስለ ሥራ ያለውን ትንታኔ ባዶ የሚያስቀርበት ነው። የያዕቆብ መልእክት የቅዱስ ጳውሎስን ትምህርት ልንገነዘብበት የሚገባንን ሚዛናዊ ዕይታ የሚያቀርብልን ታላቅ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ቅዱስ ጳውሎስ እምነትን ከእግዚአብሔር ጸጋ አንጻር ያቀርብልናል። ቅዱስ ያዕቆብ ደግሞ እምነትን ከእግዚአብሔር ህግ አንጻር ያቀርብልናል። እነዚህ ሁለቱም ለክርስቲያኖች የሚያስፈልጉ ናቸው። ለጽድቃችንና ለቅድስናችን የሚሆኑ መልእክታት ኣላቸውና።

ማርቲን ሉተር ግን ይህን ስላልተረዳ በያዕቆብ መልእክት ላይ ጦርነትን መክፈት መረጠ። በ1545 ዓ. ም. በጻፈው የአዲስ ኪዳን መግቢያ ላይ በእርሱ ዘንድ ጠቃሚ የሚላቸውን መጻሕፍት ሲዘረዝር እንዲህ በማለት ነበር የጻፈው፥

*«በአጭሩ የዮሐንስ ወንጌልና የመጀመሪያ መልእክቱ የጳውሎስ መልእክታት በተለይም የሮሜና የገላትያ የኤፌሶን መልእክታት የቅዱስ ጴጥሮስ የመጀመሪያ መልእክት ከዚህ በፊት ሌላ መጽሐፍ ባታዩም አንዳች ትምህርት ባትሰሙም እንኳን ክርስቶስን የሚያሳዩአችሁና አስፈላጊና መልካም የሆነውን ነገር የሚያስተምሩአችሁ መጻሕፍት ናቸው። <u>ከእነዚህ ጋር ሲተያይ፥ የያዕቆብ መልእክት በእውነቱ የገለባ መልእክት ነው። የወንጌልም ባሕርይ የለበትም።</u> »*[26]





*እንደዚሁም ለያዕቆብ መልእክት በጻፈው መግቢያ ላይ ይህን ሐሳቡን ሰፋ አድርጎ ሲገልጥም «ምንም እንኳዋን ይህ የያዕቆብ መልእክት በጥንታውያኑ ዘንድ ተቀባይነት ባይኖረውም እኔ ግን መልካም መጽሐፍ በመሆኑ የሰዎችን ትምህርት ስለማያስቀምጥና በእግዚአብሔር ሕግ ላይ ትኩረት ስለሚያደርግ አከብሬ እይዘዋለሁ። ነገር ግን ማንንም ሳላስቀይም ሀሳቤን ለመግለጥ ግን <u>መልእክቱ የማንም ሐዋርያ መልእክት አይደለም</u>። ምክንያቴም ይህ ነው።*
*አንደኛ፥ መልእክቱ በቀጥታ ቅዱስ ጳውሎስንና ሌሎችንም ቅዱሳት መጻሕፍት በቀጥታ ይቃወማል። ጽድቅን ለሥራ ይሰጣል አብርሃም ልጁን በማቅረቡ በሥራው እንደ ጻደቀ ይናገራል። ቅዱስ ጳውሎስ ግን በተቃራኒው በሮሜ ምዕራፍ 4 ላይ አብርሃም ልጁን ከማቅረቡ በፊት በእምነት ብቻ ያለ ሥራ እንደ ጻደቀ ይናገራል። ....*
*ሁለተኛ፥ ዓላማው ክርስቲያኖችን ለማስተማር ቢሆንም በዚህ ሁሉ ትምህርቱ አንድም ጊዜ የክርስቶስን ሕማምና ትንሣኤ ወይም የክርስቶስን መንፈስ አያነሳም።*[27] *ክርስቶስን ብዙ ቦታ ይጠራል። ነገር ግን ስለ እርሱ ምንም አይናገርም። በእግዚአብሔር ስለማመን ብቻ ይናገራል።....*
*ይህ ያዕቆብ ሕግንና ሥራን ከማስተዋወቅ ያለፈ ምንም አይሠራም። ሥርዓት በሌለው መንገድ ሁለቱን ማለትም ሕግንና ሥራን የሚቀላቅል ነው።*

---

(26) *Martin Luther, Preface to the New Testament 1545 in Rupp and Drewery, pp. 93-94*
(27) *እዚህ ላይ ሉተር የዘመናችንን አንዳንድ አላዋቂዎች ይመስላል። ጳውሎስ ስለዚህ ለምን አልጻፈም በማለት ታላቁን ሐዋርያ የሌላ እምነት ተከታይ ለማድረግ የሚሞክሩ ሰዎችን ሰምተናልና።*



www.ethiopianorthodox.org

*እኔ እንደሚመስለኝ ጸሐፊው አንዳንድ የሐዋርያት ስብከቶችን የሰማና በወረቀት ላይ ያሠፈረ መልካም ቅዱስ ሰው ይመስለኛል። ምናልባትም የያዕቆብን ስብከት በሰማ በአንድ ሰው ተጽፎ ሊሆን ይችላል። ሕግን ቅዱስ ጳውሎስ የባርነት ሕግ የቁጣ የሞትና የኃጢአት ሕግ ሲል፥ ይህ መልእክት ግን የነጻነት ሕግ በማለት ይቃረናል። ...*

*በዚህ ምክንያት ይህን መጽሐፍ ከዋናዎቹ መጻሕፍት እንደ አንዱ አድርጌ አልቆጥርም፤ ማንም በወደደው ቦታ ቢያስቀምጠው ወይም እንደወደደው አድርጎ ቢያየው (ቢቀበለው ወይም ባይቀበለው) ግን አልከለክለውም።.... »*(28)

ማርቲን ሉተር ከቅዱሳት መጻሕፍት ያላስገባው የያዕቆብን መልእክት ብቻ ሳይሆን የይሁዳን መልእክትና የዮሐንስ ራዕይን ጭምርም ነው። ለራዕየ ዮሐንስ በጻፈው መግቢያ ላይ *«ስለ ዮሐንስ ራዕይ ማንም ሰው የወደደውን ሊኖረው ነጻ ነው። በኔ አስተያየትና ግምገማ ማንም ሰው ሊያዝ አይገባውም። የምናገረው የተሰማኝን ነው።*(29) *ብዙ ነገር ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ አጥቼበታለሁ። ይህም ሐዋርያዊ ወይም ትንቢታዊ አድርጌ እንዳልይዘው አድርጎኛል፤»*(30) በማለት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ እንደማይቀበለው ግልጥ አድርጎአል።

## አናባፕቲስቶችና መጽሐፍ ቅዱስ

የሉተርን ሃሳብና ትምህርት ነገር ወዳልታሰበው የሉተር ዓላማ ያደረሱት አናባፕቲስቶች ናቸው። ብዙዎች

*(28) Martin Luther Preface to the Epistle of Saint James 1545. in Rupp and Drewery. Pp. 97-98*
*(29) ፕሮቴስታንቶች በጣም የሚወዱአት ዓረፍተ ነገር ናት።*
*(30) Ibid. p.98*





ዘመናውያን የታሪክ ጸሐፊዎች እነዚህን ቡድኖች «አክራሪዎች» «ጽንፈኞች» እያሉ ነው የሚጠሩአቸው። ይህ ምናልባት በዚህ ዘመን አንዳንዳንድ ቡድኖች እንደሚጠሩበት ነው። ችግሩ ግን ከእነርሱ ሳይሆን መሠረታዊ የሆነውን ትምህርት ካስቀመጠላቸው ሰው ነው። የትምህርቱ መደምደሚያ ወደሚወስደው ስፍራ ከደረሱ ጥፋቱ የእነርሱ ሳይሆን ከመጀመሪያ ከተሰጠው ትምህርት ነው።

አናባፕቲስቶችም የሉተርን ትምህርት እንደሰሙ መጀመሪያ የተቃወሙት መጽሐፍ ቅዱስን ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ምንም እንደማያደርግላቸውና የሚመሩትም በልብ ብርሃን ብቻ እንደሆነ ማስተማር ጀመሩ። አንዳንዶችም ቅዱሳት መጻህፍትን ሰብስበው ማቃጠል ጀመሩ። ከአናባፕቲስቶች ዋና ከሆኑት መካከል አንዱ የሆነው ቶማስ ሙንሰር የተባለው እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው በመንፈስ ነው የሚናገረው በማለት የመጽሐፍ ቅዱስን ሥፍራ ዝቅ ያደርግ ነበር።

በሥፍራው ስንደርስ እንደምናየው ዛሬም ቢሆን በፕሮቴስታንቱ አደባባይ ለእግዚአብሔር ቃል ክብር የለም። የእግዚአብሔር ቃልን በማንበብ ላይ ያተኮረ ሰው « ቃል ብቻ » «ጸጋ የሌለው ደረቅ » ይባላል። ነገር ግን መገለጥ አለኝ እግዚአብሔር ተናገረኝ የሚል ሰው « በጸጋ የሚያገለግል » ይባላል። እንደሚታየውም ብዙ ተከታዮችም ይኖሩታል። ለመሆኑ ከእግዚአብሔር ቃል በላይ ጸጋን የሚሰጥ አለን? ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች « ያንጻችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችል ለጸጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ።» አይደለም ያለው? ሐዋ 20፥32-33።



www.ethiopianorthodox.org

## የጀርመን «ቴዎሎጂ» እና መጽሐፍ ቅዱስ

የጀርመን ፕሮቴስታንቶች መጽሐፍ ቅዱስን እንዳለ መጠራጠር የጀመሩት ከሉተር ሞት ብዙም ሳይርቅ ነው። ለዚህም በዋናነት የሚጠቀሰው ራሱ ሉተር እንደሆነ ፓል ቲሊች የተባለ የጀርመን ቴዎሎጂ ተከታይ እንዲህ በማለት ነበር የገለጠው ፤ «ሉተር ድፍረት የተሞላበት ነገር መናገር ይችል ነበር። ለምሳሌ ይሁዳና ጲላጦስ የክርስቶስን መልእክት ቢያስተምሩ ሐዋርያውያን መሆን ይችሉ ነበር፤ ጳውሎስና ዮሐንስ ደግሞ የክርስቶስን መልእክት ባያስተምሩ ሐዋርያት ሊሆኑ አይችሉም በማለት ይናገር ነበር። ሌላ ቀርቶ እንደነቢያትና ሐዋርያት ኃይለኛ የሆነ መንፈስ ያለው ማንኛውም ሰው ዛሬም ቢሆን አዲስ የሆነ አሥርቱ ትእዛዛትና ሌላ ኪዳን መጻፍ ይችላል በማለት ይናገር ነበር.።»[31] ሉተር ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ስላለው አመለካከት ሲናገርም «ሉተር ግሚስ ሃይማኖታዊና ግሚስ ታሪካዊ ሂስ ያለበት የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከትን ነበር ያራምድ የነበረው። ...ሉተር የነቢያት መጻሕፍት ዝብርቅርቅ ያሉ እንደሆኑ በሚገባ ከማወቁም በላይ መሠረታዊ የሆኑት የነቢያት ትንቢቶች ስህተት እንደነበሩ አረጋግጦአል...» ብሎአል። የሉተር ትምህርት ለዘመናዊው ክህደት የከፈተውን በር እንዲህ በማለት ገልጦአል። «...ይህ የሉተር ነጻነት (የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛነት መጠረጣሩ) በዓለም ላይ ያለ ሃይማኖት በሙሉ ሊያደርግ ያልቻለውን ፕሮቴስታንቲዝም እንዲያደርግ አስችሎታል፤ ይህም ታሪካዊ ምርምርን ለመጽሐፍ ቅዱስ ማዋል ነው።»[32]

(31) *Paul Tillich , A History of Christian Thought, ed, Carl E. Beraaten p243*

(32) *Paul Tillich, p.244*





ፓል ቲሊች እንደ ታላቅ ስኬት የቆጠረው ይህ ታሪካዊ ምርምር የፕሮቴስታንቱን ዓለም ወደ ባሰ ስህተት የመራ ነው። ይህም ሊታወቅ የጀርመን ሉተራን ቴዎሎጂያን በምርምራቸው የደረሱት ወደ እግዚአብሔር ክብር ሳይሆን የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ሙሉ በሙሉ ወደ መሻር ነበር።

በምዕራብ አውሮፓ በተለይም በጀርመን የተጀመረው የእግዚአብሔርን ቃል በውስጡም ያለውን ታሪካዊ እውነትና ተአምራት በመካድ የእግዚአብሔርን ሕልውና የክርስቶስን ከድንግል መወለድ ትንሣኤውንና ሌላ ቀርቶ ትምህርቱን ከክርስትና እምነት ውጭ ለማድረግ መሞከር፥ ዛሬ በዋናነት የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የአስተሳሰብ መሠረት ሲሆን፤ ለዚህም የሚጠቀሙበት «መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምርመራ» biblical criticism ነው። ይህም ከላይ እንዳልነው የነገረ መለኮት ትምህርት ቤቶቻቸው ዋና መመሪያ ነው።[33]

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምርመራ
## (Biblical Criticism)

ይህ በብዙ የነገረ መለኮት ትምህርት ቤቶች ከፍተኛ ጭቅጭቅ እያስነሳ ለብዙዎች መውደቅና ስብራት ምክንያት የሆነ ነው። በተለይም በአንዳንዶች ዘንድ ለበለጠ ክህደት በር እየሆነ የሄደ የምርመራ ዘዴ ነው። ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ለዘዴው አዲስና እንግዳ ስላይደሉ ትክክለኛ የሆነውንና የቤተ ክርስቲያንን መሠረታዊ እምነት የማይጋፋውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምርመራ ትጠቀማለች። ይህ ሊታወቅ ትርጓሜዎቻችን ዘሩን ሲያብራሩ «ከጸሐፊ

*(33) መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በእርሱ ይቃረናል፥ ስለ ክርስቶስ አምላክነት አያስተምርም በማለት ክርስትናን ይዋጋ የነበረው ሙዋቹ አህመድ ዲዳት ሐሳቡን ያገኘው ከፕሮቴስታንቶች የነገረ መለኮት ትምህርት ነው።*



www.ethiopianorthodox.org

ስህተት ነው፥ እንዲህ ሲል ነው፥ እብራይስጡ እንዲህ ይላል ፥ ሌላው መምህር እንዲህ ይላል »በማለት መጻሕፍት አምላካውያት በምሥጢር የማይለያዩ ተፋልሶ የሌለባቸው እንደሆኑ ያሳያሉ። ይህ ዓይነቱ ኦርቶዶክሳዊ ምርመራ፥ ዓላማው የሰዎችን አዲስ ሐሳብ በቃለ እግዚአብሔር ላይ ለመጨመር ሳይሆን የተገለጠውን የእግዚአብሔር ቃል በሚገባ ለመረዳት ስለሆነ እምነትን ይጨምራል እንጂ አይቀንስም። ይህ ዓይነቱ አካሄድ በዘልማድ lower biblical criticism ይባላል።

ከዚህ ተቃራኒ በሆነ መንገድ በዘመነ አብርሆት የተጀመረው ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነት ለማራከስ የሚደረገው ምርመራ ነው። ይህም ምርመራ higher biblical criticism ተብሎ ይታወቃል ። ይህ በፕሮቴስታንቱ ዓለም በሰፋት ጥቅም ላይ የዋለውና ከቫቲካን ሁለተኛ ስብሰባ በኋላ በአንዳንድ የካቶሊክ ዩንቨርስቲዎች የሚታየው ይህ ትምህርት ብዙ ዘርፎች አሉት።

1.የዘር ምርመራ

(Textual criticism)

ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ጽሑፍ ከመጀመሪያው ምንጭ ሲቀዳ በትክክል መገልበጡን ለመመርመርና ትክክለኛውን የመጀመሪያ ዘር ለማግኘት ነው። ይህ ምርመራ ቀደም ባለው ጊዜ በመልካም ነገር ላይ ጥቅም ላይ ውሎ ቢገኝም በአሁኑ ወቅት ግን ፕሮቴስታንቱ ዓለም ወደ ሌላ ጽንፍ እየመራው ይገኛል። ይህም ብዙዎች የመጽሐፍ ቅዱስን ምንባባት የኋላ ሰዎች አስገብተውት ነው እያሉ ቃላቱን እያወጡ እንዲጥሉ አድርጎአቸዋል።





2. ጽሑፋዊና ታሪካዊ ምርመራ

(Literary and historical criticism)

ይህም የቅዱሳት መጻሕፍትን ጽሑፍ ጸሐፊውን፥ የተጻፈበትን ወቅትና የጽሑፉን ይዘት በመመርመር ጽሑፉን ለመረዳት የሚደረግ ጥናት ነው። ይህ ጥናት ከዚህ በተጨማሪ የጽሑፉን ታሪካዊ አውድ በማጥናትና ውስጣዊና ውጫዊ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ ለመተርጎም ይሞክራል። ከዚህ በፊት የተመለከትነው ጁልየስ ዌልሃውሰን በዚህ መንገድ የብሉይ ኪዳን ምንባባትን በተለይም አምስቱ ብሔረ ኦሪትን (ፔንታቱክን) ለማጥናት በመሞከር የብሉይ ኪዳንን ታሪካዊነት የካደ ሲሆን ከእርሱ ጥናት በኋላ የተገኙ የአርኪኦሎጂ ጥናቶችና ግኝቶች የእርሱን ግምታዊ ድምዳሜ ውድቅ አድርገውታል።

በዚህ የጥናት ስልት ላይ በመመርኮዝ፥ በአዲስ ኪዳን ላይ በተለይም በሐዋርያትና በመጀመሪያዎቹ ክፍለ ዘመናት የክርስትና ጉዞ ላይ ጥናት ያደረገው ፍሬድሪክ ባየርና የትውቢንጌን ትምህርት ቤት፥ በጴጥሮስና በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን የነበረውን የወንጌል አተረጓጐም፥ በጳውሎስና በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ትምህርት እርስ በእርሳቸው እንደሚቃረኑ አስቀምጠዋል። ከሁለተኛው ክፍለ ዘመን በኋላ የተስፋፉት የነገረ መለኮት ትምህርቶችና አመለካከቶች በጳውሎስ አስተሳሰብና ትምህርት ላይ ብቻ እንደተመሠረቱና የጴጥሮስና የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ተቀባይነት እንዳላገኘ በመተንተን የራሳቸውን መላ ምት ሰንዝረዋል።

የትውቢንጌን ትምህርት ቤት አስተማሪዎች ይህን ሲያስተምሩ በአእምሮአቸው ያለው ድብቅ ዓላማ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ እንደሆነ ያስተማረው ጳውሎስ ብቻ እንደሆነ፥ እንዲሁም



www.ethiopianorthodox.org

በአይሁድ መካከል ላለችው ቤተ ክርስቲያን የባሕርይ አምላክ መሆኑ እንግዳ እንደሆነ ለማሳየት ነው። ይህ ክህደት ዛሬ በፕሮቴስታንቶች የነገረ መለኮት ትምህርት ቤቶች የተለመደ የአስተሳሰብ መስመር ሆኖአል።

### 3. ትውፊታዊና ይዘታዊ ምርመራ
### (Tradition and form criticism)

ይህ ምርመራ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ከተለያዩ ትውፊታዊ[34] ታሪኮች ተቀድቶ የተጻፈ ነው ከሚል መላምት በመነሣት የሚካሄድ ነው። በመላ ምት ላይ የተመሠረተ መሆኑ ሊታወቅም የአንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ወስዶ ይህ ምንባብ በጽሑፍ ከመቀመጡ በፊት በአፈ ታሪክ የሚነገር የነበረው ወይም በቃል ይተላለፍ የነበረው ይህ ነው ብሎ ለማስቀመጥ ታሪካዊ ማስረጃዎች (ዶክመንት) አለመኖራቸው ነው።

### 4. የአርትኦት ምርመራ
### (Redaction criticism)

ይህ ደግሞ የትውፊታዊና የይዘታዊ ምርመራ ቅጥያ ሲሆን ጸሐፊው ከተቀበላቸው ትውፊቶችና የጽሑፍ ማስረጃዎች የትኞቹን ለጽሑፋ ተጠቅሞባቸዋል የሚል ነው። በዚህም የጸሐፊውን ዓላማና ሐሳብ እንረዳለን የሚል ነው። ይህ ዓይነቱ ምርመራ ግን ጸሐፊዎቹ በእለብዎተ እግዚአብሔር ሳይሆን በራሳቸው አመለካከት እንደተጻፉ አድርጎ ወደ መውሰድ ስለሚያመጣቸው፥ ብዙዎቹን ፕሮቴስታንቶች ጸሐፊው ይህን የጻፈው በዚህ ምክንያት ስለሆነ አንቀበለውም ወደሚል ድምዳሜ አድርሶአቸዋል።

(34) *የፕሮቴስታንት ሊበራል የነገረ መለኮት ሰዎች ትውፊት ሲሉ እኛ ኦርቶዶክሳውያን በምንተረጉምበት መንፈስ ሳይሆን ከአፈ ታሪክ ጋር አጫፍረው ነው።*





### 5. ቀኖናዊ ምርመራ
### (Canon criticism )

ይህ ደግሞ የጥንቲዋ ቤተ ክርስቲያን የመጻሕፍትን ቁጥር ለመወሰን ያደረገችውን ጉባኤያት ውሳኔዎችን ጨምሮ፥ መጻሕፍቱ እርስ በእርሳቸው ያላቸውን ዝምድና፥ ሥነ ጽሑፋዊ አንድነትና የነገረ መለኮት ተያያዥነት የሚመረምር ነው። ይህ ምርመራ የጽሑፉን ሐዋርያዊነት ወይም በብሉይ ኪዳን አበው ተቀባይነት ማግኘቱን ሳይሆን የራስን መላ ምትና ሰዋዊ ፍልስፍና መሠረት በማድረግ የሚደረግ ስለሆነ ብዙዎች ጥቂት መጻሕፍትን ብቻ እንዲቀበሉ አድርጎአቸዋል።

### 6. መዋቅራዊ ምርመራ
### Structural criticism

ይህ ደግሞ በሥነ ቋንቋ ምርምር ብቻ የመጽሐፉን ዓላማ መረዳት እንችላለን ተብሎ የሚደረግ ጥናት ነው። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትን ዓላማ የጸሀፊዎችን ማንነት ታሪካዊ አውዱን ገንጥሎ በማውጣት የሥነ ጽሑፍን ሰዋስዋዊ እና መዋቅራዊ ምርምርን ብቻ በመመርኮዝ የሚደረግ ስለሆነ ወደ እውነት የሚያደርስ አይደለም።

በአጠቃላይ ከላይ ያየናቸው የምርመራ ስልቶች የእግዚአብሔር ቃልን ከዘመኑ ሰዋዊ ሃሳብ ጋር ለማስታረቅ የተደረገ ስለሆነ ስኬታማ ሊሆን አልቻለም።

## «የእምነት እንቅስቃሴ» እና መጽሐፍ ቅዱስ

በፕሮቴስታንቱ ዓለም ውስጥ፥ የእግዚአብሔርን ቃል በማጣመምና የራስን የተሳሳተ አመለካከት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በመቀየጥ ብዙ እንቅስቃሴዎች



www.ethiopianorthodox.org

ተከስተዋል። ከእነዚህም አንዱ፥ በአሁኑ ወቅት መላውን የካሪዝማቲክና የፔንቴኮስታል ተከታዮችን በማጥለቅለቅ ላይ ያለውና በሀገራችንም በኢትዮጵያ በመላው የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የተንሰራፋው፥ «የእምነት እንቅስቃሴ» ተብሎ የሚታወቀው የትምህርት አስተሳሰብ ነው። በኢትዮጵያውያን ፕሮቴስታንቶች ዘንድ በሰፊው የሚታወቁት እን ኬኒት ሄገን፥ ኬኒት ኮፕላንድ፥ ቤን ሂን፥ ሞሪስ ሱሩሎ፥ ሬንሀርድ ቦንኬ በዋናነት ከሚጠቀሱት የእንቅስቃሴው መሪዎች መካከል ናቸው።

«የእምነት እንቅስቃሴ» የእግዚአብሔርን ቃል ከሥፍራው በማሳነስ፥ በመውሰድ የሰባኪውን ወይም የተናጋሪውን ቃል የእግዚአብሔር ቃል ያህል ቦታ የሰጠ ነው። ቤተ ክርስቲያን ያቆየቻቸው ዶግማዎች በሙሉ በእነርሱ ቦታ የላቸውም። እንዲያውም እነዚያ ትምህርቶችና ትምህርቱን የያዙ ሰዎች በአደባባይ ይሰደባሉ ይወቀሳሉ። ቤን ሂን የተባለው የእነርሱ ሰባኪ ተከታዮቹን በአንድ ወቅት «እዚህ የተሰበሰባችሁት እስከ ዛሬ የሰማችሁትን ለመስማት አይደለም» በማለት እርሱ የሚናገረው ዶግማ እርሱ የሚናገረው ትምህርት ለቤተ ክርስቲያን እንግዳ የሆነ ትምህርት እንደሆነ ገልጦአል። የሚያሳዝነው ደግሞ «አዲስ መገለጥ» የተባለው «ጥንታዊ ስህተት» መሆኑ ነው። ለምሳሌ ቤን ሂን ያንን ቃል በተናገረበት ዕለት ያስተማረው ትምህርት እግዚአብሔር ዘጠኝ መለኮት እንዳለው የሚያስተምር ነበር። ይህ ደግሞ የቤንሂን ሊቅነት ሳይሆን የቀደመውን ስህተት በንግድ ቃል የማስቀመጥ ችሎታ ነው።

«በእምነት እንቅስቃሴ» ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል የመዋረዱን ያህል ሰባኪዎቻቸው ደግሞ የዚያን ያህል





ይመለካሉ። የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ለእነርሱ ምኞትና ሴሰኝነት አገልጋይ አድርገው ሲመለከቱት፥ በእነርሱ አፍ የሚነገሩት ቃላት «አዲስ መገለጦች» የእግዚአብሔር ቃል ተደርገው ነው የሚታዩት። ከእነርሱ የመጣውን ቃል የጠረጠረ ሰብእናው እስኪዋረድ ድረስ ተበሻቅጦ ይሰደባል።

የትሪኒቲ ብሮድካስቲንግ ኔት ወርክ (ቲ. ቢ. ኤን) መሥራች የሆነው ፖል ክሮች የእምነት እንቅስቃሴን መሪዎች ትምህርት ጥያቄ ውስጥ የከተቱ አንዳንድ የራሱን ድርጅት አባላት፥ እኔ ባልገላችሁም እግዚአብሔር ይገላችኋል በማለት በማስፈራራት፥ ለእግዚአብሔር ቃል መታዘዝ ወይም በእግዚአብሔር ቃል የተመሠረተ ዶግማ ወይም ዶክትሪን ምንም እንደማያስፈልግ አስተምሮአል።(35) በዚህ እምነት ተከታዮች መሠረት እግዚአብሔር የሚሠራው እንደቃሉ ሳይሆን «እንደ ቃላቸው» ማለትም እንደ እነርሱ የእምነት ቃል ነው። ከቃሉ ጋር የተቃረነ ቢሆን ወይም የእግዚአብሔር ፈቃድ ባይሆን እንኳን እግዚአብሔር ከእምነት እንቅስቃሴ ተከታዮች አፍ የሚወጣውን ያከናውናል ለፈቃዳቸው ይገዛል።

---

*(35)"I think God's given up on a lot of that old rotten Sanhedrin religious crowd, twice dead, plucked up by the roots. I think they're damned and on their way to hell and I don't think there's any redemption for them...the heresy hunters that want to find a little mote of illegal doctrine in some Christian's eye and pluck that little mote out of their eye when they've got the whole forest in their own lives and in their own eyes. I say to hell with you! Oh hallelujah. Get out of God's way, quit blocking God's bridges or God's gonna shoot you if I don't! I refuse to argue any longer with any of you out there. Don't even call me. If you want to argue doctrine, if you want to straighten out somebody over here, if you want to criticize Ken Copeland for his preaching on faith, or Dad Hagin. Get out of my life! I don't even want to talk to you or hear you. I don't want to see your ugly face! Get out of my face in Jesus' name."*



www.ethiopianorthodox.org

መጽሐፍ ቅዱስ ግን በሚገባ እንደሚያስተምረን፥ ሰማይና ምድር የሚታዘዙለትና የጸኑበት፥ እኛም የምንመራበት ሕያው የሆነ ብርሃን የእግዚአብሔር ቃል ነው። የእግዚአብሔር ቃል ስንልም፥ ሰዎች ታየልን ተገለጠልን የሚሉትን ትንቢትና መገለጥ ወይም «በእምነት ተናገርነው የሚሉትን «የእምነት ቃል» ሳይሆን፥ ነቢያትና ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የጻፉትና እስትንፋስ እግዚአብሔር የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ዛሬ «የእምነት እንቅስቃሴ» መሪዎች ከራሳቸው ምኞት ጋር እየቀየጡ ያሉት ይህን የእግዚአብሔር ቃል ነው።

ይህ ዓይነቱ ትምህርት ምን ያህል በፕሮቴስታንቱ ዓለም በተለይም በኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችን መካከል በጣም ተስፋፍቶአል። እንዲያውም በዚህ ጉዳይ የውጭዎቹ ፕሮቴስታንቶች እነዚህ ከክርስትና ውጭ ያሉ መሆናቸውን ተገንዝበው አውግዘዋቸዋል። ለምሳሌ ከእነዚህ የእምነት እንቅስቃሴ አባላት አንዱ የሆነው ሞሪስ ሱሩሎ በእንጊሊዝ የኢባንጀሊካል አሊያንስ የተወገዘና በእነርሱ አብያተ ክርስቲያናት እንዲሰብክ የተከለከለ ሲሆን፥ በእኛዎቹ ኢትዮጵያውያን ፕሮቴስታንቶች ዘንድ እንደ አምላክ የሚታይ ነው። እነ ቦንኬ ምን ያህል በሀገራችን ሕዝቡን እንዳሳበዱት ሁላችንም የምናውቀው ነው።

የእነርሱን ርካሽ ስብከት በመሸከም ቤተ ክርስቲያናችንንና ምእመኖቻችንን ግራ የሚያጋቡትን እነዶክተር ቶሎሳ በስብከታቸው መካከል የራሳቸውን የግል ልምምድ እንዴት እንደ ሚጠቀሙበት መመልከቱ በነዚህ ሰዎች ልምምድ ምን ያህል እንደተበከሉ የሚያሳይ ነው። በወንጌል ስብከት ውስጥ፥ ያለፍንበት መንገድ፥ የሕይወታችን ልምምድና ኑሮአችን ለተነሳንበት የስብከት ርዕስ ምሳሌ ሊሆነን





ይችላል። ይህ ልምምዳችን ግን፥ በምንም ዓይነት ሁኔታ የትምህርታችን ርዕስና የእምነታችን ምንጭ አይሆንም። የእምነታናንና የትምህርታችን ምንጭ፥ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። የእምነት እንቅስቃሴ ሰባኪዎች መጽሐፍ ቅዱሱን ለትምህርታቸው የሚጠቀሙት በምሳሌነት ብቻ ነው። ትምህርታቸውና ስብከታቸው የሚመሠረተው «እግዚአብሔር ተናገረኝ»፥ «አዲስ መገለጥ አገኘሁ»፥ «የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ቢልም እኔ ግን እንዲህ እለዋለሁ» በሚሉ ግላዊ አባባሎች ነው።[36] ይህ ምን ያህል ወደ ስህተት እንደመራቸው በሚቀጥለው ምዕራፍ እናያለን።

*(36) ፓስተር ቶሎሳ የቤተ ክርስቲያናችን መነኮሳት የእግዚአብሔርን ቃል የማያውቁ ናቸው ብለው በተናገሩበት ስብከታቸው ላይ በተደጋጋሚ «የሆነ ነገር ከመንፈሴ ገባ» «እግዚአብሔር ተናገረኝ» የሚል ቃል ሲናገሩ ይሰማሉ።*



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አምስት

## ፕሮቴስታንትና ነገረ እግዚአብሔር

*እግዚአብሔርን ማሰብ በነፍስ ውስጥ ከስፈንና ከጸና፣ የዚህ ዓለምን ነገር ከማየት የሚመጣ የሥጋ ሐሳብ ይጠፋል። የጥበብን መንፈስ ገንዘብ ያደረገ ልቡናም፣ የተሰናዳች መርከብን በባሕር ውስጥ ያገኘ ሰውን ይመስላል።*

*ማር ይስሐቅ አንቀጽ 28፥ም2*

### መግቢያ

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በነገረ እግዚአብሔር ትምህርትዋ፥ ጠላቶቹዋ እስከመሰክሩላት ድረስ የአባቶቹዋን ትምህርት ይዛ የቆየች ናት። በተለይም በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርትዋ ከልሳለች በርዛለች ተብላ የማትጠረጠር፥ ዛሬ ዛሬ ሌሎች እንኳዋን ሳይቀሩ የአምልኮዋን ምሥጢር ሊማሩባት እየሞከሩ ያሉባት ናት።

ቴዎሎጂዋም እንደ ምዕራቡ ዓለም ግልብ በሆነ የቃላት ጨዋታና ሰዋዊ አመክንዮ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ጥልቅ በሆነ ውዳሴ ማሰላሰልና መለኮታዊ ራእይ ላይ የተመሰረተ ነው።[37] በዚህም ምክንያት ከንቱ ከሆነ የቃላት ክርክር የሚመነጨው ክህደተ

(37) *" a theology deeply rooted in the fathers, is far removed from the theological abstractions common in the West . Adoration, contemplation, and vision, not rational intellection, characterize the Eastern tradition."*





እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪክ ውስጥ አልታየም። ምሥጢረ ሥላሴ ወይም በአጠቃላይ ነገረ እግዚአብሔር በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ የአምልኮ መሠረት ነው እንጂ ለአንዳንዶች እንደሚመስላቸው የሊቅነት መገለጫ አይደለም። በቅዳሴው በዝማሬው የዜማዎችና የጸሎታችን መጀመሪያ የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት ነው። በቅዳሴያችንም ታላቁ አዋጅ «አንዱ አብ ቅዱስ ነው። አንዱ ወልድ ቅዱስ ነው። አንዱ መንፈስ ቅዱስ ቅዱስ ነው።» የሚለው ነው። በዚህ ወቅት ነፍስ ሁሉ በጸጥታ በታላቅ ተመስጦ በመሆን ይህን አዋጅ ይሰማል። ካህኑ አዋጁን እንዳሰማም ሕዝቡ በአንድነት «በእውነት አብ ቅዱስ ነው፥ በእውነት ወልድ ቅዱስ ቅዱስ ነው፥ በእውነት መንፈስ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ነው።» በማለት የእግዚአብሔርን ፍጹም አምላክነት፥ አንድነትና ሦስትነት፥ ቅድስና፥ ኃይልና ጥበብ በመናገር ተአምኖታቸውን ይገልጣሉ። ይህ ዘመን የማይሽረው እውነት እስከዛሬ ድረስ በሚገባ ሲነገር ኖሮአል።

### የፕሮቴስታንቱ ዓለም እና ነገረ እግዚአብሔር

በፕሮቴስታንቱ ዓለም የሚታየው ግን ከዚህ የተለየ ነው። ምንም እንኳን ማርቲን ሉተርና የፕሮቴስታንት መሥራቾች የእግዚአብሔርን ሕልውና ባይክዱም፥ ፕሮቴስታንቱ ዓለም ወደዚህ ዓይነት ስህተት ውስጥ እንዲገባ ግን በር ከፍተውለታል ብንል ማጋነን አይደለም። ይህም በአሁኑ ወቅት ተስፋፍቶ እግዚአብሔር የለም ከሚለው የሊዘብተኛ ፕሮቴስታንቶች ጀምሮ፥ እኛ እግዚአብሔር ነን እስከሚሉት የእምነት እንቅስቃሴ መሪዎች ድረስ የሚታየው ስህተት፥ የፕሮቴስታንቱን ዓለም ግራ



www.ethiopianorthodox.org

በማጋባት ላይ ይገኛል። ይህም በዋናነት የሚነሳው፥ ባለፈው ምዕራፍ ላይ እንዳየነው ፥ስለመጽሐፍ ቅዱስ ፕሮቴስታንቱ ዓለም ካለው አመለካከት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በዘመናዊ አመክንዮና በሳይንሳዊ ምርመራ ማብጠልጠል የጀመረ አካል፥ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን እግዚአብሔር ቢክድ ምንም አያስደንቅም።

ማርቲን ሉተርም ሆነ የስዊስ ፕሮቴስታንት ጀማሪዎች ካልቪንና ዝዊንግሊ፥ ስለ ነገረ እግዚአብሔር የቀደሙትን የቤተ ክርስቲያን አበው ትምህርት እንቀበላለን ቢሉም፥ አንዳንድ አቅዋማቸው ግን ግልጥ አልነበረም። ይህም ለተከታዮቻቸው ወደባሰ ስህተት መግባት ምክንያት ሆኖአቸዋል። ለምሳሌ ጆን ካልቪን የተጣራ የምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት ስላላስተማረ፥ በጊዜው የነበሩት አንዳንድ የነገረ መለኮት ሊቃውንት አርዮሳዊ ትምህርት ያስተምራል ብለው ከሰውታል። ከክሱ በኋላ ስለምሥጢረ ሥላሴ ያለው ትምህርት ከቤተ ክርስቲያን አበው ትምህርት የተለየ እንዳይደለ በመናገር በታዋቂ መጽሐፉ በስፋት ቢዘግብም በጄኔብ በነበረበት ወቅት «አካል» እና «ሥላሴ» የሚለውን ቃል ከመጠቀም ይጠነቀቅ ነበር።[38]

ይህ የካልቪን አስተሳሰብና አመለካከት በፕሮቴስታንቶች የነገረ እግዚአብሔር አስተሳሰብ ላይ ጠልቆ ከመግባቱ የተነሳ፥ ዛሬም ቢሆን የምሥጢረ ሥላሴ ነገር በጣም ይከብዳቸዋል። ለዚህም የሚሰጡት ምክንያት ራሱ ካልቪን ይሰጥ የነበረውን ምክንያት ነው። ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው በላይ እንዳንሄድ እንጠነቀቃለን የሚል ነው። ይህም ግልብ የሆነ የነገረ እግዚአብሔር

(38) *Louis Berkhof, The History of Christian Doctrines p. 95*





አስተሳሰብ ያላቸውና ምሥጢረ ሥላሴን የማይቀበሉ ሰዎች እንዲነሡባቸው ምክንያት ሆኖአል።

በፕሮቴስታንቱ ዓለም ውስጥ፥ የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት በሚገባ አስረግጦ ማስተማር ስላልተለመደ፥ ይህን የክርስትና እውነት መካድ የተጀመረው ወዲያው ከምሥረታው ነው። የሉተር ተከታዮች የነበሩትና በስተኋላም በራሱ በሉተር አካሄድ ተጠቅመው ወደ ባሰ ስህተት ውስጥ የገቡት አናባፕቲስቶች፥ በአብዛኛው ምሥጢረ ሥላሴን ይቃወሙ ነበር። ለዚህም የሚሰጡት ምክንያት የኒቅያው ጉባኤ የተወሰነው በግሪክ ፍልስፍናና በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ተጽእኖ ነው የሚል ነው።[39] ሶስንያውያን የሚባሉትና በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን የነበሩት የፕሮቴስታንቶች ወገኖች ሦስቱ አካላት ማለትም አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ ባሕርይ አላቸው ብሎ ማስተማር ከሰዋዊ አመክንዮ ተቃራኒ (contrary to reason) ነው በማለት ክደዋል። እነዚህ የፕሮቴስታንት ወገኖች፥ ከአርዮስ አካሄድ አልፈው በመሄድ የወልድን ዘላለማዊነት ከመካዳቸውም በላይ፥ ክርስቶስ የእግዚአብሔር መንፈስ የሞላበትና ስለ እግዚአብሔር ልዩ ዕውቀት ያለው ሰው ብቻ ነው ብለው ያስተምሩ ነበር። መንፈስ ቅዱስንም የሥላሴ አካልነቱን ክደው ከእግዚአብሔር ወደ ሰው የሚፈስ ኃይል ነው ብለው የሚያምኑ ነበሩ። ዛሬ ይህ ትምህርት በሃይማኖት አንቀጻቸው ላይ ባይገለጥም፥ በብዙዎች ፔንቴኮስታሎችና ካሪዝማቲክ ቡድኖች ትምህርትና ልምምድ ውስጥ በግልጥ ይታያል። መንፈስ ቅዱስን

(39) *George H. Williams, The Radical Reformation . Philadelphia, Westminster Press pp 319-325 ከአናባፕቲስቶች በአብዛኛው በነገሥታቱና በመሳፍንቱ ላይ ያመጹ ገበሬዎች ስለነበሩ ጸረ ነገሥታት አቅዋም ነበራቸው እንጂ እነርሱ እንደሚሉት የቆስጠንጢኖስ ተጽእኖ በኒቅያ አንቀጸ ሃይማኖት ላይ አልነበረም።*



www.ethiopianorthodox.org

እንደ አምላክ ሳይሆን እነርሱ እንደፈለጉት የሚያዙት የእግዚአብሔር ኃይል አድርገው ነው የሚመለከቱት። መፍሰስ፥ መሞላት፥ መቀባት የሚሉትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት በሚገባ ስለማያስተውሉአቸው መንፈስ ቅዱስ አካል ያለው መሆኑን የሚያዘነጋቸው ሆኖአል። ከጆን ካልቪን ጋር ስለ እግዚአብሔር ሉዓላዊ ፈቃድ ያልተስማሙት፥ የአርሚኒየስ ተከታዮች የሆኑት የፕሮቴስታንት አስተማሪዎች ኢፒስኮፒየስ ሊምቦርክና የመሳሰሉት፥ ሦስቱ አካላት በባሕርይ አንድ እንደሆኑ ቢያምኑም በክበበ ሥላሴ ውስጥ የክብርና የኃይል ቅደም ተከተል እንዳለ ያምናሉ። ይህ ደግሞ ወደ ሦስት አምላክነት (ትራይቴይዝም) የሚወስድ አካሄድ ነው።

ይህ በጀርመንና በሌላው ክፍል የታየው የፕሮቴስታንቱ ክህደት፥ በአጭር ጊዜ ወደ እንግሊዝ ተስፋፍቶ የንግሥቲቱ የቤተ መንግሥት ሰባኪ የሆነው ሳሙኤል ክላርክ የአርዮስን የቆየ የጥገኝነት ትምህርት (ሰቦርዲኔሽን)፥ በአዲስ መልክ ማስተማር ጀመረ። ትምህርቱንም በጽሑፍ አሳተመ። ክላርክ በትምህርቱ «አብ የሁሉ ገዢ አስገኝ ኃይልና አስገኝ የሆነ አምላክ ነው። ከእርሱ ጎን ከመጀመሪያ የነበረ ሁለተኛ መለኮታዊ አካል አለ። እርሱም ወልድ ይባላል። ባሕርዩን ከአብ ሁኔታዊ ፈቃድ ያገኘው ነው እንጂ ከአምላክ የተገኘ አምላክ አይደለም።[40] ከአብና ከወልድ ጋር ባሕርዩ ከአብ በወልድ በኩል የተገኘ ሶስተኛ መለኮታዊ አካል አለ። እርሱም መንፈስ ቅዱስ ነው። እርሱም በባሕርዩ ከአብና ከወልድ በመዐርግ ያንሳል።» ይላል።

(40) *His being and all His attributes from the Father , not by a mere necessity of nature , but by an act of the Father's optional will.* *ይህ የክላርክ ትምህርት በቀጥታ ከአርዮስ የተቀዳ በሥላሴ ዘንድ መአርጋትን የሚፈጥር ነው። አርዮስ ይህን ትምህርት የወሰደው ከአርጌንስ ነው ብለው አንዳንድ ሊቃውንት ይናገራሉ።*





መንፈስ ቅዱስ ከአብም ከወልድም ይሰርጻል የሚለውን ትምህርት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የተቃወመችው እንዲህ ዓይነቱ ክህደት ማለትም ሦስቱን አካላት በመዓርግ ማበላለጥ እንዳይኖር ነበር። ይህ አይነቱ ትምህርት ሞናርኪያኒዝም (የአንድ ገጽ) የስህተት ትምህርት ያመጣል። ምክንያቱም ሁሉን ወደ አብ በመውሰድ የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን የባህርይ አምላክነት ይክዳልና። የሮም ቤተ ክርስቲያን ድርጊቱን ያየችው ከነገረ መለኮት አንጻር ሳይሆን ከፓፓውን ሥልጣን አንጻር ነው። ይህ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን ጎዳት እንጂ አልጠቀማትም። ይህ የሳሙኤል ክላርክ የክህደት ትምህርት በአጭር ጊዜ ውስጥ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያንን የወረሳት ሲሆን ወደፊት በየቦታው እንደምንመለከተው ዛሬ ያ አድጎ በዘመናችን ወደምናየው አደጋ አድርሶአታል።

ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን አትናቴዎስ ሐዋርያዊ *«እስመ ወልድ አኮ እምህላዌ ባህቲቱ አላ እምህላዌ አብ ዘኢተወልደ ወሎቱ ብሉየ መዋእልና እንዘ ኢይዴህር እምአቡሁ፥ ወልድ በግሉ ህላዌ ባሕርይ ብቻ አይኖርም ነገር ግን ተወላዲ ካልሆነው ካልተወለደው ከአብ ህላዌ ባሕርይ ዘንድ ይኖራል። መገኘቱም ተረክቦው ከአብ በኋላ አይደለም። ብሉየ መዋዕልነት ዘላለማዊነት ገንዘቡ የሆነ ነው እንጂ።»* በማለት የገለጸውን ስለመንፈስ ቅዱስም ቅዱስ ቄርሎስ በድርሳኑ *«እስመ መንፈስ ቅዱስ ውእቱ መንፈስ እግዚአብሔር። ወአኮ ውእቱ ነኪር እመለኮተ እግዚአብሔር ልዑል በኵሉ። አላ ውእቱሰ እምዝንቱ አሃዱ መለኮት ወህልው ውስቴቱ መንፈስ ቅዱስ። መንፈስ ቅዱስሰ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚሆን የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። እርሱም ከልዑል እግዚአብሔር መለኮት በሁሉም ነገር የተለየ አይደለም። ነገር ግን ህልው ከሚሆንበት ከዚሁ*



www.ethiopianorthodox.org

ከአንዱ መለኮት ያለና የሚኖር ነው።» ብለው ያስተማሩትን ታስተምራለች ታሳምናለች።(41)

ወደ አዲሱ ዓለም ወደ አሜሪካ የካልቪን ደቀ መዝሙርን የቴዎዶር ቤዛን ትምህርት ይዘው የመጡት የእንግሊዝ ፕሮቴስታንቶች «ፒዩሪታንስ» ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደ ባሰ ክህደት ውስጥ መግባት ጀመሩ። እነዚህ በአሜሪካ በኒው ኢንግላንድ የነበሩት የፕሮቴስታንት አስተማሪዎች የወልድን የዘላለም ልጅነት ከመካዳቸው ሌላ «አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የአንዱን እግዚአብሔር በመዳን ታሪክ ውስጥ በተለያየ ሁኔታ መገለጥ ለማሳየት የሚረዱ ቃላት ናቸው እንጂ በክበበ ሥላሴ ያለውን የሥላሴን ሦስትነት የሚያመለክቱ አይደሉም» ብለው የሚያስተምሩ ሆነው ነበር።(42)

ይህ የተመለከትነው መላቅጡን ያጣ የፕሮቴስታንቱ አለም የነገረ እግዚአብሔር ትምህርት በፕሮቴስታንቱ አለም ምስቅልቅሉ የወጣ እግርና እጁ የማይጨበጥ ትምህርት እንዲታይ አድርጎታል። በአገራችን ኢትዮጵያም ፕሮቴስታንቲዝም በይፋ እንቅስቃሴ እንደጀመረ ዓመታት ሳይቆጠሩ ጥቂት የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ከየመጽሐፉ በተባራሪነት ያነበቡትን የምዕራቡን ዓለም የፔንቴኮስታል ልምምድ ለመጠቀም በየጓዳው ሙከራ ያዙ። የእንቅስቃሴው መሪዎች የሆኑትም በመንፈስ ቅዱስ እንደተጠመቁ በመናገር በአዲስ «ቋንቋ» መናገር ጀመርን አሉ። የሚገርመው ይህ እንቅስቃሴ ገና በሚንተከተክበት ወቅት የሰባልዮስን

(41) ሃይማኖተ አበው ገጽ 79 ክፍል 4 ቁ. 34 እና ገጽ 267 ክፍል 1 ቁጥር 34።

(42) ይህ በቀጥታ የሰባልዮስ ትምህርት ነው። ሰባልዮስ ጥንታውያን ተዋንያን የተለያየ ጭንብል (ማስክ) አድርገው የተለያዩ ገጸ ባሕርያትን እንደሚለብሱ አንዱ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ጊዜ አብ፥ በአዲስ ኪዳን ወልድ፥ ከበዓለ ጰራቅሊጦስ በኋላም መንፈስ ቅዱስ ሆኖአል ብሎ ያስተማረ ነው ።





ወቅት የሰባልዮስን ትምህርት ተቀብለናል የሚሉ ወጣቶች ከፔንጤኮስታሎቹ ተለይተው ለብቻቸው «የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን» ነን በማለት አዲስ ድርጅት የከፈቱት። ይህ ድርጅት «ኢየሱስ ብቻ» በማለት የሰባልዮስን የስህተት ትምህርት የሚያስፋፋ በፍጥነት እያደገ የመጣ የፕሮቴስታንት ቅርንጫፍ ነው። ብዙዎች ጴንጤዎች ወደዚህ ድርጅት በብዛት ይገባሉ። ዋና መገለጫቸውም የምንጠመቀው በኢየሱስ ስም ብቻ ነው ብለው ማስተማራቸው ነው። በዚህም ምክንያት «ኦንሊ ጂሰስ» የሚል ስም ተሰጥቶአቸዋል። ጸረ ሥላሴ ትምህርታቸውም ከአርዮሳውያን ጋር አንድ ያደርጋቸዋል። በኢትዮጵያ ውስጥ የድርጅቱ መስራች «ሙሉ ወንጌል» ተብሎ የሚጠራውን ድርጅት ከመሠረቱት መካከል አንዱ የሆነው የጴንጤ ሰባኪ ነው። ለብዙዎች ጴንጤዎች መግለጥ ያቃታቸው እነርሱም ሆኑ ጸረ ሥላሴ አቅዋም ያላቸውና ሐዋርያት ነን ባዮች «ሰባልዮሳውያን» አንድ ዓይነት የአምልኮ ዘዬና «በመንፈስ የመሞላት» ልምምድ ባለቤት መሆናቸው ነው። ይህም ለነጋሪ ያስቸገረ ሁኔታ በኢትዮጵያ ጴንጤዎች መካከል ብቻ ሳይሆን በሌሎቹም ጴንጤዎች ዘንድም ጸረ ዶግማ አቅዋም anti doctrine እንዲኖራቸውና በዓለም አለ የሚባለው የክህደት ትምህርት ጎሬዎች እንዲሆኑ እያደረጋቸው ነው። በዚህም ምክንያት በአሁኑ ወቅት በመላው ዓለም ባሉት ጴንጤዎች ዘንድ ታዋቂ የሆኑ ሰባኪዎች በምስጢረ ሥላሴ ትምህርታቸው ፍጹም ሰባልዮሳውያን ናቸው።

በብዙዎች የፕሮቴስታንት ጽሑፎች ላይ የማንንም ዶክትሪን የማይወግን ነው የሚል ማየት የተለመደ ነው ። ይህ አላዋቂ የሆነ አነጋገር ከፖለቲካ አደባባይ የተዋሱት ነው እንጂ የቤተ ክርስቲያን ይትበሃል



www.ethiopianorthodox.org

አይደለም። በዚህ ጸረ ዶግማ አቅዋማቸው የገዛ ሀገራቸውን ታሪክና የታሪክ ምንጭ የሆነችውን ኢትዮጵያዊት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንዲገነዘቡ አይደረግም። በዚያ ፈንታ ከምዕራብ ዓለም የሚላኩትን የስህተት ትምህርቶች በየቀኑ ይግቱአቸዋል። በአንጻሩ ግን በአፍሪካ በአሜሪካና በካሪቢያን የሚኖሩት ጥቁር ሕዝቦች ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለመማር ይጓጓሉ። ለዚህ ታላቅ ምስክር የሚሆነው ከሦስት ዓመት በፊት ኢትዮጵያን የጎበኙ አንድ ታላቅ ጋናዊ የነገረ መለኮት ሊቅ ንግግር ያደርጉ ነበር። ከንግግራቸው መጨረሻ የጥያቄና መልስ ጊዜ ላይ አንድ ኢትዮጵያዊ ፕሮቴስታንት ስለ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምን አስተያየት እንዳላቸው ይጠይቃቸዋል። ኢትዮጵያዊው ይህን የጠየቀው እንደለመደው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንድትሰደብለት ነበር። ነገር ግን የሰማው ያልጠበቀውን ነበር። ሊቁ «በሚቀጥለው ጊዜ ሳባቲካል ፈቃድ ሳገኝ የምመጣው ወደ አዲስ አበባ ነው። መጥቼም ከኦርቶዶክስ ሊቃውንት ሥር ቁጭ ብዬ መማር እፈልጋለሁ።» ብለው ነበር የመለሱለት።

በዘመናችን የሚገኙ ለዘብተኛ የፕሮቴስታንት ሊቃውንትም ገፋ ብለው ሄደው እግዚአብሔር ብለን የምንጠራው ባዶ የሆነ የምናብ ወይም የቃላት ሁኔታ እንደሆነ አድርገው በማስተማር ህልውናውን ክደዋል። እነ ካርል ማርክስን የመሳሰሉት ቀንደኛ ከሃድያን ስለ እግዚአብሄር ህልዎት ክደው በሚሊዮን የሚቆጠሩትን ያስካዱት በፕሮቴስታንቱ ዓለም የሚሰጠውን ትምህርት በመንደርደሪያነት ወስደው ነው። ለምሳሌ ካርል ማርክስ ብዙ ትምህርቱን የወሰደው ፍየርባህ ከሚባል ጀርመናዊ ነው። ፍየርባህ የሔግል ተማሪ ሲሆን በስተኋላ ከሔግልና ከሸለይማከር ከሌሎችም





የጀርመን ለዘብተኛ የነገረ መለኮት ሊቃውንት የወሰደውን ወደ መጨረሻው መደምደሚያ በማድረስ የእግዚአብሔርን ሐልዎት የሚክድ ሆኖአል። ካርል ማርክስ በፓለቲካል ኢኮኖሚ ጽሑፎቹ ፍሩድ በሥነ አእምሮ ጥናቱ ላይ ያስፋፉትን «ሃይማኖት የሰዎች የምናብ ውጤት ነው» የሚለውን ለመጀመሪያ ጊዜ ያንጸባረቀው ፍየርበህ ነው። ታዲያ ብዙዎች የታሪክና ነገረ መለኮት ሊቃውንት እንደሚስማሙበት ፍየርባህን ሐልዎተ እግዚአብሔርን የሚክድበት ትምህርት መሠረት ያደረገው ከለዘብተኛ ፕሮቴስታንቶች ዓለም ያገኘው ትምህርት ነው። በዘመናዊዎቹ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በከፍተኛ አክብሮት የሚጠራው ፍሬድሪክ ሸለይማከር ስለ እግዚአብሔር የተሳሳተ ትምህርት ከማስተማሩ በላይ ምሥጢረ ሥላሴን ሙሉ በሙሉ ክዶአል።[43]

የፕሮቴስታንቱ ዓለም መምህራን፥ በነገረ እግዚአብሔር ትምህርታቸው የደረሱበትን የመጨረሻ አደጋ የምንመለከተው፥ ታዋቂ የሆኑ የፕሮቴስታንት መሪዎች ስለ እግዚአብሔር የጻፉትን ወይም የተናገሩትን ስንመለከት ነው። ምንም እንኳዋን ይህን እዚህ ላይ ላማተት ቦታው ባይሆንም ከሊበራሉ የፕሮቴስታንት አካል የተገኙት እነ ጆን ኮብ ዴቪድ ግሪፍን ሌሎችም የፕሮቴስታንት መምህራን እግዚአብሔር ዓለምን እምህበ አልቦ - ካለ መኖር ያመጣው መሆኑን በመካድ የዝግመተ ለውጥን ንድፈ ሃሳብ በማምጣት እግዚአብሔር በዓለማት ውስጥ ሥርዓትን አስይዞ ይሆናል እንጂ ዓለማትስ ከጥንት ነበሩ ብለው አስተምረዋል። ሌሎችም የእንግሊዝ ፈላስፎች ያስተማሩትን የዴይዝም ፍልስፍና በመያዝ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ የራቀና ዓለምን በሜግቦቱና

(43) *we have no formula for the being of God in itself as distinct from the being of God in the world." Schleiermacher , The Christian Faith, 172.2*



www.ethiopianorthodox.org

በጥበቃው የማያስተዳድር አድርገው አስተምረዋል። ሌሎቹም ከነጭራሹኑ ሐልዎቱን ክደዋል። ሐልዎቱን ከካዱት መካከልና በዘመናችን ደግሞ መግቦቱንና ጥበቃውን ከካዱት መካከል ጥቂቱን እንመልከት።

## « ቴዎታናሲ,ያ» (the Death of God)

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1965 ዓ.ም በአሜሪካ ታዋቂ የሆነው «ታይም» መጽሔት «እግዚአብሔር ሞቶአል» God is dead በማለት በሽፋኑ ላይ ዐቢይ ርዕስ አድርጎ አውጥቶ ነበር። ይህ ፍልስፍና ወይም በእግዚአብሔር ላይ የተነገረ ጽርፈት የዓለማውያን ሥራ ሳይሆን የታወቁ የፕሮቴስታንት መምህራን የትምህርት ውጤት ነበር። ይህም ሊታወቅ በፌብሩዋሪ 16 ቀን 1969 ዓ. ም. ላይ ባወጣው እትሙ ላይ ታዋቂው የፕሮቴስታንት መጽሔት «ክርስቲያን ሴንቸሪ» በፌዝ የተሞላ ቅጽ ለአንባቢያኑ አቅርቦ ነበር። ቅጹም «ጎድ ኢዝ ዴድ ክለብ» ለመግባት የሚያስችል ነበር።

ይህ ትምህርት በዋናነት የተመሠረተው በውስጡ ባደረበት የክህደት መንፈስ ወደ እብደት በደረሰው የጀርመን ሰው «በፍሬድሪክ ኒቼ» ፍልስፍና ነው። ይህ ፍልስፍና በተለይ የምዕራቡ ዓለም የደረሰበትን የእምነት ቀውስ በገሃድ ግልጥ አድርጎ ያሳየ ነው። ኒቼ በ1882 ዓ.ም. «እግዚአብሔር ሞቶአል! እግዚአብሔር ሞቶ ይቀራል! እኛም ገለነዋል!» ብሎ በመናገር በምዕራቡ ዓለም ለእግዚአብሔር ሥፍራ እንደሌለ ግልጥ አደረገ። ይህም እግዚአብሔር ከዓለሙ ተለይቶአል የሚለው «የዴይዝም» ፍልስፍና የመጨረሻ ደረጃ ነበር። ይህንን የኒቼንና የዓለሙን መንፈስ ተከትለው የፕሮቴስታንቱ መምህራንም በክህደቱ ጎራ





ተጉዋዙበት። ከነዚህም መካከል ፖል ባን በረን Secular meaning of the Gospel በሚለው መጽሐፉ፥ እግዚአብሔር የሚለው ቃል ትርጉም መስጠቱ ስላቆመ ወንጌልን ንጹሕ በሆነ የኤቲክስ ትምህርት መተርጎም እንዳለበት ሲናገር፥ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርትም ስለ ሥነ ምግባር ያስተማረውንና የሕይወት ምሳሌነቱን ብቻ መውሰድ እንዳለብን በመጻፍ በእግዚአብሔር ማመን መቅረት እንዳለበት ጽፎአል።(44)

## «ኦፕን ቴይዝም»

ስለ እግዚአብሔር ያለው የስህተት አመለካከት በለዘብተኛ የነገረ መለኮት ትምህርት ቤቶች ብቻ የተገደበ አይደለም። ስህተቱ እያንዳንዱን የፕሮቴስታንት ክፍል አንካኩቶአል። ለምሳሌ በኖቬምበር 19 ቀን 2004 ዓ. ም. በአሜሪካ የሚገኘው የወንጌላውያን የቴዎሎጂ ማኅበር Evangelical Theological Society በአባላቱ መካከል ስለነበረው የነገረ መለኮት አመለካከት ድምጽ ሰጥቶ ነበር። ድምጽ የተሰጠበትም ትምህርት «እግዚአብሔር የወደፊቱን አያውቅም፥ ከሰዎች ሁኔታ ጋር እግዚአብሔር ሀሳቡን ይቀይራል» የሚል ነው። ይህም በእንግሊዘኛው ኦፕን ቴይዝም በመባል ይታወቃል።

የኦፕን ቴይዝም ትምህርት በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት እየተስፋፋ ያለ የእግዚአብሔርን ሁሉን አዋቂነት ምሉዕነት፥ አለመለወጥ በሙሉ የሚክድ ትምህርት ነው። በሌላ በኩል ያለው አንድምታ በእስትንፋሰ እግዚአብሔር የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ስህተት አለበት የሚል ነው። ለምሳሌ ክላርክ

(44) *Alister E, McGrath, Christian Theology. An introduction, third edition. Blackwell publishers. Pp.279-280.*



www.ethiopianorthodox.org

ፒኖክ የተባለ ታዋቂ የወንጌላውያን የቴዎሎጂ መምህርና የዚህ ስህተት አራማጅ በዚህ ፍልስፍና ላይ በመመስረት «አንዳንድ የብሉይ ኪዳንም ሆኑ የአዲስ ኪዳን ትንቢቶች ትርጉም የማይሰጡበት ወቅት አለ» ብሎ አስተምሮአል።

ጆን ሳንደር የተባለ ሌላው የዚህ ስህተት አስተማሪ ደግሞ «ተጸጸተ» «አዘነ» «ከቁጣው ተመለሰ» የሚለውን በሰብአዊ ቃላት የተገለጸውን የእግዚአብሔር ክንውን[45] በመያዝ እግዚአብሔር ሐሳቡን እንደሚለውጥ ከማስተማሩም በላይ የእኛ ድርጊት በእግዚአብሔር ውሳኔ ላይ ለውጥ ያመጣል በማለት እኛ የእግዚአብሔርን ውሳኔ መለወጥ እንደምንችል አስተምሮአል።

ይህ ትምህርት ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ከሚያስተምረው ፍጹም የሚቃረን ነው። በኢሳ 40፥13 ላይ «የእግዚአብሔርን መንፈስ ያዘዘ ወይስ አማካሪ ሆኖ ያስተማረው ማን ነው? ወይስ ከማን ጋር ተመካከረ ወይስ ማን መከረው? የፍርድንም መንገድ ማን አስተማረው? ዕውቀትንስ ማን አስተማረው? የማስተዋልንስ መንገድ ማን አሳየው?» እንደተባለ እግዚአብሔር በማንም ሐሳብና ውሳኔ ላይ የማይደገፍ ብቻውን ምሉእ የሆነ ነው። ውሳኔዎቹና ፍርዱ (ፍትሐ ጽድቁ) የተመሠረተውም በሁሉን አዋቂነቱ በምሉዕነቱ በሁሉን ቻይነቱ እንጂ በእኛ ድርጊት ወይም ፈቃድ ላይ አይደለም።እኛ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ፈቃዳችንን የምናስገዛውም ለዚህ ነው።

የሚገርመው ይህን በመሰለ ስህተት ውስጥ የገቡት ሰዎች ከነስህተታቸው በማኅበሩ ውስጥ እንዲቆዩ በድምጽ ብልጫ ተወስኖአል። ይህን ዓይነቱ የነገረ

(45) በነገረ መለኮት ቋንቋ «አንትሮፖምርፎሲዝም» ይባላል።





መለኮት ትምህርትን በድምጽ ብልጫ መወሰን፥ በየጊዜው በፕሮቴስታንቱ ውስጥ የሚታይ ሲሆን ከዚህ በፊት እንዳልነው ማለቂያ ወደሌለው ችግር ውስጥ የሚከት ነው። በአሁኑ ሰዓት በመላው የፕሮቴሳንት አብያተ ክርስቲያናት ይህን የመሰለ በውሳኔ ድምጽ የነገረ መለኮት ትምህርትን መወሰን እየተለመደ መጥቶ ለጊዜው በድምጽ ብልጫ እግዚአብሔር ግብረ ግብረ ሰዶምን እንደሚፈቅድ፥ የእግዚአብሔር ሐሳብ በሰዎች ተጽእኖ እንደሚደረግበት እግዚአብሔር ሁሉንም እንደማያውቅ ተወስኖአል። ለወደፊት የሚሆነውን ደግሞ በአግራሞት እየጠበቅን ነው።

## «የእምነት እንቅስቃሴ» እና ነገረ እግዚአብሔር

ዛሬ ዛሬ ከታላቁ ጀምሮ እስከ ታናሹ ድረስ የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንቶች እየተበከሉበት ያሉበት አዲስ ስህተት ቢኖር የእምነት እንቅስቃሴ faith movement የሚባለው ነው። ይህ እንቅስቃሴ ብዙ የስህተት ትምህርቶች ቢኖሩበትም በዋናነት ሊጠቀስ የሚችለው ስለ ነገረ እግዚአብሔር ያለው ትምህርት ነው።

### እግዚአብሔርን በሰው ቁመት

የእምነት እንቅስቃሴ መሪዎች ስለ እግዚአብሔር ያላቸው ትምህርት ፈጽሞ የተሳሳተ ከመሆኑም በላይ በእግዚአብሔር ላይ ስድብን የሚናገሩ ናቸው። ለምሳሌ ኬኒት ኮፕላንድ የተባለው አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንቶች የሚያመልኩት የእምነት እንቅስቃሴ መሪ «እግዚአብሔር እንደኔና እንደናንተ የሆነ ስድስት ጫማ ከሶስት ኢንች ክብደቱም ሁለት መቶ ፓውንድ ገደማ ነው። የእጁም ስንዝር ዘጠኝ



www.ethiopianorthodox.org

ኢንች ርዝማኔ ያለው ነው»(46) በማለት እግዚአብሔርን ከአንድ ካው ቦይ ቁመና ጋር ሲያመዛዝን፥ ጄሪ ሳቤል የተባለው ሌላ የዚሁ እንቅስቃሴ መሪም የኮፕላንድን ትምህርት ሲያብራራው «እግዚአብሔር የሰማይን ርዝመት የሚለካው በዘጠኝ ኢንች ስንዝር ነው። የኔ ስንዝር ዘጠኝ ኢንች አይሞላም። ስለሆነም እርሱ ከእኔ ይልቅ ታላቅ እንደሆነ አውቃለሁ። አሜን። ነገር ግን ያን ያህል ታላቅ አይደለም...»(47) በማለት እግዚአብሔርን እርሱ በሚያውቃቸው ሰዎች ልክ ወስኖታል።

በኢትዮጵያም በዚህ በሀገረ አሜሪካም ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ፕሮቴስታንቶች ጋር ጥብቅ ዝምድና ያለው ሞሪስ ሴሩሎ ደግሞ «መንፈሴ ከስጋዬ ከወጣ በኋላ የእግዚአብሔር ክብር ተገለጠልኝ የተገለጠልኝም ስድስት ጫማ ርዝመት የነበረው ሲሆን ከሰዎች ትንሽ ሰፋ ያለ ነው» ብሎአል።(48)

በኢትዮጵያውያን ፕሮቴስታንቶች ዘንድ የእርሱን ድርጊት ለመኮረጅ ብዙ ጥረት የሚደረግበት ቤን ሂንም በአንድ ወቅት «በአንድ ወቅት እግዚአብሔርን በግልጥ ከማየቴም በላይ የለበሰውን እንኩዋን ልብስ ልነግራችሁ እችላለሁ» በማለት ተናግሮአል። በዚህ ወቅት ከእርሱ ጋር አብራ የነበረችው ጄን ክሮች (የፖል ክሮች ባለቤት) «የለበሰው መንፈስ ቅዱስን ይሆን?» ብላ ስትጠይቀው ከባድ የሆነ የነገረ መለኮት ችግር ውስጥ እንደገባ

(46) *Kenneth Copeland , spirit, soul and body I (Fort worth TX, Kenneth Copeland ministries,1985) audiotape #01-0601 side 1.*
(47) *Jerry Savelle, Framing Your World with the Word of God, Part 2 (Fort Worth, TX: Jerry Savelle Evangelistic Association, Inc., n. d.), audiotape #SS-36, side 1.*
(48) *Morris Cerullo, The Miracle Book (San Diego, CA: Cerullo Word Evangelism, Inc., 1984), x-xi*





በማስተዋል ትንሽ ከዘገየ በሃላ ግን «አዎን» በማለት መንፈስ ቅዱስ አምላክነቱ ተክዶ ልብስ እንደሆነ ተናግሮአል።(49)

## ሰው እንደ አምላክ

የ«እምነት እንቅስቃሴ» አራማጆች ከፍተኛ ስህተት ውስጥ የወደቁት እግዚአብሔርን በሰው ቁመትና ወርድ በመለካት ብቻ አይደለም። ሰውንም ወደ እግዚአብሔር ክብር በመውሰድም ነው። እነዚህ ሰዎች ይህን የሚያደርጉት «እኔነትን» ማምለክ የምእራቡ ፈተና ስለሆነና ዓለሙም ስለሚከተላቸው ነው። ስለ ሰው አምላክነት ያስተማሩትን እስቲ እንመልከት።

የዚህ እንቅስቃሴ አባት ይባል የነበረውና በቅርቡ የሞተውና መጻሕፍቱ በኢትዮጵያውያን ፕሮቴስታንቶች ዘንድ በሰፊው የሚነበብለት ኬኒት ሃገን «ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እኩል በሚሆንበት ሁኔታ ነው የተፈጠረው። ... በእግዚአብሔር ፊት ያለምንም የታናሽነት ሃሳብ በእኩልነት መቆም ይችላል። እግዚአብሔር እኛን የፈጠረን በተቻለ መጠን በሁሉም ነገር እርሱን እንድንሆን አድርጎን ነው። የፈጠረን እርሱ ባለበት ሁኔታና ዓይነት ነው። ሰው በእግዚአብሔርነት ውስጥ የሚኖር ከእግዚአብሔር ጋር እኩል የሆነ ነው። ይህን የሚያምን ክርስቶስ ነበረ። እኛ እንደዚህ ነን። እኛ ክርስቶሶች ነን።» በማለት እግዚአብሔር የፈጠረው ራሱን እግዚአብሔርን እንደሆነ አስተምሮአል።(50)

(49) *Benny Hinn and Jan Crouch, Praise the Lord program on TBN (October 3, 1991*
(50) *Kenneth M. Hagin, Zoe: The God-Kind of Life (Tulsa, OK: Kenneth Hagin Ministries, Inc., 1989), 35-36, 41.*



www.ethiopianorthodox.org

በአሁኑ ወቅት የእንቅስቃሴው መሪ እንደሆነ የሚነገርለት ኬኒት ኮፕላንድ እግዚአብሔር ሰውን ስለፈጠረበት ዓላማ ሲናገር «እግዚአብሔር አዳምን የፈጠረበት ዓላማ ራሱን እግዚአብሔርን እንደገና ለማባዛት ከነበረው ዓላማ አንጻር ነው። አዳም በትንሹ የእግዚአብሔር ነገር ያለበት፥ እግዚአብሔርን የሚመስል ወይም የእግዚአብሔር ተገዥ ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር ነበር።»(51)

ከላይ የጠቀስነው ሞሪስ ሱሩሎም እግዚአብሔር ራሱን ማባዛቱ በአዳም ብቻ እንደማያቆም ሲያስተምር «ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ የእግዚአብሔር ዓላማ የነበረው ራሱን መፍጠር እንደነበረ ታውቃላችሁ? እናንተ እነማን ናችሁ? ተናገሩ እንጂ እናንተ እነማን ናችሁ? አይዞአችሁ በሉት «የእግዚአብሔር ልጅ» በሉት! ተናገሩት! በእናንተ ውስጥ የሚታየው ነገር በሙሉ የእግዚአብሔር መገለጫና እግዚአብሔር ያለውን ነገር በሙሉ ነው። ስለዚህ በፊታችሁ ስቆም የምታዩት ሞሪስ ሱሩሎን ሳይሆን፥ እግዚአብሔርን ነው። ኢየሱስን ነው።»ብሏል(52)

---

*(51) Kenneth Copeland, Following the Faith of Abraham I (Fort Worth, TX: Kenneth Copeland Ministries, 1989), tape #01-3001, side 1.*

*(52) Morris Cerullo, The Endtime Manifestation of the Sons of God, (San Diego: Morris Cerullo World Evangelism, n.d.), audio-tape 1, sides1 & 2*





# ምዕራፍ ስድስት

## ፕሮቴስታንትና ነገረ ሥጋዌ

*የሮም ሰዎች ሆይ፥ እግዚአብሔር ፍጡር ሥጋን ከመለኮት ጋር አስተካክለው ሲሉአችሁ በመደሰት ፈንታ ታዝናላችሁን? በእውነትስ ሥጋችሁ ከፍጡራን በላይ ስለ ነገሠ ልትደሰቱ ይገባችሁ ነበር። ከመላእክት አልተዋሐደም። የአብርሃምን ዘር ከፍ ከፍ አደረገ እንጂ።*

*ኢትዮጵያዊው አባ ጊዮርጊስ*

ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ደግማ ደጋግማ እንደምታስተምረው የኦርቶዶክሳዊ ነገረ መለኮትና የስብከት ዘዴ ማዕከል ክርስቶስ ነው። ይህንንም የክርስቶስን ነገር (ምሥጢረ ሥጋዌን) በነገረ መለኮት ትምህርትዋ በሚገባ አስፋፍታ ታስተምራለች።

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የምሥጢረ ሥጋዌ ነገር ታላቅ ትርጉም አለው። ለዘመናት ነቀፋን የተቀበለችበት አባቶቹዋ በጽድቅ የተሰደዱበት ስለሆነ የተሰደበችበትን የአባቶቹዋን ትምህርት «ተዋሕዶን» የስሙዋ መጠሪያ አድርጋ ትታያለች። በተዋህዶ ትምህርታችን ላይ በካቶሊኮችና በኬልቄዶናውያን ፕሮቴስታንቶች ብዙ ስድቦች የተጻፉብን ሲሆን አንዳንዱ ታሪክን የሚያዛባ ፍጹም ሐሰትን የተሞላ ነው። ለምሳሌ፥ በጆናታን ሂልደብራንት የተጻፈውና በጌቱ ግዛው ወደ አማርኛ የተተረጎመው «የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአፍሪካ የሚለው» መጽሐፍ የግብጽ ቤተ ክርስቲያንንና



www.ethiopianorthodox.org

*የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ቀያይጦና ቀስጦ ለመጻፍ የሞከረ ከመሆኑም በላይ ኬልቄዶንን አክብሮና ቀባብቶ ሲጽፍም «በ451 ዓ. ም. ቤተ ክርስቲያንን ይፈታተኑዋት የነበሩትን አዳዲስ ጥያቄዎች ለመመርመር ዓለም አቀፍ የአብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ኬልቄዶን ላይ ተካሂዶ ነበር። በዚህ ጉባኤ እንደገና የተነሳው ቁልፍ ጥያቄ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚመለከት ነው። ከግብጽ የመጡ አንዳንድ ጳጳሳት ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንጂ ሰው የነበረበት ጊዜ ጨርሶ የለም የሚል እምነት ነበራቸው።»* ይላል።[53] ይህ ዓይን ያወጣ የሐሰት ታሪክ ቴዎሎጂን ወይም የቴዎሎጂን ቋንቋ ካለማወቅ አይደለም። ታሪክን እንደገና ለመጻፍና የዋህ ምእመናንን ለማሳሳት ተብሎ ታስቦ የተጻፈ ነው እንጂ ኦርቶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ በተዋህዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ብላ ማስተማሩዋን አጥተውት አይደለም። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ፍጹም አምላክነትና ፍጹም ሰውነት አምልቶና አስፍቶ ማስተማር የኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ተግባር ነው። የክርስቶስን ፍጹም አምላክነትና ፍጹም ሰውነት በተዋህዶ ማስተማር ግን ኬልቄዶናውያን የሚያስተምሩትን «ሁለት ባሕርይ» ትክክል እንደሆነ የሚያስቆጥር አይደለም።

ቤተ ክርስቲያናችን ከሌሎች የኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናት ጋር በመሆን የፖለቲካ ጉባኤ ከሆነው ከኬልቄዶን ጉባኤ ውሳኔና ትምህርት ራሱዋን ለይታለች። አባታችን ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ያለስሙ ስም ሰጥተውት ሃይማኖቱን ለዚያውም የቄርሎስን ሃይማኖት ሳይናገርና ዕድል ሳይሰጡት ስላሳደዱት በስብሰባውም ላይ የነበሩት የቁስጥንጥንያን ቤተ

*(53) ጆናታን ሂልደብራንት፤ ጌቱ ግዛው፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአፍሪካ ገጽ 24-25።*





መንግሥት ፖለቲካና የልዮን ቀዳማዊን ውሳኔ በተግባር ለመወሰን የሚቸኩሉ እንጂ በመንፈስ ቅዱስ የሚመሩ ስላልሆኑ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤውን አልተቀበለችም። ውሳኔውንም የንስጥሮስ ትምህርት በሌላ መንገድ ሌላ ልብስ ለብሶ እንደመጣ ቆጥራዋለች።

ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት የግሪክ ኦርቶዶክስንና የሮማ ካቶሊክን ጨምሮ ብዙዎች ኬልቄዶናውያን ውሳኔያቸውን እየመረመሩ ናቸው። በተለይም የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ የሚያጠኑ ሊቃውንት በግልጥ እንደተገነዘቡት የኬልቄዶኑ ጉባኤ ፊት ለፊት የተቃወመው ቅዱስ ዲዮስቆሮስን ሳይሆን ታላቁን የምሥጢረ ሥጋዌ አስተማሪ ቅዱስ ቄርሎስንና በእርሱ እየተመራ እውነተኛ የሆነውን የተዋሕዶ ምሥጢር በሚገባ ያስረገጠውን የኤፌሶኑን ሲኖዶስ ነው። በዚህም ምክንያት በአሁኑ ወቅት በምዕራባውያን አብያተ ክርስቲያናትና በሌሎችም ኬልቄዶናውያን ዘንድ ጉባኤ ኤፌሶንንና ጉባኤ ኬልቄዶንን ለማስታረቅ ችግር ላይ ናቸው። ዲዮስቆሮስ ያስተማረው አዲስ ትምህርት ሳይሆን የቄርሎስን ትምህርት ስለሆነ ዲዮስቆሮስን ማውገዝ ቄርሎስን መካድ እንደሆነ እየተገነዘቡ የመጡ ይመስላሉ። ሂደቱን ኬልቄዶንን አንቀበልም ያሉ እውነተኞች ኦርቶዶክሳውያን በቅርብ እየተከታተሉት ነው።

## <u>የኤፌሶን ጉባኤ እና ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን</u>

የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ የነበረው ንስጥሮስ አንዱን ክርስቶስ ለሁለት ከፍሎ ሁለት ባሕርይና ሁለት አካል ነው ያለው ሲልና ወላዲተ አምላክ (ቴዎቶኮስን) ሳይሆን ወላዲተ ሰብእ (አንትሮፖቶኮስ) መባል አለባት



www.ethiopianorthodox.org

ሲል ቤተ ክርስቲያን ወደ ከባድ አደጋ ውስጥ ነበር የገባችው። ምክንያቱም የንስጥሮስ ትምህርት ቤተ ክርስቲያን ስለ ምሥጢረ ሥጋዌና ስለ ምሥጢረ ድኂን (ሴትዮሮሎጂ) ያላትን ትምህርት ከሥሩ የሚያፈልሰው ነበርና።ይህን አደጋ በሚገባ የተገነዘበው ደግሞ የኦርቶዶክስ ምስክር የሆነው ቅዱስ ቄርሎስ ነበር። ቅዱስ ቄርሎስ ከስህተቱ እንዲመለስ ደጋግሞ ንስጥሮስን ቢለምነው እምቢ ስላለ በአሥራ ሁለት አናቴማ (መርገም) አወገዘው። የንስጥሮስ ደጋፊዎች የሆኑ ቅዱስ ቄርሎስን በመናፍቅነት ለማስወገዝ ቢጥሩም ሃይማኖታቸው በቀና አባቶች እውነተኛ ምስክርነትና በቅዱስ ቄርሎስ ትምህርት የኤፌሶን ጉባኤ ንስጥሮስንና ተከታዮቹን አውግዘው ለይተዋቸዋል።

ቅዱስ ቄርሎስና የኤፌሶን ሲኖዶስ አባቶች እመቤታችንን ወላዲተ አምላክ ሲሉና የመለኮትንና የትስብእትን (የሥጋን) ተዋህዶ ሲያውጁ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደረጉትና አንዱን ክርስቶስን ላለመክፈል ነበር። ሁለት አካልና ሁለት ባሕርይ በማለቱ ንስጥሮስ አንዱን ክርስቶስ በመክፈል «ክርስቶስ ጸዋሬ እግዚአብሔር (ቴዎፎሮስ) ማለትም እግዚአብሔርን የተሸከመ ነው እንጂ እግዚአብሔር አይደለም። የሚመለከውም እግዚአብሔር ስለሆነ ሳይሆን እግዚአብሔር በውስጡ ስላለ ነው[54] ወደሚል የህድረትን ትምህርት ደርሶ ስለነበር እነ ቅዱስ ቄርሎስ ስህተቱን ነቅፈውና አጸይፈው የትስብእትንና የመለኮትን ተዋህዶ በሰፊው አትተው አስተማሩ።

ከዚህም በተጨማሪ እንደ ንስጥሮስ ትምህርት ከሄድን አንዱን ክርስቶስ ገነጣጥሎና ምንታዌነትን (ሁለትነትን)

(54) አምላክነቱን የካዱ ዘመናውያን ለዘብተኛ የነገረ መለኮት አስተማሪዎች ይህን የንስጥሮስን ትምህርት በሚገባ ወስደውታል።





ከተዋሕዶ በኋላ ስለሰጠ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተማሩትን የክርስቶስ የማዳን ሥራ የሚቃረን እንደሆነም አሳዩ። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ከሰው ልጆች ጋር ያለውን ዝምድና በሚገባ በማሳየትም፥ የዚህ ዝምድና ምክንያት የሆነችውም የአንዱ ጌታና አምላክ እናት የሆነችው ቅድስት ድንግል ማርያም እንደሆነች በማስተማር፥ በአማን ወላዲተ አምላክ በእውነት የአምላክ እናት እያሉ አስተማሩ። ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ይህን የየጥንታውያን አበውን እምነት ይዛ በተዋህዶ የከበረውን አምላክ ታመልካለች። ድንግል ማርያምንም በእውነት ወላዲተ አምላክ ትላለች።

## የንስጥሮስ አስተሳሰብ እና የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንቶች።

ይህ ከላይ ያየነው ጥንታዊው የህድረት ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ ከወሰዳቸውና ምሥጢረ ተዋሕዶን የጎሪጥ ከሚመለከቱት የእምነት ክፍሎች መካከል በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የፕሮቴስታንት ክፍሎች ዋናዎቹ ናቸው። የፕሮቴስታንት ክፍሎች እንደ ምሥጢረ ሥላሴ በምስጢረ ሥጋዌውም ምንም ብስለት ያለው ትምህርት ስለሌላቸው ለብዙ የስህተት ትምህርት የተጋለጡ ናቸው። በተለይም ደግሞ የንስጥሮስ የህድረት ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ በውስጣቸው ከመግባቱ የተነሳ እንደዋና ትምህርት እያደረጉ ለአባላቶቻቸው ያስተምራሉ።

በተለይም የፔንቴኮስታልና የባፕቲስት ትውፊት ያላቸው የፕሮቴስታንት ክፍሎች ይህን የክህደት ትምህርት የሚያስተምሩት የእምነታቸው አካል እንደሆነ አድርገው ነው።[55] ከድርጅቶቻቸው ትውፊት በተጨማሪም ልክ እንደ ሕጻናት ጥምቀት፥ ይህንንም



www.ethiopianorthodox.org

የሚቃወሙት ወደ እነርሱ የሚያስኮበልሉአቸውን የኦርቶዶክስ ልጆች ለዘላለም ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው ለመለየትና በፍጹም ቤተ ክርስቲያኗዋን እንዲጠሉ ለማድረግ ነው።

በተለይም ወላዲተ አምላክን ማስጠላትን እንደታላቅ ስኬት አድርገው የሚቆጥሩ አንዳንድ ሰባኪዎቻቸው የእመቤታችን ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክነትን ከመካዳቸው በላይ ተራ በሆነ ቋንቋ «የእርስዋ አገልግሎት እንደ ሳጥን ነው ማደሪያ ብቻ ናት» እያሉ የሚያስተምሩ ሆነዋል።

ለመሆኑ ፕሮቴስታንቶች ይህን የሚያስተምሩት ምንን መሠረት አድርገው ነው? ለትምህርታቸው ምስክር የሚያደርጉት አለቦታው የሚጠቅሱትን ጥቅስ ነው። ይህም «መሥዋዕትንና መባን አልወደድህም ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ በሙሉ በሚቃጠል መሥዋዕትና ስለ ኃጢአት በሚሠዋ መሥዋዕት ደስ አላለህም። በዚያን ጊዜ እነሆ በመጽሐፍ ጥቅልል ስለ እኔ እንደተጻፈ አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ።» የሚለውን የዳዊት መዝሙር ነው። መዝ 39፥6።

ከዚህም በኃይለ ቃልነት የሚጠቅሱት «ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ» የሚለውን ነው። በእነርሱ አነጋገር ሥጋን አዘጋጀህልኝ የሚለው አነጋገር ልዩ ሥጋ ለወልድ ተዘጋጅቶለታል የሚል ትርጉም አለው። ይህ ዓይነቱ ክህደት ለቤተ ክርስቲያን አዲስ አልነበረም።

(55) George Williams, Radical Reformation. *በአሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን የተነሱት አና ባፕቲስቶች ክርስቶስ የለበሰው ሰማያዊ ሥጋን ነው ብለው ያስተምሩ ነበር። ትምህርታቸውም ሁለት ቅርንጫፍ ነበረው። አንደኛው ክርስቶስ ሥጋን ከሰማይ ይዞ ወርዶአል ይህም ይዞት የመጣው ሥጋ ከጥንት ጀምሮ ከእርሱ ጋር ነበር የሚል ነው። ሌሎች ደግሞ ክርስቶስ መንፈሳዊ አካል ነው የነበረው። በማህፀነ ማርያም ሲያድር ያው መለኮትነቱ ወደ ሥጋነት ተለውጦአል የሚል ነው። እነዚህ ሁለት ዓይነት ትምህርቶች በኢትዮጵያ ፕሮቴስታንቶች ዘንድ በሰፊው ይታያሉ።*





ሥጋን ይዞ ከሰማይ ወርዶአል የሚል የስህተት ትምህርት ከቀድሞ ጀምሮ ነበር። የዚህ የክህደት ትምህርት ዓይነተኛው አደጋ ከላይ እንደጠቀስነው የደኅንነትን ምሥጢር ማፋለሱ ነው።

ይህን የፕሮቴስታንቶችን ትምህርት ብንቀበል ኖሮ፥ አንደኛ፥ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ሆኖአል የሚለውን ትምህርት መቀበል ባልቻልን ነበር። ምክንያቱም ሰው የምንለው ከሰው ዘር የገባ ሐረገ ትውልድ የሚቆጠርለት ነውና። ጌታችን የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ሥጋና ነፍስን ስለነሳ በእርሱዋ ሐረገ ትውልድ ተቆጥሮአል። «ከሴቲቱ ዘር» የተባለው የብሉይ ኪዳን ትንቢት በልደቱ ተፈጽሞአል። ሁለተኛ ክርስቶስ የሰው ልጆች ቤዛ ባልሆነም ነበር።[56] ምክንያቱም ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ እንደምንመለከተው ቤዛ የሚሆነው የቅርብ ዘመድ ወይም የሥጋ ዘመድ ነው። ይህን ሐዋርያው በዕብራውያን መልእክት ላይ ግሩም አድርጎ አስቀምጦታል። «እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ እርሱ (ክርስቶስ) ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር ይኸውም ዲያብሎስ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለሞት ፍርሃት በባርነት ታሥረው የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ። የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም።» ዕብ 2፥14-16።[57]

*(56) ቅዱስ ቄርሎስ በኤፌሶን ለተሰበሰቡት አባቶች የንስጥሮስ ትምህርት የሚያመጣውአደጋ ብሎ ያስቀመጣቸው እነዚህን ነጥቦች ነው። ንስጥሮስም ሆነ የዛሬዎቹ ፕሮቴስታንቶች የእመቤታችን ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክነት ሲክዱ የሚክዱት የወልደ እግዚአብሔርን ሰው መሆንና ቤዛነቱን ነው።*

*(57) «ኢይደሉ ይትፈለጥ መለኮቱ እምትስብእቱ እምድህረ ተዋህዶ ከመ ኢይስአር ረባሁ ለተዋህዶ። የተዋህዶ ጥቅሙ (ቁም ነገሩ) እንዳይሻር መለኮትን ከትስብእት መለየት አይገባም» ያሉት አበው የተዋህዶ ምስጢር ከተፋለሰ የቤዛነቱን ነገር መናገር ስለማይቻል ነው።*



www.ethiopianorthodox.org

ጌታ የነሣው ከሰማይ የወረደ ሥጋን አይደለም። የመላእክትን አይደለም። የነሳው የአብርሃምን ነው። በዚህም የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ ተብሎ ሐረገ ትውልድ ተቆጥሮለታል። «የሚቀድሰውና የሚቀደሱት ከአንድ ስለሆኑም... ወንድሞች ብሎ ሊጠራቸው አያፍርም» እኛም ቤዛችን ብለን ለመጥራት አናፍርም። ዕብ 2፥11፥13።

በኢትዮጵያ የሚገኙ አብዛኛዎቹ ፕሮቴስታንቶች ይህን የንስጥሮስን የህድረት ትምህርት ሲቀበሉ አብረውም የውላጤን ትምህርት ተቀብለዋል። በተለይም «ቃል ሥጋ ሆነ» የሚለውን የዮሐንስ ወንጌላዊ የተዋሕዶ ንባብ «ሆነ» የሚለውን ተለወጠ አሰኝተው ቃል (ሎጎስ) ራሱ ተለውጦ ሥጋ እንደሆነ ያስተምራሉ። ይህም ትምህርት ልክ በህድረት የስህተት ትምህርት ላይ እንዳየነው የክርስቶስን የቤዛነት ትምህርት የሚያስክድ ነው።

## «የታሪካዊ ኢየሱስ» ትምህርት በፕሮቴስታንቱ ዓለም።[58]

የፕሮቴስታንቱ ዓለም ከምሥረታው ጀምሮ የተከተለው ሰዋዊ አመክንዮን (ራሽናሊዝምን) ስለሆነ እምነት ታች ወርዳ የአመክንዮ አገልጋይ የሆነችው ብዙም ውሎ ሳያድር ነው። በተለይም ደግሞ ጊዜ የማይለውጠውን የእግዚአብሔርን ቃል፥ ከጊዜው ነፋስ ጋር መቀያየርን እንደታላቅ ሊቅነት ስለያዙት መጨረሻ ላይ ይህ «ምርምራቸው» ያደረሳቸው የክርስቶስን ታሪካዊነት ወደ መጠራጠር ነበር።

*(58) ይህም በዚህ በውጭው ዓለም Quest of the Historical Jesus ብለው የሚጠሩት ነው። ይህን የክርስቶስን አምላክነት የሚክድና ብሎም ክርስቶስ በታሪክ ውስጥ ያልነበረ ልብ ወለዳዊ ገጸ ባሕርይ ነው ብሎ የሚያስተምረው ክፉ ዘር ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የቴዎሎጂ ኮሌጆች ውስጥ በሚገባ ሰርጎ እየገባ ነው።*





ባለፈው የፕሮቴስታንቱ ዓለም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያለውን እይታ በተመለከትንበት ወቅት እንዳየነው መሥራቾቹ ለራሳቸው አልስማማ ያላቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እውነተኛነት መጠራጠር ጀምረው ነበር። ይህ ጥርጥር በዚህ አላበቃም። በመቀጠል የሆነው ነገር ቢኖር ወንጌላት ስለ ክርስቶስ የሚናገሩት ሁሉ እውነትነት እንደሌለው ማስተማር ጀመሩ። የዚህ የክህደት ትምህርት በሦስት አስተያየቶች ላይ የተመሠረተ ነው።

1ኛ) ወንጌላቱ ስለክርስቶስ የሚያስተምሩት ስህተት እንደሆነና ወንጌላቱም የተጻፉት ከሁለተኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ እንደሆነ፤

2ኛ) በእምነት የሚመለከው ወይም የሚታመነው ክርስቶስ ከ«ታሪካዊው ኢየሱስ» ልዩ እንደ ሆነ፤[59]

3ኛ) ቅዱስ ጳውሎስ ያስተማረው የክርስትና ትምህርትና ክርስቶስና ሐዋርያት ያስተማሩት ትምህርት እርስ በርሳቸው ይቃረናሉ ብሎ የሚል ነው። በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ውስጥ ዋና ዋና የሆኑትን ሰዎችና ያስተምሩ የነበሩትን ክህደት ለማየት ያህል፥

1. <u>ሬይመራስ።</u> ሄርማን ሳሙኤል ሬይመራስ ከ1694-1768 ዓ. ም. የኖረ ጀርመናዊ ነው። ሬይመራስ ክርስትናና ይሁዲነት በተዛባ መሠረት ላይ የቆሙ ናቸው ብሎ ያስተምር ነበር። በሕይወት ዘመኑ ሳለ ያላሳተመውና በስተኋላ በተገኘው ጽሑፉ ላይ፥ መሠረታዊ የሆኑትን የክርስትና እምነቶች የተቸ ሲሆን በዋናነትም ያተኮረው ስለ ትንሣኤ ታሪካዊነት ማለትም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ ታሪካዊ እውነት አይደለም በሚለው ላይ ነው።

*(59) ይህ ቀድሞ በአንደኛውና በሁለተኛው ክፍለ ዘመን የተነሱ መናፍቃን (ግኖስቲኮች) ያስተማሩትን የስህተት ትምህርት ይመስላል። በእነርሱ ትምህርት ኢየሱስና ክርስቶስ የተለያዩ ሲሆኑ የተሰቀለው ኢየሱስ እንጂ ክርስቶስ አይደለም። የእስልምና መስራቾች ከዚህ ወስደው ሳይሆን አይቀርም ነቢ ኢሳ አልተሰቀለም የሚሉት።*



www.ethiopianorthodox.org

በሌላ በኩል ደግሞ ስለ ኢየሱስ በጻፈው መጽሐፉ ላይ፥ ወንጌላት የጻፉትን ሐሰት ነው በማለት ስለ ኢየሱስ የተጻፈው በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ተዛብቶ የቀረበ ነው ብሎአል። ለሬይመራስ የኢየሱስ ትምህርትና የሐዋርያት ትምህርት የተለያየ ነው። በእርሱ አስተሳሰብ ክርስቶስ አምላክ ነኝ አላለም። የዚህ ዓለም አምላክ የተባለው ዲያብሎስ ዓይኑን አሳውሮት ነው እንጂ፣ ክብር ይግባውና ክርስቶስ ራሱ ከአብ ጋር አንድ መሆኑንን ተናግሮአል። እስከ መስቀል ያደረሰውም ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ይላል የሚለው ክስ ነበር።

2. <u>ዌሊያም ሬዴ።</u> ከሉተራን ቤተ ሰብ የተወለደውና ከታዋቂው ሊበራል የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሊቅ ከሀርናክ ጋር የተማረው ሬዴ፥ ከሬይመራስ እልፍ በማለት ወንጌላቱ በሙሉ እምነት ሊጣልባቸው የማይገባ የታሪክ መዛግብት ናቸው ብሎ አስተማረ። በእርሱ እምነት መሠረት ስለ ክርስቶስ በሐዋርያት የተሰጡት የተጻፉት ትምህርቶች በሙሉ ከአይሁድ የተለያዩ ቡድኖች የተገኙ ነው። ወይም ወንጌላቱን የጻፉት ከራሳቸው አመለካከት አንጻር የጻፉት ነው። ይህ እንግዲህ ዛሬ መላውን የፕሮቴስታንቱን ዓለም እያመሰ ካለው የክህደት ትምህርት በጥቂቱ ነው።

## «<u>የእምነት እንቅስቃሴ» እና ምሥጢረ ሥጋዌ</u>

የእምነት እንቅስቃሴ መሪዎች እንደ ሌሎቹ ወንድሞቻቸው ስለ ክርስቶስ የሚያስተምሩት መያዣና መጨበጫ የሌለው ነው። የክርስቶስን አምላክነት ከመካድ አንስቶ፥ ክብር ይግባውና ኃጢአት የሌለበትን እርሱን ኃጢአት የማድረግ ችሎታ





እንዳለው፥ ከሰይጣን ጋር አንድ እንደሆነ በሲኦል ዳግም እንደ ተወለደ አስተምረዋል። እስኪ ከእነርሱ አንደበት እንስማ፥

## «<u>አምላክነት የሌለው ኢየሱስ</u>»

ኬኒት ኮፕላንድ «ኢየሱስ» ነገረኝ ብሎ ሲያስተምር *«ሰዎች ስለ አንተ ክፉ ነገር ሲናገሩ አትረበሽ። እኔን በመሰልክ ቁጥር እንደ እኔ ያደርጉሃል፤ እግዚአብሔር ነኝ ብለሃል ብለው እኔን ሰቀሉኝ። እኔ ግን እግዚአብሔር ነኝ አላልኩም። ከእግዚአብሔር ጋር አብሬ የተጉዋዝኩኝና እግዚአብሔር ያደረብኝ ነኝ አልኩ እንጂ»*[60] ሲል በሌላም ቦታ ሲናገር *«እግዚአብሔር ይሆን ሁሉ የከፈለው ለምን ይመስላችኋል? የመጀመሪያውን ሰው የመሰለ ሰው ያስፈልገው ነበረ። ያንንም የመሰለ ሰው (ኢየሱስን) አገኘ። እርሱ ሙሉ በሙሉ ሰው መሆን ነበረበት። እግዚአብሔር በመሆን በምድር ሲመላለስ በባሕርይ መገለጫዎቹና በክብሩ መታየት አይችልም ነበር። ይህ ለሰው የተለመደ አይደለም። እንደዚያም ማድረግ አይችልም ሕጋዊም አይደለም።»* ብሏል።[61]

ቤን ሂን *«መንፈስ ቅዱስ እንደምን አደርክ?»* በሚለው *መጽሐፉ ላይ «...መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ጋር ባይሆን ኖሮ ኢየሱስ ይበድል ነበር። ልክ ነው፥ ንጹሕ እንዲሆን የጠበቀው ኃይል መንፈስ ቅዱስ ነው። ከሰማይ መምጣት ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ ተብሎም ስለተጠራ ኃጢአት ለማድረግ ችሎታ ነበረው፥ መንፈስ ቅዱስ ሐሳቡን ቢቀይር ኖሮ ኢየሱስ በመቃብር ይቀር ነበር»*

---

*(60) Kenneth Copeland, Take Time to Pray, Believer's Voice of Victory 15, 2 (February 1987): 9*

*(61) Kenneth Copeland, What Happened from the Cross to the Throne (Fort Worth, TX: Kenneth Copeland Ministries, 1990), audiotape #02-0017.*



www.ethiopianorthodox.org

በማለት ክርስቶስን ለስም አጠራሩ ክብር ይግባውና የኃጢአት ባለቤት ያደርገዋል።(62)

ይህ የቤን ሂን ትምህርት ፍጹም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እንዴት እንደሚቃረን ለማንም ግልጥ ነው። የንጹሐ ባሕርይ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው መሆን ከኃጢአት ውጭ እንደሆነ ሐዋርያው ሲያስረዳ *«ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው»* በማለት ክብር ይግባውና ጌታችን የኃጢአት ፈተናም የኃጢአት ችሎታም እንደሌለው አስተምሮአል። ዕብ 4፥14።

ኃጢአት ከሰው ጥንተ ተፈጥሮ ጋር የነበረ ሳይሆን ከውድቀቱና ከበደሉ ጋር የመጣ መሆኑንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲያትት *«ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ፤ በኃጢአትም ሞት»* በማለት ኃጢአት የውድቀት ውጤት መሆኑን ገልጦአል። ሮሜ 5፥12። ጌታችን የእኛን የሰውነት ባሕርይ ነው የተዋሃደው እንጂ የውድቀታችንን ወይም የኃጢአታችንን ባሕርይ አይደለም።

## መስቀል እና ሰይጣን

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ብዙ ተቃዋሚዎች ከተነሱበት ትምህርት አንዱ የመስቀሉ ነገር ነው የክርስትና ማዕከል ወንጌል ነው፤ የወንጌልም ልብ ጸጋ ነው፤ የጸጋም ማዕከል ነገረ መስቀሉ ነው። ነገረ መስቀሉን ከትምህርታችን ውስጥ ካወጣን ለክርስትናችን ትርጉም አናገኝም። በዚህ ምክንያት ሰይጣን ክርስቶስ አልተሰጠም ከሚለው ጀምሮ ክርስቶስን ምትሃት አድርጎ እስከመጥራት ሰዎችን ሲያደርስ እናስተውላለን። የእምነት እንቅስቃሴ

---
*Benny Hinn, Good Morning, Holy Spirit (Nashville: Thomas Nelson, 1990), 135-36.*





መሪዎችም በዋናነት የተዋጉትም የመስቀሉን ነገር ነው።

ቤን ሂን መንፈስ ቅዱስ ለግሌ የነገረኝ ነው ባስተማረው ትምህርት ላይ እንዲህ ነበር ያለው *«ክቡራንና ክቡራት፥ እባቡ የሰይጣን ምሳሌ ነው። ሰይጣንን ድል የማድረጊያ ብቸኛው መንገድ ከሰይጣን ጋር በባሕርይ አንድ በመሆን እንደሆነ ሰይጣን አውቆ ነበር። ይህን ስል «ምንድነው ያልከው? ምን ዓይነት ስድብ ነው?» ትሉኝ ይሆናል። አዎ ስሙኝ የኔን ኃጢአት አልወሰደም ኃጢአት ሆነ እንጂ ... ሰይጣንን የሠራው ኃጢአት ነው። ኢየሱስ «ኃጢአት እሆናለሁ ወደ ታች እሄዳለሁ አለ። ኢየሱስ ኃጢአት ሲሆን የወሰደው ከ«ሀ» እስከ «ፐ» ሁሉንም ነው። ... የሰይጣን ባሕርይ ጋር አንድ የሆኑት ከእርሱ ጽድቅ ይካፈሉ ዘንድ ኢየሱስ ከሰይጣን ባሕርይ ጋር አንድ ሆነ፤»*(63)

ኬኒት ሀገን ይህን የቤን ሂንን ዓይን ያወጣ ስድብ ደግፎ ሲያስተምር *«መንፈሳዊ ሞት ማለት ከእግዚአብሔር ከመለየት የበለጠ ነው። መንፈሳዊ ሞት ማለት የሰይጣንን ባሕርይ መውሰድ ነው። ክርስቶስ ሞትን ማለትም መንፈሳዊ ሞትን ቀምሶአል»* ብሎአል።(64)

የእምነት እንቅስቃሴ መሪዎች ይህን የሚያስተምሩት አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ገንጥለው በመውሰድ ነው። ይህም በ2ኛ ቆሮ 5፥21 ላይ የሚገኘውንና *«እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው።»* የሚለውን እንደራሳቸው ተርጉመውት ነው።

---
*(63) Benny Hinn, Benny Hinn program on TBN (Dec 15, 1990*
*(64) Kenneth E. Hagin, The Name of Jesus (Tulsa, OK: Kenneth Hagin Ministries, 1981), 31*



www.ethiopianorthodox.org

*አደረገው።»* የሚለውን እንደራሳቸው ተርጉመውት ነው። ይህ ቃል እነርሱ እንደሚሉት ከሰይጣን ጋር አንድ መሆን የሚያመለክት ሳይሆን የኛን ኃጢአት ክብር ይግባውና ንጹሐ ባሕርይ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሸከመው የሚያመለክት ነው።

በዚህ በሎስ አንጀለስ ከተማ ውስጥ በቅምጥል ኑሮው የሚታወቀው ፍሬድሪክ ፕራይስ *«ኢየሱስ በመንፈስ ሞቶአል»* የሚለውን ሲያስተምር *«በጌቴሴማኒ በነበረበትና በመስቀል ላይ በተቸነከረበት መካከል አንድ ቦታ ኢየሱስ በመንፈሱ ሞቶአል። በግሌ ቦታው በጌቴሲማኒ የአትክልት ሥፍራ ይሆናል»* ብሎአል።[65]

እነ ዶክተር ቶሎሳ ይህንን ትምህርት በአደባባይ አያወግዙም። ምክንያቱም ከዚህ ትምህርት ጋር አንድ ናቸውና። ከዚህ ይልቅ ከመከራዋ ጋር ሃይማኖትዋን የጠበቀችውን ቤተ ክርስቲያን ሊሰድቡ ተነሱ። ኢትዮጵያውያንን ሰብእናቸውን ለማዋረድ ሞከሩ። አብዛኛው ስድባቸው የተመሠረተው በእነዚህ ሰዎች ትምህርት ላይ ነው። የክርስቶስን መስቀል መለማመድ ለዶክተሩም ሆነ ለእነዚህ ሰዎች ሰዎች ቀልድ ነው። በመስቀሉ ላይ ያላቸውን የድፍረት ቃልና ስህተታቸውም ምን ያህል እንደከፋ የምንመለከተው ኢየሱስ በገሃነም ዳግም ተወልዶአል ብለው የሚያስተምሩትን ስንመለከት ነው።

ፍሬድሪክ ፕራይስ ስለዚህ ሲያስተምር *«ስለ ኃጢአታችን የተከፈለው ፍርድ በመስቀል ላይ መሞት እንደሆነ ታስባላችሁ? ያ ቢሆን ኖሮ በመስቀል የተሰቀሉት ሁለቱ ወንበዴዎች ስለ ኃጢአታችሁ ዋጋ*

(65) Frederick K. C. Price, *Identification #3 (Inglewood, CA: Ever Increasing Faith Ministries, 1980), tape #FP545, side 1*





*በከፈሉ (ቤዛ በሆኑ) ነበር። ፍርዱ ወደ ገሃነም መሄድና በዚያም ፍርድን መቀበል ከእግዚአብሔር መለየት ነበር። ኢየሱስ ወደ ገሃነም በወረደ ጊዜ ሰይጣንና አጋንንት በሙሉ ያገኙትና ድል ያደረጉት መስሎአቸው ነበር። በዚህም መንገድ በገሃነም መከራን ተቀብሎ የኃጢአታችንን ዋጋ ስለ እኛ ከፈለ»* ይለናል።[66] ፕራይስ ይህንን ትምህርት የግብር አባቱ ዲያብሎስ ካላስተማረው በስተቀር ከየት እንዳመጣው አልተናገረም።

ፕራይስም ሆነ ሌሎቹም የእምነት እንቅስቃሴ መሪዎች ክርስቶስ በገሃነም ተሰቃይቶአል ብለው አያቆሙም። ክርስቶስ በገሃነም ዳግም ተወልዶአል የሚል ትምህርትም አላቸው። ቤን ሂን ተገለጠልኝ ብሎ ይህን ክህደት ሲያስተምር *«ታውቃላችሁ መንፈስ ቅዱስ አንድ ነገር እያሳየኝ ነው። ኦህ! እየተጫጫነኝ ነው። እውነቱን ነው የምነግራችሁ በዚህ ሰዓት በእኔ ላይ ከብዶብኛል፤ ኢየሱስ ከመሬት በታች (በሲኦል) ነው ። እግዚአብሔር በዚያ የለም፥ መንፈስ ቅዱስ በዚያ የለም፥ መጽሐፍ ቅዱስ በዚያ ተወለደ ይለናል። ተወለደ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ፣ ዳግም ተወለደ ማለት ነው። ሌላ የሚያስደንግጥ ነገር ትፈልጋላችሁ። እናንተ ዳግመኛ ተወልዳችኋል፤ እርሱም ደግሞ እንደ እናንተ ዳግመኛ ተወልዶአል። ምን እያልክ ነው ትሉኝ ይሆናል ዳግም ተወልዶአል። ዳግመኛ መወለድ ነበረበት። እርሱ ዳግመኛ ባይወለድ ኖሮ እኛ ዳግመኛ አንወለድም ነበር። »*[67]

(66) Frederick K.C. Price, *Ever Increasing Faith Messanger (June 1980), 7*
(67) Benny Hinn, *Our Position 'In Christ,' Part 1 (Orlando, FL: Orlando Christian Center, 1991), videotape #TV-254.*



www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ በዚህ ምዕራፍ እንዳየነው ፕሮቴስታንቱ ዓለም በምን ዓይነት ስህተት ውስጥ እንደገባ ለማንም ግልጥ ነው። የሀገራችን ወጣቶች በፕሮቴስታንቱ አደባባይና በየጓዳው እየተለማመዱት ያሉት ይህን አይነቱን ልምምድ ነው። ምስክር የሚሆናቸው ከስህተት የሚጠብቃቸው ስለሌለ መሪዎቻቸውም በድርጅት ፍቅር ታውረው ለንስሃ ፈቃደኞች ስላይደሉ ክብራቸውን ሥልጣናቸውን እንዳይቀሙ ስለሚፈሩ ፕሮቴስታንቱ ዓለም ስላለበት ጉድ የሚያወሩት በጓዳቸው ነው እንጂ በሕዝባቸው ፊት አይደለም።

የተወደድክ አንባቢ ሆይ፥ ይህን ክፍል የምደመድመው አንድ የምክር ቃል በማስቀመጥ ነው። ክርስትናህ ክርስቶስን የሚያዋርድ «እኔነትን» ከፍ የሚያደርግ ከሆነ ያ ክርስትና ከመጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን ከሌላ ሥፍራ ነው፤ የእግዚአብሔርም አይደለም። በወጣትነትህ ዘመን ለእግዚአብሔር ያለህ ፍቅር ወደ ብዙዎች ሥፍራዎች ይወስድህ ይሆናል። በተለያዩ ሥፍራዎችም ስለ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ብዙ ነገር ሰምተህ ይሆናል። ነገር ግን አንድ ጥያቄ እንድጠይቅህ ፍቀድልኝ። ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንህን ታውቃታለህን? ይህን ያህል ዘመን ክርስትናህን ይዛ የቆየችውን ቤተ ክርስቲያን አምላኳን እንዴት እንደምታመልክ እንዴትስ እንደምትቀድሰው አይተሃታል? ወይስ ሌሎች ስለ ሰደቧት ብቻ ዝም ብለህ የሰዎችን ቃል ታስተጋባለህ?

ቆም ብለህ የምታስብበት ጊዜ ቢኖር አሁን ነው። ንስሓ ግባ። ወደ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሂድ የአባቶችህን መጻሕፍት በእርጋታ መርምር። ጥያቄ ሲኖርህም በድርጅት እና በንግድ መንፈስ ወደ ታወሩትና የዚህች ቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ወደ ሆኑት ሳይሆን ወደ ቤተ ክርስቲያን





አበው ዘንድ ሄደህ ጠይቅ። የእውነት አምላክ ደግሞ ወደ እውነቱ ቦታ ይመራሃል፤ አሁንም ይምራህ።



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ሰባት

## ፕሮቴስታንቶች በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የሚያነሱአቸው ክሶችና መልሶቻቸው

*የሰው ትዕግስቱ መከራውን ያርቀዋል። የነፍስ ስህተት የስቃይ እናት ናት። ትዕግስት ደግሞ የጸጋ ምክንያት ናት። ኃይልም ከሰፊ ልብ ትወለዳለች።*

*ማር ይስሐቅ አንቀጽ ሃያ ሁለት ም. 1*

*«... መላእክትን፣ ሰማእታትን፣ ድንግል ማርያምን የሚጠራ ሰው የቀወሰ ሰው ብቻ ነው። ማርያም ተገለጠችልኝ፣ ተክለ ሃይማኖት፣ ጳውሎስ እንዲህ አለኝ፣ ጴጥሮስ ተገለጠለኝ የሚል ይህ የመጨረሻ ቅዥታም ሰው ነው።»*

*ፕሮቴስታንታዊው ዶክተር ቶሎሳ*

### መግቢያ

ምንም እንኳን ፕሮቴስታንቱ ዓለም፥ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መንገድ፥ በክህደተ እግዚአብሔር በግብረ ሰዶምና በሌሎችም ርኩስ ግብሮች ላይ የተዘፈቀ ቢሆንም፥ ይህችን የሕዝቡዋን መንፈሳዊ ሕይወት ጠብቃ የኖረች ቤተ ክርስቲያንን በብዙ መንገድና ዓይነት መክሰሳቸው አልቀረም። እነዚህ ክሶች በምቀኝነት በስውር ተንኮል የተዋቡ ፍቅርና ሥነ ምግባር የጎደላቸዋል ናቸው። ከላይ የጠቀስነው የዶክተር ቶሎሳ ንግግር ለዚህ ዓይነተኛ ምስክር ነው። ምንም እንኩዋን የእነርሱን ጉድ ማሳየት አላማችን ቢሆንም ለአንዳንድ ክሶቻቸው ግን





መልሶችን እንሰጣለን።

ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለእመቤታችን ድንግል ማርያም፥ ለቅዱሳን ጻድቃን፥ ሰማዕታት እና ለቅዱሳን መላእክት የምንሰጠው ክብር ፍጡርና ፈጣሪ ተቀላቅሎብን ይመስላቸዋል። ቤተ ክርስቲያናችን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስላገኘችው እርቅ ምንም እውቀት እንደሌላት አድርገውም ለማስቀመጥ ይሞክራሉ። አንዳንዶቹማ «*ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ ይሰበካል ወይ?*» ብለው ይጠይቁናል። ለዚህም ነው በዚህ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ የኢትዮጵያዊውን ሰማዕት የብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን ቃለ ሃይማኖት ያስቀመጥነው። ይህንንም ምዕራፍ የምንጀምረው ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያገኘችውን እርቅ እንዴት እንደምትመለከት በማሳየት ነው።

### በጌታችን በኩል የሆነልን እርቅ(68)

በብሉይ ኪዳን የነበሩ አገልጋዮችና የመገልገያ ምክንያቶች ማለትም ካህናት፥ መሥዋዕታት፥ ቁርባናት፥ ሥራቸውን ጨርሰው ቦታቸውን ሲለቁ ጌታ በቦታቸው ገባ በብሉይ ኪዳን የነበረው ችግር ካህኑም እንደ ሕዝቡ ደካማ ነበር። ስለዚህ የሰው ግዳጅ በሌዋውያን ክህነትና አገልግሎት ሊፈጸም የማይችል ስለሆነ እንደ አሮን ያለ ሳይሆን እንደ መልከጼዴቅ ያለ ካህን እንደሚነሣ፥ የኃጢአት መሥዋዕትም ቀርቶ «ስለ ኃጢአት የሚቀርበውን መስዋዕት አልወደድኩም። ሥጋህን ንጹህ መሥዋዕት አድርግልኝ።» የሚል ቃል ቀደም ብሎ ተነገረ። መዝ 109፥4፤ ዕብ 1፥1-4።

*(68) ጽሑፉ የተወሰደው ከአለቃ አያሌው ታምሩ፤ ምልጃ እርቅና ሰላም። 1992 ዓ. ም. አዲስ አበባ ገጽ 21-27።*



www.ethiopianorthodox.org

ጊዜው ሲደርስም የእግዚአብሔር ልጅ ሰው ሆኖ፥ በሥጋ ተገልጦ፥ ካህንነቱን፥ መስዋዕትነቱን፥ አስታራቂነቱን፥ ታራቂነቱን፥መታረቂያነቱንም ራሱ ወሰደ። ስለዚህም «የእስራኤል ጠባቂ ሆይ ስማ ኃይልህን አንሣና አድነን ሥጋህን ንጹሕ መሥዋዕት አድርግልኝ» ለሚለው ጥሪ፥ «ስለ በጎቼ ቤዛ ራሴን የምሰጥ ቸር ጠባቂ እኔ ነኝ» ብሎ ጌታ መልስ ሰጠ።

መልሱ በሥራና በቃል ነበረ። ስለዚህም በተሰቀለበት ዕለት በካህኑ ፋንታ ሆኖ «እኔ ስለ እነዚህ እለምናለሁ። ስለ ዓለም ዓለምንም ስለሰጠኸኝ እንጂ፤ የአንተ ናቸውና። የእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው። የአንተውም የእኔ ነው። እኔም ስለእነርሱ ከብሬአለሁ፤ ከዚህም በኋላ በዓለም አይደለሁም። እነርሱም በዓለም ናቸው። እኔም ወደ አንተ እመጣለሁ። ቅዱስ አባት ሆይ እነዚህን የሰጠኸኝን በስምህ ጠብቃቸው። ከእነርሱም ጋር በዓለም ሳለሁ የሰጠኸኝን በስምህ እኔ እጠብቃቸው ነበር። ጠበቅኋቸውም።... በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነውና። አንተ እኔን ወደ ዓለም እንደላክኸኝ፥ እንዲሁ እኔ ወደ ዓለም ላክሁዋቸው። እነርሱም ደግሞ በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ እኔ ራሴን ስለ እነርሱ እቀድሳለሁ። ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ ከቃላቸው የተነሳ በእኔ ስለሚያምኑትም ደግሞ እንጂ፥ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም።» ዮሐ 17፥9-20።

ስለ ጠቅላላ ምእመናን ባቀረበው ጸሎትም በመስቀል ላይ ሳለ «አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ።» ብሎ በመናገር «ራሴን ስለ በጎቼ ቤዛ አሳልፌ እሰጣለሁ» ብሎ የተናገውን ቃል ሲፈጽም «አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ እሰጣለሁ» ብሎ ነፍሱን ከሥጋው በመለየቱ ከአሮን ክህነት በላቀና በረቀቀ የክህነት ሥርዓት፣ ካህን፣ አስታራቂ፣ መታረቂያ፣ መሥዋዕት ሆኖ





በፈጸመው በሞቱ የሰውና የእግዚአብሔር እርቅ ከፍጻሜ ደረሰ።

ከአብ፥ ከመንፈስ ቅዱስ ጋርም ይቅር ባይ፣ ታራቂ፣ መሥዋዕት ተቀባይ፣ ሕይወትን አዳይ፣ ዋጋ ከፋይ በመሆኑ፣ በኃጢአት ምክንያት ተቋርጦ የነበረው የሰውና የእግዚአብሔር አንድነት በተዘምዶውና በቤዛነቱ ታደሰ። የሰው ልጆች የዕዳ ደብዳቤ ተደመሰሰ። በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው የጥል ግድግዳ በመስቀሉ ደም ፈረሰ። ኤፌ 2፥14-18። በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና በምድር ሰላም ለሰው ልጆች እርቅ ሆነ።

ስለዚህ «ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማይሞት ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ አቤቱ ይቅር በለን፤ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማይሞት በዮርዳኖስ የተጠመቀ፤ በዕፀ መስቀል ላይ የተሰቀለ አቤቱ ይቅር በለን። ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማይሞት በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሣ፤ በምስጋና ወደ ሰማይ ያረገ በአባቱ ቀኝ የተቀመጠ፤ በሙታንና በሕያዋን ሊፈርድ ዳግመኛ የሚመጣ፤ አቤቱ ይቅር በለን እያለች ቤተ ክርስቲያን ዘወትር ታመሰግነዋለች።

በዚህ ከፍተኛ እርቅ እንመካለን። የምንመካውም በመታረቃችን ብቻ አይደለም። ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው እርቃችን በልጁ በኩል በመሆኑም ጭምር ነው እንጂ፤ ጠላቶቹ ስንሆን በልጁ ሞት ታርቆናልና። ሮሜ 5፥6-12። ይህ ምልጃና እርቅ የአንድ ጊዜ የአንድ ቀን አይደለም። ፈቅዶ ባቀረበው በሥጋው ቁርባንነት እኛ ለዘላለም እንቀደስ ዘንድ ራሱን አንድ ጊዜ ለዘላለም በመሠዋቱ፥ ለዘላለም



www.ethiopianorthodox.org

የማትሻር የማትለወጥ መሥዋዕትንም በመሥራቱ፥ ባቀረበው ጸሎት፥ በፈጸመው እርቅ፥ ለቤተ ክርስቲያን ዘላለማዊ ሥልጣን ሰጠ። ዕብ 7፥21-28።

ይህ እንግዲህ በጠቅላላው የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ነው ቤተ ክርስቲያናችን የቅዱሳንን ምልጃ የቅዱሳንን ርዳታና በረከት ስትጠይቅ ዶክተር ቶሎሳ በስድባቸው እንዳስቀመጡት *«የክርስቶስ ሞት አልበቃኝም»* ብላ ሳይሆን በክርስቶስ ሞት ባገኘችው በረከት ላይ ተመስርታ ነው። የቅዱሳን ጸሎት መነሻ የክርስቶስ ጸጋ ነው። በክርስቶስ የተገኘው አንድነት ነው ።

ስለ ቅዱሳን ምልጃ በሚገባ ለመረዳት በተለይም የቤተ ክርስቲያንን መሠረታዊ ትርጉም ማወቅ ያስፈልጋል። በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን ወይም «የቅዱሳን አንድነት» ስንል በጌታቸን አዳኝነት አምነው በሃይማኖት ያረፉትን አሁንም በእውነተኛው እምነት ያሉትንና ወደፊትም የሚመጡትን ነው። በዚህም የተነሳ አንድነታቸን በሚታየው ምድራዊ የጊዜና የቦታ ስሌት አይወሰንም። ቤተ ክርስቲያን በሰማይም በምድርም ያሉትን የምታቅፍ ነች።

ስለዚህ የቅዱሳንን ምልጃ ስንጠይቅ የምንጠይቀው ሩቅ ያሉትን አይደለም ከእኛ ጋር በአንድነት ያሉትን ነው። አንድነታቸውንም ከላይ እንደጠቀስነው ሞት አይወስነውም። ሞት በክርስቲያኖች ዘንድ ከነስሙ «ዕረፍት» ነው። ክርስቲያን ሞቱ ክቡር ነው። ወደ አምላኩ ዘንድ ነውና የሚሄደው በደስታና በመላእክት ምስጋና ወደ ሰማይ ይሄዳል። በዚያም በምድር የጀመረውን የአምልኮ የቅዳሴ የውዳሴ የምልጃ ሥራ ይቀጥላል።





## ገድላት፣ ተአምራት እና ድርሳናት

ባለፉት ዓመታት እጅግ በተጠና የንግድ ተልዕኮ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ስድባቸውን የሚተፉ መጻሕፍት እየተጻፉ ናቸው። እነዚህን መጻሕፍት የሚያዘጋጁትና ለሕትመት የሚያቀርቡት ሙሉ በሙሉ የሕትመቱን ወጪ የሚሸፍኑት የፕሮቴስታንት ድርጅቶች ናቸው። ድርጅቶቹ እነዚህን መጻሕፍት የሚያሳትሙበት ዓላማም ለቤተ ክርስቲያን አዝነው ወይም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተለያየ መንገድ ገብተው ያሉ የተለያዩ ሃሳቦች ቢገኙ እንዲታረሙ ሳይሆን፥ ቤተ ክርስቲያኒቱን በማስጠላት ምእመኖቿን ለማስኮብለል ነው።

ቤተ ክርስቲያን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚቃረኑ ምንባባት ቢገኙ ምን መደረግ እንዳለበት የምትወስነው ራሳቸው በስህተት ማጥ ውስጥ ባሉት በፕሮቴስታንቶች ጩኸትና ክስ አይደለም። ከጥንት ጊዜ ጀምሮ እንደምታደርገው ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊውን እርማት የምታከናውነው በቅዱስ ሲኖዶስ ነው። ሐሳቡንም ማቅረብ ያለባቸው የቤተ ክርስቲያን ልጆች ናቸው እንጂ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች አይደሉም። ቤተ ክርስቲያናችን በገድላት በተአምራት በድርሳናት ስላላት ትምህርት በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት የታተመውና በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የተዘጋጀው መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት የተባለው መጽሐፋችን ሲናገር፦

*«በቤተ ክርስቲያናችን ከብሉይና ከሐዲስ የማይቆጠሩ አዋልድ የተባሉ ብዙ የብዙ ብዙ ድርሳኖች ተአምሮችና ገድሎች ይገኛሉ። እነዚህንም ሰሎሞን ስሳ እማንቱ ንግሥታት ወ80 እቁባት አዋልድ እለ አልቦን ሁልቁ ወአሀቲ እምኔዎሆን ርግብየ ፍጽምትየ ሲል ስሳውን አንድ ብሎ ሰማንያውን አመጣው*



www.ethiopianorthodox.org

*ሰማንያ ወአሃዱ ማለቱ ነው። ከነዚያም ለይቶ አንዲቱ ፍጽምት ርግቤ ናት ያላት ወንጌልን ነው። ሥፍር ቁጥር የሌላቸው አዋልድ ያላቸው ድርሳናትን ተአምሮችንና መጻሕፍተ ታሪክን ነው።»*

*«አዋልድ ማለትም ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወለዱ መጽሐፍ ቅዱስን ተከትለው የተጻፉ ማለት ነው። እነዚህ መጻሕፍቶች ግማሾቹ ስለ ሃይማኖትና ስለ መንፈሳዊ ምግባር ያላቸው አስተያየት ሲናገሩ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርገው ነው። ገሚሶቹ ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ንባቡ ያጠረውን በማስረዘም ምስጢሩ የረቀቀውን በማብራራትና አጉልቶ በማስረዳት የተጻፉ ናቸው። እንዲሁም በመጽሐፍ ውስጥ በንባብ ተቃጥቶ ሳይሞላ የቀረውን አሙዋልተው የተመሰለው (በምሳሌ የተቀመጠውን) ተርጉመው የተጠቀሰውን አራብተው የያዙ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ መጻሕፍት አሉ። እነዚህ ሁሉ ድርሳን ተአምር ገድል መጽሐፈ ታሪክ ተብለው በጠቅላላ አዋልድ የተባሉ ናቸው።»ይላል።*(69)

ይህ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የጻፉትና ቤተ ክርስቲያንም አምናበት የምታስተምረው ስለ መጻሕፍተ ታሪክ እና ስለ አዋልድ መጻሕፍት በጠቅላላው ያለው አስተያየት ነው። ለነገሩ አውቀውትም ይሁን ሳያውቁት ፕሮቴስታንቶቹ አብያተ ክርስቲያናት ስለ ትምህርታቸው አስረጅ አድርገው የሚጠቅሱት አዋልድ መጻሕፍትን ነው። ለምሳሌ ስለ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሰይፍ ተሰይፎ መሞትና ስለ ቅዱስ ጴጥሮስ የቁልቁሊት ተሰቅሎ መሞት ከየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አላገኙትም። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አንዳንድ ሐዋርያት አገልግሎትማ ጭራሹኑ አያነሳም። በርተሎሜዎስ የት አስተማረ።

*(69) መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ። 1988 ዓ.ም። ገጽ 155*





እንድርያስ ምን ሆነ። ማቴዎስ ወንጌሉን የት ጻፈው። የት አስተማረ። እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን የምናገኘው በትውፊት ከተቀበልናቸው መጻሕፍተ ታሪክና ገድላት ላይ ነው። በተለይ እኛ ኢትዮጵያውያን የታሪካችን ምስክሮችም እነዚህ በጽሑፍ የቀሩልን ገድላትና ዜና መዋዕላት ናቸው።

ሆኖም ግን ቤተ ክርስቲያናችን እነዚህን ገድላትና ድርሳናት በቀኖና የቁጥራቸው ልክ ከተወሰነው መጻሕፍት አምላካውያት ጋር እኩል አድርጋ አትቆጥርም። እስትንፋሰ እግዚአብሔር ናቸው እርምት አይደረግባቸውም አትልም። ቤተ ክርስቲያን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የተቃረኑ ሃሳቦች ያለባቸውን መጻሕፍት ምን ማድረግ እንዳለባት ቀደም ሲል የጠቀስነው መጽሐፍ ሲናገር፥

*« ... ከመጽሐፍ ቅዱስ የወጣ ኃይለ ቃል ያላቸውን መጻሕፍተ ታሪክ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተቀብላለች አንልም። ከአሁንም ቀደምም አልተቀበለችም ወደፊትም አትቀበልም እንላለን። ከወንጌል ቃል የተለየ አስተያየት ሥርዋጽ ያለውንና ያልተስማማውን ንባብና ልብ ወለድ ኃይለ ቃል አስፍረው የተገኙ መጻሕፍት ቢኖሩም እንኳ በበር በኩል ያልገቡ አንዳንድ ጉሀልያዎች የሰነቀሩዋቸው ናቸው ብለን እንሰርዛቸዋለን እንጂ አሜን ብለን አንቀበላቸውም። ለምሳሌ፥ አንዳንድ ገድሎችና ድርሳኖች እግዚአብሔርን ክደው ጻድቃንን ቅዱሳንን ወይም እመቤታችንን የተማጸኑትን ሰዎች አማልደው አስማሩዋቸው ብለው ሲሉ ቢገኙ ተቀባይነት የላቸውም። እመቤታችን ሆነች ጻድቃን ሰማዕታት ሁሉ ቢያስተምሩ በጌታ ቃል በወንጌል አምነው ሥነ ምግባር የጎደላቸውን እንጂ ሃይማኖት የሌላቸውን ማልደው አስማሩ ያስምራሉ የሚለውን ሥርዋጽ*



www.ethiopianorthodox.org

*አንቀበልም።*»[70] በማለት የቤተ ክርስቲያናችንን አቅዋም ግልጥ አድርጎአል።

## ክብረ ቅድስት ድንግል ማርያም

እዚህ ላይ ፕሮቴስታንቱ ዓለም ስለ እመቤታችን ያላቸውን አመለካከት ማንሳቱ ተገቢ ይሆናል። ምክንያቱም በቅርቡ ከፕሮቴስታንቱ ዓለም የሚወጡ አንዳንድ ጽሑፎች እመቤታችንን እናከብራለን ማርያምን ማክበር ይኖርብናል የሚሉ ሆነዋል። ይህ አለምክንያት የሆነ አይደለም። በአንድ በኩል ግልብ የሆነ ስሜታዊነትን ያራቁ አንዳንድ የፕሮቴስታንት የነገረ መለኮት ሊቃውንት ድንግል ማርያም በደኅንነት ታሪክ ውስጥ ያላትን ሚና እስከ ዛሬ ድረስ መዘንጋታችን ስህተት ነው ብለው ተነስተዋል። በዚህ በሀገረ አሜሪካ ቁጥር አንድ የሆነ ታዋቂ የፕሮቴስታንት መጽሔት «ክርስቲያኒቲ ቱዴይ» ዐቢይ ርዕስ አድርጎ ባወጣው ጽሑፉ ላይ «ወንጌላውያን ድንግል ማርያምን ከእንግዲህ ወዲህ ልንረሳት አይገባንም» የሚል ርዕስ ነው ያወጣው።

እዚህ ላይ ጥያቄው ይህ አባባል የእግዚአብሔር ቃልን የቤተ ክርስቲያን ትውፊትን ከማጥናት የመነጨ ነው ወይስ ባዶ የሆነ የፖለቲካ አስተያየት ነው? በእውነት ከልብ የሆነ ለውጥ ከሆነ ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያምን ከጥንት ጀምሮ ሲያከብሯት ከነበሩት ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ስለ ክብረ ቅድስት ድንግል ማርያም (ማሪዮሎጂ) ሊማሩ ይገባል እንላለን። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከቅዱስ ገብርኤል እና ከቅድስት ኤልሳቤጥ የተቀበለችውን ሰላምታ የመሰለ ውዳሴ እንጂ ባዶ የፖለቲካ እውቅና አትቀበልም።

*(70) መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት፤ ገጽ 156*





በሌላ በኩል ደግሞ ጥቅማቸውን አስልተው ይህን የሚያስተምሩ አሉ። በተለይም ከኮሚኒዝም መውደቅ በኋላ ካፒታሊዝምንና ምዕራባዊነትን ጣዖት አድርጎና በኢኮኖሚ ዳሽቆ ቅስሙ ከተሰበረው ሕዝብ መካከል በተለይም የምሥራቅ ኦርቶዶክስ (የባልካን) አገሮችን ለማስኮብለልና በሥነ ምግባር ቀውስ ችግር ውስጥ የገባውን አብዛኛውን የካቶሊክ ምእመን በተለይ የላቲን አሜሪካን ሕዝብን ለመማረክ ሆን ብለው የሚያስተምሩ አሉ። እንዲህ ዓይነቱ ፖለቲካ ደግሞ በእኛም ሀገር ያስተምሩ በነበሩ አንዳንድ ሚሲዮናውያን በሰፊው ታይቶአል። እምነት ከመስማት ነው መስማትም ከእግዚአብሔር ቃል ነው እንዳለ የእግዚአብሔር ቃል ፥ ከአምላካችን የሰማነውን ቃል ነው እንጂ የዲኖምኔሽን ምንደኛ ሆኖ በሚያባብል ቃል የዋሁን ሕዝብ ማሳሳት በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስፈርድ ነው።

ያም ሆነ ይህ ፕሮቴስታንቶች ስለ እመቤታችን ያላቸው ትምህርት ምንኛ የተዛባ እንደሆነ ከዚህ በታች እናያለን።

በእስክንድርያ በቅዱስ ማርቆስ መንበር የተቀመጡት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሽኑዳ ሣልሳዊ በሚገባ እንዳስቀመጡት፥ በፕሮቴስታንቱ ዓለም የሚታየው በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ላይ ያላቸው አመለካከት የተመሠረተው ከመጽሐፍ ቅዱስ ባገኙት ትምህርት ሳይሆን የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ባላት የተጋነነ ትምህርት ላይና በሮማ ቤተ ክርስቲያን ላይ ባላቸው ጥላቻ (ሮማ ፎቢያ) ነው። ይህም ግልጥ የወጣ ጥላቻ ከትምህርታቸው አልፎ በሚተረጉሟቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ላይ ይታያል።



www.ethiopianorthodox.org

## ለእመቤታችን የተሰጡ ምስጋናዎች

እመቤታቸን ቅድስት ድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ ተመርታ ከተናገረቻቸው ነገሮች አንዱ ስለ ክብሯ የተናገረችው ነው። «ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል» ትውልድ ሁሉ ስትል ከልደተ ክርስቶስ ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚነሳው ትውልድ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ብፅዕት (የተመሰገነች) ብሎ እንደሚያወድሳት ያመለከተ ነው። የእመቤታችን ክብር የመነጨው ጌታ እርሷን ለአምላክ እናትነት ስለመረጣት እንደሆነ እርስዋ ራስዋ በመንፈስ ቅዱስ ተመርታ «ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጎአል።» በማለት ተናግራለች።

ቅዱስ ሉቃስ በወንጌሉ ላይ ለእመቤታችን የቀረቡትን ምስጋናዎች ዘግቦልናል። ቅዱስ ሉቃስ የጌታችንን አገልግሎት ሲናገር ስለ እመቤታቸንም ጽፏል። ለእመቤታችን ምስጋና ያቀረቡት ሰዎችና መላእክት ናቸው። ከሰዎች ለእመቤታቸን ምስጋና በማቅረብ የመጀመሪያዋ ቅድስት ኤልሳቤጥ ናት። ቅድስት ኤልሳቤጥ ምንም እንኳን እድሜዋ ከእመቤታችን እናት ከቅድስት ሐና ጋር እኩል ቢሆንም፥ ስለ እመቤታችን የተናገረችው ግን እጅግ አስደናቂ ነበር። «አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ የማህጸንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል፥ የሰላምታሽ ድምጽ ወደ እኔ በመጣ ጊዜ ጽንሱ በማህጸኔ በደስታ ዘሏል።» ምንኛ አስደናቂ ውዳሴ ነው። ቅድስት ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ ተመርታ የጌታዬ እናት ብላ አመሰገነቻት። ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም የኤልሳቤጥን ምስጋና አርአያ አድርጋና በመንፈስ ቅዱስ ተመልታ፥ «እመ እግዚእ ወላዲተ እግዚእ» የጌታ እናት ጌታን የወለደች እያለች ታመሰግናለች።





እመቤታችን የተመሰገነችው በሰዎች ብቻ ሳይሆን በመላእክትም ነው። ስለዚህም ቤተ ክርስቲያናችን በምስጋናዋ «ውድስት በአፈ መላእክት» በመላእክት አንደበት የተመሰገነች ብላ ትጠራታለች። ከመላእክት መካከል እመቤታችንን በማመስገን የመጀመሪያው የብሥራት መልአክ የሆነው ቅዱስ ገብርኤል ነው። ቅዱስ ገብርኤል ለእመቤታችን ባቀረበው ሰላምታ «ደስ ይበልሽ! ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፥ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው። አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ» ብሏታል። ሉቃ 1፥28። ይህ በኃጢአት ወድቀው ባሉት በሰው ልጆች መካከል ያልተሰማ አዲስ ምስጋና አዲስ ዜና ነበር። ይኸውም በእርሱዋ የማህጸን ፍሬ ዓለም የሚያገኘውን ጸጋ የሚያገኘውን በረከት ያመላከተ ነው። በዚህም ምክንያት ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እመቤታችንን «ምክንያተ ድሂን» የደኅንነታችን ምክንያት ብላ ትጠራታለች።

## የታቦት ክብር

ዶክተር ቶሎሳ ቤተ ክርስቲያኒቱን ከሰደቡበት ነገር አንዱ በታቦት ላይ ቤተ ክርስቲያናችን ስላላት ትምህርት ነው። ዶ/ሩ ቤተ ክርስቲያኒቱን ብቻ ሳይሆን ክርስትናን ራሱን ገና እንዳልተረዱ የምናውቀው ቤተ ክርስቲያኒቱን ከጣዖት አምላኪዎች ጋር አንድ አድርገው ሲጠሩ ነው። ለመሆኑ ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ታቦት ያላት ትምህርት ምንድነው? እርሳቸው እንዳሉት በእርግጥ ቤተ ክርስቲያናችን ጣዖት አምላኪ ናት? ወይስ ኦሪት ናት? እስቲ ኦርቶዶክሳውያን አበው ያሉትን እንመልከት፥

*«ታቦት በኢትዮጵያ ውስጥ በልማድ ያለ አይደለም ወይም አንዳንድ የዋሆች እንደሚሉት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ኦሪትን ከሥርዓተ ወንጌል*



www.ethiopianorthodox.org

ጋር በባላንጣነት የምታታግል አይደለችም። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ መጀመሪያ ላይ እንዳነሳነው ከክርስትና በፊት የብሉይ ኪዳን አገር የነበረችው ኢትዮጵያ በክርስትና ጊዜም ከብሉይ ኪዳን ያገኘቻቸውን ጠቃሚ ነገሮች በክርስትና መንፈስ እየተረጎመች ትጠቀምባቸዋለች። ከብሉይ ኪዳን ከወሰደቻቸውም አንዱ ጽላተ ኪዳን ታቦተ ሕግ ነው። አዲስ ቤተ ክርስቲያን በሚሰራበት ጊዜ ከእጽ ወይም ከእብነ በረድ ተቀርጾ በላዩ የእግዚአብሔር ምስጢራዊ ስም (ህቡእ ስም) «አልፋ ኦሜጋ» የመጀመሪያውና የመጨረሻው ማለት ነው። ይህ ቃል ከተጻፈበት በኋላ በኤፒስ ቆጶሱ እጅ ተባርኮና ሜሮን ተቀብቶ በመንበሩ ይሰየማል (ይቀመጣል)። በቅዳሴም ጊዜ ሕብስቱና ወይኑ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ቄሱ ሥርዓተ ቅዳሴውን የሚያከናውነው ሕብስቱን ሥጋ መለኮት፣ ወይኑን ደመ መለኮት ወደ መሆን የሚለውጠው በዚህ በታቦቱ ላይ ነው። የደብተራ ኦሪት ጽላት እግዚአብሔር በደመና ተከናንቦ ሙሴንና አሮንን የሚያነጋግርበት ለእስራኤል ብቻ በረድኤት የሚገለጥበት ዙፋን ነበር ። ይህ ግን የአምላክ ሥጋና ደም የሚፈተትበት ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው። ሥጋዬን ብሉ ደሜንም ጠጡ እያለ ያመኑትን ሁሉ የሚጠራበት የምሕረት ምሥዋዕ (መሠዊያ) ነው። ክብርና ስግደትም የሚደረግለት ስለዚህ ነው።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለ ታቦት ያላትን ትምህርታዊ መመሪያ ያልገባቸው አንዳንዶች እንደመሰላቸው ቢተረጉሙት ቤተ ክርስቲያናችን በሙሴና በክርስቶስ በብሉይና በሐዲስ ወይም በጥላና በእውነት በምሳሌና በአማናዊ ያለውን ልዩነት ስለምታውቅ ለሚጠይቁዋት ሁሉ ይህን እምነቱዋን ከማስረዳት ተቆጥባ አታውቅም።»(71)





«ታቦት በሐዲስ ኪዳንም በቤተ ክርስቲያናችን አምልኮተ እግዚአብሔር ይፈጸምበታል። ታቦት እውነተኛው የሕይወት ምግብ የክርስቶስ ሥጋና ደም የሚቀርብበትና የሚፈተትበት መሠዊያ ነው። የሚከበረውና የሚሰገድለትም ስለዚህ ነው።»(72)

ይህ እንግዲህ የቤተ ክርስቲያናችን ይፋ የሆነ ትምህርት ነው። በዚህ የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት እንዳየነው ቤተ ክርስቲያናችን ከብሉይ የወሰደችውን በአዲስ ኪዳን ተርጉማ የምትጠቀም ናት። በዚህም ምክንያት ቤተ ክርስቲያናችን የምትጠቀምበት ታቦተ ምሥዋዕ (መሠዊያ) ቅዱስ ቁርባን የሚከብርበት ነው እንጂ እንደ ብሉይ ኪዳን የምንጠቀምበት አይደለም።

## የፕሮቴስታንት «ታቦት»

መንፈሳዊነትን እንለማመዳለን ከሚሉት ጀምሮ «ቅዳሴ» አለን እስከሚሉት ድረስ ካሪዝማቲኮችም ሆኑ ጴንጤቆስጤዎች የእግዚአብሔር መገኛ ምልክት ብለው የሚያስቀምጡት አለ። አንዳንዱ ከጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት የተቀዳ ሲሆን ሌላው ደግሞ ገሚስ አረማዊና ገሚስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። ከሚጠቀሙባቸውም መካከል፥

1. ጠረጴዛ፥ በዋናነት በሉተራኖችና በሌሎችም የሉተራንን ትውፊት በሚከተሉ በሙሉ ይታያል። ጠረጴዛውን ነጭ ልብስ አልብሰው ሕብስትና ወይን በዚያ ላይ ያስቀምጣሉ በፊቱ ይንበረከካሉ። ይሰግዳሉ። በጠረጴዛው ግራና ቀኝ አልፎ አልፎ ሻማ ወይም አበባ ያስቀምጣሉ።

(71) አባ ጎርጎርዮስ - የሸዋ ሊቀ ጳጳስ ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ። ጥር 1994 ዓ. ም. አራተኛ እትም። ገጽ 94-95።
(72) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት። ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት። ገጽ 62።



www.ethiopianorthodox.org

2. ባዶ ወንበር፥ ይህ አልፎ አልፎ በፔንቴኮስታሎቹ ጉባኤ የሚታይ ሲሆን፥ ጌታ ወደ ጉባኤያችን መጥቶ ይቀመጥበታል ተብሎ ባዶውን የሚቀመጥ ነው። ይህ አልፎ አልፎ ከፓስተሩ ጎን አለበለዚያም ከፊት ፊት ለፊት ካሉት ባዶ ወንበሮች አንዱን ያደርጋሉ።

3. የተከፈተ መጽሐፍ ቅዱስ፥ ይህ በብዙዎች ዘንድ የተለመደ ባይሆንም አንዳንዶች የተከፈተ መጽሐፍ ቅዱስ በጠረጴዛው ላይ ያስቀምጣሉ። አልፎ አልፎም መጽሐፍ ቅዱሱን ከፍ አድርገው በማንሳት ክብር እንደሚሰጡት ያሳያሉ።

4. የተለያዩ ቁሳቁሶች፥ ይህ ከፊል አረማዊ ከፊል መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ነው ።በተለይ በካሪዝማቲክና በ«እምነት እንቅስቃሴ» አራማጆች ዘንድ የተለመደውና «ፖይንት ኦፍ ኮንታክት» በመባል የሚታወቅ ነው። አረማዊነቱ ሥርዓቱ የሰውን ነፍሳዊ ኃይል (ሶል ፓወር) እንጂ የቃለ እግዚአብሔርን ኃይል የሚያሳዩበት አይደለም።

በተጨማሪም ብዙዎች የዚህ ሃሳብ አራማጆች የሚጠቀሙበት ገንዘብ ከተከታዮቻቸው ለመሰብሰብ ነው። ለምሳሌ፥ ማርሊን ሀኪ የተባለች ታዋቂ የ«እምነት እንቅስቃሴ» ሰባኪ ሁለት ሁለት ሳንቲሞችን በመላክ ሁለቱ ሳንቲሞች ያች መበለት የጣለችው መሐልቆች ምሳሌ እንደሆኑና ሳንቲሞቹ ላይ ጭነው የፈለጉትን እንዲመኙ፥ ሲመኙም በመቶ ሺ ዎች የሚቆጠሩ ዶላሮች እንዲለምኑ ትነግራቸዋለች። ከዚያም ለእርስዋ በስጦታ መልክ በደንብ አድርገው በርካታ ዶላሮች ከሳንቲሞቹ ጋር እንዲልኩላት ትነግራቸዋል። ይህች ሴት ቃል እንደምትገባው ከሆነ፥ ሳንቲሞቹ ላይ እንደገና





እርሷ እጇን እንደምትጭንና በእርሷና በላኪዎቹ መካከል ሳንቲሞቹ «ፖይንት ኦፍ ኮንታክት» እንደሚሆኑ ትናገራለች።

እነርሱ ከራሳቸው ሐሳብ አንቅተው ገሚሱን ለንግድ ገሚሱን ለአምልኮ ከተጠቀሙ፥ እኛ የብሉይ ኪዳኑን ስያሜ በአዲስ ኪዳን መንፈስ ተርጉመን «ታቦተ ምሥዋዕ» ብለን መጠቀማችን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ እምነት ይዘዋል ተብሎ ያስመሰግነናል እንጂ አያስወቅሰንም። ይህም ልማድ በሁሉም ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ ያለ ነው እንጂ እኛ ከኦሪቱ ስላገኘው ብቻ እንዳልሆነም ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በሚገባ ገልጠውታል።

*«ከኢትዮጵያም ሌላ በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ታቦት የተለመደ ሕግ ነው። ሥጋውን ደሙን የሚፈትቱት በታቦቱ ላይ ነው። ለምሳሌ ግብጻውያን ታቦቱን ሉህ ይሉታል።[73] ጽላት ሰሌዳ ማለት ነው። ያለ እርሱ ሥጋውንና ደሙን አይፈትቱም። የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ተብለው የሚጠሩት የግሪክ የሩሲያ የሩሜኒያና ሌሎችም ወደ ክርስትና የተመለሱት ከአረማዊነት ስለሆነ የታቦትን ምሥጢር አያውቁትም። በታቦቱ ፈንታ ከመንበር የማይነሳ እንደ ታቦት የሚከበር የጌታ የስቅለቱ ወይም የግንዘቱ ስዕል ያለበት የነጭ ሐር መጎናጸፊያ አላቸው። ያለ እርሱ ሥጋውን ደሙን አይፈትቱም። ይህንንም በጽርእ «አንዲሚንሲዮን ይሉታል። «ህየንተ ታቦት» ስለ ታቦት ፈንታ ማለት ነው። የሮማ ካቶሊኮች ሜንሳ ይሉታል ጠረጴዛ ማለት ነው።»[74]*

(73) በግብጽ ያሉትን ገዳማት ስጎበኝ እንዳየሁት «ሉህ» በተለተያዩ ቀለማት ያማረ ሐረግ ያለው ነው።
(74) አባ ጎርጎርዮስ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ። ገጽ 95።



www.ethiopianorthodox.org

## ገዳማዊ ሕይወት

በዚህ ዘመን በሌሎች የዓለም ክፍሎች በከፍተኛ አክብሮት የሚታየውና በኢትዮጵያ ውስጥ ግን በሚስዮናዊ እይታ አእምሮአቸው በጨለመ አንዳንድ ሰዎች ዘንድ ከፍተኛ ተቃውሞ የሚደርስበት ገዳማዊ ሕይወት ነው። ገዳማዊ ሕይወት በዋናነት የተነሳው ዛሬ ዛሬ አንዳንድ ሰዎች እንደሚናገሩት ከግኖስቲኮች ትምህርት ሳይሆን ዓለማዊ አስተሳሰብ ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባቱን ከመቃወም ነው።

ክርስትና በየዋሻውና በየጉራንጉሩ የሚሰደድ ሃይማኖት ከመሆን ወጥቶ የመንግሥት ብሔራዊ ሃይማኖት ሲሆን፤ ብዙዎች ሰዎች የነገሥታቱን ወዳጅነት ለማግኘት፤ ብሎም በሕዝብም ዘንድ ከበሬታ ለማግኘት ክርስቲያን መሆን ጀመሩ። አንዳንድ ፈላስፋዎችም የፍልስፍናቸውን ሃሳብ የክርስትና ካባ ደረቡበት። ይህ ለቤተ ክርስቲያን አደጋ ነበረ።

ቤተ ክርስቲያን መስቀል ተሸክማ ያልተረታችውን፣ መሪዎችዋ እየታረዱባት፣ ሰም ተቀብተው የአትክልት ሥፍራ መብራት ሆነው፣ እንደ ዱቄት ተፈጭተው ተዘርተው ያልተፈታችውን ወደ ቤተ መንግሥት ስትገባ አስቸጋሪ ነገር መጣ። ይህ የአንዳንድ ቅዱሳንን መንፈስ ረበሸ። እናም ዓለምንና በዓለም ያለውን አሁን ግን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልኮ ለመግባት የሚሞክረውን መንፈስ ለመዋጋት ተነሡ።

አንዳንዶች አምላካቸው በቃሉ ጠራቸው። ለምሳሌ ርዕሰ ገዳማውያን እንጦንስን ለገዳማዊ ሕይወት አምላኩ የጠራው ወንጌልን ሲያዳምጥ ነበር። አንዳንዶችን ከከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን ሌሎችንም ከክህነት አገልግሎታቸው ሌሎችንም





ከኃጢአት ሥፍራቸው ጠራቸው። ገዳማውያን አበው የዓለማዊውን ሃሳብ ሲቃወሙም በዚህ ዓለም ትዳር መሥርተው ልጅ ወልደው ካሉት እንሻላለን ብለው አይደለም። ራሳቸውን ከሌሎች ከፍ አድርገው አጽድቀው ያዩበት ወይም ይህ የሚያደርጉት ሥራ የክርስቶስን ሞት ለመሸፈን ብለው አስበው እንዳይደለ፤ ይልቁኑም በጾም በጸሎት ለመትጋት ብለው እንደሆነ በትሕትና በመጻሕፍቶቻቸው ተናግረዋል።

ስለዚህ ሁኔታ «ማር ይስሐቅ» ሲናገር፥ አንድ ያልተማረ ባሕታዊ ነው። ሂዶ ከበረሃ ተቀምጦ ሳለ ሰይጣን መጥቶ «ምነው ከዚህ ብቻህን ተቀምጠሃል?» አለው። ባሕታዊውም መልሶ «እጸድቅ ብዬ ነው» አለው ። ሰይጣኑም ዝም ብሎት ሄደ። ለሁለተኛ ጊዜም ሄዶ «ምነው ብቻህን ተቀምጠሃል?» አለው። ባሕታዊውም መልሶ ክርስቶስን ባገኘው ብዬ አለው። ሰይጣኑም ያሁኑ ይባስ ብሎት ሄደ። አባ መቃርስ የተባለው ታላቁ ገዳማዊ አባት ወደዚያ ባሕታዊ ሄዶ «ካንተ ዘንድ ሰው አልመጣም ወይ?» አለው። «አልመጣብኝም» አለው ። ግድ ንገረኝ ቢለው መጥቶ ነበር አለው። ምን አለህ አለው ። «ብቻህን ለምን ተቀምጠሃል አለኝ፤ እጸድቅ ብዬ አልኩት። ዝም ብሎ ሄደ። ሁለተኛም መጥቶ ምነው ብቻህን አለኝ፤ ክርስቶስን ባገኝ ብዬ አልኩት። ያሁኑ ይባስ ብሎኝ ሄደ» አለው። አባ መቃርስም «ምነው እንዲህ ማለትህ የምትጸድቅ ክርስቶስን የምታገኝ አንተ ብቻ ነህን? በዓለሙ ያለ ሁሉ ክርስቶስን የማያገኝ ሁኖ ነው? ሁለተኛ የመጣ እንደሆነ እንዲህ ብለህ መልስለት ግብሩ የከፋ ውሻን አሥረው ለብቻው እንዲያኖሩት፥ እኔም ባሕርዬ ቢከፋ፤ ግብሬ ከሰው ባይስማማ ከዚህ መጥቼ ተቀምጫለሁ በለው እንጂ እንዲህ አትበለው» አለው። ሰይጣኑም ሲመጣ



www.ethiopianorthodox.org

ባሕታዊው ለሰይጣኑ አባ መቃርስ እንደመከረው መለሰለት። ያን ጊዜም «አኮ አንተ ዘገበርከ ዘንተ አላ መቃሪ ውእቱ - ይህን ያደረገ መቃሪ ነው እንጂ አንተ አይደለህም።» ብሎት ሄዶአል።

ዛሬ ዛሬ ምዕራቡ ዓለም ከእነዚህ አበው የተገኙትን አባባሎች «የምድረ በዳ አበው አባባሎች እያለ ወደ እንግሊዘኛ እየተረጎመ በመላው ዓለም እየተጠቀመባቸው ናቸው። እነዚህ አባባሎች የእነዚህን አባቶች ጥልቅ መንፈሳዊ ሕይወት ትሕትና በአምላካቸውም ያገኙትን ጥልቅ የሆነ እረፍት የሚገልጡ ናቸው።

ዶክተር ቶሎሳ እንደ ፈረንጆቹ ገና ለቁሳዊው ዓለም ዕድል ስላላገኙም ይሁን ወይም የእርሱ ፍቅር ስላልወጣላቸው ከእነዚህ አባቶች መንፈሳዊ ሕይወት ከኑሮአቸው እርካታ ይልቅ እነርሱ ንቀው የተውትን የዚህን ዓለም ጉድለት ለማየት ሞክረዋል። ቁሳዊው ዓለም ባዶ እንደሆነ ማን በነገራቸው?





# ምዕራፍ ስምንት

## ታላላቅ የፕሮቴስታንት ሊቃውንት ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት መመለስ

*ጥቂቶች ያይደሉ ፕሮቴስታንቶች ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እየመጡ ያሉት በፕሮቴስታንቱ ዓለም በሚያዩት ቀውስ ስለተረበሹ ነው። ዋና ዋና የፕሮቴስታንቶች ዲኖሚኔሽኖች በቤተ ክርስቲያን ዶክትሪን ላይ እየተጫወቱ ይገኛሉ። ክርስቶስ በድንግልና ከመወለዱ እስከ ትምህርተ ሥላሴ ድረስ ያለውን ተጠራጥረዋል። ወንጌላውያን ነን የሚሉትም ሥርዓት በሌለው መንገድ ከአንዱ አመለካከት ወደ ሌላው የሚገለባበጡ ናቸው። በዚህ ምክንያት ለእነዚህ ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለሚመለሱ ሰዎች፥ ፕሮቴስታንቲዝም ማለት መሠረት የሌለውና ለዘመናት ከነበሩት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው ማለት ነው።*

*ሐሮልድ ብራውን፤ የቴዎሎጂ ፕሮፌሰር*

በአሁኑ ወቅት በአሜሪካ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናትና በዩኒቨርስቲዎቻቸው ዘንድ ታላቅ መነጋገሪያ እየሆነ ያለ ጉዳይ ቢኖር፥ በትምህርታቸው እጅግ የተመሰገኑና የተከበሩ የፕሮቴስታንት ሊቃውንት ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መመለስ ነው። ይህም ያለምክንያት የሆነ አይደለም። ከላይ የጠቀስነው ታዋቂ የቴዎሎጂ ፕሮፌሰር እንደተናገረው ከፕሮቴስታንቱ ዓለም ችግር በላይ፥ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እነዚህ ሰዎች ያጡትን ይዛ ተገኝታለች። ከእነዚህም መካከል፥

1. ትውፊት፤ ሐሮልድ ብራውን ትውፊትን



www.ethiopianorthodox.org

ሲተረጉመው «የእግዚአብሔር ሕዝብ ቀጣይነት» ይለዋል፤ ይህም ማለት በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ የነበረው አምልኮ ያለማቋዋረጥ እዚህ ደርሶአል። በፕሮቴስታንቱ ዓለም ካየን ግን ሁሉም «አዲስ» ወይም መሠረት የለሽ ነው። ዛሬ የነበረው የአምልኮ ሥርዓት ነገ ሲደገም አይታይም። በዚህም ምክንያት ጉባኤያቸው ወደ ሥርዓት አልባ ትርምስ ይለወጣል። የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት ደግሞ ሥርዓት ያለው አምልኮን ለመምራት ከማስቻሉም ባሻገር ሌላ የሚሰጠው ታላቅ ቁም ነገር አለው።

2. የጸና እምነት፥ ይህ ታዋቂ የሆነ የነገረ መለኮት ሊቅ ሲናገር *«በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሚታየው ጠንካራ የሆነ ትውፊትና ሥርዓት ያለው ቅዳሴና ጸሎት ለቤተ ክርስቲያንዋ መረጋጋትን ስክነትን ሰጥቶአታል።»* ብራውን ይህን በምሳሌ ሲያስረዳ፥ *«በአንድ ከፍተኛ የነገረ መለኮት ትምህርት ቤት የሚያስተምር አንድ ኦርቶዶክሳዊ ጉዋደኛ ነበረኝ። በሀርቫርድ ዩንቨርስቲ የነገረ መለኮት ትምህርቱን ሲያጠና ስለ ወንጌል እውነት ጥርጥር አደረበት። ነገር ግን ኦርቶዶክሳዊ ቄስ ስለነበረ ሁል ጊዜ እሑድ እሑድ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የተሞላውን ሥርዓተ ቅዳሴ መምራት ነበረበት፤ ከጊዜ በኋላ በአእምሮው ላይ ያደረበትን ጥርጥር አስወገደ። ለዚህም የረዳው ደግሞ እሑድ እሑድ የሚያደርሰው ቅዳሴ ነበር። ቅዳሴው በጥርጥር ላይ የነበረው አእምሮው ሙሉ በሙሉ እስኪጸዳ ድረስ ወደ ክርስትና እውነት ይጎትተው ነበር። ፕሮቴስታንቶች እምነታቸውን ቢጠራጠሩ እንዲህ በእምነት ላይ የሚያጸናቸው ትውፊት የላቸውም»* ነበር ያለው።

በአእምሮ ከሚፈጠረው ጥርጥር ባሻገር ኦርቶዶክስ





ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓለም የፖለቲካ መድረክ ለሚነሱት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት፥ ጥልቅ መሰረት አላት። በፕሮቴስታንቱ ዓለም ውስጥ እንደሚታየው ከሆነ ዓለም በአንድ ነገር ላይ ጥርጥር ውስጥ ከገባ ፕሮቴስታንቱም ዓለም ጥርጥር ውስጥ ይገባል። ዓለም በአንድ ነገር ላይ ክርክር ውስጥ የገባ እንደሆነ ፕሮቴስታንቱም ዓለም ክርክር ውስጥ ይገባል። ለዚህም በምሳሌ በምዕራቡ ዓለም ያለውን በውርጃ (አቦርሽን)፥ በግብረ ሰዶም ላይ ያለውን ክርክር ያጤኑአል።

3. አምልኮአዊ ውበት፤ ስለዚህ ጉዳይ ብራውን ሲናገር፥ «ፕሮቴስታንቲዝም ወደ ሰዋዊ አመክንዮና ዓለማዊነትን ማዕከል ወደ ማድረግ ያመዝናል። በፕሮቴስታንት አምልኮ ውስጥ ብዙ የሚያስጸይፍ ንግግር አለ። ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ግን በቅዱሳን ሥዕሎች በመዝሙራት እና በምልክቶች (ሲምቦልስ) የተዋበ፣ መንፈሳዊ ነገርን በተመስጦ እንዲያሰላስሉ የሚያደርግና የእግዚአብሔርን ሕልዎት (መገኘት) እስኪሰማ ድረስ ከፍ ወዳለ ደረጃ የሚያሳድግ ቅዳሴ አላት።

እንግዲህ በአጠቃላይ በፕሮቴስታንቱ ዓለም ያለውን ችግር በሚገባ የተገነዘቡና በኦርቶዶክስ ዓለም ያለውን መንፈሰዊ በረከት በሚገባ ያወቁ ፕሮቴስታንቶች ሁለት ዓይነት መፍትሔዎችን መርጠዋል። አንደኛው የኦርቶዶክሳውያን አበውን ትምህርቶችና የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት በማጥናት ከፕሮቴስታንቱ ዓለም የተለዩና ወደ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የተመለሱ ናቸው። ሁለተኛው ደግሞ ምንም እንኳን ከፕሮቴስታንቱ ዓለም ባይወጡም የፕሮቴስታንቱን ዓለም የስህተት አቅጣጫ በማስተዋል ከኦርቶዶክሳውያን አበው መጻሕፍት ጋር መተዋወቅና



www.ethiopianorthodox.org

ለፕሮቴስታንቱም ዓለም ስለ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታላቅነት ሐዋርያዊ ትምህርትዋን ማስተዋወቅን ሥራቸው ያደረጉ ናቸው። ሁሉቱም መፍትሔ በክንውኑ ይለያይ እንጂ አንድ ዓይነት አቅጣጫ ላይ ያተኮረ ነው፣ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንንና ትምህርትዋን መፈለግ።

## ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የመጡ

ባለፉት ዓመታት በምዕራቡ ዓለም ከታዩት አስደናቂ ክስተቶች መካከል በቁጥር ጥቂት ያይደሉ የፕሮቴስታንት መሪዎችና ተከታዮቻቸው ወደ ኦርቶዶክሳዊት እምነት መጥተዋል። የተሟላ ጥናት ባይደረግም ስማንያ ከመቶ የሚሆኑት የመጡት ከወንጌላውያንና ከካሪዝማቲክ እንቅስቀሴዎች ነው። ለምሳሌ፥ ከካምፓስ ክሩሴድ (በአገራችን ታላቁ ተልዕኮ የሚባለው ነው)፣[75] ከወጣት ለሕይወት፣ ወጣት ለክርስቶስ፣ ቫይን ያርድ ፌሎውሺፕ፣ ዘኢቫንጀሊካል ፍሪ ቸርች፣ ባፕቲስት ሚሽነሪ አሊያንስ ሌሎችም ናቸው። ሃያ ከመቶዎቹ የመጡት ከአንገሊካኒዝም፣ ኤፒስኮፓሊያኒዝም፣ ከሉተራን፣ ከሜቶዲስት እና ከፕሬስቢተሪያን ነው።

ይህ እንቅስቃሴ በኦርቶዶክሱ ዓለም ብቻ ሳይሆን በፕሮቴስታንቱ ዓለምም ከፍተኛ የሆነ መወያያ ሆኖአል። በአሜሪካ አገር ታዋቂ የሆነው የነገረ መለኮት ሊቅ ሚላርድ ኤሪክሶን ይህ እንቅስቃሴ የአሜሪካንን የወደፊት አካሄድ በሙሉ የሚወስንና ታላቅ ተጽዕኖ የሚያሳድር እንቅስቃሴ ነው ብሎአል።

*(75) በአገራችን ያሉት የዚህ ድርጅት መሪዎች ምናልባትም በዚህ ስለተናደዱ ይመስላል፥ ከፍተኛ የሆነ ኦርቶዶክስን የማጥላላት ዘመቻ ይዘዋል። «ዘመቻ ፊልጶስ» «የጽድቅ ጸሐይ» እያሉ የጥላቻ ጽሩር የሚወረውሩ እነርሱ ናቸው። ከዚህ ባሻገርም ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚሰድቡ ድርጅቶች በማደራጀት በብዛት መጻሕፍት እያሳተሙ የሚያወጡት እነርሱ ናቸው።*





እንዲህ ሊል የቻለውም እንቅስቃሴው በፕሮቴስታንቱ ዓለም ታዋቂ የሆኑ ሰዎችን ስላካተተ ነው። ከእነዚህም መካከል ዋና ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

**ፒተር ጊልከስት**[76]

በ1987 ዓ. ም. ላይ አንድ አስደናቂ ሁኔታ ተከስቶ ነበር። ያም ከሉተራን ከጴንጤቆስጤ ከባፕቲስት እና ከሌሎችም የፕሮቴስታንቶች ድርጅቶች የወጡና በ17 አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የተደራጁ ሁለት ሺህ ምእመናንና መሪዎቻቸው ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መምጣት ነበር። ይህንን ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መምጣት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የተቀበለቻቸውን ቀን የገለጡትም «እውነተኛዋን ቤተ ክርስቲያን ለማግኘት የተደረገው ረጅም ጉዞ የተጠናቀቀበት ክቡር ቀን» ብለው ነበር።

ይህን ጉዞ ከመሩት መካከልም አንዱና ዋናው ፒተር ጊልከስት ናቸው። በሉተራን ውስጥ ያደጉት ፒተር ጊልከስት ታዋቂ በሆነ የፕሮቴስታንት የነገረ መለኮት ትምህርት ቤቶች በዳላስ ቴዎሎጂካል ሴሚናሪ፣ በዊተን የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የተማሩ ሲሆን በፕሮቴስታንቱ ዓለም ታዋቂ የሆነው የካምፓስ ክሩሴድ ሪጅናል- ዳይሬክተር ነበሩ። በአሁኑ ወቅት በሰሜን አሜሪካ የአንጾኪያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ መምሪያ ዳይሬክተር የሆኑት ጊልከስት በፕሮቴስታንቱ ዓለም ታዋቂ የሆኑ ሰባኪ ነበሩ። ነገር ግን በአገልግሎታቸው ውስጥ አንድ ጥያቄ እንደ ተፈጠረባቸው ፒተር ጊልከስት ይናገራሉ። ያም የፕሮቴስታንቱ ዓለም በየጊዜው በተለያየ ምክንያት ከእውነተኛው እምነት እየራቀ መምጣትና

*ታሪኩ በዋናነት የተመሠረተበትና እንዴት ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንደመጡ የሚናገረው Peter E. Gillquist, Becoming Orthodox: A Journey to the Ancient Christian Faith, rev. ed. ( Ben Lomond, CA: Conciliar Press, 1992)*



www.ethiopianorthodox.org

የቤተ ክርስቲያን እውነተኛ ባሕርያት በፕሮቴስታንቱ ዓለም መታጣት ነበር። በዚህ ወቅት የተወሰኑ ከተለያዩ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያን የተውጣጡ መሪዎች ስለ ቤተ ክርስቲያን ማጥናት ጀመሩ። በመጨረሻም በአዲስ ኪዳን የተገለጠችውን ቤተ ክርስቲያን ሲያጠኑ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ፣ ምስጢራትና፣ ጸጸሳት እንደነበሯትና ይህንንም ባሕርይ አሟልታ የምትታየው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነች በማስተዋል ምእመኖቻቸውን ይዘው ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለመግባት ወሰኑ።

ዛሬ ፒተር ጊልክስት ወደ ቀደሙት ወንድሞቻቸው በመሄድ በብዙ መድረኮች ስለ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊነትና ታሪካዊነት በመመስከር ላይ ናቸው። ወደ አንጾኪያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከገቡ ጊዜ ጀምሮ 32 አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት የተተከሉ ሲሆን ከስድስት ሺህ አምስት መቶ በላይ የሆኑ ፕሮቴስታንቶችን ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መርተዋል።

<u>ፍራንክ ሼፈር</u>

ሌላው ወደ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት የመጣውና በፕሮቴስታንቱ ዓለም ከፍተኛ ነውጥ የፈጠረው ፍራንክ ሼፈር ነው። ይህም ያለ ምክንያት አይደለም። ፍራንክ ሼፈር ማለት በፕሮቴስታንቱ ዓለም ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም ባሉት የፍልስፍናና የነገረ መለኮት ትምህርት ቤቶች ታዋቂ የነበረው የታዋቂው የፍራንሲስ ሼፈር ልጅ ነው። ፍራንሲስ ሼፈር ከሞተ በኋላም በእግሩ ይተካል ይባል የነበረውና፣ በራሱም ታዋቂ ጸሐፊና ዶክመንታሪ ዘገባዎችን አዘጋጅ የነበረው ፍራንክ ሼፈር፥ ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለምን እንደመጣ «ለብቻ





መጨፈር» (Dancing Alone) በሚለው መጽሐፉ ላይ በሰፊው ገልጧል።[77]

ሼፈር በመጽሐፉ ላይ «ብዙ ባነበብኩኝ እና ብዙ ባስተዋልኩ ቁጥር ታሪካዊ ከሆነችው ቤተ ክርስቲያን ጋር እንዳልተገናኘሁ አስተዋልኩ.... የዕድሜዬን ግማሽ በወንጌላውያን ፕሮቴስታንት ቤተ ሰብ ውስጥ ስኖር አንዲት ቅንጣት እንኳን ስለ ጥንታውያን አበውና ስለ ትምህርታቸው አላውቅም ነበር።» በማለት በፕሮቴስታንቲዝም ውስጥ የነበረውን መሠረት የለሽ አካሄድ እንዴት እንደጎዳው አሳይቶአል።

በአሜሪካ ውስጥ ለሚታየውም መንፈሳዊ ድርቀት ዋና ምክንያት የሆነው በፕሮቴስታንቱ ዓለም የሚየታየው አዳዲስ ዓለማዊ አስተሳሰቦችን ማጋበስና አንጻራዊ ሥነ ምግባር እንደሆነም ገልጦአል።[78] ሼፈር ይህን በፕሮቴስታንቱ ዓለም የሚታየውን ቅጥ ያጣ ሁኔታ ወደ የት እንደሚወስድ በማየቱ ምክንያት ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንደተመለሰ ተናግሮአል። ይህ የሼፈር አገላለጥ የጅምላ አመለካከት ነው ብለው አንዳንድ የፕሮቴስታንት ሊቃውንት ቅሬታቸውን ቢገልጡም፥ አሁን አሁን ግን ራሳቸው ፕሮቴስታንቶችም ይኸንኑ የሼፈርን አስተሳሰብ እየተናገሩት ነው። እንደ ሼፈር ያለ ጠንካራ እርምጃ ባይወስዱም ግን በፕሮቴስታንቱ አካሄድ አለመርካታቸው በግልጥ እየታየ ነው።

(77) *Frank Schaeffer, Dancing Alone: The Quest for Orthodox Faith in the age of False Religion ( Brookline, MA: Holy Cross Orthodox Press )*

(78) *" the dreadful mixture of dehistoricalized Evangelical Protestantism Enlightenment Secularism and secularized, American- style Roman Catholicism that has become our nation's civil religion"*



www.ethiopianorthodox.org

**ጆርስላቭ ፔልካን**

በያዝነው ክፍለ ዘመን ዓለማችን ካፈራቻቸው ታላላቅ ሊቃውንት አንዱ የሆነው ጆርስላብ ፔልካን ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የገባው በሰባ አራት ዓመቱ ነው። ፔልካን ለምን ይህን እርምጃ እንደወሰደ በገለጠበትና ቀድሞ አባል ለነበረበት የወንጌላውያን ሉተራን ቤተ ክርስቲያን አባላት በላከው ይፋ ደብዳቤ እንዳለው ውሳኔው «በአእምሮዬና በመንፈሴ የነበረው ለዘመናት የነበረው ሃሳብ የመጨረሻ መደምደሚያ» ነበር ያለው።

የታላቁ የዬል ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር የነበረው ፔልካን ከሠላሳ ሦስት መጻሕፍት በላይ የጻፈ ሲሆን በዋናነት የሚታወቀው በአምስት ቅጽ የጻፈው «የክርስቲያን ትውፊት» የሚለው መጽሐፉ በመላው ዓለም አድናቆት አትርፎል። ይህ መጽሐፉ በክርስትናው ዓለም ያለውን ትውፊት በጥልቀት የመረመረ መጽሐፍ ስለአሆነ ማርክ ኖል የተባለ የታሪክ ሊቅ «በሃያኛው ክፍለ ዘመን ያልተሞከረ የክርስትና ትውፊት ታሪክ» ብሎታል።

በሐርቫርድ በፕሪንስተን በደክ በአበርዲን ዩኒቨርስቲዎች ያስተማረው ፔልካን ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካን ጨምሮ በዓለም ታዋቂ የሆኑ መጽሔቶችና የምርምር ዘገባዎች (ጆርናሎች) ኤዲተር ነበር። ከዚህ በተጨማሪም የአሜሪካ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ማኅበር ፕሬዚደንት፥ የዓለም አቀፍ የሉተር ምርምር፥ ፕሬዚደንት የአሜሪካን የሳይንስና ሥነ ጥበብ አካዳሚ ፕሬዚደንት፣ የናሽናል ሁማኒቲ ማዕከል የቦርድ አባልና ዘሴንተር ኦፍ ቴዎሎጂካል ኢንኩዋየር አባል ነበረ።





# በኦርቶዶሳውያን አበው ትምህርት ከስህተት የተመለሰ።

**ቶማስ ኦዴን**[79]

ይህ ደግሞ ከሌሎች የሚለየው በፕሮቴስታንቱ ዓለም ውስጥ ያሉና ነገር ግን የፕሮቴስታንቱ ዓለም አመክንዮአዊ ትምህርት ወደ ስህተት የወሰዳቸው ምንም እንኳዋን ከፕሮቴስታንቱ ዓለም ባይወጡም በኦርቶዶክሳውያን አበው ትምህርት ከስህተታቸው የተመለሱና ይህንንም ለዓለም የሚያሳውቁ ሊቃውንትን የሚመለከት ነው። ከእነዚህም መካከል አንዱ ቶማስ ኦዴን ነው። ቶማስ ኦዴን በኦርቶዶክሳውያን አበው ትምህርት ሳይማረክ በፊት የታወቀ ለዘብተኛ ፕሮቴስታንት ነበር። በአሜሪካ አሉ ከሚባሉት ትምህርት ቤቶች እጅግ ታዋቂ ከሆኑ ፕሮቴስታንቶች ከነሪቻርድ ኒበር[80] ሥር የተማረው ኦዴን በኤግዜንሺያሊዝም ፍልስፍናና[81] በፍሩድ[82] የሥነ ልቦና ትምህርት በመንገድ

(79) ስለ ሕይወት ታሪኩ በዋናነት የተጠቀምኩበት Christopher A. Hall, Reading Scripture with the Church Fathers, InterVarsity Press የሚለውን መጽሐፍ ነው።

(80) ሪቻርድ ኒበር በታላቁ የየል ዩኒቨርስቲ አስተማሪ የነበረ ሲሆን እምነት በአንጻራዊ ዕይታ ላይ የተመሰረተ ነው ብሎ የሚያስተምር ነበር። እውነት የምንለው ነገር ሁሉ በታሪክና በባሕል የቀለመ ስለሆነ ፍጹማዊ እውነት የለም ብሎ ያስተምር ነበር።

(81) ማናቸውም ነገር ትርጉም የለውም ይህም ያለው ሕይወትም ጽልመታዊ የሆነ መከራ ስቃይና ባዶነት (አልቦነት) ብቻ ነው ብሎ የሚያምን የፍልስፍና ዘርፍ ሲሆን በዋናነት በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ በፈረንሳይ ሀገር በነበሩ ደራስያን የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች የሥነ ጥበብ ውጤቶች ፍልስፍናው ተስፋፍቶአል። የሚበዙት የፍልስፍናው አራማጆች እግዚአብሔር የለሾች ናቸው።

(82) ሲግመንድ ፍሩድ የዘመናዊ ሥነ አእምሮ ጥናት አባት ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ህልዎተ እግዚአብሔርን የሚክድ ነበር። በ1913 ዓ. ም. ላይ በጻፈው መጽሐፉ ላይ ሃይማኖት ሰዎች ከሥነ ልቡናቸው ችግር «ኤዲፐስ ኮምፕሌክስ» (ወንዶች ልጆች በአባታቸው ላይ ሳያውቁት ከሚኖራቸው ጠላትነት) እና ከኋላ ቀርነት የሚመነጩት ነው ብሎ ያስተማረ ነው። ፍሩድ የተመሠረተባቸው ንድፈ ሐሳቦች (ቲዎሪ) ዛሬ በሳይንሱ ዓለም ሳይቀር ሐሰት እንደሆነ ተደርሶበታል።



www.ethiopianorthodox.org

አብዛኛውን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት የካደ ነበር። በእነዚህ ዘመን አመጣሽ ትምህርቶች ውስጥ በተነከረ ቁጥርም ስላለፈው የክርስትና ታሪክ ያለው አመለካከት እየመነመነበት መጣ። በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው በፕሮቴስታንቱ ዓለም እንደሚታየው ታላቅ አክብሮት የሚሰጠው ዘመን አመጣሽ የሆነው ነገር እንጂ የቆየው እንዳልሆነ ሁሉ ኦዴንም ይህንኑ መንገድ ተከትሎ ሄደ።

ይህ የተሳሳተ ትምህርትና አመለካከት ወደ ምን ዓይነት የተሳሳተ አቅጣጫ እንደሚመራ ኦዴን የተመለከተው ምዕራብ አውሮፓና አሜሪካ በባሕል አመጽ በታመሱበት በስልሳዎቹ ውስጥ ነው። በዚህ ወቅት ብዙዎች የኦዴን ጉዋደኞች የጊዜው በነበረው የወሲብ አብዮትና የአደንዛዝ ዕጽ ማዕበል ውስጥ ገብተው ሲሰጥሙ ለምን ወደዚህ ጥፋት እንደደረሱ አስተዋለ። የተሳሳተ ትምህርት የተሳሳተ ሕይወትን እንደሚወልድ የተጣመመ መንገድ ወደ ሞት እንደሚያደርስም አየ።

ቶማስ ከዚህ ዓይነት አስቸጋሪ የስህተት ማጥ የሚወጣበትን መንገድ የሚያሳይ ምክር ያገኘው ካልጠበቀው ሰው ነው። ይህ ሰው በዩኒቨርስቲ ውስጥ አብሮ ከኦዴን ጋር ያስተምር የነበረ አይሁዳዊ ነው። አይሁዳዊው የሃይማኖትህን ጥንታውያን አባቶች ተመልሰህ ማንበብ ካልቻልክ የቱንም ያህል የቴዎሎጂ ሊቅ ብትባል መሠረት አይኖርህም ብሎ መከረው።

ኦዴን በአይሁዳዊው ምክር የተዋወቃቸው የቤተ ክርስቲያን አበው ለእርሱ አዲስ ነበሩ። እርሱ የነበረው ፍልስፍና ከሉተር የተማረው ለእርሱ ርዕዮተ ዓለም የማይስማማውን ማናቸውንም ትምህርት አለመቀበል ነበር። አሁን ግን የክርስትና አምድ ሆነው





የቆዩትን አበው አትናቴዎስን ጎርጎርዮስን ባስልዮስን ዮሐንስ አፈወርቅን ቄርሎስን ኢያሩኒሙስን (ጀሮም) ማንበብ ጀመረ። የእነዚህ ታላላቅ አበው ታሪክና ትምህርት ባነበበ ቁጥር ነፍሱ ያጣችውን እርካታ ማግኘት ቻለ። ምንም እንኳን ከፕሮቴስታንቱ ዓለም ወጥቶ ወደ ኦርቶዶክሱ ዓለም ባይገባም ለብዙዎች ፕሮቴስታንቶች ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መመለስ ምክንያት ሆኗል።

ቶማስ ኦዴን በአሁኑ ወቅት በድሪው ዩኒቨርስቲ የሲስተማቲክ ቴዎሎጂ አስተማሪ ሲሆን «የጥንታውያን አበው ትርጓሜ በመጽሐፍ ቅዱስ» ላይ በሚል ርዕስ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ያለውን የአበው ትርጓሜ ከሮማይስጥ (ከላቲን) እና ከጽርእ (ከግሪክ) ወደ እንግሊዘኛ የተረጎመ ይገኛል። ይህ የኦዴን ትርጉም በዓለም አብያተ ክርስቲያናት በተለይም በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ከፍተኛ ተቀባይነትን ያገኘ ትርጓሜ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

# ቅጥያ

## የአንድ ትውልድ ሮሮ

## ተሐድሶ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ ሃይማኖተ አበው እና እኔ

### መግቢያ

የመጽሐፉ ዓላማ ስለ ፕሮቴስታንቶች ሆኖ በተሐድሶና በማኅበረ ቅዱሳን ላይ መጻፍ ለምን አስፈለገ የሚል ጥያቄ ከአንባቢዎች ይነሣ ይሆናል። መልሱ ፕሮቴስታንቱን ዓለም በአሁን ወቅት ከማንም በላይ የጠቀሙትና በብዙ ሺህ ለሚቆጠሩ ኦርቶዶክሳውያን ወደ ፕሮቴስታንቱ ዓለም መኮብለል ምክንያት የሆኑትና እየሆኑ ያሉት እነዚህ ሁለት ክፍሎች ስለሆኑ ነው።

የዚህን ጸሐፊ የቀደመ ተሞክሮ ወይም የደረሰበትንና ያለፈበትን የሕይወት ውጣ ውረድ የሰሙ ሰዎች በመጀመሪያ የሚጠይቁት ጥያቄ «ይህ ተሐድሶ የሚባል ድርጅት ምንድን ነው? ዓላማውስ ምንድን ነው?» የሚል ነው። ብዙ ጊዜ እንዳስተዋልኩት ከሆነ መልሴ ብዙዎችን አያረካም። ይህም ስለ ሁለት ምክንያት ነው። አንደኛው ብዙ ሲነገራቸው የነበረውን ሁሉ ስለምሸርባቸው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከጉዳዩ ውስብስብነት የተነሳ በውስጡ ካለፉበት ሰዎች በስተቀር ሁኔታውን በቀላሉ መረዳት ስለሚያዳግት ነው።





ሆኖም አሁን በቤተ ክርስቲያናችንና በዙሪያዋ የምንሰማው «ተሐድሶ» ምንድን ነው? ይህ ቃል በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ለምን ጥቅም ውሎ ነበር? ቃሉን ከዚህ በፊት የተጠቀሙበት ሰዎች አሉ ወይ? ኦርቶዶክሳውያን ሰዎችስ በዚህ ተጠቅመው ነበር ወይ? «ኦርቶዶክስ ተሐድሶ» የሚለው ቃል መቼ ተጀመረ? የሚለውንና ከዚህም ጋር ማኅበረ ቅዱሳን የኦርቶዶክስ ተሐድሶ አራማጆች ነን ከሚሉ ሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት እንመለከታለን።

### 1. ተሐድሶ ምንድን ነው?

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አብያተ ክርስቲያናትን በሰፊው እያነጋገረ ያለው ነገር ቢኖር «ተሐድሶ» የሚለው ቃል ነው። ቃሉ እንዲህ እንደ አሁኑ ፕሮቴስታንታዊ ለሆነ አስተሳሰብ ከመዋሉና አከራካሪ ከመሆኑ በፊት፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚጠቀሱት ታላላቅ የነገረ መለኮት ቃላት አንዱ ነው። ንስሓንና ውስጣዊ የሆነ የሕይወት ለውጥን ወደ እግዚአብሔር መመለስን የሚያመለክት ነው። በሌላም በኩል ደግሞ ሲኖዶሳዊ የሆነ ለውጥን (መሻሻልን)[83] ሊያመለክት ይችላል። አሁን ግን ፕሮቴስታንቱ ዓለም ብቻ ሳይሆን የፓለቲካው ዓለምም እየተጠቀመበት ስለሆነ አስቸጋሪ ቃል ሆኗል።

(83) ሲኖዶሳዊ ለውጥ (ማሻሻል) ያልኩት፥በቅዱስ ፓትርያርኩና በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ታስቦበትና ተመክሮበት፥ ለቤተ ክርስቲያን መሻሻልና ዕድገት ይረዳሉ የሚባሉ መሻሻሎችን፥ ለውጦችንና አዳዲስ ተቋሞችን ሁሉ ያመለክታል። ቤተ ክርስቲያናችን በገዛ ልጆቹዋ ሊቃነ ጳጳሳት መመራት ከጀመረችበት ወቅት አንሥቶ ብዙ መሻሻሎችንና ለውጦችን አድርጋለች። ከነዚህም ታላቁና ቤተ ክርስቲያንን በአስቸጋሪ መከራ ውስጥ መኸታ ሆኖ እንድታልፍ ያደረጋት የሰበካ ጉባኤ መቋቋምና የቃለ አዋዲ ድንጋጌ ነው። ይህ የሰበካ ጉባኤና የቃለ አዋዲ ድንጋጌ ብዙዎች እንደሚያስቡት የሰዎች የአስተሳሰብ ፈሊጥ ሳይሆን የሲኖዶስ ቀኖናዊ ውሳኔ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

## ተሐድሶ በኦርቶዶክሱ ዓለም

ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን እምነትን የምትጠብቅ እንጂ እምነትን በዘፈቀደ ወይም ባሰኛት መንገድ የምትቀያይር ስላይደለች ዛሬ አንዳንዶች ከዚህች ቤተ ክርስቲያን የወጡ ሰዎች እንደሚናገሩት ተሐድሶ የሚለውን ቃል እምነትን በተመለከተ አታውለውም። ሃይማኖት ምን ዓይነት መልክ እንዳላት ሐዋርያው ይሁዳ በመልእክቱ ጽፎልናል «አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለቅዱሳን የተሰጠች በማለት» ስለሆነም አትበረዝም አትከለስም፤ ወይም ብልየት እርጅና አያገኛትም። በሌላ በኩል ግን የክርስቲያን ሕይወት ዕለት ዕለት ይታደሳል። ውስጣዊ የሆነውን የሕይወት ተሐድሶ የሚያገኘው በንስሓ በጾም በጸሎት ነው። ይህን በተመለከተም በብዙ ቦታዎች ቅዱሳት መጻሕፍት ይናገራሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ አስተዳደራዊ የአሠራር ለውጦችና አልፎ አልፎ ቀኖናዊ ለውጦች ይኖራሉ። እነዚህም ቢሆኑ የሚከናወኑት በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ስለሆነ ለውጡ ሲኖዶሳዊ ነው እንጂ የአመጽ ወይም የጥቂት ግለሰቦች አይደለም።

ይህም በኦርቶዶክሱ ዓለም የተለመደ እንደሆነ በቤተ ክርስቲያናችን የከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች ለብዙ ዓመታት በማስተማር ሥራ ላይ የተሰማሩትና አያሌ ደቀ መዛሙርትን ያፈሩት ሉሌ መላኩ « የቤተ ክርስቲያን ታሪክ» በሚለው መጽሐፋቸው በግብጽ ቤተ ክርስቲያን የነበረውን ሲኖዶሳዊ ተሐድሶ ሲገልጡ፦
«በኮፕቶች (በግብጾች) ዘንድ የተሐድሶ አባት በመባል የሚታወቀው ቄርሎስ አራተኛ(1854-1861) የእክስንድርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ነው። ዋነኛ ዓላማ አድርጎ የተነሣው ትምህርትን ማስፋፋት





(ማስራጨት) ስለነበር፥ በግብጽ ካህናት ዘንድ ሰፍኖ የነበረውን የትምህርት ጉድለት ዝቅተኛነትን ለማሻሻል ካህናት ተግተው እንዲማሩ አደረገ። ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤትም ከፍቶ ዓለማዊና መንፈሳዊ ዕውቀት የነበራቸውን በማሠማራት መጻሕፍትን በገፍ በማቅረብ ካህናትና ምእመናንን የቅብጥ (ኮፕት) የዐረብኛ፣ የእንግሊዘኛ፣ የፈረንሳይኛ፣ የኢጣልያንኛ፣ የቱርክ ... ወዘተ ቋንቋዎችና የተለያዩ መንፈሳዊ ትምህርቶችን እንዲማሩ አደረገ።» ይሉናል።[84]

## ተሐድሶና ነፍሰ ገዳዩ ቡድን

ተሐድሶ የሚለውን ቃል በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሥልጣን ትግል አንጻር የተጠቀሙበት ሰማዕቱን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን ለማስገደልና ሥልጣን በቤተ ክህነቱ ውስጥ ለመያዝ የተነሡ ሰዎች ናቸው። ስለ እነዚህ ሰዎች አቡነ ጳውሎስ በጻፉት የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ታሪክ ላይ እንዲህ ብለዋል፥

«ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ባላቸው ኃላፊነት መሠረት የቤተ ክርስቲያንን መብት ለማስከበርና ለማስጠበቅ የሚያደርጉት ጥረት የኮሚኒስት ፍልስፍና አራማጅ የነበረውን የደርግ መንግሥት አስከፋው እንጂ አላስደሰተውም። በመሆኑም በሥራቸው ጣልቃ በመግባት ቀደም ሲል ያቋቋሙትን የአስተዳደር ጉባኤ አፍርሶ ዓላማውን የሚያስፈጽምለት «ጊዜያዊ የቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጉባኤ» በሚል ሽፋን የራሱን ቡድን አቋቋመ።[85]

*(84) ሉሌ መልአኩ፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥ ለሦስተኛ ጊዜ ተሻሽሎ ታተመ። ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት አዲስ አበባ 1986 ዓ. ም.። ገጽ 114።*
*(85) በአንዲት ሀገር ሊኖር የሚችለው አንድ የወጣት ማኅበር ማለትም የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ወጣቶች ማኅበር ብቻ ነው በማለት ከደርግ ጋር ተባብሮ ሃይማኖተ አበውን ያስዘጋውና የሃይማኖተ አበው የዕድሜ ልክ ጠላት የሆነው «አጠቃላይ ጉባኤ» የሚባለው የወጣት ማኅበራት ሕብረት የተቋቋመው በ«ተሐድሶ ጉባኤ» ነው።*



www.ethiopianorthodox.org

የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ከመንግሥት አስተዳደር ነጻ ሆኖ በአንድ ሊቀ ጳጳስ እንዲመራ ሲያደርጉም ጳጳሱን አንስቶ የራሱን ሥራ አስኪያጅ ሾመ። ከዚህ በኋላ በቤተ ክርስቲያኑዋ አስተዳደር አዛዥና ናዛዥ ሆነ።.... እንግዲህ ደርግና ጥቂት የጊዜያዊ ጉባኤ ሴረኞች በእንደዚህ ያለ ጣልቃ ገብነትና በካድሬዎቻቸው ዘለፋ አላሠራ ብለው ፈተና ሲያሳዩአቸው ከቆዩ በኋላ የካቲት 9 ቀን 1968 ዓ. ም. ምሽት ላይ ከሕግ መንፈሳዊም ሆነ ከሥጋዊ ሕግ ውጭ በአምባ ገነንነት ከሥልጣናቸው አውርደው፥ ለእስራት ዳረጓቸው። በታሰሩ ማግስት የካቲት 10 ቀን «ሲጠበቅ የቆየ ፍርድ» በሚል ርዕስ በጥቂት የተሐድሶ ጉባኤ አባላት የተዘጋጀ የቅዱስነታቸውን ስም ጥላሸት የሚቀባ የሐሰት ሰነድ በሬዲዮና በጋዜጣ ተላለፈ።»[86]

እነዚህ ግለሰቦች ቅዱስነታቸው ያላደረጉትን፤ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም ያከናወኗቸውን መልካም ሥራዎች ወደ ከፋት እየቀየሩ በዓለም አደባባይ ሲከስዋቸው መፈክራቸው «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ያስፈልጋታል» በሚል ነበር። ይህም አመጽ ቅዱስ ፓትርያርኩን በግፈኞች እጅ እንዲገደሉ ሲያደርግ ሁለት ሊቃነ ጳጳሳትን ጨምሮ የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ሊቀ ሥልጣናት የነበሩት አቡነ መልከጼዴቅ ለእስር ዳረጋቸው። ይህ በጥቂት ሰዎች የሥልጣን ጉጉት የሚመራ «አስተዳደራዊ ተሐድሶ» (administrative reformation or transformation) በብዙ መንገድ የአመጽ መንፈስ ስላለበት ኦርቶዶክሳውያን አበው ባይደግፉትም አሁንም ዘሩ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የወጣ አይመስልም።

(86) አባ ጳውሎስ፤ የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ አጭር የሕይወት ታሪክ፥ ከምዕራብ ጉብኝት በፊትና በኋላ። አዲስ አበባ ሐምሌ 1987 ዓ.ም። ገጽ 85-86።





በተለይም «ማኅበረ ቅዱሳን» የተባለው አዲስ ማኅበር፥ ዋና ዓላማው ይህን «አስተዳደራዊ ተሐድሶ» ማምጣት እንደሆነ አመራሮቹ በተለያዩ መድረኮች ላይ እየተናገሩ ናቸው። ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ መሠረታዊ የሆነውን የኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናትን ቀኖናና ዶግማ ካለማወቅ ከፕሮቴስታንቱና ከዓለማዊ (secular) ፍልስፍና ተጽዕኖ የሚመነጭ ነው።

በኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እያንዳንዱ አስተዳደራዊም ሆነ ሃይማኖታዊ አካሄድ ቀኖናዊ ነው። ይህም ማለት ለውጦች እንኳን ቢያስፈልጉ በአመጽ በስርብትናዊ (ፓለቲካዊ) አካሄድ ወይም በገንዘብ ኃይል (ሲሞኒዝም) ማካሄድ አይቻልም። ቀኖናን የሚሠራው ቅዱስ ሲኖዶስ ስለሆነ ቅንጣት የምታህል ለውጥ ቢያስፈልግ ኃላፊነቱም ሥልጣኑም የቅዱስ ሲኖዶስ ነው። ሌሎች ቤተ ክርስቲያንን እንደ አንድ ሕዝባዊ ድርጅት ስለሚመለከቷት አመቺ ነው ያለውን አስተዳደራዊ አካሄድ ይከተላሉ። ቢያሻቸው ይሾማሉ። ቢያሻቸው ያወርዳሉ። በእኛ በኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ግን እንዲህ አይደለም።

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል የሆነች መንፈሳዊት ናት። ሕብረትነቷም ከሰማያውያን ቅዱሳን ጋር ነው። በሰማይም በምድርም ያለች ወይም ሰማይንና ምድርን የምታገናኝ ናት። ይህም ስለሆነ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ራስ ከሆነው ከክርስቶስ መንጭቶ በመንፈስ ቅዱስ በተሾሙ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የሚመራ ነው።

«በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን



www.ethiopianorthodox.org

ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ» ብሎ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዳስገነዘባቸው፤ ቤተ ክርስቲያን የምትመራው በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ነው። ሐዋ 20፥28።

በአሁኑ ወቅት በቤተ ክርስቲያናችን የተከሰተው «የቀኖና ክርክር» አንዳንዶች ባሰቡበትና በወደዱት መንገድ እንዲሄዱ ምክንያት የፈጠረላቸው ይመስላል። ጉዳዩ የቱንም ያህል ከባድ ቢሆንም የራሳችንን ሃሳብና አመለካከት በቤተ ክርስቲያናችን አካሄድ ላይ ለመጫን የአባቶቻችን ትምህርትም ሆነ ሕገ ቤተ ክርስቲያን አይፈቅድልንም። በ«ክርክሩ» ላይም ውሳኔ ሰጭዎች ለመሆን ከአቅማችን በላይ ይመስለናል። ታዲያ ምን እናድርግ? የክርክሩ ምንጭ የብፁዓን አባቶቻችን መለያየት ስለሆነ እነርሱ አንድ ላይ ሆነው የሚነጋገሩበት የሚወያዩበትን ብሎም ለሕዝበ ክርስቲያን አንድነትና ለመጪውም ትውልድ ብለው ውሳኔ የሚሰጡበትን መንገድ ማመቻቸት አልብን። አለበለዚያ አሁን የሚታየው አካሄድ ወደ አደገኛ ድምዳሜ ወደ ደረሱት ወደ ፕሮቴስታንቶች መበጣጠስ የሚወስደን ነው።

## ተሐድሶ በፕሮቴስታንቱ ዓለም

ከዚህ በፊት በሰፊው እንዳየነው ቃሉን ለራሳቸው ዓላማ የተጠቀሙት ፕሮቴስታንቶች ናቸው። በተለይም ማርቲን ሉተር በ15ኛው ክፍለ ዘመን ያደረገውን እንቅስቃሴ ፕሮቴስታንቶች «ታላቁ ተሐድሶ» ብለው ነው የሚጠሩት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፕሮቴስታንቶች እንቅስቃሴያቸውን በሙሉ በዚህ ስም ከመጥራታቸውም ባሻገር በኔዘርላንድ፥ በስኮትላንድና በጄኔቭ የነበሩት የጆን ካልቢን ተከታዮች ራሳቸውን የተሐድሶ አብያተ ክርስቲያናት (ሪፎርምድ ቸርች) እያሉ ይጠራሉ። በዘመናዊ የፕሮቴስታንቶች ታሪክም





ብዙዎች ፕሮቴስታንቶች ከየድርጅታቸው ተገንጥለው ሌላ ድርጅት ሲከፍቱ የሚጠቀሙበት «ተሐድሶ» የሚለውን ቃል ነው። በዚህ ምክንያት የፕሮቴስታንቱ ዓለም አጠቃቀም ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ስሜት አንድ ላይ አድርጎ የያዘ ከመሆኑም ባሻገር የቤተ ክርስቲያንን ዶግማና ቀኖና ከስር ከመሠረቱ ከመቀየር ጋርም የተያያዘ ነው። ይህን በሰፊው ስላየን አሁን እዚህ ላይ አንደግመውም።

## ተሐድሶና የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን

ፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ስለ ተሐድሶ ያላቸውን ሐሳብ ያገኙት ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ነው። የሮም ካቶሊክ የተሐድሶ ሐሳብ ዶግማንና ቀኖናንም ያጠቃለለ ስለሆነ በየጊዜው በምታደርጋቸው ጉባኤያት ከዚህ በፊት የነበሩት አበው ያላስተማሩትን በትምህርቱዋ ላይ ስትጨምር ታይታለች። ከነዚህም መካከል ስለ መንፈስ ቅዱስ መሥረጽ የአበውም ሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት «ከአብ የሠረጸ» የሚል ሲሆን በቶሌዶ ከተማ ባደረገችው ጉባኤ «ከወልድም» ይሠርጻል ብላ የፊልዮኬ ሥርዋጽን አስገባች። በመጀመሪያው ቫቲካን ስብሰባ ላይም ፓፓው አይሳሳትም የሚለውን አንቀጽ በማስገባት ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ውጭ የሆነ ትምህርት አስገብታለች።

ይህ ልክ የሌለው ተሐድሶ ራሱዋን እየጎዳት እንደሆነ ይታወቅ ዘንድ በውስጧ ሥር የሰደደው ዓለማዊነት ዛሬ ገሐድ ወጥቶ በከፍተኛ ደረጃ በዓለም ላይ እያሳቀላት ይገኛል። ብዙዎች የሮም ካቶሊክን አካሄድ ያጠኑ ሊቃውንት እንደሚናገሩት ከሁለተኛው ባቲካን በኋላ የሮም ቤተ ክርስቲያን «ታሪካውያን አብያተ ክርስቲያናት» ከሚባሉት ውጭ የሆነ አካሄድ በመከተሏ ዛሬ በዘመነኞቹ የነገረ መለኮት ሊቃውንት



www.ethiopianorthodox.org

ዘንድ እጅግ የሚያስደነግጥ አስተያየቶች በስመ «ተሐድሶ» እየተሰጠ ነው።

በሌላው በኩል ደግሞ ከትሬንት ጉባኤ ጀምሮ ከትሬንቱ ጉባኤ ጀምሮ ያደረገችው ውስጣዊ መሻሻሎችና ለውጦች ለቤተ ክርስቲያኑዋ ታላቅ የሆነ መስፋፋትና ኃይል ሰጥቶአታል። ዛሬ በላቲን አሜሪካና በተባበሩት የአሜሪካ ግዛቶች የሚገኙት የካቶሊክ ተከታዮች የተገኙት በዚህ ወቅት ነው።

## 2.«<u>ኦርቶዶክስ ተሐድሶ</u>»

ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ ፕሮቴስታንቱ ዓለም ተሐድሶ የሚለውን ቃል መጠቀም የጀመረው ከወታደራዊ ደርግ አስተዳደር መውደቅ በኋላ ነው። ኦርቶዶክስን እናድሳለን የሚለው የፕሮቴስታንቱ ድብቅ እንቅስቃሴ የተጀመረውም የጴንጠቆስጤው የ«ሙሉ ወንጌል» ውስጥ ሰባክያን ነን በሚሉ ሰዎች ነው። እነዚህ ፕሮቴስታንቶች ወደ ሙሉ ወንጌል አስኮብለው የወሰዳቸውን አንድ መነኩሴና አንድ በረድእነት ሳለ ከገዳም የተመለሰ ሰው በመያዝ የተሐድሶ ጉባኤ በማለት ማሰባሰብ ጀመሩ። የጉባኤውም ዓላማ ኦርቶዶክሳዊ በሚመስል አምልኮ የተሳበውን ሕዝብ ፍጹም ወደ ሆነ የጴንጠቆስጤዎቹ ልምምድ ውስጥ ማስገባት ነበር። በመቀጠልም ይህን ወደ ጴንጠቆስጤ ልምምድ ውስጥ የገባውን ወይም ጴንጤ የሆነውን ሰው በእነርሱ ድርጅት ውስጥ የልጅነት ስሙን አስክደው ማስጠመቅ የዓላማቸው ግብ ነበር።

ይህን ዓላማቸውን ለማስፈጸም ይረዳቸው ዘንድ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ከፍተኛ እውቀት ከነበራቸው ሰዎች ዘንድ በመሄድ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያናችንን አባባሎች ሥርዓቶችን





መጠያየቅ ጀመሩ። በዚህ ወቅት የእነርሱ ያይደለውንና እነርሱ ያልጻፉትን ጽፈናል ብለው በየአቅጣጫው ማሳተም ጀመሩ። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን «<u>ኢትዮፒስ</u>» የሚለው መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ አንዳንድ ንግርቱንና የራሱን የሙሉ ወንጌል የሃይማኖት አንቀጽ ጨምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን የሚሰድብና ሙሉ ወንጌልን የሚሰብክ ከመሆኑ ባሻገር ለፔላጂያሪዝም ጥሩ ምሳሌ የሚሆን ነው።(87)

በተለይም «<u>ኢትዮፒስ</u>» ከተጻፈ በኋላ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ልጆችን ፍጹም ከቤተ ክርስቲያናቸው ለይቶ በድርጅቶቻቸው ጥላ ሥር በሚያስገቡ ሰዎችና አንዳንድ ግራ ተጋብተው ከቤተ ክርስቲያን ርቀው ባሉ ነገር ግን ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው ለመመለስ በሚፈልጉ ሰዎች መካከል ከፍተኛ ግጭት ተፈጠረ። አንዳንድ የፕሮቴስታንት መሪዎችም በጭፍን የድርጅት ፍቅር ይህን ሁኔታ ለዓላማቸው መጠቀሚያ ለማድረግ ፈለጉ። እነዚህ በቁጥር እጅግ ውሱን የሆኑ ሰዎች ማንም የማያውቃቸውና በማንም ኦርቶዶክሳዊ ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው ቁጥራቸውም ከፕሮቴስታንቱ ጋር ነበር። እስከ ዛሬ ድረስ ለብዙዎቻችን ምስጢር በሆነ ሁኔታ በአንድ ጀንበር ተሐድሶን በመላው ኢትዮጵያ በማስተዋወቅ ለፕሮቴስታንቶቹ ሰፊ በር መክፈት የጀመረው ማኅበረ ቅዱሳን ብቅ ያለውም በዚህ ወቅት ነበር።

### <u>ማኅበረ ቅዱሳንና ተሐድሶ</u>

የማኅበረ ቅዱሳን በመላው ኢትዮጵያ ዕውቅና ማግኘትና የተሐድሶ መስፋፋት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው።

*(87) የሰዎችን ጽሑፍ እየወሰዱ የራስ አድርጎ መጻፍን የተማረው ከመምህሮቹ ነው። በእምነት እንቅስቃሴ ውስጥ የእንቅስቃሴው አባት የሚባለው ኬኒት ሄገን ቃል በቃል ኬንየን ከሚባለው ከሌላ የስህተት አስተማሪ ቀድቶ ራሴ ነው ብሎ ጽፎአል፤ አጥሩን ቆርጥ ይባላል እንዲህ ነው።*



www.ethiopianorthodox.org

ገጽታዎች ናቸው። ማኅበረ ቅዱሳን ያለ ተሐድሶ አሁን የደረሰበት ደረጃ አይደርስም ነበር። ተሐድሶም ያለ ማኅበረ ቅዱሳን እንዲህ ያለ መተዋወቅና መስፋፋት አያገኝም ነበር። አንደኛው የሌላኛው ሕልውና መሠረት ነው።

ማኅበረ ቅዱሳን ከብላቴ ጦር ሠፈር የተመለሱ ጥቂት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችና በዝዋይ የካህናት ማሰልጠኛ ለሁለትና ለሦስት ወራት ከሰለጠኑ ካህናት የተወሰኑትን ይዞ ሲቋቋም ዓላማው አድርጎ የተነሳው በከፍተኛ ትምህርት ተቅዋማት ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የቤተ ክርስቲያናቸውን እምነትና ሥርዓት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ያደርጉት እንደ ነበረው ዶግማን ወይም እምነትን ከቀኖናና ቀኖናውን ከባሕል ባሕሉን ደግሞ ከአጉል ባሕል እየለዩ ማስተማርን ነበር። ነገር ግን ገና ከምሥረታው ማኅበሩን የረጅም ጊዜ ዓላማ የነበራቸው ሰዎች ያሰባሰቡአቸው ልጆች መቆጣጠርና ለዓላማቸው መጠቀሚያ ማድረግ ጀመሩ። በተለይም የከፍተኛ ተቅዋማትን በማስተማር አያሌ የቤተ ክርስቲያኒቱዋን ልጆች ያፈራውን ሃይማኖተ አበውን ለማፍረስ ዕድሜ ልካቸውን ሲያውጠነጥኑ የነበሩት ሰዎች አሁን ሃይማኖተ አበውን አፍርሰው ማኅበረ ቅዱሳንን ለመተካት ይማስኑ ጀመር።

ቁጥሩ ከሠላሳ ሚሊየን በላይ ለሆነው የኢትዮጵያ ምእመናን እነዚህ ሁለት የወጣቶች ተቅዋማት ቢያንሱበት እንጂ አይበዙበትም። ይሁን እንጂ ገና ከጅምሩ የአንዳቸው ሕልውና በአንዳቸው መጥፋት የሚወሰን እስኪመስል አንዱ አንዱን እስኪያጠፋ ድረስ ከፍተኛ ግብ ግብ ውስጥ ገቡ። ይህ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ሁለቱም ማኅበራት በሥራቸው አቅፈው ለያዙት ሕዝብ የሚጠቅም አልሆነም።





ማኅበረ ቅዱሳን ከምስረታው ሕዝባዊ ድጋፍ ለማግኘት የማኅበሩ አቅዋም ወግን በማጥበቅ መጓዝ እንደሆነ ግልጥ አደረገ። አባላቱ ጥብቅ የሆኑ የሥርዓት መመሪያን እንዲማሩ ተደረጉ። ሴቶቹ ምንም ዓይነት ጥለት ያልገባበት ነጭ ልብስ እንዲለብሱ ነጭ ሻሽ እንዲጠመጥሙና ከፀጉራቸው አልፎ እስከ ግንባራቸው ድረስ እንዲከናነቡ (ይህ ቅዳሴና ስብሰባቸው ላይ ብቻ ነው) ወንዶቹም እንደዚሁ ነጭ ልብስ እንዲለብሱ ታዘዙ። በሠርጋቸውም ወቅት ከመዝሙር ውጭ ባሕላዊም ሆነ ዘመናዊ ዘፈን እንዳይዘፍኑ ወይም እንዳያዘፍኑ ተነገራቸው። ማኅበሩ ሌላው ቀርቶ በቤተ ክርስቲያኒቱ የተዘጋጁትን መጻሕፍት እንደገና መመርመር የሚችል የኤዲቶሪያል ቦርድ አቋቋመ። የማኅበሩን ትምህርትና አቋም የሚገልጥም «ሐመር» እና «ስምዓ ጽድቅ» የሚባል ጋዜጣ ማዘጋጀት ጀመረ።

ነገር ግን ይህ ሁሉ መልካም ሆኖ ሳለ፥ ወዲያው ማኅበሩ የሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበርን ኦርቶዶክሳዊነት ጥያቄ ውስጥ አስገብቶ መጠየቅ ጀመረ። ምንም ሃይማኖተ አበው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ነባር ማኅበር እንደሆነ የተቋቋመውም ጀስዊትስ ወይም ኢየሱሳውያን የተባሉትን በዩኒቨርስቲና በሌሎችም የትምህርት ተቅዋማት የሚያደርጉትን መስፋፋት ለመከላከል ቢሆንም፣ ንጉሠ ነገሥቱ የበላይ ጠባቂ ፓትርያሪኩ ሊቀ መንበር ሆነው የሚመሩት የቤተ ክርስቲያኒቱ አካል እንጂ የተገነጠለ የአገልግሎት ክፍል አለመሆኑ ቢታወቅም ማኅበረ ቅዱሳን ግን ሃይማኖተ አበው የመናፍቃን ማኅበር ነው። አሠራሩም ሆነ አካሄዱ በኑፋቄ የተሞላ ነው እያለ ይጽፍ ነበር። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በሃይማኖተ አበው ጉባኤ ላይ እየተገኙ ያስተምሩ ነበር።



www.ethiopianorthodox.org

የሃይማኖተ አበው አባላትም ይህ የማኅበረ ቅዱሳን አካሄድን ለመከላከል ይመስላል አንዳንድ ቃላትን በማኅበረ ቅዱሳን ላይ መወርወር ጀመሩ። የቃላት ውርወራውና እምባጉዋሮው ከሁለቱ ማኅበራት አልፎ ወደ ቤተ ክርስቲያንዋ ከፍተኛ ትምህርት ቤቶች ሁሉ ገባ። የማኅበረ ቅዱሳን ልጆች፣ መንበረ ፓትርያርክ ጊቢ ውስጥ ይካሄድ ወደነበረው ወደ ሃይማኖተ አበው የሚሄዱትን «መናፍቃን» ሲሉአቸው የሃይማኖተ አበው ልጆች ደግሞ፣ ወደ ምስካየ ሃዙናንና ግቢ ገብርኤል የማኅበረ ቅዱሳን ጉባኤዎች የሚሄዱትን «ጋኔን ሳቢዎች መተተኞች» ይሉአቸው ጀመር። በዚያ የልጅነትና ጭፍን የድርጅት ፍቅር የነበረውን መወጋገዝ ዛሬ ያ የልጅነት ጊዜ አልፎ ስናየው እንዴት የሚያሳፍር ነው። በዚያ ወቅት በዚያ የቃላት ድብድብ ላይ እንሳተፍ የነበርነው የሁለቱም ወገኖች የምናገለግለው የየግላችን ድርጅቶችን እንጂ ቤተ ክርስቲያንን እንዳልነበረ የምናውቅ ስንቶች ነን።

## የገሞራው ጋዜጣ ጽሑፍ እና የሃይማኖተ አበው መዘጋት

እንግዲህ በዚህ ወቅት ነው ማን እንደጻፈው የማይታወቅ ጽሑፍ «ገሞራው» በሚባልና አሁን ከሕትመት ውጭ በሆነ የግል ጋዜጣ ላይ የወጣው። ጽሑፉ ሰፊ የሆነና የተሐድሶ ማኅበር እንዴት እንደሚንቀሳቀስና ዓላማውም ምን እንደሆነ የሚገልጥ ነበር። ከሁሉ የሚገርመው ግን ጽሑፉ ስለተሐድሶ ሆኖ ሳለ ከጽሑፉ ጋር አብሮ የወጣው ግን በጎፋ ገብርኤል ለረጅም ጊዜ ያገለገሉና የኢትዮጵያዊው ሰማዕት የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ልጅ የሆኑ መነኮሴና እርሳቸው የሚያስተምሩአቸው የሃይማኖተ አበው ተማሪዎችን የያዘ ፎቶ ነበር። የጽሑፉ





መደምደሚያ ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የተሐድሶ ድርጅት አካል እንደሆነ የሚናገር ነበር።[88]

ወዲያው በግል ጋዜጣ የተጀመረውን ሰፋ አድርጎ ማኅበረ ቅዱሳን «ስምዓ ጽድቅ» በሚባለው ጋዜጣው ላይ አወጣው። ሃይማኖተ አበውም እንዲዘጋ ጥያቄ አቀረበ። ለአርባ ዓመት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታላቅ ሥፍራ የነበረውን፥ ብዙ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ያፈራ በሃይማኖት ያጸና ማኅበር በአንድ የግል ጋዜጣ ላይ በተጻፈ ጽሑፍና በማኅበረ ቅዱሳን ከሳሽነት እንዲዘጋ ተወሰነበት። በየሳምንቱ ቅዳሜ ይሰበሰብ የነበረውም በሺህ የሚቆጠረውንም ወጣት መናፍቅ ስለሆናችሁ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ሥፍራ የላችሁም ተብለው አውሬ እንዲበላቸው በውጭ ተጣሉ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ጉዳዩን እናጣራ ያለ፥ የእነዚህ ሁሉ ወጣቶች ዕጣ ፋንታ ምንድን ነው ያለ አንድም ሰው አልነበረም። አምላካችን የአንድ ሰው መጥፋት የሚያሳዝነው አምላክ ነው። እንዲያውም ወደዚህ ዓለም እኛን ለማዳን የመጣበትን የአመጣጡን ሁኔታ የገለጠልን የጠፋችውን አንዲት በግ የጠፋውን አንድ ልጅ የጠፋውን አንድ መሐልቅ የጠፋውን አንድ ድሪም በምሳሌ በማቅረብ ነው። ለአንዱ የሚገደው ነውና። ሐዋርያውም ክርስቶስ የሞተለትን ወንድም በምግብ ምክንያት አታሰናክለው በማለት ክርስቶስ ለዚያ

(88) እኒህ አባት ጋዜጣው በወጣ ማግሥት ያለ ምንም ጥያቄ ከሚያገለግሉበት ደብር እንዲወገዱ ተደረገ። እምነት ከህደታቸውን የጠየቀ አጥፍተውም ከሆነ በንስሓ እንዲመለሱ የመከረ ማንም አልነበረም። ማኅበረ ቅዱሳንም አባ እገሌ መናፍቅ ናቸው እያለ ይጽፍ ጀመር። ይህ ሁኔታ ቢያሳዝናቸውና አቤት የሚሉበት ቦታ ቢያጡ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ወስደው ከብዙ እንግልት በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው እንዲመለሱ ተፈርዶላቸዋል። ዛሬ የቤተ ክርስቲያን ልጅ መሆናቸው ስለተረጋገጠ በታላቅ የሥልጣን ማዕረግ ላይ ናቸው።



www.ethiopianorthodox.org

በሌላው ሰው ዓይን ለማይሞላ ወይም በምን ግዴሌሽነት ለሚታይ ግለሰብ የከፈለውን ዋጋ በግልጥ አሳይቶአል። ለዚህ ነው ለአንዱ አርዮስ እኒያን የመሰሉ ቅዱሳን አበው የተሰበሰቡት፣ የለመኑት፣ የመከሩት። በዚያ ወቅት ግን ለነዚያ ለተበተኑት ልጆች ይህን ዕድል የሰጠ፥ እስቲ አንድ ደቂቃ እናነጋግራቸው ያለ የለም ነበር። ከሁሉ የሚያሳዝነው ደግሞ፥ በየሳምንቱ ቅዳሜ በመንበረ ፓትርያርክ ግቢ ውስጥ ይሰበሰብ የነበረው ሕዝብ ሃይማኖተ አበው መዘጋቱን ያወቀው ቅዳሜ ሲመጣ አጥሩ ላይ ከተለጠፈ ወረቀት ነው።

ይህም ሁኔታ ለማኅበረ ቅዱሳን አመቺ ስለሆነለት በተቻለው መጠን የሃይማኖተ አበውን ስም ማጥፋቱን ገፋበት። ትናንት ከትናንት ወዲያ ሀገሪቱ ካፈራቻቸው ፕሮፌሰሮችና ታላላቅ ምሁራን ጋር ሆነው በአባልነት የደከሙበት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ምን እንዳሉ ባላውቅም ማኅበረ ቅዱሳን ግን የሃይማኖተ አበውን ወንጀል ይዘረዝር ገባ። ከወንጀሎቹ አንዱ የዓለም ተማሪዎች ሕብረት ፌዴሬሽን አባል መሆኑ ነበር። አይ አለማወቅ ለንግሥና ሲያበቃ ። የዚህ መጽሐፍ ዓላማ አይደለም እንጂ ብዙ ለማለት ይቻል ነበር። አባልነትን ካነሣን ከአባልነት በላይ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ውስጥ የነበርንበትና መሪዎቹ እየመጡ የሚጎበኙን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ምንድን ነው? በእምነት አንድ ስለሆንን ነው አባል የሆንነው? አይደለም። አንድ በሚያደርጉን ሌሎች ነገሮች አብሮ ለመሥራት ነው እንጂ በእምነት ከሆነ የመጨረሻው የስህተት አጋፋሪዎች የሚገኙት በዚህ ዓለም አቀፍ ድርጅት ውስጥ ነው።

ዘመናዊው «የኤኩሜኒዝም» መንፈስ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ያላቸውን ሕብረት ወደ እምነት





አንድነት እየወሰደው ስለሚገኝ ነገሩ አሳሳቢ ስለሆነ ዛሬ ዛሬ ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት እየለቀቁ ነው። ማኅበረ ቅዱሳኖች ምን እንደሚሉ አላውቅም እንጂ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤትን የሞሉት ግብረ ሰዶማውያን ክርስቶስን የሚክዱና በለዘብተኛ የነገረ መለኮት ክህደት የተመረዙ መሪዎች ናቸው። እንዲያው ስለተነሳ ነው እንጂ ይህን ለማንሳት ቦታው አይደለም። እጅግ ከረከሱ ቡድኖች ጋር የሚደረግን አንድነት ልክ እንደ ሌሎቹ ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ቤተ ክርስቲያናችን ልታስብበት ይገባል። የሆነው ሆኖ ግን ማኅበረ ቅዱሳን ግን ቤተ ክርስቲያናችን አባል በሆነችባቸው የዓለም መድረኮች ላይ አባል ስለሆነ ነበር ሃይማኖተ አበውን ይከሰው የነበረው።

ሃይማኖተ አበው ምንም እንኳን ከመንበረ ፓትርያርክ ግቢ ውስጥ በግፍ ቢባረርም በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙት አባላቱ በሃይማኖታቸው ጸንተው ሁኔታውን በትዕግስት እንዲያሳልፉ አሳሰበ። በሐረር በጅጅጋ በደብረ ብርሃን በባሕር ዳርና በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙት አባላቱም ወደ አባቶች አቤት ማለቱን ተያያዙት።

ማኅበረ ቅዱሳን የሚፈልገው ደግሞ የሃይማኖተ አበውን ስም አጠራር ከምድረ ገጽ አጥፍቶ የራሱን ድርጅት ከዳር እስከ ዳር ማጠናከር ነበር። ይህ አልሆን ሲለው ከዚህ በፊት ተደርጎ በማይታወቅ ሁኔታ ሌላ ነገር ለማድረግ ወሰነ ያም በጉልበት መጠቀም ነበር።

## የድሬዳዋው የወሮበሎች ድብደባና ነፍስ ግድያ

በድሬ ዳዋ ያለው የሃይማኖተ አበው ቅርንጫፍ



www.ethiopianorthodox.org

የተደራጀና በቁጥር በዛ ያሉ አባላት ያሉት ሲሆን ለቤተ ክርስቲያናቸው ቀናኢ የሆኑ በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው ከፍተኛ አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ ናቸው። በግል ጋዜጣ ላይ የወጣውን ጽሑፍ ተከትሎ ዋናው ጽሕፈት ቤት በመዘጋቱና የማኅበሩ ተቃዋሚዎች በየአቅጣጫው በሚያናፍሱት ወሬ አባላቱ በመደናገጣቸው አባላቱን ለማረጋጋት ቅርንጫፍ ማኅበሩ ነሐሴ 21 ቀን 1986 ዓ. ም. የእመቤታችን ዕለት ታላቅ ጉባኤ ለማድረግ አባላቶቹን ጠራ።

ሁኔታው የማኅበሩን መበተን ለማየት የሚጠባበቁትን ስላናደዳቸው ጉባኤው እንዳይካሄድ ለክልሉ ጊዜያዊ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት አቀረቡ። በተለይም አቀራረባቸው የዛቻና የዱላ ስለነበረ የአስተዳደር ጽሕፈት ቤቱ ጥያቄያቸውን ውድቅ ከማድረጉም በላይ ጥያቄውን ባቀረቡት ግለሰቦች አማካይነት አስተባባሪነት አንዳች ጉዳት ቢደርስ በኃላፊነት የሚጠየቁ እንደሆኑ አስጠነቀቃቸው። ሆኖም የአስተዳደር ጽሕፈት ቤት ማስጠንቀቂያ ወደ ጎን በመተውና ጥቂት የዋህ ምእመናን ሃይማኖትህ ተወረረብህ በማለት እንዲሁም ሥራ ፈት የሆኑ ወመኔዎችን በገንዘብ በማባበል አሰልፈው የሃይማኖተ አበው ተማሪዎች ማኅበር አባላት ወደ ተሰበሰቡበት አዳራሽ መጥተው አዳራሹን ከበቡት።

ዕለቱ የእመቤታችን ቀን ስለሆነ የጉባኤው መክፈቻ «ወትቀውም ንግሥት በየማንከ ንግስቲቱ በቀኝህ ትቆማለች» የሚለው ምስባክ ተሰብኮና ጸሎተ ወንጌል ደርሶ የዕለቱ መምህር የዕለቱን ወንጌል ማስተማር ሲጀምሩ፤ የቀጠሩአቸው ወሮበሎች አዳራሹን ወረሩት።[89]

(89) *ወሮበሎቹ የመጡት የፈለጋችሁትን መዝረፍ ትችላላችሁ ተብለው ነው። በወረራውም ወቅት ከሴቶች ልጆች ጆሮ እየበጠሱና ቆዳቸውን እየዘለዘሉ ብዙ ወርቅ ወስደዋል።*





ዱላ ጩቤና ሌላም የጦር መሳሪያ ይዘው ስለ ነበረና በቁጥርም የሚበዙ ስለነበሩ ከፍተኛ ጉዳት አደረሱ፤ በድብደባውም ነፍስ ጡሮች የተጎዱ ሲሆን በተለይም ለመውለድ ሦስት ቀን የቀራት ልጅ «ስለ እመ ብርሃን ልወልድ ሳምንቴ ገብቶአል» ብላ ብትለምናቸውም ክፉኛ ደብድበዋት ሆስፒታል ሄዳ በከፍተኛ ችግር ልጁ ወጣ። ሦስት ልጆች አካለ ጎዶሎ የሆኑ ሲሆን አንድ ወንድማችንን ገደሉት። በቦታው የነበረውንም ግምቱ መቶ ሺህ ብር የሚያወጣ የመንግሥት ንብረት አጠፉ።

ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ በጊዜው ለጵጵስና እየተዘጋጁ የነበሩትና በስተኋላም የሐረርን ሰንበት ትምህርት ቤት ያዘጉት መምህር ብርሃነ ሥላሴ በኋላም እዚህ አሜሪካ ባሉት ታላቁ አባት በብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ምትክ ዜና ማርቆስ የተባሉት በእነዚህ ልጆች ተንኮል ውስጥ መግባታቸው ነው።[90]

በጊዜው የጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ የነበረው አቶ መርስዔ ኃዘን አበበ ለአቡነ ጳውሎስ ባቀረበው ሪፖርት «የፀቡ ምክንያት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በማለት ራሳቸውን በመጥራታቸው በቤተ ክርስቲያን ስም መናፍቃን ሊነግዱ አይችሉም በሚል ነው» ካለ በኋላ ስለ ሃይማኖተ አበውም ሲናገር «ራሱን ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በማለት የሚጠራው አካል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አድባራት ውስጥ ባሉት ሰንበት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በቡድን ተዳርጅተው ከቤተ ክርስቲያናችን እምነትና ሥርዓት ውጭ እየተንቀሳቀሱ በመገኘታቸው

(90) *አንዳንድ ሰዎች እንደሚናገሩት ከሆነ እኝሁ ሰው ከዚህ በፊትም በዚህ ዓይነት ሁኔታ ለንጹሐን ሰዎች ሞት ምክንያት ሆነው ነበር ይባላል። እኛ ግን እውነቱን ለሚያውቅ ለእግዚአብሔር ሰጥተነዋል።*



www.ethiopianorthodox.org

በተለያዩ ሰንበት ትምህርት ቤቶች እንዲታገዱ መደረጉ ተገልጦአል» ይላል። ከሁሉ የሚያስቀው ደግሞ ማኅበሩ ስብሰባውን የጠራው «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተሐድሶ ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር» በሚል ስም ነው ማለቱ ነው።

ጋዜጠኛው መርስዔ ኀዘን አበበም ጉዳዩ የቤተ ክርስቲያን ሐፍረት መሆኑን ዘንግቶት በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ የሰበካ ጉባኤ ስብሰባ ላይ ለገዳዮቹ ሽልማት እንዲሰጥ አደረገ።

ይህ መቼም በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን አዲስ ክስተት ነበር። መግደል ንስሐ ያስገባል ያሳዝናል ከሹመት ያሽራል እንጂ አያሽልምም። የወደመውን ንብረት እንዲከፍል ቤተ ክህነት ስለተጠየቀ ኃላፊነት ወስዶ ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ አድርጎ ከፈለ። በድሬዳዋ የተከናወነው የወረበሎች ድርጊት በድሬዳዋ የነበሩትን ወጣቶች ቅስም ሰበረ ። በገዛ ወገናቸው የተደበደቡም በደም እንደጨቀዩ በዚያው አምርረው እንደወጡ ቀሩ።

<u>ከበስተጀርባው ያለው ማነው?</u>

በአሁኑ ወቅት በሚወጡት የማኅበረ ቅዱሳንም ሆነ የቤተ ክርስቲያናችን ልሳን በሆነው በዜና ቤተ ክርስቲያን ላይ ተመሳሳይ የሆነ ኃይለ ቃል እናገኛለን። ዜና ቤተ ክርስቲያን «የስልሳ ዓመቱ አረጋዊ በአሥር ዓመቱ ሕፃን ተሰደበ» በሚል ባወጣው ጽሑፍ ላይ ማኅበረ ቅዱሳንን በአዲስ ስም ያዋቀሩት ወይም አሁን በዓላማ የሚጠቀሙበት ቀድሞ «አጠቃላይ ጉባኤ» ይባል የነበረው ቡድን እንደሆነ ይጽፋል። ይህ እውነት ከሆነ «አጠቃላይ ጉባኤ» ሃይማኖተ አበውን በማዘጋት ሁለት ጊዜ ተሳክቶለታል ማለት ነው። ቀድሞ ሀገሪቱ በማርክሲስታዊ ርዕዮተ ዓለም ስትመራ በነበረበት ወቅት «ሃይማኖተ አበው የፖለቲከኞች መሰብሰቢያ ነው» ብሎ በፖለቲካ





ከማስመታት ጀምሮ በስተመጨረሻም እንዲዘጋ ያደረገው ይህ ራሱን «የወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበራት አጠቃላይ ጉባኤ» እያለ ይጠራ የነበረው ማኅበር ነው።

እዚህ ላይ ከሁሉም የሚገርመው ይህ «አጠቃላይ ጉባኤ» የሚባለው ማኅበር በ1973 ዓ. ም. ተመሳሳይ የሆነ ድብደባ በመንበረ ፓትርያርክ አዳራሽ ተሰብስበው በነበሩ የሃይማኖተ አበው ተማሪዎች ላይ በመፈጸም አካል የማጉደልና ንብረት የማውደም ወንጀል በመፈጸሙ በወቅቱ የነበሩት አባቶች «አጠቃላይ ጉባኤን» ከቤተ ክርስቲያን መድረክ አግደውት ነበር። ለነገሩ የሃይማኖተ አበው ተማሪዎችን ከማስደብደብ በላይ ይህ «አጠቃላይ ጉባኤ» ቤተ ክርስቲያኒቱን የመጠቅለል ዓላማም ስለነበረው ነው ከቤተ ክርስቲያኒቱ መድረክ ያስወገደው። በ1986 ዓ. ም. አጠቃላይ ጉባኤ በአዲሱ ስሙ ማኅበረ ቅዱሳን ተብሎ ግድያ ሲፈጽም የተደረገው ነገር ቢኖር ገዳዮቹን መሾምና መሸለም ብቻ ሳይሆን፥ የቤተ ክርስቲያን አደባባዮችን ለገዳዮች መስጠትም ጭምር ነበር።

በቤተ ክርስቲያናችን ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ እጅግ አሳፋሪ የሆኑ ድርጊቶች ተከናውነዋል። ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ሠላሳ ዓመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ አንደኛውን ፓትርያርክ አስገድለናል። አንደኛውን ፓትርያርክ ለስደት ዳርገናል። በአሁኑ ወቅትም ሁለት ፓትርያሪኮች በሕይወት ያሉባት ቤተ ክርስቲያን ሆናለች። ይህ የእያንዳንዳችን የታሪክ ሸክም ወይም መርገም ነው። ከፖለቲካው ለውጥና ነውጥ ጋር እነዚህን ነገሮች በማድረግ በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሰው ይህ አጠቃላይ ጉባኤ የሚባለው ነው። ይህን ደግሞ አሁን ያሉት አባቶች



www.ethiopianorthodox.org

በሙሉ ያውቁታል። ጉዳዩ በአብዛኛው ተጨባጭ ከሆነ ማስረጃ ጋር ስለማይነሣ ተሸፋፍኖ ይቀራል። የታሪክ ጸሐፊዎችና የቤተ ክርስቲያኑዋ ልጆች ይህንን ታሪክ እውነቱንና ሐሰቱን የመመርመር ኃላፊነት አለብን። አጠቃላይ ጉባኤ የሚባለው ማነው? መሪዎቹ እነማን ነበሩ? አሁን የት ይገኛሉ? በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ግድያ ላይ ተሳታፊነታቸው ምን ያህል ነበረ? ፓትርያርኩን አቡነ ቴዎፍሎስን ይቃወሙ የነበሩት ለምንድን ነው? በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ላይ የተቃውሞ እንቅስቃሴውን ያደርጉ የነበሩት አሁንም በአቡነ ጳውሎስ ላይ ውስጥ ለውስጥ የተቃውሞ እንቅስቃሴ የሚያደርጉት ምን ፈልገው ነው? ማኅበረ ቅዱሳንን እንመራለን ከሚሉት ወጣቶች ጋር ምን ግንኙነት አላቸው? ለሚሉትና ለሌሎችም ጥያቄዎች የቅርቡን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እናጠናለን የምንል በሚገባ ማጥናት አለብን። አለበለዚያ መንግሥት በተለዋወጠ ቁጥር እያደባ መንበሩን ካልጨበጥኩ እያለ በይፋ ጦርነት የሚያውጀው አካል የቤተ ክርስቲያን ልጆችን በሙሉ እንዳይጨርስ ያሰጋል።

## በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተጀመረው ዘመቻ።

ማኅበረ ቅዱሳን ሃይማኖተ አበውን ካስዘጋና ድሬዳዋን ካስደበደበ በኋላ ማኅበረ ቅዱሳን መንገዴ ላይ ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ ያላቸውንና በአባልነት ወደ እርሱ ጎራ ለመግባት እምቢ ያሉትን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን «ተሐድሶዎች» ናቸው በማለት ስማቸውን በዝርዝር በጋዜጣ ላይ ማውጣት የጀመረው ውሎ ሳያድር ነው። አገልጋዮች የሆኑ ካህናትንም ከቤተ ክርስቲያን እንዲባረሩ የየሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጆችንና ሊቃነ ጳጳሳትን መመወትወት ጀመረ። በጥቂት ጊዜ ውስጥ ማንም የማያውቀውና እዚህ ግባ





የማይባለውን በፕሮቴስታንቶች የተጀመረውን ተሐድሶ ተብየ እንቅስቃሴ ማኅበረ ቅዱሳን ለመላው ኢትዮጵያ ከማስተዋወቁም በላይ የየዕለቱ መነጋገሪያ አደረገው። በተለይም የማኅበረ ቅዱሳን መሪዎች ጳጳሳቱም አሉበት በማለት መናገር ስለ ጀመሩ ሕዝበ ክርስቲያኑ በሙሉ ጳጳሳት ሁሉ ያሉበት ይህ ተሐድሶ የሚሉት ምንድን ነው ማለት ጀመረ።(91)

ሁኔታው በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ታይቶና ተሰምቶ በማይታይ ሁኔታ በ«ጫካ ሕግ» የቤተ ክርስቲያኒቱ ሊቃውንት የተረገጡበት፤ በአላዋቂዎች የተዋረዱበት ነው። ማኅበረ ቅዱሳን በነዚያ ወቅቶች ያከናወናቸው ድርጊቶች ሁለት ወቅቶችን ያስታውሱኛል። አንደኛው ቁስጥንጥንያ ውስጥ የተደረገን ነገር ሲሆን ሌላው ካምቦዲያ ውስጥ የተደረገ ነው።

ጊዜው እግዚአብሔር ያስነሣው ታላቁ ፓትርያርክና የሰባክያን መሥፍን ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ መላዋን ቁስጥንጥንያን በትምህርቱ ይገስጽ ይመክር የነበረበት ወቅት ነው። ትምህርቱ የቁስጥንጥንያን ቤተ መንግሥት ሰዎች ቢጎረብጣቸው፤ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የትምህርት ጸዳል ያገለላቸውን ጥቂት ወሮበሎች አስነሡበት። ከእስክንድርያ ደግሞ የሥልጣን ጥም ያናወዛቸውን ሰዎች አመጡበት። ሌላው ቀርቶ መናፍቃንን በትምህርቱ ይመክት የነበረውን ኤጲፋንዮስን እስኪያሳስቱ ድረስ፥ «ዮሐንስ አፈወርቅ መናፍቅ ሆኗል ድረስልን» ብለው አሳስተው አመጡት።

*(91) የማኅበረ ቅዱሳን የአመራር አባላት በሚያዘጋጁዋቸው መጽሔቶቻቸው ላይ በመናፍቅነት ከሚያነሱዋቸው መካከል በዛሬዋ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለሃይማኖታችን ምስክር ሆነው በሲኖዶስ ሊጠየቁ ከሚችሉ በጣት ከሚቆጠሩ ሊቃውንት መካከል ያሉ ሊቃነ ጳጳሳትም ጭምር ናቸው። በተለያየ መንገድ አራት ሊቃነ ጳጳሳትን መናፍቅ ናቸው ብሎ ማኅበረ ቅዱሳን ከሷቸዋል። አንዳንዶቹንም የከሰሳቸው ወደ ሀገረ ስብከቶቻቸው እናስገባም ስላሉ ነው።*



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ግን ነገሩን አይቶ ቀስ ብሎ ወደ ሀገሩ ወደ ቆፕሮስ ሲመለስ መንገድ ላይ አረፈ። ሌሎቹ ግን ያን ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ዓይን መናፍቅ ነው ብለው ፈረዱበት። ከገዛ መንበሩ አጋዙት፤ አንገላቱት። በስደት ሳለም ከሕመምና ከእንግልት የተነሳ አረፈ። የሚገርመው ግን መናፍቅ ነው ብለው የፈረዱበትና ያወገዙት ቤተ ክርስቲያኒቱን የማያውቁ ጊዜ ያነሳቸው ወሮበሎች መሆናቸው ነው። አለማወቅ አዋቂነት የሆነበት አዋቂነት ወንጀል የሆነበት ዘመን ነበርና።

ሌላው በዘመናችን የተደረገ ነው። ካምቦዲያ ውስጥ ኬሚን ሩዥ የተባለው ኮሚኒስታዊ ድርጅት ሥልጣኑን ይዞ ከአንድ ሚሊየን በላይ የሆኑ የገዛ ወገኖቹን በገደለበት ወቅት ነው። በዚያ ወቅት በሀገሪቱ እየተፈለጉና እየታደኑ ይገደሉ የነበሩት አሉ የሚባሉት የሀገሪቱ ምሑራን ነበሩ። በዚያ ወቅት በካምቦዲያ መማር ወንጀል ነበር። ለመማር መጣጣር የሚያስቀጣ ነበር። የነሞርዛትን ረቂቅ ሙዚቃ ያስማምሩ የነበሩ እጆች የምዕራባውያንን ባሕል ልታመጡ ነው ተብለው ተቆረጡ። የታሪክ መዛግብትን የሚመረምሩ ዓይኖች በአብዮቱ ላይ ታሴራላችሁ ተብለው እንዲጠፉ ተደረጉ። ሊቃውንቱ በቁማቸው ተቀበሩ፤ ገደል ተወረወሩ። ማወቅ ወንጀል የሆነበት ወቅት ነበርና።

ያ ጊዜ ተመልሶ የመጣ የመሰለበት ወቅት አሁን በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ማኅበረ ቅዱሳን አምጥቶልናል። ሊቃውንቱን በመጀመሪያ የመናፍቅነት ጥላሸት ማስቀባት፤ ቢቻል የሆነ የሚከሰስበት ነገር መፈለግ፤ ቤተ ክርስቲያን መናፍቅ ትበለውም አትበለውም በእነርሱ ጥቁር መዝገብ መናፍቅ እንደሆነ ማወጅ፣ ማሳደምና እንዲባረር ማድረግ።





ከሳሽ ማኅበረ ቅዱሳን፣ ምስክር ማኅበረ ቅዱሳን፣ ፈራጅ ማኅበረ ቅዱሳን፥ ሕግ አስፈጻሚ ማኅበረ ቅዱሳን። ለዚህ አሳዛኝ ሁኔታ ምሳሌ የሚሆነን በአንድ ወቅት ማኅበሩ በሚያወጣው ጋዜጣ ላይ የቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ የቴዎሎጂ ኮሌጅን ከምክትል ዲኑ ጀምሮ የኮሌጁን ዋና ጸሐፊ፤ በኮሌጁ የአዲስ ኪዳንና የግእዝ መምህር፤ በኮሌጁ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መምህር፤ የኮሌጁ ሥራ መሪና የእንግሊዘኛ መምህር እና ስድስት ተማሪዎችን ጨምሮ ተሐድሶዎች ናቸው ብሎ አውጥቶአል። ይህም የኮሌጁን ሊቀ ጳጳስ ጨምሮ ወደ ቅድስት ሥላሴ የተዛወሩ ሦስት አስተማሪዎችን ተሐድሶ ማለቱን ሳይጨምር ነው። ይህ ጸሐፊ እስከሚያስታውሰው ኮሌጁ ያሉት አስተማሪዎች ከስምንት እስከ አሥር ቢሆኑ ነው። ስለሆነም በማኅበረ ቅዱሳን ሚዛን ኮሌጁ ካሉት አስተማሪዎች ዘጠና በመቶዎቹ መናፍቃን ነበሩ ማለት ነው።

ይህን ታሪክ ስጽፍ በስሜታዊነት ቢሆን አትፍረዱብኝ። ልቤ እየደማ ነውና የምጽፈው። ወደማን አቤት ይባላል? ወደ ማንስ ይኬዳል? እግዚአብሔር እንዲፈርድ ከመጥራት ሌላ ምን ይባላል?

ለመሆኑ የእነዚህ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ስም አደባባይ የወጣው ቤተ ክርስቲያን መክራበት ነው? ለምናቸው አልቅሳላቸው እባካችሁ ልጆቼ ስህተት አግኝቼባችሃለሁና ተመለሱ ብላቸው ነው? በፍጹም! በጭራሽ! ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት እንኳን የእነዚህን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የተከሰሱበትን ምክንያት አያውቁም። ወንጀሉን የሚያነቡት ከማኅበረ ቅዱሳን ጋዜጣ ላይ ነው። ከዚያም በየቤታቸው እነዚህን ካላባረራችሁልን የሚል ማስፈራሪያ ይመጣል።



www.ethiopianorthodox.org

ለመሆኑ ይህ ሁሉ እወጃ «ጳጳሳቱ ተሐድሶ ሆኑ» ቤተ ክርስቲያኒቱ ከነበራት ኮሌጅ ውስጥ ከዲኑ ጀምሮ እስከ አስተማሪዎቹ ድረስ ተሀድሶ ሆነዋል ብሎ ማወጅ ማንን ነው የሚጠቅመው? ለማነው የልብ ልብ የሚሰጠው? የቤታችንን ጉድ ጓዳችን ይዘን ድብቅ አድርገን ተዋቅሰናል? ተላቅሰናል? እረ ቤተ ክርስቲያን ትምክርበት። እረ ለቤተ ክርስቲያን የምታስቡ ቆም ብለን እንወያይበት። የበደለ ቢኖር እንኳን አሁን ማኅበረ ቅዱሳን በሚያደርገው ዘመቻ ንስሓ ይገባል ወይ? ይህ እኮ በሕዝብ ላይ የተነጣጠረ ጠላትነት ነው። ለመሆኑ ይህን ያህል ሰው የለንም ወይ? ይህን ያህል አገር ተፈትቶአል ወይ?

ለነገሩ ቤተ ክርስቲያኒቱ ባዘጋጀችው ትምህርት ቤቶች ያላለፉ እነዚህ ወጣኒያን፣ ቅድስት ሥላሴ ኮሌጅ ገብቼ እነዚያን ሊቃውንት ላስተምር ሲሉ፣ ቴዎሎጂያን ሆነው በምስጥረ ሥጋዌ ላይ መጽሐፍ ሲጽፉ፣ መምህር እየተባባሉ እርስ በእርሳቸው ሲሞከሻሹ፣ ጎጃም ቅባት ሆኗልና እንዳኘው ብለው የጎጃም ሊቃውንትችን ሰብስበው ሲውሉ ከዚህ የባሰ የሀገር መፈታት ምን አለ?(92) እረ ለመሆኑ «የቅባት ማቅለጫዎች» የጎጃም ሊቋውንት በስመ ቅባት ማንም ወፍ ዘራሽ ሲሳለቅባቸው ምን አሉ ይሆን? የሊቁ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ፣ የሰማዕቱ የቴዎፍሎስ፣ የሊቁ የድሜጥሮስ አጽም እንዴት አለ ይሆን? ስንቱ ሊቅ በጥንቃቄ የነገረ መለኮት ኃይለ ቃላትን ሳያማታ ምሥጢር ሳያፋልስ ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጋር በጥንቃቄ እየመከረበት ሲመልስ የነበረውን ጉዳይ እነዚህ ወጣቶች የሚመልሱት ቤተ ክርስቲያኒቱ ሊቃውንት አጥታ ነው?

---

*«ጉባኤው ሕዝቡን ከቅብአት ነን ባዮች ውዥንብር የታደገ ነው።» ስምዓ ጽድቅ ጋዜጣ 10ኛ ዓመት ቁ. 6 መጋቢት 1995። ገጽ 6።*





ማኅበረ ቅዱሳን ፍላጎቱ አውድማው እንዲህ እንዲሆንለት ነው። የትናንቶቹ አቶዎች ዛሬ ቄስ ተብለው፣ ከዚያም አልፈው ራሳቸውን መምህር አሰኝተው፣ በድግሪ ያጡትን ገንዘብ በቤተ ክርስቲያን፣ በፖለቲካ ያጡትን ሥልጣን በቤተ ክርስቲያን ጓሮ በኩል ለማግኘት እንዲችሉ ቤተ ክርስቲያን ወልዳ ያሳደገቻቸውን ገለል እንዲሉ ማድረግ ነበረባቸው። እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ልጆች አንዳንዶቹ በማኅበሩ ግፊት ከቤተ ክርስቲያን ከተባረሩ በኋላ በሠሩት ሥራ ተጸጽተው ቤተ ክርስቲያናቸውን ለበደሉት በደል ለሰደቧት ስድብ ለሌሎች መሳሳት ምክንያት ለመሆናቸው በሙሉ ንስሓ ገብተው ተጸጽተው ቤተ ክርስቲያናቸውን ቢጠይቁ ያ ለማኅበረ ቅዱሳን የሞት ሞት ነው። ምክንያቱም ለእነርሱ የእነዚህ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያን አደባባዮች መታየት ለሕልውናቸው አስጊ ነው። ብሩ፣ ፎቅ ቤት መሥራቱ ሊቀር ነው። እውነት ሊገለጥ ነው። እንዲህ ያለ አስተማሪ የት አፍናችሁ አስቀምጣችሁ ነበር ሊባሉ ነው። ስለዚህ ከዚህ ይልቅ እንደምንም ብሎ ማሳደድ አውሬ እንዲበላው ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤ ሲጠፉላቸው ደግሞ በአውሬ የተበሉት ራሳቸው ናቸው፤ ወደ ጴንጤ የሄዱት ራሳቸው ናቸው ብሎ ማላዘን ይሄ ነው ልማዳቸው። በ«ወልድ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው» የሚለውን ለውጠው «በማኅበረ ቅዱሳን የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው» ብለው ያመኑ ይመስል ዛሬ በማኅበረ ቅዱሳን እስካመኑ ድረስ ከሃዲ ቢሆን ቤተ ክርስቲያንን የሚዘርፍ ቢሆን ዘማዊ ቢሆን ግድ የለም። የማኅበሩን ኅልውና አይነካምና።

<u>በሰንበት ትምህርት ቤቶች ላይ የተከፈተው ዘመቻ</u>

ማኅበረ ቅዱሳን ሃይማኖተ አበው ከተዘጋለትና ሥልጣኑን ካደላደለ በኋላ ተሐድሶ የሚለውን ቃል



www.ethiopianorthodox.org

አስፍቶ ማናቸውም በቅድስት ሥላሴ የሰንበት ትምህርት ቤት የአዘማመር ስልት የሚዘምሩ በሙሉ ተሐድሶ ናቸው በማለት አዲስ አንድምታ አበጀለት። መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ከግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ በስጦታ በተሰጠው ኦርጋንና በግርማዊነታቸው ትእዛዝ በሠለጠኑ የቤተ ክርስቲያኑዋ ልጆች በነ ዶክተር ኢሳይያስ ዓለሜነህ በተዘጋጀው መዝሙር የሚጠቀም፤ ለመጀመሪያ ጊዜ በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ሴቶች ቆመው የዘመሩበት ቦታ ነው።

የቅድስት ሥላሴ መዝሙራት መንፈስን የሚመስጡ የግጥማቸውም ስልት ሥርዓትን የጠበቀ ካቴድራሉ ባሉት ምሑራን እየተመረመረ የሚወጡ ስለነበር በአብዛኛው ወጣቶች ዘንድ ተወዳጅነት ነበራቸው። በዚህም ምክንያት ለብዙ ወጣቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት ከቤተ ክርስቲያናቸው እምነትና ሥርዓት ጋር መተዋወቅ ምክንያት ሆኖአቸው ነበር።

እንግዲህ ማኅበረ ቅዱሳን በጊዜው ባገኘው ኃይል ተጠቅሞ የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴን የአዘማመር ስልት ይከተሉ የነበሩትንና በአዲስ አበባ በልደታ ለማርያም፣ በቅድስት ሥላሴ፣ በሳሪስ አቦ፣ በጴጥሮስ ወጳውሎስ ሰንበት ትምህርት ቤቶች፤ በሐረር በስድስቱም አብያተ ክርስቲያናት፤ በአማሬሳ፣ በሒርና በአሰበ ተፈሪ፣ በድሬዳዋ በቅድስት ማርያም ፣ በጊዮርጊስ፤ በደብረ ማርቆስ፣ በናዝሬት የሚገኙ የሰንበት ትምህርት ቤቶች በሙሉ እንዲዘጉ አስደረገ። ወጣቶቹንም ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገቡና በቤተ ክርስቲያን እንዳይሰበሰቡ አሳገደ።

በአሁኑ ወቅት ከቤተ ክርስቲያን ስለተባረሩ ወጣቶች ማኅበረ ቅዱሳን የሚያወጣቸው ዘገባዎች ፍጹም ሐሰትን የተመሉ ናቸው። ስለ እነዚህ ልጆች ያለው





እውነታ የሚከተለው ነው፥

1ኛ) ከቤተ ክርስቲያን እንዲባረሩ አቤቱታም ክስም ለደብር አስተዳዳሪዎችም ሆነ ለሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጆች ያቀርብ የነበረው ማኅበረ ቅዱሳን ነው።

2ኛ) እነዚህ ልጆች ከመባረራቸው በፊት በኦርጋን የቅድስት ሥላሴን መዝሙር አትዘምሩ ከሚል ውጪ የተከሰሱበት የክህደት ትምህርት የለም። በየትኛውም ሥፍራ ጉዳያቸው በስብሰባ አልታየም።

3ኛ) ከቤተ ክርስቲያን ከተባረሩ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገቡ፣ እንዳያስቀድሱ፣ ቢወልዱ ክርስትና እንዳያስነሱ፣ በማኅበረ ቅዱሳን አስተባባሪዎች ስለ ታገዱ ትንሽ ጊዜ በአዳራሽ በየቤታቸው እየተሰባሰቡ እርስ በእርሳቸው ቢጽናኑም፥ ከማኅበራዊ ኑሮ ግፊት ከፕሮቴስታንቱ ዓለም ማባበልና ከማኅበረ ቅዱሳን የጥላቻና ደብድቡልኝ አባሩልኝ የሚል የጥላቻ ጩኸት በስተቀር በፍቅር የሚመልሳቸው ስላላገኙ ጠፍተው የቀሩ ናቸው። አንዳንዶቹም የከዳቻቸው፣ ደጅ የወረወረቻቸው እናት ቤተ ክርስቲያናቸው መስላቸው የግለሰቦችን ኃጢአት እና የቤተ ክርስቲያንን ቅድስና መለየት አቅቷቸው የቤተ ክርስቲያናችን ጠላቶች ሆኑ። አንዳንዶችም አጥፍተን ከሆነ ይቅርታ ይደረግልን ቢሉ ማኅበረ ቅዱሳን ግብረ አበሮቹን አሰማርቶ አስደበደባቸው። አንዳንዶቹንም በፖለቲካ አስከሰሰ፤ አንዳንዶቹንም አስገደለ። በድሬዳዋ የሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር አባል የነበረውና የሀገር ልብሱን ለብሶ ጭራውን ይዞ የእመቤታችንን በዓል አከብራለሁ ብሎ ወጥቶ ተሐድሶ ነው ተብሎ በማኅበረ ቅዱሳን አባላት የተገደለው ወንድማችን አዳም ከእነዚህ ስማቸውን ከማላውቃቸው አእላፋት ወጣቶች አንዱ ነው። የነዚህን ደም የሚጠየቀው ማን ይሆን? ይህ ሁሉ ሲሆን ወደ የት እንደሚሄዱ ግራ የገባቸውን ወጣቶች በግልጥ ያገኘው የፕሮቴስታንቱ ዓለም ወደ የራሱ ጎራ



www.ethiopianorthodox.org

በመውሰድ ኦርቶዶክስ ተሐድሶ ናችሁ ስለዚህ ነው ያባረሩአችሁ እያለ መስበክ ጀመረ። በአንዳንድ ከተሞችም ከየቤተ ክርስቲያኑ በማኅበረ ቅዱሳን የተባረሩትና ሰብሳቢ አጥተው የተበተኑትን ወጣቶች ለመንጠቅ የፕሮቴስታንት ድርጅቶች እርስ በእርሳቸው ከፍተኛና የመረረ ግጭት ውስጥ ገብተው ነበር። በተለይም ደግሞ ዳግመኛ ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው እንዳይመለሱ ዳግም በማጥመቅ የእነርሱ ታማኝ ተከታዮች በማድረግ ለዘላለም ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው ለይተዋቸዋል።

## <u>ሐረር</u>

ሐረር ጥንታውያን ከሚባሉት የኢትዮጵያ ከተሞች አንዷ ከመሆኑዋ በላይ እንደ አሜሪካዋ ቦስተን ለብዙ ሥልጣኔዎች የመጀመሪያዋ በር ከፋችም ናት። የቀድሞው ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም የተወለዱበት አካባቢ እንደመሆኑ መጠን በዚያ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጡ ነበር። በከተማዋውም የሚመደቡት የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንትና ሊቃነ ጳጳሳት በእውቀታቸውና በትምህርታቸው ከፍተኛ ተደናቂነት ያላቸው ነበሩ። ለዚህም ምስክር ይሆን ዘንድ በሊቀ ጳጳስነት ሀገረ ስብከቱን የመሩት ኢትዮጵያዊ ሰማእት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን መጥቀስ ይቻላል። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ታላላቅ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን ያፈራ የካህናት ማሰልጠኛ አቋቋመው ካህናትን ከማስተማራቸውም በላይ ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት ካላቸው ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ ለወጣቱ ሃይማኖተ አበውን በከፍተኛ ደረጃ ከማጠናከራቸውም በላይ ምእመናንን ካህናትን በአንድነት ያሰባሰበና ዐቢይ ተልእኮውም ወንጌልን በአካባቢው ማስፋፋት የሆነ «ከሳቴ ብርሃን» የሚል የወንጌል ማኅበር አቋቋመው ነበር። ይህ ማኅበር





በአደረጃጀቱ በጊዜው ተወዳዳሪ የሌለው ሲሆን የግሉ የሆነ ማተሚያ ቤት ባለ ቤትም ነበረ። ነገር ግን በነበረው የመንግሥት ለውጥ ምክንያት ማተሚያ ቤቱም ሲወረስ ማኅበሩም ፈርሶ ባለቤት አልባ ሆነ።

ከለውጡ በኋላ የአገር መሪዎች በተከተሉት ማርክሲስታዊ ርዕዮት ምክንያት ትውልዱ ከቤተ እግዚአብሔር ቢሸሽም ያን የቀደመውን የወንጌል እንቅስቃሴ እንዲቀጥል ለማድረግ ሌት ተቀን የሚለፉ የቤተ ክርስቲያን አባቶች አልጠፉም ነበር። ከእነዚህም አንዱ የአደሬ ጢቆ መካነ ሥላሴ ደብር አስተዳዳሪ የሆኑት መላከ ሰላም ጴጥሮስ አዘነ ናቸው። ሌት ተቀን ለጸሎትና ለአገልግሎት የማይደክሙት እንደ መላእክት ስሉጥ የሆኑት ኦርቶዶክሳዊው ሊቅ መልአከ ሰላም ጴጥሮስ አዘነ እያንዳንዱን የቤተ ክርስቲያናችንን ሥርዓት በተግባር የሚያሳዩ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን አባት ናቸው። ተንባላት በከበቡአት ምድር ሰዓታቱን ቆሞ ስብሐተ ነግሁን አድርሶ ጸመ ድጓውን አድርሶ፤ ውሎ ቅዳሴው አስቀድሶ ማታ ምሕላውን አድርሶ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቹን አስተምሮ ውዳሴ ማሪያምን በዜማ አድርሶ ለጥቂት ሰዓታት ተኝቶ እንደገና ሰዓታት ለመቆም የሚነሳው ስንቱ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነው? መልአከ ሰላም ጴጥሮስ እንዲህ ያሉ ታላቅ አባት ናቸው። እኒህ አባት ወጣቱ ሃይማኖቱን አጽንቶ እንዲይዝና ከሌሎች የእምነት ክፍሎች ተፅዕኖ የጸዳ እንዲሆን ከፍተኛ ትግል ያደርጉ ነበር። አገልግሎታቸውም ፍሬ አፍርቶ በተለይ ከ1980 ዓ. ም. ጀምሮ ወጣቶች በብዛት በአፀደ ቤተ ክርስቲያን መሰብሰብ ጀመሩ። የእርሳቸውንም አርአያነት ተከትለው በተለይ ወጣቶች ማታ በሠርክ ጸሎት ላይ፥ ጠዋት በኪዳን ቤተ ክርስቲያኒቱን አጣበው «መሐረነ አብ» ሲሉ፥ መቋሚያ ሲያቀብሉ ቤተ ክርስቲያን ሲያጸዱ



www.ethiopianorthodox.org

መመልከት ምንኛ የሚያስደስት ነበር።

ይህ በመካነ ሥላሴ የተጀመረው ወደ አባቶች ትምህርት ወደ አፀደ ቤተ ክርስቲያን የመመለስ እንቅስቃሴ የበለጠ ተጠናክሮ በሌሎችም አድባራት ቀጠለ። በመሆኑም በደብረ ገነት መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን፣ በቅዱስ ሚካኤል፣ በተክለ ሃይማኖት፣ በአቦከር ደብረ ጸሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስና በስተኋላ በተተከለው በቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው አባቶች እና እናቶችና ይሰበሰቡ ጀመር።

እዚህ ላይ ይህ በሐረር ከተማ የነበረው እንቅስቃሴ እጅግ ከሚያስቆጣቸውና ከሚያናድዳቸው መካከል በዚያ አካባቢ የሚገኙ ፕሮቴስታንቶች ነበሩ። ምክንያቱም ወደ እነርሱ አዳራሽ ማንም ሰው አይሄድም ነበር። ምእመኑ ሁሉ ለእነርሱ በሚመልሰው መልስ በሚገባ የታጠቀ በቤተ ክርስቲያኑ አገልግሎት የሚረካ ነበር። እንዲህ እንደ አሁኑ በየቦታው የማታ ጉባኤ ሳይጀመር ሐረር በየቤተ ክርስቲያኑ ታላቅ ጉባኤ በየቀኑ ይደረግ ነበር። ይህም ፕሮቴስታንቱን ዓለም ስላናደደ የማይናገሩት ነገር አልነበረም።

ከተለመዱት ንግግራቸው አንዱ «እንዲህ በደንብ የሚያስተምሩት የኛ ተማሪዎች ስለሆኑ ነው» «እግዚአብሔር ሁሉንም ማርኮ ሁሉንም ለእኛ ይሰጠናል» «ኦርቶዶክሶች እንዲህ የሆኑት እኛ ስለ ጸለይንላቸው ነው» «አስተማሪዎቻቸው የእኛ አባላት ናቸው» እና እንዲህ የመሳሰሉት ነበሩ። ይህም መምህራኑን ለማስመታትና ጉባኤውን ለመበተን ነበር። ባሳለፉኳቸው የአገልግሎትና የስደት ዓመታት እንዳስተዋልኩት ፕሮቴስታንቶች ታዋቂ የሆኑ ሕዝቡን





የሚያስተምሩ አንደበተ ርቱእ የሆኑ የቤተ ክርስቲያናችንን መምሕራን በሕዝባችን ለማስጠላት የሚጠቀሙት በዚህ ዓይነት መንገድ ነው። በሐረር ግን ማኅበረ ቅዱሳን መጥቶ የሃሳባቸውን እስኪያሟላላቸው ድረስ አልተሳካላቸውም ነበር።

## የሐረር ሰንበት ትምህርት ቤቶች ተሐድሶ መባል

ፕሮቴስታንቶች እንዳችም ሊያደርጉት ያልተቻላቸውንና በሌሎች ሃይማኖት በተከበበች ምድር አስደናቂ እንቅስቃሴ ያደርግ የነበረውን የሰንበት ትምህርት ቤቶች እንቅስቃሴ በድርጅታዊ ፍቅር ታውሮ የበታተነው ማኅበረ ቅዱሳን በሚል ስም የተቋቋመው ማኅበር ነበር። ማኅበረ ቅዱሳን ሐረር ላይ ያለውን የሰንበት ትምህርት ቤቶች እንቅስቃሴ በክፉ ዓይን ማየት የጀመረው አለማያ ግብርና ዩኒቨርስቲ ውስጥ ገና እግሩን በተከለበት ወቅት ነው። በዚህ ወቅት ማኅበረ ቅዱሳን የሚባል ማኅበር በሐረር ስሙም የማይታወቅ ስለነበረ በሐረር ያሉ ካህናትም ሆኑ ምእመናን ቦታ አልሰጡትም ነበር። ነገር ግን ጥቂት ቆይቶ ማሕበረ ቅዱሳን ለጠቅላይ ቤተ ክህነትና ለሐረርጌ ሀገረ ስብከት አቤቱታ አስገባ። አቤቱታውም ሐረር ውስጥ ያሉት ሰንበት ትምህርት ቤቶች በሙሉ ተሐድሶ ናቸው የሚል ነበር። ለጊዜው የሀገረ ስብከቱ ጽሕፈት ቤት የማኅበሩን ክስ አጥብቆ ተቃወመ። የሐረር ሕዝበ ክርስቲያንም ሁኔታውን ሲሰማ አጥብቆ ተቃወመ።

## የሐሰት ሰነድና የሐረር ሰንበት ትምህርት ቤቶች መዘጋት

ማኅበረ ቅዱሳንን ሐረር ምድር ላይ ላለማስገባት ከፍተኛ የሆነ እንቅስቃሴ ተጀመረ። ሁኔታው ያላማረው ማኅበረ ቅዱሳን የሐረር ሕዝበ ክርስቲያንን የሚከፋፍልበትን አንድ ረቂቅ ተንኮል አርቅቆ አወጣ።



www.ethiopianorthodox.org

ያም በሐረር የሚገኙ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን የተሐድሶ አባላት እንደሆኑ የሚያሳይ የሐሰት ሰነድ ነበር። ሰነዱ በቃለ ጉባኤ መልክ የተዘጋጀ ሲሆን የተሀድሶ አባላት የሆኑ ከመላው ኢትዮጵያ ተሰብስበው ለሐረር እንቅስቃሴ ከፍተኛ ገንዘብ እንደሚሰጡ ለሐረርም መሪዎችን እንደሾሙ የሚናገርና ስሞችንም የሚዘረዝር ነበር።

በዚህ የሐሰት ሰነድ ላይ መላከ ሰላም ጴጥሮስ አዘነን ጨምሮ የሀገረ ስብከቱን ሥራ አስኪያጅ የሀገረ ስብከቱን የመዝገብ ቤት ኃላፊ ሌሎች ካህናትና ታዋቂ ምእመናን የያዘ ነበር። በሰነዱ ላይ የተዘረዘሩት ቀንደኛ የሆኑ ማኅበረ ቅዱሳንን አላፈናፍንም ያሉ ሰዎች ነበሩ። በወቅቱ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሆነው የተሾሙት መምሕር ብርሃነ ሕይወት (አባ ዜና ማርቆስ የተባሉት) በደስታ ቸኩለው ተሐድሶዎች ቤተ ክርስቲያኔን ወረዋል በማለት በሸኚ ደብዳቤ የሀገረ ስብከቱን ሥራ አስኪያጅ ካህናቱን የደብር አስተዳዳሪውንና ታላቁን ሊቅ መላከ ሰላም ጴጥሮስ አዘነን ከሥራና ከደመወዝ አገዷቸው። ቤተ ክርስቲያኑንም ለማንም ወጣት የተከለከለ እንደሆነ አስታወቁ። በብዙ ሺህ የሚቆጠር የሐረር ሕዝብ ሥዕለ ማርያምን ይዞ በነቂስ ወጥቶ ውሳኔውን ተቃወመ ለቤተ ክህነት አቤት አለ። ሰሚ ግን አላገኘም። እነዚህ በሐረሩ የሐሰት ሰነድ የተጠቀሱት እንደ አዲስ አበባው ዘገባ ዝም ብለው አልተቀበሉትም። ወዲያውኑ ጉዳዩን ለፍርድ ቤት አቀረቡ። ፎርጅዱን የሠራው ተያዘ። ከማኅበረ ቅዱሳን አባላት አንዱ ይህን እንዲሠራ እንደ ጠየቀው ተናገረ። የፖሊስ የምርመራ አባላትም ሰነዱ የሐሰት ሰነድ (ፎርጅድ) እንደሆነ ለፍርድ ቤቱ አስታወቁ። ጉዳዩ ፍርድ ቤቱንም የሐረርን ሕዝብ አስቆጣ። ፍርድ ቤቱም የሐሰት ሰነዱን በሸኚ ደብዳቤ





የበተኑት ሊቀ ጳጳሱ ስለሆኑ በኃላፊነት እንደሚጠየቁ ወሰነ። ከሦስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት ሊፈረድባቸው ፍርዱ እየተጠበቀ እያለ ማዕከላዊ መንግሥት ጣልቃ ገብቶ ጳጳሱ ይቅርታ እንዲጠይቁና በሐሰት ስማቸው የጠፋውም ክሳቸውን እንዲያነሱና በየስማቸው ከጠቅላይ ቤተ ክህነትና ከሀገረ ስብከት ንጹሐን እንደሆኑ ደብዳቤ እንዲጻፍላቸው ተወሰነ። ሊቀ ጳጳሱም ያሳሳቱኝ ልጆቼ (ማኅበረ ቅዱሳን) ናቸው ብለው ይቅርታ ጠየቁ።

አሳዛኙ ነገር ግን ይህ ውሳኔ የተሰጠው ድርጊቱ ከተፈጸመ ከሰባት ዓመት በኋላ መሆኑ ነው። በዚህ ሰባት ዓመት «ተሐድሶ» ናችሁ ተብለው ከገዛ ቤተ ክርስቲያናቸው የተባረሩና ቅጽረ ቤተ ክርስቲያን እንዳይደርሱ የተደረጉ፤ በዚህም ተበሳጭተው መሂጃ አጥተው ዓለም የበላቻቸው፤ ደግሞም በስህተት አረንቋ የሰጠሙ፤ በፕሮቴስታንቱ ዓለም የተወሰዱ ስንቶች ናቸው። ለእነዚህ መጥፋት ተጠያቂውና ኃላፊውስ ማንው?

ማኅበረ ቅዱሳን ግን ዛሬም ራሱ ያዘጋጀውንና በፖሊስና በፍርድ ቤት ሐሰትነቱ የተረጋገጠበትን የሐሰት ሰነድ በመያዝ እነ እከሌ «ፓስተር» ናቸው። ከቤተ ክርስቲያን የወጡት የመናፍቅነት መንፈስ ይዞአቸው እንጂ ማንም አላባረራቸውም እያለ ይጽፋል። ከእነዚህ በግፍ ከተባረሩት ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ በይቅርታው ወደ ቤቱ ከመለሳቸው አንዱ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ነው።

## ግላዊ ምስክርነት

ይህን ታሪክ የምጽፍላችሁ የዚህች አነስተኛ መጽሐፍ አቅራቢ ተወልጄ ያደግሁት በዚህች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። ከሕጻንነቴ ጀምሮ በሥርዓተ



www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ክርስቲያን ኮትኩተው ያሳደጉኝ፤ የቤተ ክርስቲያን ፍቅር እንዲኖረኝና በማዕረገ ክህነት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንዳገለግል ያዘጋጁኝ ኦርቶዶክሳዊው ሊቅ ወላጅ አባቴ መሪጌታ ባወቀ ተረፈ ናቸው። ገና ደግና ክፉን ሳላውቅ እጄን ይዘው እርሳቸው በሚቆሙባት ቅኔ ማኅሌት አጠገብ ከእግራቸው ሥር እንድሆን በማድረግ እንደ ሃሳባቸውና እንደ ምኞታቸው ባልሆንም፥ ፍቅረ ቤተ ክርስቲያንን፣ ፍርሃተ እግዚአብሔርን ተምሬ አድጌአለሁ።

አብዛኛውን የሕፃንት ጊዜዬን ያሳለፍኩት በደቡቡ የሀገራችን ክፍል ሲሆን በተለይም ባደኩባት በአዋሳ መካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ገና ከታናሽነቴ ጀምሮ በስብከተ ወንጌል በማገልገል በመቀጠልም ከብፁዕ አቡነ በርተሌሜዎስ ማዕረገ ዲቁናን በ1976 ዓ. ም. በመቀበል እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለአራት ዓመት በዲቁና በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ አገልግያለሁ።

በዚህ ወቅትም በውስጤ ያለውን ፍላጎት ብፁዕነታቸው በቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርት ራሴን እንዳበለጽግ ከፍተኛ የሆነ አባታዊ ምክራቸውና ቅን ሃሳባቸው አልተለየኝም ነበር። በተለይም ወደፊት ስለሚኖረኝ ሁኔታ ከወላጅ አባት በላይ ስለ እኔ በማሰብ በአደባባይ ሳይቀር «መላኩን አዲስ አበባ ልኬ አስተምረዋለሁ» በማለት ለእኔ ያላቸውን የወደፊት ሃሳብ ይገልጡ ነበር።

በተጨማሪም ኦርቶዶክሳዊ በሆነ ስብከታቸው በጊዜው ታዋቂዎች የሆኑት መልአከ ሰላም ኃይለ ኢየሱስ ከበደ፣ መልአከ ምሕረት ጳውሎስ ቀጸላ፣ መምህር ኃይለ ሥላሴ ይግዛው ኦርቶዶክሳዊ የስብከተ ወንጌል ምን ዓይነት እንደሆነ በማሳየት አርዓያቸውን ተከትዬ እንዳድግ ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት ፍቅር





እንዲኖረኝ አድርገውልኛል።

በተለይም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ አስተማሪነታቸው ጥልቅ የሆነ እውቀት ከማስተማር ተሰጥኦ ጋር ያላቸው መምህር ኃይለ ሥላሴ ይግዛው፥ በአዋሳ የካህናት ማሰልጠኛ በሰጡኝና ቀን ከሌት በትጋት ባስተማሩኝ ትምህርት ስለ ቤተ ክርስቲያኔና ስለ ዓለም አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ የበለጠ እንዳነብና የአበውን ትምህርትና ታሪክ የመመርመር ፍቅር እንዲያድርብኝ አድርገዋል።

<u>ወጣትነት እና ሐረር</u>

በአዋሳ ለአምስት ዓመት ካገለገልኩ በኋላ በወላጆቼ መካከል የተፈጠረው መለያየት ስለ አሳዘነኝ በዚያ የወጣትነት ወቅት ተነስቼ ወደ ሐረር ሄድኩ። ወደ ሐረር የሄድኩት በጊዜው በአዋሳ የማውቃቸው ቀሲስ መዘምር የክፍለ ሀገሩ ሥራ አስኪያጅ ሆነዋል የሚል ዜና ስለ ሰማው ነበር። በወቅቱ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ታላቁ ኦርቶዶክሳዊ አባት ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል የዕድሜዬን አነስተኛነት አይተው ወደ ወላጆቼ ዘንድ እንድመለስ መክረውኝ ነበር። ነገር ግን ካደኩባት መንደር ስወጣ ወስኜ ስለ ነበር ብፁዕነታቸውን በእርሳቸው ሀገረ ስብከት እያገለገልኩ መኖር እንደምፈልግ ነገርኩዋቸው።

በሐረር ለመጀመሪያ ጊዜ በዲቁና ያገለገልኩት በታላቁ ደብርና የብዙ ሊቃውንት ቦታ በነበረው በደብረ ገነት መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ነበር። በዚያም ከአስተማሪ እጦት የተነሳ ተዘግቶ የነበረውን የሰንበት ትምህርት ቤት በአዲስ በማደራጀትና በዲቁና አገለግል ነበር። ምንም እንኳ ከወላጅ ርቄ በራሴ የምኖረው ኑሮ ከወጣትነት ስሜትና ከችኩልነት ጋር ተዳምሮ ከባድ ቢሆንም፤ አገልግሎቴን በተቻለ መጠን



www.ethiopianorthodox.org

ለመወጣት እጥር ነበር።

በዚህ መካከል ነበር በዚያን ወቅት ሕይወቴን በአያሌው የለወጠው ነገር የተከሰተው። ይኸውም፥ በየዓመቱ የሚደረገውን የቀዳም ስዑር በዓል ምክንያት በማድረግ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤልን እንኳን አደረስዎት ለማለት በሐረር ከሚገኙ አድባራት የተሰበሰብን ካህናት በመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተሰብስበን ለዕለቱ የሚገባውን ሥርዓት እያደረስን እያለን የመካነ ሥላሴ ወጣቶች ልብ የሚነኩ መዝሙራትን አቀረቡ። ከመዝሙራቱም መካከል «ፍቅሩ አይለወጥም» «የሞት ላብ አላበው» እና የመሳሰሉት የሃይማኖተ አበው መዝሙራት ነበሩ። የመዝሙሮቹ መልእክትና ዜማቸው እጅግ ልብን የሚነካ ስለነበር በዚያ የተሰበሰበውን ምእመን በሙሉ የሳበ ነበር። ከዚያም ከዚህ ቀደም በሩቅ ብቻ የማውቃቸው የደብሩ አስተዳዳሪ መላከ ሰላም ጴጥሮስ አዘነ በአጠቃላይ በአባትነታቸው የሚያከናውኑት ነገር ልቤን ስለነካው እርሳቸውን በግል ማነጋገር እንዳለብኝ ወሰንኩ። ወደ ቤታቸውም በመሄድ ሳናግራቸው በዚህ በወጣትነቴ ቤተ ክርስቲያኔን እንዴት ማገልገል እንዳለብኝ መከረውኝ፤ እግረ መንገዳቸውንም በመካነ ሥላሴ ክፍት የዲቁና ቦታ ስላለ እዚያ መጥቼ ባገለግል በዚያውም በጅምር የቀሩትን አንዳንድ ትምህርቶቼን ማጠናቀቅ እንደምችል በማሳሰብ እንድመጣ ነገሩኝ። በእውነቱ እንደ አባት የሚቆጣኝና የሚመክረኝን የምፈልግበት ወቅት ስለነበር ይህ ለእኔ ተአምር ነበር።

ወደ መካነ ሥላሴ እንደመጣሁም ሰንበት ትምህርት ቤቱን በአዲስ ለማደራጀት ከፍተኛ እንቅስቃሴ ስለነበረ በዚያ ወቅት ወጣቶችን በማስተማር በስብከተ ወንጌልና በዲቁና ማገልገል ጀመርኩ። በዚያም ያለው





የሰንበት ትምህርት ቤቱ እንቅስቃሴ ወደ ሌሎቹም አድባራት ተስፋፍቶ በኢትዮጵያ ምድር በአርአያነት ሊጠቀስ የሚችል የሰንበት ትምህርት እንቅስቃሴ በሐረር ስድስቱም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ነበር።

በተለይም ወጣቱ ትውልድ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲቀርብና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያውቅ የበኩላችንን ጥረት እናደርግ ስለነበረ፥ ጠዋት ለኪዳን ጸሎት ማታ ለሠርክ ጸሎት ወጣቱ ቤተ ክርስቲያኒቱን አጣቦ ይታይ ነበር። በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት በሚገባ የታጠቀ ስለሆነ በመናፍቃን ትምህርት ተታሎ ወደ የትም ቦታ እንዳይሄድ ለማድረግ ተችሎ ነበር።

## ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት ቤት መግባቴ

ይህ በእንዲህ እንዳለ የሐረሩ የስብከተ ወንጌል እንቅስቃሴ ከፍተኛ ደረጃ ከመድረሱም በላይ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ መሥርተውት በጅምሩ የቀረውን የስብከተ ወንጌል እንቅስቃሴ በሚገባ ለማንቀሳቀስ በቤተ ክርስቲያኒቱ ከፍተኛ ትምህርት ቤት በሚገባ የተማረ ካህን እንደሚያስፈልግ በማስተዋል ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ የነገረ መለኮት ትምህርት ቤት ለመሄድ መዘጋጀት ጀመርኩ። በጊዜው ሀገረ ስብከቱ በጀት የለኝም ስላለ ከትምህርት ቤት ወጥቼ ከመጣሁ በኋላ ደመወዝ ላለመጠየቅ ፈርሜ ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት ቤት ገባሁ። ይህ ሁሉ ሌሎች አይገንዘቡት እንጂ፤ ማለቂያ ከሌለው የቤተ ክርስቲያኔ ታላቅ የእውቀት ሀብት ለመካፈል ነበር። በጊዜውም መላው የሐረር ምእመን በታላቅ ኃዘን ተሰናብቶኝ ወደ ትምህርት ቤት ገባሁ።

ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ ትምህርት ቤትም እንደገባሁ እግዚአብሔር ሁሉን አሟልቶ ከሰጣቸው



www.ethiopianorthodox.org

ከመምህራኖቼ በሃይማኖቴ ላውቀው የሚገባኝን፤ እንደ ካህንነቴም ላስተምረው የሚገባኝን በሚገባ ተምሬአለሁ። በማናቸውም ቦታና ሁኔታ ውስጥ የቤተ ክርስቲያናችን ተጠያቂ የሆኑት ታላቁ ኦርቶዶክሳዊ ሊቅ ብፁዕ አቡነ መርሀ ክርስቶስ ከማያልቀው ማዕዳቸው፤ ታላቁ ሊቅ መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ከጥልቅ ምርምራቸው፤ ዶክተር የማነ ገብረ ማርያም ከታላላቆቹ የፍልስፍና ምንጮች፤ መምህር ሉሌ መላኩ ከቤተ ክርስቲያናችን ታሪክና ከአዲስ ኪዳን ሀብት አስተምረውኛል።

እነዚህ አባቶች የሰጡኝን ትምህርትም በተግባር ለመተርጎም፥ በዚያው እየተማርኩ በታላላቆቹ የቤተ ክርስቲያን አድባራት በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስት ማርያም፤ በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ፤ በየካ መካነ ሳሕል ቅዱስ ሚካኤል፤ በገብረ ክርስቶስ በአዲሱ ሚካኤልና በሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ሳምንታዊ የሰብከተ ወንጌል ትምህርት ነበረኝ። በዚህም በዚያች ታናሽ አድሜዬና ዕውቀቴ ያገኘኋትን ለብዙዎች ለማካፈል ጥሬአለሁ።

## በሰዋስወ ብርሃን የተፈጠረው ክፍፍል

በሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ የቴዎሎጂ ትምህርቴን በምከታተልበት ወቅት እንደ አዲስ የተፈጠረው ክስተት በሃይማኖተ አበው አባላትና አዲስ በተቋቋመው በማኅበረ ቅዱሳን አባላት መካከል የተፈጠረው የቡድንነት ስሜት ነበር። ዛሬ ያ የልጅነትና የእልክ ዘመን አልፎ በዚያ ውስጥ ያሳለፍኩትን የአለመብሰል ጊዜ ሳስታውሰው እገረማለሁ። ለነገሩ ያ የድሮው ስህተት ሳያንስ ዛሬም በማኅበረ ቅዱሳን አባላት መካከል የሚታየው ጭፍን የሆነ የድርጅት ፍቅር ቤተ ክርስቲያንን የሚጎዳ እንደሆነ ማን በነገራቸው?





በዚያ ወቅት በትምህርት ቤቱ ውስጥ የነበርነው ደቀ መዛሙርት ለሁለት የተከፈለ አቋም ነበረን። አንዳንዶቻችን የሃይማኖተ አበው ልጆች በሚሰበሰቡበት በመንበረ ፓትርያርክ ስንሰበሰብ ሌሎቹ ደግሞ በግቢ ገብርኤልና በምስካየ ሐዙናን በሚደረገው የማኅበረ ቅዱሳን ጉባኤዎች ላይ ይሰበሰቡ ነበር። በተለይም በሃይማኖተ አበው ስብሰባዎች ላይ በመገኘት አስተምር ስለነበረ እኔ በማኅበረ ቅዱሳን ጥቁር መዝገብ ላይ ለማስፈር ጊዜ አልወሰደባቸውም ነበር።

በትምህርት ቤቱ የነበረው ቡድንተኝነት ከዚህ በፊት ከተማርንባቸው ትምህርት ቤቶች ጀምሮ ያልታየ እስከ ዘር ማንዘራችን የእያንዳንዳችንን መንደርና ቀየ የምንቆጣጠርበት ስለነበረ አስጸያፊ ነበር። እከሌ የዝዋይ ልጅ ነው፤ እከሌ ከወሎ ነው፤ እከሌ ጎጃሜ ነው፤ እከሌ ሸዋ ነው የሚለው የብዙ ደቀ መዛሙርትን አእምሮ ያቆሸሸ ነገር ነበር። ከሁሉም በላይ ማኅበራቱ እርስ በእርሳቸው ለመጠፋፋት ቃል የገቡ እስከሚመስሉ ድረስ አንዱ አንዱን ለማጥፋት እንጂ ለቤተ ክርስቲያን ክብር ለወንጌል መስፋት የሚጥር የለም ነበር።

ሁኔታውን ለማለዘብም በጊዜው አብረውኝ የነበሩትን ሁለት የትምህርት ቤቱን ተማሪዎች በመያዝ ማኅበረ ቅዱሳንን ከሚመሩት ወጣቶች ጋር በመንበረ መንግሥት ግቢ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ያደረግሁት ስብሰባ ያለ ፍሬ ነበር የተበተነው። የስብሰባው ዓላማ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ልጆች ለምን በከንቱ እንበላላለን። ይህ የሚጠቅመው ሌሎችን ነው የሚል ቢሆንም፤ ያገኘው ምላሽ ቢኖር፥ ከሃይማኖተ አበው ጉባኤ እንዳንሄድና በኦርጋን የሙዚቃ መሣሪያ



www.ethiopianorthodox.org

የሚጠቀሙትንና የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ሰንበት ትምህርት ቤቶችን የአዘማመር ስልት የተከተሉትን ሰንበት ትምህርት ቤቶችን እንድናወግዝ ነበር። ይህ ደግሞ የቤተ ክርስቲያናችን እምነትም ሆነ ሕያው የሆነው ታሪኳ ስለማይፈቅድልኝ አልተቀበልኩዋቸውም።

ምንም እንኳን በየአብያተ ክርስቲያናቱ የምሰጠው የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ተወዳጅ ቢሆንም፤ ማኅበረ ቅዱሳን ግን የእኔንም ሆነ በሃይማኖተ አበው እና በሌሎች ሰንበት ትምህርት ቤቶች የምናገለግለውን በመናፍቅነት ከመፈረጅ ወደ ኋላ አላለም ነበር። በተለይም አገልግሎታችን እየሰፋ ሕዝቡም ስብከታችንን ትምህርታችንን እየወደደ ሲመጣ፤ የኛ በአጸደ ቤተ ክርስቲያን መታየት ለማኅበረ ቅዱሳን ሕልውና አደጋ እንደሆነ እየተቀጠረ መጣ። በተለይም የማኅበረ ቅዱሳን ቀኝ እጅ በሆኑ አንዳንድ የጠቅላይ ቤተ ክህነት የመምሪያ ኃላፊዎች አማካይነት በሊቃነ ጳጳሳትና በደብር አስተዳዳሪዎች ዘንድ ስማችንን ለማስጠላት ከፍተኛ ዘመቻ ተጀመረ። ለዚህም ከፍተኛ ዘመቻ ያደርግ የነበረው ቡድን የቀድሞው አጠቃላይ ጉባኤ አባላት የነበሩ የመምሪያ ኃላፊዎች በዋናነት ተጠቃሽ ነበሩ። በተለይም የትምህርት ቤታችንን ዲን ብፁዕ አቡነ መርሐ ክርስቶስን ወደ ትምህርት ቤቱ የላኩኝ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤልን የናንተ ልጅ እየበጠበጠን ነውና አስወጡልን እየተባሉ በየስብሰባው ይወቀሱ ጀመር። እነዚህም አባቶች ምንም እንኳ ስለ እኔ ቢከራከሩም፤ ስማቸው በየስብሰባው መነሳቱ ሳያሳዝናቸው አልቀረም።

እዚህ ላይ መጠቀስ የሚገባው ይህ ሁሉ ሲሆን በእኛ በኩል የመላእክት ባሕርይ ይታይብን ነበር ማለት አይደለም። በተለይም የቤተ ክርስቲያን አባቶች





የሚሉንን አለመስማት ችኮላ፣ የሕፃንነት ባሕርይ፣ አለመብሰል ከጉድለቶቻችን ዋናዎቹ ናቸው። ውጊያችን ለዘመናት የቤተ ክህነቱን ሥልጣን ለመጨበጥ ከሚያደባና፤ ስንት ሊቃውንትን ሲቻለው በአደባባይ ሳይቻለው በስውር ሲያጠፋ ከነበረ ቡድን ጋር መሆኑን አለማወቃችን በብዙ ጎድቶናል። ያም ሆነ ይህ የዚህ ቡድን ችሎታ የት ድረስ እንደሆነ የተገነዘብኩት ድሬዳዋ በነበረው ግድያ ነው።

## የድሬዳዋው ግድያ

በቅዱስ ጳውሎስ በቆየሁባቸው ዓመታት የክረምትን ወቅት የማሳልፈው በመጣሁበት ሀገረ ስብከት ማለትም በሐረርጌና አልፎ አልፎ ደግሞ በወላጆቼ አካባቢ ነበር። በ1986 ዓ. ም. ክረምትን ለማሳለፍ የሄድኩት ወደ ሐረር ነበር። ሐረር እንደደረስኩም ከድሬዳዋ የሃይማኖተ አበው ተማሪዎች መልእክት ተቀምጦልኝ ነበር። መልእክቱም ነሐሴ 21 ቀን 1986 ኣ. ም. ጉባኤ እናከናውናለንና እባክህ መጥተህ ብታስተምረን የሚል ነበር። በእውነቱ በጣም ነበር ደስ ያለኝ። ምክንያቱም እነዚህ ልጆች በብዙ የተገፉ ነበሩ። በእኔ የልጅነት ሃሳብ የቤተ ክህነት ሰዎች የማኅበረ ቅዱሳንን ውትወታ ሰምተው ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ቢያስወጡአቸውም አንድ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው ሊመለሱ ስለሚችሉ እነዚህን ማጽናናት ማረጋጋት ይገባል የሚል ነበር።

ጉባኤው ወደ ሚደረግበት ወደ ድሬዳዋ የገባሁት አንድ ቀን ቀደም ብዬ ነበር። በዚያ ያሉት ወጣቶች በሙሉ ልባቸው ለጉባኤው እየተዘጋጁ ነበሩ። ወረብ የሚያጠኑ ነበሩ። የተለያዩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶችን የሚጽፉ ነበሩ። ለሚመጡት እንግዶች እህል ውኃ የሚያዘጋጁ ነበሩ። ነገ የሚሆነውን የገመተም ያሰበም የለም። ሁሉም የሚያስቡት አንድ ቀን ያ የሚወዱት ማኅበራቸው ከተሰደበበት



www.ethiopianorthodox.org

እንደሚነሳ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የእነዚህን ወጣቶች ምኞትና ሃሳብ አንድ ቀን እንደሚያዩት፥ መናፍቅ እንዳይደሉ ነበር። ይህ ነበር የነዚያ የዋሆች ልብ።

ጠዋት ድሬዳዋ እንደ ልማድዋ ደምቃለች። እኔም ያደርኩበት ቤት በእንግዶች ግርግር ደምቋል። አብረን ያደርነው እንግዶች በአንድነት ወደ ጉባኤው አዳራሽ ሄድን። ጉባኤው የሚካሄደው በከተማው አስተዳደር መሰብሰቢያ አዳራሽ ነበር። አዳራሹ ከመቶ ዘጠና እጅ መስታዎት ብቻ የሆነ ውብ አዳራሽ ነበር።

ጉባኤው ምስባክ ተሰብኮ በጸሎተ ወንጌል ከተከፈተ በኋላ የሃይማኖተ አበው ወጣቶች የሀገር ልብሳቸው እንደለበሱ የዕለቱን መዝሙር አቀረቡ። መዝሙሮቹ ስለ ሃይማኖት ጽናትና ዕለቱ የእመቤታችን ስለነበረ ስለ እመቤታችን አማላጅነትና ክብር የሚናገር ነበር። በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለን ከፍተኛ የሆነ የሕዝብ ጩኸት ሰማን ወዲያውም፤ የመጀመሪያው ድንጋይ የተሰበሰብንበት አዳራሽ መስታዎት ሲሰብር ተሰማን። የሰዎቹን ቁጥር ለማየት ለሌሎች አዳጋች ቢሆንም ለእኔ ግን በግልጥ ይታየኝ ነበር። ምክንያቱም በዕለቱ ፕሮግራሙን እየመራሁ የነበርኩት እኔ ነኝና።

በመጀመሪያ የመጡት ጥቂት ሰዎች ቢሆኑም «ያዘው! ስበረው!» ጩኸት ያሰሙ የነበሩት ግን ብዙ ነበሩ። በድንጋይ መስታወቱን በአንድ ጊዜ ሲያደቅቁት በበሩ የነበረው ታጣቂ (ቦታው የአስተዳደር አዳራሽ ስለነበር ነው) ወደ ሰማይ ለመተኮስ ቢሞክርም አልቻለም። መጨረሻ ላይ ነፍስ አውጭኝ የሸሸ ይመስለኛል። ከዚያ በኋላ ሁሉም መራኮት ሆነ። «ዋናው እርሱ ነው፤ እርሱን ያዙት» የሚል ጩኸት ብሰማም የማላውቃቸው ሰዎች መጥተው ስለሸፋፈኑኝ እኔን





ለመግደል ለሞከሩት ሰዎች አልሆነላቸውም ነበር። «ሰለ እማምላክ ተውኝ» ከምትለው ነፍሰ ጡር ጀምሮ «እማዬ የት ነሽ?» እያለ እስከሚያለቅሰው ሕፃን ድረስ ታላቅ ጩኸት በአዳራሹ ውስጥ ሞላ።

መግቢያና መውጫውን እነርሱ ስለያዙት በየትም መውጫ አልነበረም። የአካባቢው የጸጥታ ኃይሎች እስኪመጡ ድረስ ሰዎቹ ይዘውት በመጡት ሁሉ መቱን። ማን ምን እንደሆነ ለማወቅ ግን አልተቻለም ነበር። በመጨረሻ የጸጥታ ሰዎች በመጡ ወቅት ግን የተወሰንነው እነርሱን ጥግ አድርገን ለማምለጥ ቻልን። ከአካባቢው እየሮጥኩ ስወጣ ታክሲ ስላገኘሁ ዘልዬ ታክሲ ውስጥ ከገባሁ በኋላ እስከዛሬ የማልረሳውን ቃል ተናገርኩ፤ «ከዚህ ቦታ ወደ ፈለግህበት ውሰደኝ።» ምንም እንኳን ይህ ለጊዜው ለባለ ታክሲው የተናገርኩት ቢሆንም፤ በዚያ ወቅት ግን ለአምላኬም የተናገርኩት ነበር። «ብቻ ከዚህ ቦታ ወደ ፈለግህበት ውሰደኝ»። ወንድሞቼ በምላቸው የገዛ ወገኖቼ፤ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ልጆች ስንደበደብ ምን ልበል? ካሳደገችኝ ቤተ ክርስቲያን ሸሚዜ በደም ጨቅይቶ እንደሌባ በገዛ ሀገሬና ወገኔ ፊት ስሸሽ ምን ልበል? (በሸፈኑኝም ሰዎች ደም ጭምር ነበር የዳንኩት፤ እነርሱ ለእኔ ደሙልኝ) እናም በታክሲው የቻለኝን ያህል ራቅሁ። የራቅሁት ግን ሕይወቴን በሙሉ ከሰጠሁበትም ቦታ ነበር።

## ሥርዓትህን እማር ዘንድ ያስጨንቅኸኝ...

ከዘጠኝ ዓመት በኋላ እንደገና በብዙ ሕዝብ ፊት ቆምኩ። ይህን ጊዜ በአዳራሽ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን፤ ዱላ በያዙ ፊት ሳይሆን በጸሎት ከአምላካቸው ፊት በቆሙ ፊት ነበርኩ። ጊዜው ማዕረገ ቅስና የምቀበልበት ወቅት ነበር። ቦታውም



www.ethiopianorthodox.org

ሎስ አንጀለስ ነው። ብፁዕ አባታችን አቡነ መልከጼዴቅ በሕዝብ ፊት «ይደልዎ! ይደልዎ! ይገባዋል! ይገባዋል! አሰኝተው ከሾሙኝ በኋላ፥ የምስክርነት ቃል እንድናገር ስለ ፈቀዱልኝ ነበር የቆምኩት። እናም ንግግሬን ከዳዊት መዝሙር ጀመርኩ «ደለወኒ ዘአሕመምከኒ ከመ አእምር ኲነኔ ጽድቅከ - ሥርዓትህን እማር ዘንድ ያስጨነቅኸኝ ለመልካም ሆነልኝ» ይህን ቃል ለመስበክ ግን በዘጠኝ ዓመት የመከራ ትምህርት ቤት በዘጠኝ ዓመት የኃፍረት ትምህርት ቤት በዘጠኝ ዓመት የውድቀት ትምህርት ቤትና በመጨረሻም በዘጠኝ ዓመት የበረከት ትምህርት ቤት ማለፍ ግድ ነበር። ከዚያ ነበር ያስጨነቅኸኝ ለመልካም ሆነልኝ ያልኩት፤

## ከሰዋስወ ብርሃን መባረርና ያልታሰበው ውግዘት

ከድሬ ዳዋው ድብደባ በኋላ ወዲያው ወደ ሐረር ነበር የተመለስኩት፤ በሐረር ሁኔታው ተሰምቶ ስለነበር ሕዝቡ ሁሉ አንድ ነገር የሆንን መስሎት ነበር። በሰላም በመመለሳችን ደስታ ቢኖርም የእኛን እግር ተከትሎ አንድ አስደንጋጭ ዜና ደረሰን። ከተደበደቡት መካከል ሦስቱ በአሳሳቢ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙና በተለይም አንደኛው በኮማ ውስጥ እንዳለ ተነገረን። ሁላችንም አለቀስን። ስለ ወንድሞቻችን፣ ስለ እህቶቻችን፣ ደግሞም በነፍሰ ገዳዮች እጅ ስለወደቀችው ስለ ቤተ ክርስቲያናችን አለቀስን። በተለይም በኮማ ውስጥ ያለው አዳም የተባለው ወንድማችን መሆኑን ስሰማ በጣም አዘንኩ። ብዙም ባላውቀው በድሬዳዋ በነበረኝ ቆይታ አግኝቼው ነበር። ቤተ ክርስቲያኑን የሚወድ የአምቦ ልጅ ነበር። ለሀገሩ ለቤተ ክርስቲያኑ ታላቅ ፍቅር ስላለው፤ የሀገር ልብሱ በባንዲራና በእመቤታችን ሥነ ሥዕል ያጌጠ ነበር። ያን ኢትዮጵያዊ ነበር አናቱን በድንጋይ የቀጠቀጡት።





የአዳምን ሁኔታም የሌሎቹንም ነገር ለማጣራት በተለያየ መንገድ ብንሞክርም ስላልተቻለ በጠዋት እንደገና ወደ ድሬዳዋ ለመሄድ ወሰንን። ጠዋት ወደ ድሬዳዋ ስንሄድ እነዚያ ሃይማኖተ ጽኑ ልጆች፤ የተዋህዶ ልጆች በለቅሶ ውስጥ ነበሩ። በኮማ ውስጥ የነበረው የሃይማኖተ አበው ተማሪ ኦርቶዶክሳዊው አዳም አርፎ ነበር። በስተኋላ እንደሰማሁት የተወሰኑ የመሥሪያ ቤቱ ልጆች ገንዘብ አዋጥተው አስከሬኑ ወደ አንቦ ተልኳል።

ከድብደባውና ከመገፋቱ በላይ እነዚያን ልጆች የወንድማቸው መገደል እጅግ የጎዳቸው ይመስለኛል። በተለይም ገዳዮቹ ራሳቸውን የኦርቶዶክስ ጠባቂ አድርገው የሚያዩት የድሮዎቹ አጠቃላይ ጉባኤዎች የአሁኖቹ ማኅበረ ቅዱሳን ሲሆኑ የበለጠ ጥቃት ተሰማቸው። ከተደብዳቢዎቹ መካከል አጠቃላይ ጉባኤ በ1970ዎቹ ያደረሰውን ድብደባ የሚያውቁ ነበሩ። ድብደባውንም በዋናነት የመሩት መምህር ብርሃን ሥላሴ (አሁን አባ ዜና በታላቁ አባት በአቡነ ዜና ምትክ የተሾሙት) ቀድሞም በልደታ ለፈሰሰው የዲያቆናት ደም ተጠያቂ እንደሆኑ ይነገር ስለነበር የብዙዎቹን ወጣቶች አእምሮ በጠበጠው።[93]

በተቻለኝ መጠን ልጆቹን አረጋግቼ፥ ወደ ሐረር ከተመለስኩ በኋላ፥ በሐረር አገልግሎቴን እየሰጠሁ ቆይቼ ትምህርት ቤት ስለ ተከፈተ ወደ ሰዋስወ ብርሃን ተመለስኩ። ወደ ትምህርት ቤቱን አደባባይ እንደ ረገጥሁም ቢሮ እንደምፈለግ ስለተነገረኝ፤ ወደ ብፁዕ አቡነ መርሐ ክርስቶስ ጽሕፈት ቤት በቀጥታ ሄድኩ።

(93) ማኅበረ ቅዱሳን ክሱን ወደ እኔ አዛውሮ ጳጳሱን ሳይቀር አስደብድቧል እያለ የሚከሰኝ በእኚህ እኛን ባስደበደቡን አከራካሪ አባት ነው። ለነገሩ እርሳቸው በአደባባይ ባይናገሩትም ንስሐ ገብቼበታለሁ የሚሉትን የማኅበረ ቅዱሳን ሰዎች እነርሱ ለምን እንደሚከዱት አይገባኝም።



www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕነታቸው መስቀል ካሳለሙኝ በኋላ የድሬዳዋውን ነገር እንደሰሙ፤ የኛም የልጅነት ችኮላ እንዳሳዘናቸው አጫወቱኝ። ነገር ግን ከበላይ ማለትም ከጠቅላይ ቤተ ክህነት አንድ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ከትምህርት ቤቱ እንደታገድኩ ከጠቅላይ ቤተ ክህነቱ ትእዛዝ እንደመጣላቸውና እርሳቸውም ትእዛዙን ከመፈጸም በስተቀር ምንም ማድረግ እንደማይችሉ ነገሩኝ። ሁኔታው በጣም ገረመኝ። የተገደልነው እኛ! የተደበደብነው እኛ! አሁን ደግሞ የተከሰስነው እኛ ነበርን። አባታችንም ጉዳዩን በትዕግስት እንድይዘውና ቤተ ክህነት ሄጄ ደጅ እንድጠና መክረውኝና ጸልየውልኝ መስቀላቸውን ተሳልሜ ከቢሮአቸው ወጣሁኝ።

ሁኔታው በሰዋስወ ብርሃን ለነበሩት ደቀመዛሙርት ታላቅ ድንጋጤ የፈጠረ ቢሆንም ለእኔ ግን እንግዳ አልሆነብኝም። ነፍስ ለማጥፋት ወደኋላ ያላሉ፥ አሁን ደግሞ የቤተ ክህነቱን ባለ ሥልጣናት ጥግ አድርገው እኝህን አባት አባርሩ ብለው ቢያዝዙ አያስደንቀኝም ነበር። ከትምህርት ቤቱ ከተባረርኩ በኋላ እገዳዬን ለማስነሳት የቤተ ክህነቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ከሆነው አቶ መርስዔ ኀዘን ዘንድ ደጅ መጥናቴን የተያያዝኩት ወዲያው ነበር። ሆኖም በሦስተኛው ቀን ወደ እርሳቸው ጽሕፈት ቤት መቅረብ እንደማልችል በጸሐፊያቸው በኩል ተነገረኝ። ሆኖም ደጅ ጥናቴን ለአንድ ወር አላቋረጥኩም ነበር። በዚህ ወቅት ያላሰብኩት ነገር ከሌላ አቅጣጫ ተነገረኝ። ካደግሁባትና የእውቀት ጡቷን ጠብቼ እንጀራዋን በልቼ ለዚህ ከበቃሁባት ቤተ ክርስቲያን መታገዴን የሚናገር ደብዳቤ በየአቅጣጫው ተበተነ። ደብዳቤው ደግሞ ወጪ የሆነው እኔ ደጅ ከምጠናበት ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ነበር። በተለይም ከሁሉ ከሁሉ አንጀቴን የቆረጠው ለእኔ አጠገባቸው ሆኜ ደጅ ለምጠናው





የእገዳዬንም ሆነ የተወገዝኩበትን ደብዳቤ በእጄ ሳይሰጡ ወይም ሳይነግሩኝ፤ አዋሳ ወርደው አባቴ በሚያገለግልበት በአዋሳ መካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ማንበባቸው ነበር። ውግዘቱ እኔ ያስተማርኩትን የስህተት ትምህርት አይናገርም። ያወገዘኝንም ጉባኤ አይናገርም። የሚናገረው ከጠቅላይ ቤተ ክህነት መላኩን ነው። በኋላ እንደሰማሁት፥ ይህን በከፍተኛ ደረጃ ለማስፈጸም ላይ ታች ይል የነበረው በጊዜው በከፍተኛ የቤተ ክህነት የሥልጣን እርከን ላይ የተቀመጠው የቀድሞው የአጠቃላይ ጉባኤ አስተባባሪ ኃይለ ጊዮርጊስ ዳኘ ነበር።

አባቴ ምንም እንኳን በሀገሪቱ በነበረው የመንግሥት ለውጥ በድካሙ ያፈራውን ሀብትና ንብረት ቢወረስበትም፤ በልጆቹ ላይ ታላቅ ትምክህት ነበረው። ያም ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸውን አንድ ቀን ይጠቅማሉ የሚል ነበር። የመጀመሪያ ወንድ ልጁ እርሱ በቆመበት ቦታ ሲወገዝ መስማትንን እንኳን በውኑ በሕልሙም አላሰበም ነበር። ለእርሱ ከዚያ ይልቅ ሞቴን ቢሰማ ይሻለው ነበር።

ይህ ውግዘት መላውን አመለካከቴን ብቻ ሳይሆን ከዚያ በኋላ ከቤተ ክርስቲያኔ ጋር ያለውንም ግንኙነት ለወጠብኝ። እንደ ልቤ ቤተ ክህነት ውስጥ ገባ ወጣ ለማለት መፍራት ጀመርኩ። «ያወገዝነው ግቢ ውስጥ ተገኘ ብለው» የቅዱሳን ማኅበር ነኝ የሚለው ቢያስገድለኝስ ብዬ በመስጋት መቅረብ አልቻልኩም። በተለይም የተበተነው ደብዳቤ በብዙ መንገድ ስለጎዳኝ ከእኔ እውቀት በላይ ልቤን አሸፈተው።

__ከጽዋ ማኅበራት ጋር__

ከቤተ ክርስቲያን ስታገድ በግል ሕይወቴ ኑሮዬን የምመራበት አንዳች ነገር ስለሌለኝ፥ ለጊዜው ጥግ



www.ethiopianorthodox.org

የሆኑኝ እንደ እኔው ከየሰንበት ትምህርት ቤቱ በማኅበረ ቅዱሳን ከሳሽነት የተበተኑት የጽዋ ማኅበራት ነበሩ። በመጀመሪያ እንዳስተምራቸው የጠየቁኝ ከቅድስት ሥላሴ የተበተኑት ልጆች ነበሩ። እነዚህ ልጆች ከሌሎቹ ለየት የሚያደርጋቸው በውስጣቸው በእድሜ በሰል ያሉ ሰዎችም የቤተ ክርስቲያን ሰዎችም ነበሩበት። ነገር ግን ፕሮቴስታንቶች ሰርገው ገብተውበታል የሚል ሃሜታ ስለነበር ብዙም አልተማመናቸውም ነበር። ሆኖም የማኅበሩ ሊቀ መንበር ቤተ ክርስቲያኑን በጣም የሚወድ ስለነበር ግልጥ አድርጌ ጉዳዩን ሳጫውተው እውነታውን ነገረኝ። አንዳንድ ፕሮቴስታንቶች ሾልከው ልጆቹን ለመውሰድ እንደሚሞክሩና፤ የቤተ ክህነት ባለሥልጣናት ቤተ ክርስቲያኒቱን ጠቀምን ብለው ለአውሬ እንደሰጧቸው ነገረኝ። ሁኔታው በአጠቃላይ የሚያሳዝን ነበር። ከእነርሱ ጋር ሆኜም አልፎ አልፎ ከማኅደረ ስብሐት ልደታ ለማርያም የወጡትንም ልጆች አስተምራቸው ነበር። እነርሱ በሚገባ የተደራጁና በተለይም ይመራቸው የነበረው፣ ከፍተኛ የሆነ ሥልጣን በመንግሥት ድርጅት ውስጥ የነበረው ቤተ ክርስቲያኑን የሚያፈቅር ሰው ስለሆነ በብዙም ባይሆን ጥቂቶችን ከጥፋት ታድጓቸዋል። እርሱ ይመራቸው የነበሩት እስከ ዛሬ በሃይማኖታቸው ጸንተው አሉ።

ከሐረርም የምሰማው አስደሳች አልነበረም። ከዚህ በፊት ታሪኩን በሰፊው እንዳነበባችሁት በሐረርም ያሉት በዚያ ሁሉ መከራ የጸኑትን በሐሰት ሰነድ ከቤተ ክርስቲያን አባረሩአቸው። ከቤተ ክርስቲያን መባረር ማለት ቀላል አድርገን የምናይ ካለን ምናልባትም በሚገባ የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪክና የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ማስተዋል አለብን። ከቤተ ክረስቲያን ስንባረር የተባረርነው ከአንድ





ድርጅት አባልነት አይደለም። የተባረርነው ጸጋ ከሚገኝበት ሥፍራ ነው። ያ ጸጋ ነው በሃይማኖት የሚያቆመው።

አንዳንዶች ሰዎች ይህን የመከራና የእንግልት ታሪክ ስነግራቸው ለምን አልጸናችሁም ነበር ይሉናል። ሌላው ቀርቶ የትናንቱ አሳዳጆቼ በቅርቡ በሬድዮ ላይ እንደ አባቶቹ በመከራም ቢሆን ለምን አልጸናም ለምን ወደቀ ብለውኛል። ለዚህ ቀጥተኛ መልሴ በመከራዬ ቀን ወደምጸናበትን ሥፍራ አላስደርስ አላችሁኝ የሚል ነው። ያችም ሥፍራ ቤተ ክርስቲያን ናት። አበው ይህን ስለሚያውቁ ነው ከቤተ ክርስቲያን መለየትን የመጨረሻ ፍርድ ያደረጉት። ቁጥሩም ከሞት ፍርድ ጋር እኩል ነው። አሁን ግን ዕድሜ ለማኅበረ ቅዱሳን ከቤተ ክርስቲያን መለየትን የድርጅት መጠቀሚያ አድርጎታል።

ከተባረርኩበት ጀምሮ ለተወሰነ ጊዜ በሐረር፣ በናዝሬት፣ በደብረ ብርሃን፣ በአዲስ አበባ ተበትነው በነበሩት ወጣቶች ዘንድ በመገኘት መጽሐፍ ቅዱስ ለማስተማር እሞክር ነበር። ነገር ግን ጥላ የሌለው ተገን የሌለው ወጣት ስለነበር፤ ጉዟችንም እንደ ወጣትነታችን ነበር።
በዚያን ጊዜ ከቤተ ክርስቲያናቸን በማኅበረ ቅዱሳን ከሳሽነት የወጡትና በስተኋላም በአብዛኛው ወደ ፕሮቴስታንቶችና ልዩ ልዩ የስህተት ትምህርቶች የገቡ ወጣቶችን ታሪክ በዝርዝር ለማቅረብ ባልችልም በአጠቃላይ ግን በነበሩባቸው ማኅበራት ውስጥ የሚከተሉት ነገሮች ይታዩባቸው ነበር።

1. <u>ግብታዊነት</u>፥ እነዚህ ወጣቶች ከቤተ ክርስቲያን ሲባረሩ ከማኅበረ ቅዱሳን ጋር እልህ ውስጥ መግባታቸውን ነው እንጂ ከየት ወደ የት እንደሚሄዱ



www.ethiopianorthodox.org

አያውቁም ነበር። በአንድ ወቅት ማኅበረ ቅዱሳን እኛን ለማባረር ከፍተኛ ዘመቻ በጀመረበት ወቅት፥ አንድ አስተዋይ ሰው በጦቢያ መጽሔት ላይ የወጣውን የሽፋን ሥዕል ምሳሌ በማድረግ አንድ ጥያቄ ጠየቀን። ምስሉ አንድ ካፖርት የለበሰ ሰው አንድ እግሩ ወደፊት አንድ እግሩ ወደ ኋላ ይራመድ ነበር። በሁለት አቅጣጫ። ከሥዕሉ ስር ያለው ካፕሽን ወደ የት እየሄድን ነው? የሚል ነበር። ሰውየውም የጠየቀን ወደ የት እየሄድን ነው? በሚል ነበር። አብዛኞዎቻችን ሰውየውን አፍ አፉን ነበር ያልነው። ጥያቄው ልናስበው የማንፈልገው ጥያቄ ነበር። ባለማሰባችን ግን እኛም ተጎዳን። ያ ሁሉ ወጣት ተጎዳ። ዛሬ እነዚያ ወጣቶች ማኅበረ ቅዱሳን ባሳረፈባቸው ዱላ ተመትተው በግብታዊነት ተጓዙ። ለጥቂት ጊዜ ቢንገታገቱም አቅጣጫ የላቸውም ነበር። ስለሆነም ስሜት ስለወሰዳቸው ሁሉም በተለያየ መንገድ ተበትነው ቀሩ። በሐረር ያሉት ግሩማን በሆኑ አባቶች ከለላ ስላገኙ የተረፉት ባለፈው በፍርድ ቤት በተፈረደላቸው ፍርድ ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው ተመልሰዋል። አብዛኛዎቹ ግን በፍርድ ቤቱ የሰባት ዓመት የፍርድ ሂደት ወቅት አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ብሎ ራሱን ለሰየመው የናዝሬት ፕሮቴስታንት ድርጅት ቅርንጫፍ ሆኑ። በድሬዳዋ ያሉት ጥቂት መሪዎቻቸው በሥራና በደመወዝ ተደልለው የመካነ ኢየሱስ አገልጋዮች ሲሆኑ፥ እነርሱ ግን እምቢ ብለው ለብቻቸው ቢቀሩም አስተማሪ ሰብሳቢ ስላጡ ዛሬ እንደምሰማው ከሆነ ከፕሮቴስታንት ለባሰ ስህተት መፈንጫ ሆነዋል።

ከናዝሬት ቅድስት ማርያም የወጡት ለተወሰነ ጊዜ በቀበሌ አዳራሽ ነበሩ። በዚያ ወቅት የምናገለግላቸው ሰዎች ከእነርሱ የማንሻል በእብደት በእልክ የታወርን ስለነበርን፥ የመንፈሳዊነታችንን ልክ የምንቆጥረው





በየቀኑ በምናስተምረው «አዲስ ትምህርት ነበር» ለትምህርታችን ምስክር የሚሆን ተጠያቂ አባትም ስለሌለ ከቤተ ክርስቲያን ጥላ ውጭም ስለሆንን ማንም በፈቀደው መንገድ ነበር የሚያስተምረው። ገሚሱ ከጴንጤ ይኮርጃል። ገሚሱ ከሉተራን ይኮርጃል። ገሚሱ ኦርቶዶክሳዊነቱን ለመጠበቅ ይሞክራል። ከሌሎች የተለየ መስሎ እንዳይታይ ይፈራል። ብቻ ያን ጉባኤ የሚመራው የቡድን ሃሳብ «mob mentality» ነበር። አንድ ወዳጄ እንዳስቀመጠው ከሁሉ የሚገርመው ግን በወቅቱ የነበሩት የቤተ ክህነት ሰዎች ሥራ ነበር። ቁጥራቸው ከአምስት እስከ ስምንት ሺህ የሚደርሱትን እነዚህን በአብዛኛው ወጣቶች መክሮ ገሥጾ አስተምሮ በፍቅር በእርጋታ እንደመመለስ፥ ያደረጉት ነገር ቢኖር፥ ኦርቶዶክስ አይደለንም ብላችሁ ፊርሙልን ብለው አስተዳደሩ ላይ እነዚያን ወጣቶች መክሰሳቸው ነበር። ይህ ሁኔታ ወጣቶቹን ወደ ሌላ አቅጣጫ ለመምራት ያደቡ ለነበሩት በር ከፈተላቸው። በመሪነት ቦታ የነበሩትም አይተውት በማያውቁት በተለያዩ ጥቅሞች ተያዙ። ወዲያውም በራቸውን ለፕሮቴስታንቶች ከፈቱላቸው። በናዝሬት በነበረው ሕዝብ መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ እጁን ያስገባው መሠረተ ክርስቶስ የሚባለው ድርጅት ነው።[94]
ምንም እንኳን ከእብደታቸው ተሳታፊ ከመሆን አልፌ የዚያ ግርግር መሪ ብሆንም፥ ፍጹም ከቤተ ክርስቲያን ለመለየት ግን ዝግጁ አልነበርኩም። በተለይም ደግሞ ከእነዚህ ድርጅቶች ጣልቃ መግባት በኋላ ወዲያውኑ «የውሃ ጥምቀት መውሰድ» የሚል ንግግር ከናዝሬትና ከአንዳንድ የአዲስ አበባ ወጣቶች መሰማት ተጀመረ። በዚህ ወቅት እኔም ራሴን ከናዝሬቱ ጉባኤ አገለልኩ። ተጎዳሁ ብዬ ቅር ልሰኝ፥

(94) አሁን እርሱም በተራው ዋጋውን እያገኘ ነው። አባላቱን ከሚንዱበት ድርጅቶች አንዱ እርሱ የበከለው ይህ ማኅበር ነው።



www.ethiopianorthodox.org

በሰዎች ላይ ቅሬታ ልይዝ በእልክ ሌሎችን አናደድኩ ብዬ ብዙ ነገር ለማድረግ ችዬ ነበር። በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቅሁባትን ጥምቀት ለመካድ ግን አቅሙም ችሎታውም አልነበረኝም። እነዚያ ጥምቀታቸውን በመካድ ሌላ ጥምቀት የተመኙት ውስለው አድረው ያልተመኙትና ያላሰቡት ነገር ላይ ያውም «አዲስ ቤተ ክርስቲያን መስርተናል» ወደሚል ቅዠት ሲደርሱ አልደነገጥኩም። መንገዱ እንዲህ ነበርና። ድንገተኛ ግብታዊና ብዙ ችግር በውስጡ ያለው ነበር።

ከሁሉ የሚገርመው እንጠማመቃለን የሚሉት እርስ በእርሳቸው ነበር። የእነርሱን ትምህርት የተቀበሉ የቂርቆስ ሰንበት ትምህርት ቤት አባላት የነበሩ ሁለት ልጆች ይህንኑ ዳግም ጥምቀት እናደርጋለን ሲሉ በውሃ ተበልተው ሞቱ። ዛሬ ማኅበረ ቅዱሳን አባረርኳቸው እያለ የሚደነፋው እነዚያ የዋህ ወጣቶች ለእንደዚህ ያለ መንፈሳዊ ግርግር ነው አልፈው የተሰጡት። ቤተ ክርስቲያኒቱንም እንጠብቃለን የሚሉትም አበው ለእነዚያ ነፍስ ገዳዮች አሳልፈው ሲያስደበድቡንና ሲያስገድሉን ከጎዱን በላይ ከቤተ ክርስቲያናችን ሲያባርሩን የጎዱን ይበልጣል። ያ ሥጋዊ ጉዳት ነበር። ይህ ሥጋዊም መንፈሳዊም ነበር።

2. <u>በጎበዝ አለቃ የሚመራ ነበር</u>። በቤተ ክርስቲያን ሳሉ ወጣቶቹን የቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርትና ሥርዓት አንድ አድርጎ የያዛቸው ሲሆን ከቤተ ክርስቲያን ከተባረሩ በኋላ በወጣቶቹ ዘንድ የሚታየው መንፈሳዊ ግርግር ሆነ።ይህ ወቅትም ለጎበዝ አለቆች አመቺ ጊዜ ከፈተላቸው። አንዳንዶች የራሳቸውን የወደፊት ኑሮ የሚያመቻቹበትን መድረክ ማሰብ ማሰላሰል ጀመሩ። ሌሎችም «ቤተ ክርስቲያን ከፍተው» ፓስተር መባል





እንደሚችሉ ማሰብ ጀመሩ። በዚህም ምክንያት ሁሉም በየፊናው የራሱን ሕልም ማሳደድ ጀመረ። ትናንት ከቤተ ክርስቲያናችን ስንወጣ «ገፍተውን ቢያወጡንም ቤተ ክርስቲያናችንን አንተውም» ያልነው ለቤተ ክርስቲያናችን ያለን ፍቅር መትነን ጀመረ። ሁሉ ተረሳ። አንዳንዶች ማን እንደሾማቸው ባይታወቅም «ፓስተር» ተባሉ ። አንዳንዶቹም ነቢይ ነን ማለት አመጡ። ሁሉም የተገኘውን ሹመት መፈለግ ጀመረ።

በዚህ ወቅት ይህን ግርግርና ግራ መጋባት በዋናነት የተጠቀሙት የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ። በተለይም መሪዎች ነን የሚሉትን ልጆች ምኞትና ድካም ስለሚያውቁ በተለያየ መንገድ ገቡባቸው። አንዳንዶቹን በገንዘብ ሌሎቹንም በመድረኮቻቸው ላይ በመጋበዝ ለማባበል ሞከሩ። ይህን ሲያደርጉ ግን በተዘዋዋሪ መንገድ ደግሞ ከቤተ ክርስቲያናቸው የወጡትን ሰዎች ቪዲዮ እያስቀረጹ «እግዚአብሔር ኦርቶዶክስን ሰጥቶናል» እያሉ እያሳዩ ገንዘብ ይሰበስቡበት ነበር።

ከቤተ ክርስቲያኒቱ በወጡት ልጆች የልጅነትና የጅልነት ሥራ ላይ በዋናነት ተጠቃሚዎቹ ፕሮቴስታንቶችና የእነዚህ ልጆች ተቃዋሚ የነበረው ማኅበረ ቅዱሳን ነበሩ። ሁለቱም የልጆቹን ቪዲዮ ተጠቀሙበት። ጴንጤው ማረከኳቸው ብሎ ሲሸጥ የቅዱሳኑ ማኅበር ደግሞ አባረርኳቸው ብሎ ይሸጥ ነበር። ሁለቱም በቁጥር የማይገመት ሀብት ማካበቻ አድርገዋቸዋል።

ይህን ታሪክ ስጽፍ በእነዚህ ግራ ተጋብተው ወደ ጥፋት በሄዱት ወጣቶች ላይ ራሴን አጽድቄ ወይም በዚያ ወቅት እኔ ከእነርሱ የተሻልኩ ነበርኩ ብዬ



www.ethiopianorthodox.org

አይደለም። ታሪኩ የኔው ታሪክ ስለሆነ በተወሰነ መንገድ ብሶቴን ኃዘኔን ንስሐዬን በአንድነት ብገልጥ ብዬ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ዛሬም በዚያ ግራ መጋባት መንገድ ውስጥ ያሉትን ማዳን ይቻላልና አባቶች እነዚያን ወጥተው ጠፍተው የቀሩትን ማዳን የሚችሉበትን መንገድ እንዲያስቡ ነው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያኔ ለእኔ ያሳየችኝን የእናትነት ፍቅር ለእነዚያም ታሳያለች በሚል ተሰፋ ነው።

ከሁሉም በላይ ግን እነዚህ ልጆች ለዚህ ሁሉ መንፈሳዊ ውድቀት እንዲደርሱ በዋናነት የሚጠየቀውና ከቤተ ክርስቲያኗ ሰፊ የእናትነት ልብ ይልቅ በድርጅት እውርነት ይመራ የነበረው ማኅበረ ቅዱሳን፥ ከዛሬ አሥር ዓመት በፊት ያደረገውን ክፉ ግብር አሁንም ለመድገም ሲሞክር፤ የንጹሐንን ሰዎች ስም በከንቱ ሲያጠፋ፤ እውነትን ሲያዛባ ያ ችግር እንዳይመጣ ልጆችን ከእናታቸው ለይቶ ማለቂያ ወደሌለው ስህተት መጨመር እንዳይደገም ከመፍራት ነው።

## ወደ ቤተ ክርስቲያን መመለስ

ወደ ቤተ ክርስቲያኔ የመመለሴ ሁኔታ በራሱ እግዚአብሔር ለልጆቹ ያለውን ፍቅርና ምሕረት የሚገልጥ ነው። ይህም የሆነው በብዙዎች ጸሎትና እንባ በተለይም በአባቴ በመሪጌታ ባወቀ ተረፈ ጸሎትና ምክር ነበር። ሁኔታዎቹን ራሱ ያዘጋጃቸው ነበር። የመጀመሪያው የውሳኔ ነጥቤ ከቤተ ክርስቲያን የወጡት ልጆች መሠረታዊ ከሆነው ኦርቶዶክሳዊ ትምህርት መራቃቸው፤ በተለይም ጥምቀታቸውን መካዳቸው ነበር። ይህ ሌላው ቀርቶ አንዳንድ የፕሮቴስታንት ድርጅቶች እንኳን አያደርጉትም። ይህን ሁኔታ ባየሁ ወቅት የከፈልኩትን ዋጋ ከፍዬ ወደ ቤተ ክርስቲያኔ መመለስ እንዳለብኝ ወሰንኩ።





የመመለሻ ጉዞው ግን ቀላል አልነበረም። ወደ ቤተ ክርስቲያኔ ለመመለስ ይረዱኛል ብዬ የተንዝኩባቸው መንገዶች አንዳንዶቹ ፈጽሞ የራቁ የፕሮቴስታንቶች መጠቀሚያዎች ነበሩ። ሆኖም እየወደቅሁ እየተነሣሁ እግዚአብሔር ከሕፃንነቴ ጀምሮ ወደ ጠራኝና እንዳገለግለው ወደ ወሰነልኝ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አድርሶኛል።

ከሁሉ አስቸጋሪ ጉዞ የነበረው ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመመለስ ቤተ ክርስቲያኔን ደጅ የጠናሁበት መንገድ ነው። ለሁለት ዓመት ቤተ ክህነቱን ደጅ ስጠና የሚደረግልኝ አንዳንድ ጥያቄ ተስፋ አስቆራጭ ነበር። ለአንዳንዶች ጥያቄዬ ከሥራ ጋር የተገናኘ መስሎአቸው፥ ሥራ መጠየቅ እንደማልችል የነገሩኝ ነበሩ። ሌሎቹ ደግሞ በግፍ መባረሬን ቢያውቁም ፓስተር እያለ ማኅበረ ቅዱሳን ስሜን የሚያጠፋበት በሐሰት መሆኑን ቢያውቁም ሌሎችን በተለይም የማኅበረ ቅዱሳንን ባላባቶች ስለፈሩ እኔን ለመርዳት ፈቃደኞች አልሆኑም።

ያቀረብኩት ግልጥ ማመልከቻ ነበር። ምንም እንኳን ምንም ኑፋቄ ሳይገኝብኝ እምነትና ክህደቴን ሳልጠየቅ በግፍ ብባረርም፤ ከቤተ ክርስቲያን ከወጣሁ በኋላ ለሠራሁት ጥፋት ለብዙዎች የስህተት ምክንያት ለመሆኔ በእልክም ለፈጸምኩት በደል ይቅርታ ይደረግልኝ የሚል ነበር። በቤተ ክህነት የኔን ጉዳይ የሚመለከቱት ሰዎችን ንስሐ ልገባ መጠየቄ ደስ ሳያሰኛቸው ያሸበራቸው በግፍ ተባርሬ የሚለው ነበር። ያን የእውነት ታሪክ ገልብጠው ወድጄ ፈቅጄ ከቤተ ክርስቲያኔ እንደ ወጣሁ እንዳምን ነበር የፈለጉት። ይህ ደግሞ አንድም ማስረጃ የሌለው የብዙዎችን የግፍ ታሪክ የሚሸፋፍን ስለሆነ በሐሰት ቃል ለመግባት አልፈለግሁም። በሕሊናዬ ንጹሕ ሳልሆን ንስሐ የለምና።



www.ethiopianorthodox.org

## ደለወኒ ዘአሕመምከኒ
## ያስጨነቅኸኝ ጠቀመኝ (ለመልካም ሆነልኝ)

ምንም እንኳ ተመልሼ መጣሁ ስል ተቀባይ ባጣም፤ የዳዊት ቃል ለእኔ ሆኖ በስተመጨረሻ በባዕድ ምድር በታላቅ ክብር ከወገኖቼ ጋር ቀላቀለኝ። ሀገራችን ያለችበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ያስተዋሉ አበው፤ እነዚያ ልጆች ጠፍተው ቀሩ፤ ሃይ የሚል ሽማግሌ ጠፋ ሲሉ የነበሩ አበው እንኳን ደህና ተመለስክ ብለው ተቀበሉኝ። በንስሐ አስጊጠውኝ አክብረውኝ ዛሬ በአገልግሎቴ ቤተ ክርስቲያኔን ለመጥቀም እየሞከርኩኝ ነው። እግዚአብሔር በቀሪው ሕይወቴ ለእርሱ ክብር ለቤተ ክርስቲያንም ጥቅም እንዲያደርገኝ ጸሎቴ ነው።



www.ethiopianorthodox.org